# አልወለድም

## ከአቤ ጉበኛ



እውነት በሌለበት
ዓለም ለመኖር
አልወለድም

Niguss
Digital Library

# አ ል ወ ለ ድ ም፡

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ


# ማውጫ


መቅድም ......17
1 ......24
2 ......25
3 ......33
የመጀመሪያው እሥራቴ ፡፡......34
የመጀመሪያው አድልዎና አድልዎን መቃወሜ ፡፡......38
4 ......43
ከቄስ ጋር ስለመጣላቴ ፡፡ ......43
5 ......46
ከጋዜጠኞች ጋር ስለመነጋገሬ ፡፡ ......46
6 ......53
የአካል ዕድገትና የአካባቢ ለውጥ ፡፡ ......53
7 ......60
ሰላማዊ ሰልፍ ስለማስነሣቴ ፡፡ ......60
8 ......67
ከጓደኞች ጋር ለግብርና ሥራ ስለመዘጋጀቴ ፡፡ ......67
9 ......76
ከሳሽ ስለመነሣቱ......76
10 ......85
ስለ ድንገተኛው ለውጥ ......85
11 ......96
ስለ አዲሱ አገዛዝ ፈጽሞ መበላሸት ፡፡ ......96
12 ......101
ከፍተኛ እንቅስቃሴ ስለመመሥረታችን ......101
13 ......112
የመጨረሻው ንቅናቄ ......112
14 ......117

ፍርድ ቤት ስለመቅረቤ ፡፡ ........................................117
15 ........................................................................127
ስለ ሁለተኛው ቀን ችሎት .........................................127
16 ........................................................................132
የትግሌና የሕይወት ዘመኔ ፍጻሜ ፡፡...................................132
ስለደራሲው በጥቂቱ........................................................148

ማንኛውም መብት የደራሲው መሆኑ በሕግ የተጠበቀ ነው።

ይህ፡ መጽሐፍ፡ ግርማዊ፡ ንጉሠ ነገሥት፡ ቀዳማዊ ኃይለ፡ ሥላሴ፡ በነገሡ በ፵፪ኛው ዘመነ መንግሥት፡ ሐምሌ፡ ፲፪፡ ቀን በ፲፱፻፷፭ ዓ.ም እንደገና በ፲፱፻፸፫ ዓ.ም ታተመ



(አቤ ጉበኛ)

# አዲስ መግቢያ ።

ይህ መጽሐፍ የዛሬ ፲፩ ዓመት ገደማ በደንቡ ምርመራ አልፎ ታትሞ በወጣ ጊዜ ታላቅ ችግር ፈጥሮብኝ ነበር ። ከአንድ ዓመት በላይ ሲያጨቃጭቀኝና በየቦታው ሲያስንትተኝ ቆይቶ በመጨረሻው በእሳት ነዶ የሰማዕትነት ጽዋውን እስከተቀበለበት ቀን ድረስ ብዙ የክርክር መልሶች እንድጽፍለት አስገድዶኛል። በፖሊስ አሳስሮኛል። ብዙ ጠላቶችም አፍርቶልኛል ።

ይህ በመሆኑ አንዳንድ ሰዎች ይህን ከመጽሐፎቼ ውስጥ በመታተም ተራ ስድስተኛ የሆነ ጽሑፌን የመጀመሪያ መጽሐፌ አድርገው ሲናገሩ ከመንግሥት ጋር የነበረኝን ከፍተኛ ችግር ሁሉ ከዚሁ ጋር ሊያያይዙት ሲሞክሩ እሰማለሁ ።

ነገር ግን « አልወለድም » ከፍ ብዬ የጠቀሴቸውን የራሱ ችግሮች ቢያስከትልብኝም የዚያ ሁሉ ችግሬ ምክንያት እርሱ ብቻ አይደለም ።

ኢትዮጵያን አሁን ካለችበት ከባድ ችግር ያደረሳት እጅግ የተበላሸ አስተዳደር ቀደም ብሎ ከተሰማቸው ሰዎች አንዱ ስለነበርሁ አልወለድምን ከመጻፌ በፊትና ከርሱ መቃጠል ቤላ እስካለፉት ጥቂት ወራት ድረስ የደረሰብኝን ሥቃይ ሁሉ ለመጻፍ ብሞክር ራሱ ከአልወለድም ዕጥፍ የሆነ መጽሐፍ ስለሚወጣው በዚህ ለመዘርዘር ቦታ የለኝም ። ነገር ግን ከመጽሐፉ ጋር ዝምድና ያለውን አንዳንድ ችግር ብገልጸው ተገቢና አስፈላጊ ይመስለኛል ።

አንዳንድ ሰዎች ስለ አገሪቱ መጥፎ ዕድልና ስለነበረው አስተዳደር አንዳንድ ነገሮችን መገንዘብ የቻልነው ከታኅሣሥ ፯ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም ወዲህ ነው ሲሉ እሰማለሁ ። እኔስ እንደዚህም አልነበርሁ ።

የተጨማለቀውን አስተዳደር ጉድለት መመልከት የቻልሁት ገና አገር ቤት ሳለሁ ከምክትል ወረዳ ግዛት ጀምሮ ነበር ። በጋዜጠኝነት ወደ መንግሥት ሥራ ከገባሁ ቤላም ብዙ ብዙ አሳፋሪ ተግባሮች በከፍተኛ ባለሥልጣኖችም እንደሚፈጸሙ ለመመልከት ቻልሁ ። በዚያ ጊዜ የተሰማኝን ድንጋጤና ቊጣ ይህ ነበር ብዬ ለመግለጽ አልችልም ። የሀገሬን ሕዝብ የሀገሬን ወግ በተለይም

ተወልጄ ባደግሁባቸው ክፍሎች ያለውን ሕዝብ ስሜት በሚገባ ዐውቅ ነበር። አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በእግዚአብሔር መኖር በእውነት በፍትሕ በቅንነት እንዲሁም ለነዚህና እነሱን ለመሰሉ ነገሮች ሁሉ ተቃራኒ በሆኑ ክፉ ነገሮች መኖር አምኖ እስከቻለ ድረስ ወደ በጐው ነገር ለማምራት የሚጣጣር ሕዝብ ነበር ።

ነገር ግን ይህ ቅንና መከረኛ ሕዝብ ለዚህ በጐ ዝንባሌው የተከፈለው ዋጋ ኀሊና በሌላቸው ዝቅተኛና ከፍተኛ ሹማምንት ተረግጦ መገዛትና እረኛ እንደሌለው በግ በደመ ነፍስ በሚንቀሳቀሱ ነጣቂ ተኩላዎች መበላት ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ ቅን ጐዳና ለመመራት በተዘጋጀበት ጊዜ ቅን ዓላማውን ጠማማ ለሆነው የግል ፍላጎታቸው ለመሠዋት የተዘጋጁ አራዊት በየክፍሉ ተለቀቁበት ።

ተዘረፈ ፤

ተዘርፎም ተገረፈ ።

ራሱ ተበደለ ፤

ራሱ ተገደለ ።

የሰው ሥጋ ለሰው እርም ባይሆን ኑሮ ባለፉት ዓመታት ውስጥ ከቀን ወደቀን እየከፋ በሔደው አስተዳደር በፍርሃትና በየዋህነት የማይፈራገጡ ተገዥዎች የነበሩ ኢትዮጵያውያንና ከሰው ሠራሽና ከእግዜር ሠራሽ ሕጎች ሁሉ ውጭ ሁነው የፈለጉትን ዓይነት ግፍ ይፈጽሙ የነበሩ ጥቂት ገዢዎች ገዥና ተገዥ ብቻ ሳይሆን በዪና ተበዪ በሆኑ ነበር ።

የማይሠራ ምን ዓይነት ግፍ ነበር? ይህ መሆኑን በመረዳት ሐሳቤን ለመግለጽ ዕድል ባጋጠመኝ ጊዜ ሁሉ ስሞክር ቆይቻለሁ ። በየቀኑ ያስከስሱኝ ከነበሩት በጋዜጦች የተገለጹ ብዙ ጽሑፎች ሌላ « የሮም አወዳደቅ » የተባለው መጽሐፌ ታትሞ የወጣው ከታኅሣሥ አምስቱ የመንግሥት ለውጥ ሙከራ አንድ ወር ገደማ ቀደም ብሎ ነበር ።

ከታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም ቤላ ጭቆና ስለፀናብኝ እወደው የነበረውን የጋዜጠኝነት ሥራ ትቼ ወደ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ገባሁ ።

በዚያም ጊዜ በጊዜው ባለሥልጣኖች እንደ ታላቅ ጥፋተኛ እየታየሁ በጽሑፌ በኩል ብዙ ቁጥጥር ይደረግብኝ ስለነበር «የፓትሪስ ሉሙምባ አሳዛኝ አሟሟት » የሚባለውን መጽሐፍ ለማሳተም ወደ አሥመራ መሔድ ግድ ሁኖብኛል። « አልወለድም» የተጻፈው ከዚያ ሁሉ ቤላ ነው ።

የአልወለድም ጣጣ ካለቀ ቤላ የደረሱብኝ እጅግ የሚያንገፈግፉ በደሎች ግን በልዩ ልዩ ምክንያቶች የመጡ ነበሩ ። አብዛኛዎቹ ምክንያቶችም ከፖለቲካ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ ሕይወቴ በተአምር ከመቆየቱ በቀር ያልተፈጸመብኝ በደል የለም ።

እንግዲህ አልወለድምን እንድጽፍ ወደ አስገደደኝ ምክንያት ልመለስ ። አልወለድምን ከጻፍሁበት ዓመት ቀደም ብሎ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ስሠራ በመካከለኛው ምሥራቅ በደቡብ አሜሪካና በሌሎች አንዳንድ አገሮች ደርተው ከሚሰሙት ዜናዎች ከፍተኛው የመንግሥታት መገለባበጥ ነበር። ለዚህም ዋና መሣሪያ ሆኖ የሚያገለግለው የጦር ኃይል ነበር ። በየጊዜው ከሰሜቸው ዜናዎች እንደተረዳሁት በየጊዜው በየቦታው በተገለባበጡት መንግሥታት ሕዝቦቻቸው ያገኙት ጥቅም ሽብር፣መከራና ሞት ብቻ ነበር። ይህም የሆነው መንግሥት ከገለበጡት ሰዎች ብዙዎቹ በገለበጡት መንግሥት ውስጥ ዋና ዋና ቀንደኞች ሁነው ሕዝብን እየበደሉና እየዘረፉ የቆዩ ለሕዝብ ደኅንነት ሳይሆን ለሥልጣንና ለጥቅም ሽሚያ የተነሡ ዕድል አሳዳጆች ስለነበሩ ነው ።

በዚህ ጊዜ ወድቃ ተዋርዳ ደህይታ ተንቃ የምትገኝ አገራችን በታታሪው ሕዝቧ ፈቃድና ከፍ ከፍ ሊያደርጓት በሚመኙ ቅን መሪዎች ጥረት ብቻ ልታገኝ የምትችለውን ዕድል ሳታገኝ እንደነዚያ ባሉ ሰዎች እጅ እንዳትወድቅ እጅግ ሠጋሁ ።

ከዚህም ጋር የተቸገረና መከራ ያንገላተው ሕዝብ እንደተራቡ ወፎች የተበተነለትን ምንም ዓይነት ጥሬ ሊለቅም ሲሞክር ወደ ወጥመድ የሚገባ እንደ ተራበ ዓሣ በማንኛውም ዓይነት የሥጋ ቅንጣቢ የተሸፈነ ገዳይ መቃጥንን ዘሎ የሚጐርስ መሆኑ ስለተሰማኝ ለኛ የግል ዕድገት የግዴታ አስፈላጊዎች ያልሆኑ ምናልባትም አደገኞች ሊሆኑ የሚችሉ የአስተዳደር ፍልስፍናዎች በእርግጥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስፈላጊ የሆኑትን ዓላማዎች እንዳያበላሹ ፈራሁ ። ኢትዮጵያ ረጅም የነፃነት ታሪክ ቢኖራትም የያንዳንዱ

ሰው የግል ነፃነት ፈጽሞ የተዘነጋባት የመንግሥት ሥልጣን ያላቸው ብቻ ሙሉ ሰዎች ወይም ቅዱሳን መላእክት ሁነው የሚታዩባት አገር ነበረች ።

በዚች የግላዊ ሰዎች ነፃነት ፈጽሞ ሳይታወቅ በኖረባት አገር የግል እምነትን ፣ ሃይማኖትን ፣ አስተሳሰብንና ይህን የመሰሉትን የያንዳንዱ ሰው የግል የሕይወት መመሪያዎች የሚቃወምና የሚከለክል የአስተዳደር ፍልስፍና ቢመሠረት የሀገራችንን ሕዝብ እናት ፣ አባቶቻችንን ፣ ልጆቻችንን ቀላል በሆነ የራሳቸው መንገድ ሊያገኙት የሚችሉትን መልካም ዕድል አስተን በጥንቃቄ በተጠበቀ የውሸት መላሾ እያታለልን ከአንድ ክፉ ቀንበር ወደ ሌላ ክፉ ቀንበር እንዳንወስዳቸው ፈራሁ ።

እንዲሁም በታላቁ ፎቃቸው ሥር ካለው ደረጃ ማዶ ለማዶ (እነሱ ወንድም ባይሉትም በርግጥ ወንድማቸው ነው ።) የተራበና የተራቆተ ወንድማቸው ሬሣ ወድቆ ካላዩ የበላይነታቸው ጺጋ ተሟልቶ የማይሰማቸው የመንፈስ ድሆች ይህን ከንቱና ሰይጣናዊ ልማዳቸውን ለመጠበቅ ራሳችን ጥረን ግረን የተሸለች አገር ሳናደርጋት የማንንም አገር ሀብት እያሳደዱ በተዘዋዋሪ ቅኝ ገዢነት ለሚዘርፉ ኃያላን መንግሥታት ሀገራችንን እንዳይሸጧት ተጨነቅሁ ።

በዚህ የስሜት ጭንቀት ላይ እንዳለሁ ይህን ሐሳቤን የምገልጽበት መንገድ ፈለግሁ። ከባዱ የሐሳብ መግለጽ ቍጥጥር በአእምሮዬ መጣ። አወጣሁ አወረድሁ ። መንገድ ታጣ። ሌላ ጭንቀት ተከተለ «አዬ ጉድ! አሁን ሰው ለዚች አጭር ሕይወቱ ሲል እስከዚህ መሰሎቹን ለምን ይጎዳል? ከዚህ ሁሉ ሰው በጠቅላላው ባይፈጠር ምን ነበር? » ከነዚህ ብርቱ ስሜቶቹ አልወለድም ተወለደ ። ግን በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ስለተጠላ ነደደ። ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጀመረው ሰላማዊ እንቅስቃሴ ምክንያት የመጽሐፉን ትንሣኤ ብቻ ሳይሆን የምኞቴን በመጠኑ መሟላት ለማየት በቅቻለሁ ።

ምስኪን አገራችን ኢትዮጵያ እጅግ በበዙ የውጭና የውስጥ ችግሮች ተከባ በምትገኝበት በአሁኑ ጊዜ የርስ በርስ ጦርነት ወይም በውጭ ኃይል የተቀየሰ የለውጥ ሙከራ ቢደርስ ኑሮ ከፍ ካለ ፈተና ላይ በወደቅን ነበር ።

አንዳንድ ሰዎች በሀገራችን ውስጥ ብጥብጥ ቢፈጠር ተራውና የተጨቆነው አብዛኛው ሕዝብ ከታሰረበት ሰንሰለት በቀር የሚያጣው ነገር

ስለሌለ ተበጣብጦ ይለይለት ይላሉ። የአያያዛችን ሁሉ አለመጣም ሲታይም ይህ አባባል እውነት ያለበት ይመስላል ።

ነገር ግን በሀገራችን ከፍተኛ ሁከት ቢፈጠር በሚሊዮን የሚቈጠር የተራበና የተቸገረ ነፍስ እንዲሁም አንዳንድ የሀገራችንን ክፍሎች ካጣን ቤላ ድካምና መከራ ሲሰለቸን የውጭ ኃይል በሚቈጣጠረውና ከኖርንበት በማይሻል ወዴላ ጎታችና ጨቋኝ አስተዳደር ሥር ከመውደቅ በቀር ሌላ ምርጫ ሊኖረን እንደማይችል ግልጽ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይም ከብዙ ሰዎች ጋር እሚገት ነበር። እኛ ኢትዮጵያውያን ከማንም የተለየ የራሳችን ታሪክ የአኗኗር ወግና የአካባቢ ሁኔታ ስላለን ከማንም የምንበደረው ሐሳብ ከችግራችን አያድነንም ። ሀገራችንን ማዳን የምንችለው ከአምላካችን ኃይልና ርዳታ ጋር ራሳችን ራሳችንን ስንረዳ ብቻ ነው። ከዓለም ተለይተን መኖር ስለማንችል ከማንኛውም የዓለም ሕዝብ ጋር ንጹሕ ወዳጅነት ልንመሠርት ልንረዳና ልንረዳዳ እንችላለን ።

ነገር ግን የምዕራቡም ሆኑ የምሥራቅ ኃያላን መንግሥታት ካንገት በላይ በሆነ ወዳጅነት ስም እየገቡ የየራሳቸውን ምኞት ተገዥዎች ሊያደርጉንና የሀገራችንን የተፈጥሮ ሀብት ርካሽ ከሆነው ጉልበታችን ጋር ዘርፈው ለመሔድ የሚያደርጉትን ሙከራ ከሰው ልጆች አንድነትና መረዳዳት ጋር አለመቀኊጠር ብቻ ሳይሆን ግልጽ ጦርነት ልናውጅበት የሚገባ የሀገራችን ጠላት ነው ።

ከዚህ ላይ አሜሪካ ችካጎ ከተማ ውስጥ አንዲት አሜሪካዊት ወይዘሮ የነገሩኝን ምን ጊዜም የማልረሳው ነገር ልጠቅሰው እወዳለሁ ።

በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ክልል ውስጥ ከሚገኙት ክፍሎች በቀር ከጠቅላላው የአሜሪካ ሕዝብ ውስጥ እጅግ ቅንና ግልጽ የሆኑ ብዙ ሰዎች ለማግኘት እንደሚቻል ራሴ ለማየት ችያለሁ ። እኚሁ ወይዘሮም ግልጽና ቅን ከሆኑት የአሜሪካ ሰዎች አንዷ ሲሆኑ ልንነጋገር የቻልነው ጡረታ የወጡ ዶክተር ከሆኑት ባለቤታቸው ጋር የልደት በዓልን ጊዜ ከራሳቸው ቦታ ውጭ ለማሳለፍ ወደ ችካጎ መጥተው እኔም እንዲሁ እግረ መንገዴን ሳልፍ ባረፍንበት ሆቴል በምግብ ቤቱ ተገናኝተን ነው ።

ኢትዮጵያዊነቴን እንዳወቁ በአንድ ላይ ተቀምጠን እንድንነጋገር ጠየቁኝና ስለ አንዳንድ ነገሮች ከተነጋገርን ቤላ ኢትዮጵያዊ የሆነን ሁሉ በየደረሰበት

ቅስሙን ሲሰብረው ወደ ኖረው የሀገራችን መከራ ገባን ፡፡ እኔ እንኳ ላነሣው አልፈለግሁም ነበር፡፡ ግን ወይዘሮዋ ራሳቸው አነሡት ፡፡

« እኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ኑሬ ባላውቅም ለኢትዮጵያ ታላቅ አክብሮት ነበረኝ ፡፡ ግን የሕዝባችሁን በረኃብ ማለቅ ከልዩ ልዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ሳነብ እጅግ አዘንሁ ፡፡ ለመሆኑ እንደዚህ በረኃብ እስኪታልቁ አገራችሁ በተፈጥሮ ደሀ ናት ወይ? » አሉኝ ፡፡

« በተፈጥሮ ደሀ አይደለችም ፡፡ ግን አላለማናትም » አሌቸው ፡፡

« ብትለማም እንኳ ሀብቷን ለያንዳንዱ ሰው ደኅንነት ካላዋላችሁት ብዙዎች ወገኖቻችሁ በረኃብ ከመሞት ላይድኑ ይችላሉ ፡፡ ለመሆኑ ባገራችሁ ውስጥ ምን ምን ዓይነት ሀብት ሊገኝ ይችላል? » አሉኝ፡፡

የሀፍረት ደረቅ ፈገግታ እያሳየሁ « ምንም እንኳ አሁን በረኃብ ስናልቅ የምንገኝ መሆናችን ባይካድ ሀገሪቱ ለርሻ ምቹ የሆነች ሀገር ናት፡፡ የመካከለኛው ምሥራቅ የዳቦ ቅርጫት ልትባል ትችላለች ሲሉም ሰምተናል አሌቸው ፡፡

በዚህ ጊዜ ወይዘሮዋ በከፍተኛና በእውነተኛ ስሜት ከወንበራቸው ላይ እንደገና እየተስማሙ

« ከዚህ ላይ በርቱ ከዚህ ላይ ተጠንቀቁ ነዳጅ ዘይት ካላችሁ ሌላ ሌላው ምቾት ቢቀርባችሁ እንኳ እሱ ብቻ በራብ ከማለቅ ሊያድናችሁ ይችላል ፡፡ ግን በሚገባ መያዝ አለባችሁ ፡፡ ያለዚያ እንደ ኢኳዶር ትሆናላችሁ ፡፡ » አሉኝ ፡፡

« በኢኳዶር ምን ሆነ? » አሌቸው ፡፡

« አብዛኛው የኢኳዶር ሕዝብ (ስለግምቴ ይቅርታ አድርግልኝ) እንደናንተ ሕዝብ በጣም ችግረኛ ነው ፡፡ ታላቅ የዘይት ክምችት ተገኘ ፡፡ ያገኘነውም እኛ አሜሪካውያን ነን ፡፡ ግን ምን ሆነ መሰለህ? ደሀው ሕዝብ በርካሽ ዋጋ ጉልበቱን አበረከተ፡፡ ከኢኳዶር መሬት ቤንዚኑ ታፈሰ፡፡ ብዙው ሃብት ወደኛ መጣ፡፡ ቀሪው አገራቸውን ለሸጡት በጅ ጣት የሚቈጠሩ የፖለ+ካና የጦር መሪዎች በጉርሻ መልክ ተሰጠ፡፡ የተረፈውም (ምናልባት

ከጎረቤታቸው ከፔሩ ጋር ካልሆነ ከማን ጋር እንደሚዋጉ አላውቅም) ከአሜሪካ ታንክ ጀት አኤሮፕላን ጠመንጃና ጥይት ለመግዛት ወጪ ሆነ። አብዛኛው የኢኳዶር ሕዝብም ከቆየበት ሥቃይ ሳይወጣ ይገኛል። በርግጥ አገራችሁን የምትወዱ ኢትዮጵያውያን ካላችሁ ዘይት እንኳ ባይኖራችሁ የሀገራችሁን ሕዝብ ከመከራ የሚያድን ማገኛቸውም የሀገራችሁ ሀብት በዚህ መንገድ እንዳይዘረፍ ተጠንቀቁ » አሉኝ ።

ግልጽ ምክንያት አልነበረኝም ። ግን በደፈናው « በሀገራችን ይህ ሊሆን አይችልም » አሌቻቸው።

« እንደምን? » አሉኝ ።

« የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅን ሕዝብ ነበር ።

ከራሱ መሐል የወጡ መሪዎች ይሸጡኛል ብሎ አይጠራጠርም ። ይህ ሲሞከርበት ካገኘ ግን ይነሣል » አልሁ ።

« የጦር ኃይሉ ላገር ሻጮች ታማኝ ከሆነ መከላከያ የሌለው ሰላማዊ ሕዝብ ምን ሊያደርግ ይችላል? አሉኝ

« ይህ በቀላሉ ይቻላል ። ከሁሉ በፊት ኢትዮጵያውያን በቤተ ሰብ ፍቅር የተሳሰርን ስለሆንን እያንዳንዱ ወታደር የናት አባቱን የእኅት የወንድሙን መከራ እያየ ሀገሩን ለሚሸጡ የፖለ+ካና የጦር መሪዎች መሣሪያ ለመሆን አይሞክርም ። ሁለተኛ ማገኛውም ኢትዮጵያዊ በቆየው ልማድ መሠረት በጦር መሣሪያ የደረጀ ስለሆነ መሸጡን በርግጥ በተረዳበት አንድ ቀን ውስጥ ሁሉንም ነገር ከማፈራረስና የራሱን ደኅንነት ከመጠበቅ አይመለስም » አሌቻው ።

ከዚህ ላይ ያመኑኝ አልመሰለኝም። ለምሳሌ ያቀረቤቻው ሁለቱም ምክንያቶች ለርሳቸው ዕንግዳ ነገሮች ነበሩ። እርሳቸው ብቻ ሳይሆኑ ኢትዮጵያን ያላዩ ብዙ የውጭ ሰዎች በብዙ መቶ ሺህ ወይም በብዙ ሚሊዮን የሚቈጠሩ ኢትዮጵያውያን በታላላቅ የበዓላት ቀኖች በግ ወይም ዶሮ በየቤታቸው ያርዳሉ ። እንዲሁም ያረጀም ይሁን አዲስ ዓይነት የጦር መሣሪያ ለየራሳቸው አላቸው ብሎ የሚነግራቸውን ሰው ፍጹም ዋሾ ብለው

ከሚታዘቡት በቀር እውነቱን ሊረዱለት አይችሉም። ሁለተኛ የቤተ ሰብ ፍቅር በምዕራባውያን ዘንድ እስከዚህ ጠብቆ አይታይም ።

ይሁን እንጂ በማንኛውም መንገድ ቢሆን የሴትዮዋ ማስጠንቀቂያ ቀላል አልነበረም ። ብዙ ነፍስ በራብ ከሚያልቅባት አንዷት ትንሽ ሀገር ሒዶ በዚያ የውሻና የድመት ምግብ ለማጫረት የሬዲዮውና የቴሌቪዥኑ ማስታወቂያ በሚያዋክብበት ሰፊ አገር ይህን መሳይ ንግግር መስማት የኅሊና ዕረፍት የሚሰጥ አልነበረም ።

እንዲሁም « ተርበኻልና እንጀራ እንድታገኝ የሚያስችል አስተዳደር አመጣልኻለሁ ። ግን የግል አስተሳሰብህን ዝንባሌህን ነጻነትህንና እምነትህን መሥዋዕት አድርገህ አቅርብልኝ። የሚለው ፍልስፍና ለሀገራችን ምን ያህል አደገኛ ሊሆን እንደሚችልም ተሰምቶኛል ።

ይህ ስሜት እያወከኝ አንድ ወር ገደማ እንደ ቆየሁ አንድ ታላቅ ተአምር ሰማሁ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንም በተለመለት ከራሱ ኑሮ የማይመሳሰል ዕቅድ ሳይነዳ ራሱ የራሱን መንገድ ለመቀየስ ተነሣሣ ኢትዮጵያዊው ወታደርም የራሱን ልዩ ታሪክ ጀመረ። የተበላሸውንና ወገኑን ያዋረደና ያስጨነቀውን አስተዳደር ከዳ። ከእውነተኞች ወገኖቹ ተቀላቀለ። የውጭ ኃይሎች እጃቸውን ለማስገባት የሚሞክሩበት ቀዳዳ ተዘጋ። በዘር በሃይማኖት ይቀሰቀሳል ተብሎ የነበረውን ግጭት ሁሉም ነቅቶ ተከላከለው ።

እንደ ኢትዮጵያ በሥልጣኔ ወደ ኋላ በቀሩ ብዙ አገሮች የውጭ ኃይሎችና አገር ሻጭ ወኪሎቻቸው መሣሪያ አድርገው ሲጠቀሙባቸው የኖሩ « ወታደር ያለማመንታት ለአለቃው መታዘዝ እንጂ ለምን? ወደሚል ጥያቄ መግባት የለበትም» በሚል አጉል ፍልስፍና የሚመሩ ወታደሮችን ነበር ። ኢትዮጵያዊው ወታደር ግን በዚህ ትውልድና ታሪክ ይቅርታ በማያደርግለት ቅሌት ውስጥ ገብቶ አልተገኘም። ይህም አድራጎቱ ኢትዮጵያውያንን በዓለም ፊት እጅግ ከማስደነቁ በላይ ልዩ ታሪክ ላላት አገራችን ልዩ ምዕራፍ እንደሚከፍትላት አይጠረጠርም ።

የአንዳንድ አገሮች ወታደሮች ምን ያደርጋሉ? ዘንድሮ አንዱን ንፍጣምና የውጭ ኃይል ተገዥ የሆነ ጄኔራል ደግፈው ይነሣሉ። እርሱም አገሩን በተወሰነ ጥቅም ያንጫርርና ራሱን ማርሻል ይላል። ራሱን በራሱ በሸለማቸው ጌጣ

ጌጦች እንደ ቃልቻ በቅሎ ካዥጎረጎረ ቤላ ሀገራቸውን ሽጦ ካገኘው መጠነኛ ጥቅም ጥቂት ፍርፋሪ ይጥልላቸዋል ። ለዚህ መሠረታዊ ጥቅማቸውን አበላሽቶ ለሚጣል ፍርፋሪም በሀገራቸው ሽያጭ ይስማማሉ። ያ ማርሻል በሀገሩ ላይ የፈጸመው ወንጀል ተሰምቶትና ኅሊናው ወቅሶት የጠቅላላውን ሃገሩ ሕዝብ ደኅንነት ለማሻሻል በሚሞክርበት ጊዜ የውጭ አለቆቹ ሌላ አዲስ ቱኪ ያስነሡና በገዛ ወታደሮቹ ኃይል አስገልብጠው የተለመደ ዘረፋቸውን ይቀጥላሉ። በዚህ ምክንያት በየደሀው ሀገር በተፈጠረው አዲስና ተዘዋዋሪ የቅኝ አገዛዝ ዘዴ የተበሳጩ ሰዎች በአደባባይ ያሰሟቸውን ንግግሮች ሳዳምጥ የአንዳንድ የምሥራቅ አውሮፓ ሀገሮች ተወላጆች የቅኝ ተገዥነት መከራቸውን ከዘረዘሩ ቤላ « አሁን ደግሞ በሩሲያ ከባድ ቀንበር ሥር እንገኛለን » ሲሉ በተለይ ከደቡብ አሜሪካ የመጡት ደግሞ « አሁን በመጨረሻውም ዘራፊ በሆነው የአሜሪካ አዲስ ቅኝ አገዛዝ ሥር እንገኛለን » ሲሉ ይደመድማሉ ።

የነዚህ ሰዎች አገሮች ለስሙ ነፃዎች ናቸው። ነገር ግን ሀብታቸውን በግልጽ ከመዘረፍ ሕዝባቸውን ከችግርና ከጭቆና ለማዳን ዓቅም አላገኙም ።

ለዚህ ዓይነቱ አዲስ የሀገር ግዥና ሽያጭ ዘዴ መሣሪያ የሆነውም ከሞላ ጎደል የጦር ኃይል ነው።

እንግዲህ ይህን ስናይ ነው በኛ ወታደሮች ግሩም አሠራር መንፈሳችን የሚረካው ።

የሀገራችን የለውጥ እንቅስቃሴ ተደጋግሞ ከተወራ ቤላ ከአንድ አሜሪካዊ ጋር ስንጫወት « አገራችሁ ችጋራም መሆኗን ለማወቅ ችያለሁ ። ግን የምትሠሩት ሥራ ሁሉ ከማንም የተለየ ይመስላል።

ምክንያቱ ምንድን ነው? » አለኝ ።

« ምክንያቱም ቀላል ነው ። ለማንም የውጭ ወራሪ ሳንገዛ ስለኖርን ነው » አልሁት ።

« እሱስ ይሁን በዚህ በሐያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውስጥ አገራችሁ እንደ አሜሪካ ላለ ታላቅ ሀገር ምን ዓይነት ነገር ልታበረክት ትችላለች? » አለኝ ።

« ፕሬዚዴንትን በጥይት ሳይገድሉ መንግሥት መለወጥ እንደሚቻል ልታስተምራችሁ ትችላለች» አልሁት ። ደስ አላለውም ፊቱ ቀላና ሌላ ወሬ ቀጠልን ።

ባጭሩ ለመናገር « አልወለድም »ን በጻፍሁ ጊዜ አገሬ በጨለመ የጊዜው ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በጨለመ የወደፊት ዕድል ላይ ትታየኝ ነበር። አሁን ግን እኛው ራሳችን መልሰን ካላጠፋነው ካልተሸጥን ካልተለወጥን ፣ ምንጊዜም ያልዘነጋን አምላክ ጥሩ መንገድ ከፍቶልናል ። የአምላክን ኃይልስ እንዴት መርሳት እንችላለን? ሌላ ምሳሌ መጥቀስ ይቅርብኝና ፲፱፻፴፫ ዓ. ምን ላስታውስ። « በአሥራ ዘጠኝ መቶ በሰላሣ ሦስት .......

ይህን መሥመር በመሙላት ስንት መዝሙር ጻፍን?በእውነት ነፃ ላወጣን አምላክስ ምን ያህል መሥመሮች ደረሱት? አብዛኛውን ምስጋና አርበኛ ስደተኛ የውስጥ አርበኛ ተቀበሉት። አምላክ ተረሣ ለዚህም ያቺ የተመጻደቅንባት ቃል « ሰላሣ ሦስት » እንዳትረሣን « ሰላሣ ሦስት » ዓመት ሙሉ በተከማቸ ዕዳ ነከረን ።

ግን ከርሱ ርዳታ ጋር በእውነት ነፃ ለመውጣት ዕድል እንዳለን ተስፋ እናደርጋለን ።

ከእንግዲህ ወዲህ ወደ ነበርንበት ባርነት የምንመለስ ከሆነ ግን አሁንም ባልወለድ ሌላው ኢትዮጵያዊም ባይወለድ በተሻለ ነበር ።

ግን ተስፋ አንቁረጥ አንድ ጊዜ ኢትዮጵያውያን ሁነን ተወልደናልና!

አቤ ጉበኛ

# መቅድም

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ያገርና የሰው ስሞች እንዲሁም ታሪኮች በሐሳብ የተፈጠሩ ናቸው።

ብዙ ጸሐፊዎች በማንም አገር በማንም ሕዝብ ላይ አንድ ነገር ለመናገር ሳይፈቅዱ ሲቀሩ አንድ አገር አንድ ሕዝብ በሓሳባቸው ፈጥረው በሰው ላይ ሊደርሱ የሚችሉትን ነገሮችና ሰዎች ሊያደርጓቸው የሚገባቸውን ማንንም በማይመለከት ነፃ ዓየር መግለጽ ከጀመሩ ብዙ ጊዜ ነው ።

እኔም ይህን መጽሐፍ በዚህ መንገድ ስጽፍ ይህንኑ ዓላማ በመምረጥ ነው ።

በታሪኩ የተገለጹት ነገሮች በዓለም ውስጥ በብዙ አገሮች እየተደጋገሙ የደረሱ ናቸው። አንዳንድ ዕድለኞች አገሮች ብቻ መሠረታቸው ሳይፋለስ ደም ሳይፈስ ከተሻለ ኑሮ ለመድረስ ሲችሉ አብዛኛዎቹ አገሮች አንዱ ክፍል የነገሥታትን አገዛዝ ሲቃወም አንዱ ክፍል የሕዝብን ሥልጣን ሲቃወም ወይም « ፓር+ » የሚሉት ልዩ ልዩ ክፍል እያቋቋመ እርስ በርሱ ሲበጣበጥ የኑሮውን መሻሻል በተስፋ ብቻ የጨረሰ ሕዝብ ይገኝባቸዋል ።

ስለዚህ በማንኛውም ሁኔታ ላይ እውነት መስሎ የታየኝን ሐሳብ ማንንም በማይመለከት በሓሳብ የተፈጠረ አገር ላይ ገልጨዋለሁ ።

መጽሐፉ ለግል ሰዎች ወይም ለግል አገር የተጻፈ ሳይሆን በመላው የሰው ዘር ላይ በመላው ዓለም ሲደርሱ ለኖሩና አሁንም በብዛት ለሚደርሱ መጥፎ ነገሮች መቃወሚያ እንዲሆን የተፂፈ ነው ።

ምን ጊዜም ቢሆን በጠባብ አስተያየት መወሰን የለብንም ። ከሁሉ በፊት ክፋት የሰው ተፈጥሮ አጃቢ መሆኑን በማወቅ ከያንዳንዳችን ራስ ላይ ክፉ ስሜትን ማስወገድ ይገባናል ።

2ኛ የአንድ ማኅበራዊ ኑሮን መልካም አቋም የሕዝብ ስንፍና ጭምር እንጂ የጥቂት ሰዎች ስንፍና ብቻ እንደማያበላሸው ማመን ያስፈልጋል ።

3ኛ ስለሰው ልጆች መልካም አኗኗር በማንኛውም ዓለም የታሰበውንና የተነገረውን ያህል ታላቅ ርምጃ አለመደረጉን በመገንዘብ በራስ ሁኔታ ተስፋ

አለመቍረጥና ሁሉንም በሰፊ ዓይን መመልከት በትዕግሥትና በእምነትም መራመድ ተገቢ ነው ። በዓለም ላይ የሰው ዘር መኖር ከጀመረ ብዙ ሺ ዘመናት አልፈዋል። በያንዳንዱ ትውልድም ብዙ ክፉዎችና ደጎች አልፈዋል። ያልተስተካከሉ የሰው ጉድለቶች ግን እስካሁን አሉ። አሁን ያለነውን ሰዎችና ያለንበትን ጊዜ መርገም ወይም መመረቅ የትውልድ ሙያ ሊሆን አይችልም። ያለፈውን ጊዜ ማስታወስና ለሚመጣውም ጊዜ ማሰብ ይገባል ።

ሰው ከሚሳሳትባቸው ምክንያቶች ዋናውና አንደኛው ባለፈው ጊዜ ምን ምን ነገሮች ነበሩ? ዛሬ ምን ይደረጋል? ነገስ ምን ይመጣ ይሆን? የሚሉትን ጥያቄዎች ሳያስተውሉ ሁሉንም ነገር ለዛሬ ብቻ ሲሰጡ ነው ።

በእውነትም ይሁን በአድልዎ ለመጻፉ ትክክለኛና እርግጠኛ መረጃ ባናገኝም ታሪክ በመጠኑ ስላለፈው የሰው ዘሮች አኗኗር ብዙ ጥናት ሳይሰጠን አልቀረም ።

የሰው ዘሮች ከብዙ ዘመናት በፊት ጀምረው በሃይማኖት ፣ በአስተዳደር ፣ በማኅበራዊ ፣ ኑሮና በሌሎች ልዩ ልዩ እምነቶች እየተከፋፈሉ እርስ በርሳቸው ሲጐዳዱ ኑረዋል ።

ተገዛ አልገዛም ። እምነቴን ተቀበል አልቀበልም! ጥቅምህን ለኔ ስጥ! አልሰጥም! በሚሉ ብዙ ዓይነት ክርክሮች የብዙ ሰዎች ደም የፈሰሰባቸው ታላላቅና ታናናሽ ጦርነቶች ከመደረጋቸው በላይ እነዚህን የውጊያ ምንጮች ከሰው ማኅበራዊ ኑሮ ለማስወገድ ከክፉ ተግባሮች ጋር በመዋጋት ሕይወታቸውን ያሳለፉ የመንፈስ ጀግኖችም ብዙዎች ናቸው ።

ይህ ሁሉ ሲሆን የሰው ዘር ክፋት እንዳለ ሁኖ ወይም መልኩን እየለወጠ የሰውን መልካም አኗኗር ከሰው አርቆት ይገኛል ።

በተለይም ብዙ ሰዎች የክፉ ተግባርን ጐጂነት እያስፋፉ በሚናገሩበት ስለ ሰው መልካም አኗኗር ስለሰላምና ፍቅር በሰፊው በሚያወሩበት በአሁኑ ጊዜ ክፋትና ተንኰል የበለጠ ኃይል እያገኙ ሲሄዱ ማየት ለሰው መልኳም አኗኗር ያለውን ተስፋ ከማስቆረጥ የሚያደርስ ነው ።

በዘመናችን ክፉ ሥራዎች ካገኙዋቸው ታላላቅ ድጋፎች ዋናው ዘመናዊው የሸፍጥ ፖለተካ የሰዎችን ግብረ ገብነት ቦታ መውረሱ ነው ።

የዘመኑ ፖለ+ካም ሸንግሎም አታልሎም ራስን ብቻ መጥቀምንና ሌሎችን መጉዳትን እንደዕውቀት እንጂ እንደድንቁርና ስለማይቈጥራቸው በእውነት ካልሆነ በቀር በሌላ መንገድ ሊገታ የማይችለው የአብዛኛው ሕዝብ ፍላጐት እስካሁን እውነተኛ ሰላሙንና መልካም አኗኗሩን ከመፈለግ አላቋረጠም ።

የሰውን ልጆች በፍቅር በሰላም በወንድማማችነት ለማኖር ችግርን መከራን ደንቁርናን ጥላቻን ግፍን ለማስወገድ ብዙ ተደከመ የብዙ ሰዎች ሕይወትም ጠፋ እንጂ ዓለም ከሚፈለግባት መልካም ደረጃ ገና አልደረሰችም ።

ዓለምን ከእውነተኛ ኑሮ ለማድረስ ገና የብዙ ሰዎች ድካምና በጐ ፈቃድ ያስፈልጋል። ሰዎች ሁሉ ከአራዊት ባሕርይ ተዘምዶ ያለውን አካላቸውን ከመለኮት ተዘምዶ ባለው መንፈሳቸው ሥልጣን ሥር እስኪያውሉት በጐ ምግባር ከፉና ትዕቢተኛ ፍላጐትን ድል እስኪያደርግ ድረስ ንጹሕ የሆነ ሰላማዊና ቅዱስ ኑሮ ሊገኝ አይችልም ።

ኮንፊዩሽስ የተባለው ጥንታዊውና ታላቁ የቻይና ፈላስፋ በጐ ሥራዎችን አስተምሮ አስተምሮ «ሰዎች ሁሉ መልካም አድራጊዎች ቢሆኑ የኔ ትምህርቶች የሚፈለጉበት ቦታ የለም » ሲል ቅን ሥራ የሁሉ ነገር መሠረትና የሰላም ምንጭ መሆኑን መስክሯል ።

ሁላችንም ብንሆን ክፋትን ደግነት ፣ ጠማማነትን ቅንነት ፣ ብልግናን ጨዋነት ፣ ትዕቢትን ትኅትና ፣ ጥላቻን ፍቅር ፣ ጦርነትን ሰላም ፣ ድኅነትን በቂ ኑሮ ፣ ድንቁርናን ዕውቀት ፣ ጭካኔን ርኅራኄ ፣ ተንኰልን ግልጽነት ፣ ብልጠትን ልግሥና ፣ አቸንፈዋቸው ካየን ስለበጐነትም ሆነ ስለክፋት ብዙ እንድንናገር የሚገፋፋን ምክንያት አይኖረንም ።

ነገር ግን በዛሬው ዓለም ያለን ሕዝቦች ሁሉ የምንገኝበት ደረጃ የትንንቅና የቅሚያ ጊዜ በመሆኑ ክፋትን መቃወምና የደከመውን በጐ ምግባር ማበረታታት ግዳጃችን ነው ።

ሁሉንም ነገር የዓለም ጣጣ ነው ብለን ችላ እንዳንለው ሰዎች በዚች ዓለም ላይ በምንቆይባት አጭር ጊዜ የሚያጋጥመን ችግርና ጭንቅ የደረሰባቸውን ብቻ ሳይሆን ተመልካቾችንም የሚያሰቅቅና የሚያሠቃይ ነው ።

ሶክራትስን የመሰለ ታላቅ ፍጡር የጥቂቶቹን አጥቂነትና የብዙዎችን ተጠቂነት እያየ ለመኖር የሚያስችለው በቂ የመንፈስ ድንዳኔ በማጣቱ « አሁን መሞትና ካስቸጋሪ ነገሮች ነፃ መሆን ለኔ የሚሻለኝ መሆኑ ግልጽ ሁኖ ይታየኛል » ብሏል ።

ከዚያ ቀጥሎ ሊሞት የወደደው ለግል ጉዳዩ ወይም ለግል ቤተ ሰቡ ሳይሆን ለእውነተኛ በጐ ሥራ መሆኑን ሲገልጽ « መኳንንት! ልጆቼ ባደጉ ጊዜ ቅጧቸው ከደግ ሥራ በፊት ለገንዘብ የሚያስቡ ከሆነ እኔ እንደአሠቃዬችሁ አሠቃይዋቸው ። እነሱ ምንም ሳይሆኑ ምኖች ነን ብለው ራሳቸውን ካከበሩም እኔ እንዳሳፈሬችሁ አሳፍሯቸው ሊያስቡበት የሚገባቸውን አላሰቡምና! ምንም ሳይሆኑ ራሳቸውን ዋጋ እንዳለው ነገር በመቁጠራቸው » ሲል ተናግሮ « አሁን እኔ ወደሞት እናንተ ወደመኖር የምንሄድበት ጊዜ ነው ። ከናንተና ከኔ ማንኛችን ወደተሻለው መንገድ እንደምንሄድ እግዚአብሔር ብቻ እንጂ ማንም አያውቀውም » ካለ ቤላ እውነትን ፣ ደግነትንና እውነተኛ ፍርድን በማስተማሩ ሞት ከፈረደበት ፍርድ ቤት ፍርዱን በደስታ ተቀብሎ ወጥቷል ። ከዚህም በላይ የሚሞትበትን መርዝ በድፍረት ጠጥቶ በጸጥታና በፍጹም እርጋታ ከቆየ ቤላ ሰውነቱ ሲደክም በሞተ ጊዜ ከጥጉ ሁኖ በዕንባ ሲታነቅ የቆየውንና ታማኝ ተማሪውን ክሪቶንን ጠርቶ « ለአስክሌፒኦስ የምንሰጠው አንድ አውራ ዶሮ አለና ሳትዘነጋ እንድትከፍለው » ሲል የደግነትና የእውነት መምህር ሁኖ የኖረው ለእውነትም የሞተው ታላቁ ሶክራትስ የመጨረሻ ትንፋሹን በእውነተኛ ቃል ፈጽሞ ካለም ተሰናብቷል ።

የእውነትና የደግነት መጐዳት የተቆረቆሩለትን ለማስተማር ቀርቶ ለሞት እስኪሰጡ ድረስ ያስገድዳል ። ከፋትና ድንቁርና ቢጠፉ ግን ገዳይም ተገዳይም ባልተገኘ ነበር። እስካሁን የቆየው ዓለም ግን ብዙዎቹ የከፋት ሠራዊቶችና ጥቂቶቹ የደግነት ሠራዊቶች እየተዋጉ ከፋት ሲያሸንፍበት ደግነት ሲሸነፍበት የቆየ ነው ።

አንድ የዘመናችን ምዕራባዊ ዲፕሎማት « ባለፈው ጊዜ እንሠራው በነበረው የጋራ ስሕተት ሁላችንም እንፈርበትና እንጸጸትበት » ሲል ተናግሯል ። እውነቱን ነው ። ሰውን መግደል ጀግንነት ሰዎችን በመከራ ላይ መጣልና

መልካሙን አኗኗር መበጥበጥ የወንድነት ሙያ ሰዎችን እየዘረፉ ካስፈላጊው በላይ የሆነ ሀብት መሰብሰብ ባለጸግነት ፣ ሽፍጥ ፣ ማጭበርበርና ማታለል የፖለተካ ችሎታዎች ሌሎችም የረከሱ ተግባሮች መልካም ሥራዎች የሚባሉበትን ጊዜ ሁሉም ሰው በዕፍረትና በጸጸት ሊያስታውሰው ይገባል። ሁላችንም በተለመደውና በጊዜ ብዛት ሰፊና ቅን መስሎ ሊታይ በቻለው የድንቁርናና የአውሬነት መንገድ ከመጓዝ ይልቅ የከፋት ጫካ ባጠበበው ልናሰፋው በሚገባን የሰውነት መንገድ እንሂድ ። ቅዱስ ጳውሎስ « አሮጌውን ተዉት አዲሱንም ልበሱት » እንዳለው በሰው ማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ተገቢ ቦታውን ገና ያላገኘውን አዲሱንና የማያልቀውን የእውነት መንገድ መከተል በግድ አስፈላጊ ነው። በእውነትና በመተማመን ፣ በፍቅርና በመተዛዘን ፣ በዕኩልነትና በወንድማማችነት ያልተገኘውን ፀጥታና ሰላም እንዲሁም የደስታ ኑሮ በብልጠትና በተንኰል እናገኘዋለን ብለው የሚደከሙ ፍጡሮች በዓለም ላይ እየበረከቱ ሲሄዱ ማየት አያሳዝንም? ዘመኑ የሥልጣኔ ዘመን ተብሏል ። ሕዝቦችም የሠለጠኑ ተብለዋል ። ግን ብዙዎቹ ሰዎች በድንቁርና በበሽታና በችግር እስካሁን የሚሠቃዩበት ከመሆኑ በላይ በፍርሃት በኑሮ ውድነት በመስገብገብ በሽፍጥ ከሰላም በራቁ ወሬዎች እንደዚህ ዘመን ሰዎች የተሠቃዩበት ጊዜ ያለ አይመስልም ።

« ዲሞክራሲ » የሚሉት ውቡ ዓይነት አገዛዝ በመላው ዓለም ባሉ ባለሥልጣኖች አፍ ይሞገሳል በግብር የዋለበት አገር ግን ጨርሶ የለም ። የዓለም የዲሞክራሲና የነፃነት መንፈስ የሚመነጨው ከኔ ነው የምትለው ዘመናዊዋ አሜሪካ ነጭ ሁኖ ያልተገኘን ፍጡር መፈጠር የሚቃወሙ የሌሎችን ኑሮና ሰላም የሚበጠብጡ ዘመናውያን አውሬዎችዋ ከእውነተኞችዋ ስለሚበዙ በዚህ ወሬዋ ልትኮራበት አልቻለችም ።

በዘመናችን « ምሥራቅና ምዕራብ » ከሚባሉ አቅጣጫዎች ጋር በሁለት ስም በሚጠሩ የኮሚዩኒዝምና የካፒታሊዝም ተከታዮች መካከል « ዲሞክራሲ » የኛ ነው! የኛ ነው! የሚል ውድድር ስናይ ዲሞክራሲ የሚባል ነገር በየትም አለመኖሩን ከማስረዳት በቀር ሌላ ነገር አይገልጽልንም ።

መስኮባዊው ጠቅላይ ሚኒስትር ኒኪታ ክሩስቼቭ ከምዕራባውያን የማጐርፈው « ጨቋኞች የግል ነፃነት ጠላቶች » የሚባለው ስድብ ቢያሰለቻቸው « ቀምቶ በይዎችና ነጣቂዎች የሆኑ ምዕራባውያን ካፒታ

ሊስቶች ነፃው ዓለም እያሉ የሚጠሩት ጥቂቶች ቀማኞች ተራውን ሕዝብ ለመዝረፍ ነፃ የሆኑበትንና አብዛኛው ሕዝብ ለመዝረፍ ነፃ የሆኑበትንና አብዛኛው ሕዝብ ጥቅሙን ለመጠበቅ ድምፁንም ለማሰማት የማይችልበትን ዓለም ነው » ሲሉ ተናግረዋል ።

ነፃነትና ዲሞክራሲ በአንድ ነገር ብቻ የማይወሰን ሲሆን ባንዱ በኩል « እየበሉ ጭጭ »ባንዱ በኩል « ተቀምተህ ጩህ! » የሚባሉት እምነቶች ለሰው ፍላጐትና ለእውነተኛ ዲሞክራሲ በቂ አድራጐቶች አይደሉም ።

ይህንንና የቀሩትንም ቊጥራቸው የበዛ ሁኔታዎች በዘመናችን እያየን የሰው ልጆች ጠቅላላ ዕድል በሙሉ አለመቃናቱን መረዳት አይሳነንም ።

ስለዚህ ስለሰው ዘሮች ችግር የምጽፈው ነገር ሁሉ አንዱን አገር ወይም አንዱን ትውልድ ብቻ ከሚመለከት አስተያየት ጥቂት ሰፋ ያለ መሆኑን እንደምትረዱልኝ ተስፋ አደርጋለሁ ።

ከዚህ ቤላ ስለመጽሐፉ ዋና ፍሬ ነገር እንመለስ ። መጽሐፉ ልብ ወለድ ሁኖ መንፈሱ አንድ ሰው ከናቱ ሆድ ጀምሮ ጥንቃቄና ምቾት የሚፈልግ ሲሆን ብዙዎቹ የሰው ዘሮች በድኅነት ተወልደው በድኅነት አድገውና ኑረው በድኅነት እስከሚሞቱበት ጊዜ ድረስ የሚደርስባቸውን መከራ በጥብቅ ይቃወማል ።

መከራውንና ችግሩን እንዲቃወም በዓለም ላይ ያለውን መብትና ድርሻ ከነፃነቱ ጋር እንዲጠብቅ የተደረገው ባለ ታሪክ ከናቱ ሆድ ሳይወጣ « አልወለድም! » በሚል ቃል ከጀመረበት ቀን አንሥቶ በሀገሩ የተቋቋመ አዲስና ተጠራጣሪ መንግሥት ሞት ፈርዶበት ትንፋሹ በግንባሩና በደረቱ ላይ ባረፉት ጥይቶች እስከተቋረጠበት ጊዜ ድረስ እንዲጋደል ተደርጓል ።

ምናልባት ሕፃን ከናቱ ሆድ ጀምሮ ለመብቱና ለነፃነቱ ተሟገተ ሲባል ፍጹም ልብ ወለድ ይሆንባቼል ። እውነት ነው ሕፃን በሚወለድበት ጊዜ ዐወቀና ተከራከረ ማለት ቀርቶ ካደገም ቤላ ሳያውቅ የሚቀር አለ ሊባል ይቻላል ። ግን ደራሲው የጀመረው አንድ ሕፃን የሚወለደው ለመከራ

መሆኑን ቢያውቅ ከናቱ ሆድ እሺ ብሎ ይወለድ ኑሮ ይሆን? አንድ ሕፃን ማንኛውም ክፉ ነገር ሲደርስበት ያለቅሳል ሲታመምና ሲንገላታ ይከሳል ይደገድጋል በሕመም ስሜትም ይሠቃያል ግን አይናገርም በሚል ስሜት ስለሆነ ለማሙዬ! ወይም ለማሚቴ እኔ ልናገርላቸዋ!

ለደሀ ሕፃን ዓለም እንዴት ያለች መራራ መሆኗን የፍጹሟ ደሀ ልጅ ከሆድ ውስጥ ጀምሮ እንዲናገር ላድርገዋ!

እሱው ይናገርላችሁ! ይኸው መንገዱን ለቅቄለታለሁ ።

አቤ ጉበኛ ።

# 1

ወደዚህ ዓለም መጥቼ ከዓለም እስክወገድ ድረስ አንዳችም ወንጀል አልሠራሁም። ሰዎች ግን በዓለም ተደርጎ የማያውቅ ወንጀል እንደሠራሁ ይቈጥሩኝ ነበር። ይህ የሆነበትም ነፃነቴን ከወገኖቼ ነፃነት ጋር ያለመጠን እወድ ስለነበርና ለዚህም ብዙ እንግዳ ነገሮች ስለ ሠራሁ ነው ።

ወንጀለኛ ከሆንሁ ለወንጀሌ ኃላፊው ከነፃነት ስሜት ጋር የፈጠረኝ ፈጣሪ ነው። ወደ ዓለም መምጣቴ ኃጢአት ከሆነብኝም በኃጢአቴ የሚጠይቀው ወደዚህ ዓለም ያመጣኝ ኃይል ነው ። እኔ ግን ወደዓለም እንድመጣ ማንንም አልጠየቅሁም። ወላጆቼ ወይም ፈጣሪዬ ወደዚህ ዓለም እንድመጣ ፈልገው እንደሆነ አስቀድመው ወደዓለም መጥቼ ካለም እስክወገድ ድረስ በሰላም በፍቅር በደስታ ከሁሉም ይልቅ በነፃነት ልኖር የምችልበት ዕድል ማዘጋጀት ነበረባቸው ። ይህን ስላላገኘሁ ግን በዓመፅ ተወልጄ በዓመፅ ሞትሁ ። እንደ ሳጥናኤል ትዕቢተኛ እንደአዳም ስሕተተኛ እየተባልሁ ስረገም ኖርሁ ። እኔ ከዓለም ብዙ ነገሮችን አልፈለግሁም። የፈለጌቸው ጥቂትና ርካሽ የሆኑ ነገሮች ነበሩ ። የምተነፍስበት ነፃ ዓየር የምኖርበትና ሠርቼ የምጠቀምበት ነፃ ምድር የምጠጣውና የምታጠብበት ነፃ ውሀ ከኔ ቀድመው የተወለዱ ተመራምረውና ተምረው ያገኙትን ነፃ ጥበብና ዕውቀት ብቻ በቀላሉ ለማግኘት ፈለግሁ። ተገድጄ ላደረጌቸውና አስገድጄ እንዳስደርጋቸው ለታሰቡብኝ ነገሮች ግን ፍጹም ተቃዋሚ ነበርሁ። ወንጀሌም ይኸ ብቻ ነው ። ከናቴ ሆድ ውስጥ ጀምሮ የሠራሁትን እንግዳ ሥራ ስታዩ አንድ በሰው ሕይወት ላይ የተፈጸመ ተአምር ታያላችሁ ። በክፋት መንገድ ስትተረጉሙት « ይህ ሰው የዲያብሎስ ዲቃላ ነው » ብላችሁ ለማመን በደግ ስትተረጉሙት ግን እግዚአብሔር በነፃነት ክብሪት ለኩሶ የፈጠረው ሕይወቱን እያቃጠለ ለሰው ልጆች የነፃነትን ብርሃን የሚያሳይ የነፃነት ጧፍ ነው » ብላችሁ ለማመን እንደምትገደዱ አምናለሁ ።

ከሰው ልጆች ታሪክ ጋር ፈጽሞ የማይመሳሰለው የሕይወት ታሪኬ ሰሚዎችን ሁሉ ለማስደንገጥ የበረቀ ድንገተኛ መብረቅ ነው። የመብረቁ ጸዳል ብልጭ በሚልበት አጭር ጊዜ የዓለምን ኗሪዎች መልክ አሁን ከምታዩበት ሁኔታ የተለወጠ አድርጎ እንደሚያሳያችሁ ሙሉ በሙሉ አምናለሁ ።

ከኔ ምስክርነት ይልቅ ራሱ ታሪኩ እንዲመሰክርላችሁ እነሆ ታሪኬን አቀረብኩላችሁ ።

# 2

ሥርዓቱን ማን እንዳቃወሰው አላውቅም። እግዚአብሔር ይሁን ሰው ወይም የተፈጥሮ ጣጣ ማን እንዳበላሸው አልተረዳሁም። ግን ሥርዓቱና ለኛ ተገቢ የሚመስለን ነገር ሁሉ በተመሰቃቀለበት ዓለም ሰዎች ሁሉ ይኖራሉ ።

እኔ የተወለድሁባት ኢይዝራኤሎስ የተባለቺው ደሴት በወራሪዎች ስትበዘበዝና ስትጠቃ ስትገዛም ኑራ ነፃነቷን ካገኘች ቤላ ራሷ የተበላሸች አገር ነበረች። ይህች በታላቅ ውቅያኖስ የተከበበች አገር ዋና ከተማዋ አቃኒዮ የምትባል ስትሆን እኔም የተወለድሁት በዚችው ከተማ ነው ። ከተማዋ የተመሠረተችው በባሕር ጠረፍ ላይ በመሆኑ በኰንትሮባንድ መርከብ እየተጫኑ ያለይለፍ ወረቀት የገቡ የውጭ ዜጐች እንዲሁም ለረጂም ዘመናት ቅኝ ግዛት ሁና በኖረችበት ጊዜ እንደልብ የገቡ የባዕድ ተወላጆች ታላላቅ ባለሀብቶች ሁነው ይኖሩባት ነበር ።

ከተወላጆችዋም አልፎ አልፎ ብዙ ሀብት አንቆ ያዡ ሲኖሩ አብዛኛው ሕዝቧ ደሀ ነበር። ከተማዋ ልዩ ልዩ ቀለም ባላቸው ሕዝቦች ብቻ ሳይሆን ቁንጣን ፣ ራብ ፣ ስካርና ጥማት ከልክ በላይ የሆነ ድሎት በሽታና ችግር ተባብረው በሚያጠቋቸው የተለያዩ ሰዎች የተመላች ነበረች ።

ከሚፈለገው በላይ የሆነውንና ለአብዛኛው ሕዝብ የሚበቃውን ብዙ ሀብት የያዙ ባለሀብቶችና የአብዛኛውን ጊዜ የዕለት ምግባቸውን በሕልምና በማሽተት ካልሆነ በቀር በሌላ መንገድ ለማግኘት የማይችሉ ፍጹም ደሆች ነበሩባት ።

ሌላው ሁሉ ቀርቶ ለሁሉ እኩል ተብሎ የተደነገገው ሕግ እንኳ ባፈጻጸሙ እንደ ሰዎች ሁኔታ የሚሄድ ነበር ።

አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ተወላጆች በእኩልነትና በነፃ የሚያገኙት ዓየርንና የፀሐይ ብርሃንን ብቻ ሲሆን የቀረውን ነገር በመጠኑ እንኳ ለማግኘት ብዙ ድካምና ራስን ለባርነት አሳልፎ መስጠት ነበረባቸው።

ባጭሩ በተፈጥሮዋ ከማንኛውም መልካም አገር የማታንሰው ደሴት ከጥቂቶቹ ሀብታሞቿ ጋር ሲያይዋት መንግሥተ ሰማያት ከብዙዎች ድሆችዋ ጋር ሲያይዋት ገሐነመ እሳት መስላ በሁለት ተቃራኒ መልኮች ትታይ ነበር ።

በዚች ሁኔታዋን ለመግለጽ ቃላት በሚያጥሩብኝ ደሴት ዋና ከተማ ከሀገሯ ፍጹም ድሆች አንዷ የሆነች ሴት ነበረች ሴትዮዋ የምትኖረው ከጧት እስከ ማታ ከከተማዋ ታላላቅ መንገዶች ባንዱ ተቀምጣ በመኪና ሳይሆን በእግሩ ከሚጓዘው አላፊ አግዳሚ ምፅዋት እየጠየቀች በምታገኘው የሳንቲም ልቃሚ ነበር። እሁድ እሁድና በሌሎች የበዓላት ቀኖች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሂዳ ከመሰሎቿ ጋር እየተጋፋች ትለምን ነበር ።

መፈጠራቸው በቍጥር ለማሟላትና ሌሎችን ለማገልገል ብቻ ሁኖ ከቀረው ደሆች ከሀገራቸው ጠፍና ሰፊ መሬት ለአንድ ጠማማ ጐጆ መቀለሻና ጭሮ ቆፍሮ የዕለት ሆድ ለመሙሊያ የሚሆን ጭብጥ አፈር ከሌላቸው ምስኪኖች አንዷ የሆነቺው ይህች ሴት በዓለም ላይ ብዙ ሴቶችን አካላቸውን በመሸጥ ሊያስተዳድራቸው የቻለው በቂ ውበት ባይኖራትም ከአስቀያሚነት ያመለጠ መልክና ውብ ጠባይ ብቻ ለሚፈልግ የሷ ቢጤ ባል የምታንስ ሴት አልነበረችም ። እንዲያውም ጮሌ ባትሆን ነው እንጂ ጮሌ ብትሆን ኑሮ ጠጉርን በየጊዜው በማጋየት ፊትን በቀለምና በዶቄት በመለቅለቅ ባንጸባራቂ ጌጣጌጦች ቂጥንና ጡትን አፍጥጠው በሚያሳዩ ልብሶች በኤሌትሪክ ብርሃንና በሌላም ዘዴ ሰው ሠራሽ ውበት ከሚያገኙት ሴቶች ጋር በመወዳደር የአካል መሸጡ ገበያም እስከዚህ ባላመለጣት ነበር ።

ነገር ግን በዚህ ፈንታ የማይታጠበው የማይበጠረውና የማይቀባው ጠጉሯ በላዩ ከተሰራጨበት አቧራ ጋር ካፈር ላይ ወድቆ የኖረ ቡርሽ ይመስል ነበር ።

ችግርና ብርድ ቀለሙን የለወጠው ፊቷ ደህ መሆኗ ሁኔታዋ ባያጠራጥር በብዙ የፊት ዶቄት ፊቷን ያጨማለቀች ሴት ያስመስላት ነበር ።

የለበሰችው ልብስ መቆሸሽ ላይን ከማስቀየሙ በላይ ንጽሕና ማጣት አደገኛ በሽታን ያስከትላል የሚባለውን የሀኪሞች ትምህርት የሚያስተባብል ነበር። በየጊዜው የሚወርድባት ብርድ ምንም ስላላደረጋት የብርድ በሽታ ድሆችን ንቆ ትቷቸዋል ለማለት ያስገድዳል።

ይህች ምስኪን ሴት ዓለምን በምን ስሜት እንደምትወደው አይታወቅም እሷም እንደሌሎች ሞትን ስትፈራና መኖርን ስትፈልግ ትገኝ ነበረች ። ለሰሚው ግራ ነው። ከዚህም አልፋ ከወንዶች ጋር ትቃረብ ኑራለች። ይህስ ይቅር የተፈጥሮ ጣጣ ነው ። የሚገርመው አንድ ቀን እኔን አርግዛ ኑራለች። እኔን አርግዛ የመውለጃዋ ቀን በደረሰበት ጊዜም እንደልማዷ የዕለት ራቷን ለማግኘት በአንድ ታላቅ መንገድ ዳር ተቀምጣ ስትለምን ውላለች። ማደሪያዋም ያው የመንገድ ዳር ስለሆነ እዚያው አምሽታለች ።

በመንገዱ የሚወጡ የሚወርዱትን መኪናዎች በመንገዱ ግራና ቀኝ በቆሙት ዓምዶች ላይ ባሉት ታላላቅ አምፑሎች የሚበራውን የኤሌክትሪክ ብርሃን እጅ ለጅ ተያይዘው የሚንሸረሸሩትን ሴቶችና ወንዶች ግራና ቀኝ ያሉትን ታላላቅ ፎቆችና የቀሩትንም ብዙ ትርእይቶች እየተመለከተች በጥጓ የሚያልፍ እግረኛ ስታገኝ « ስለመድኃኔ ዓለም » እያለች ትለምናለች ።

በሆዷ ውስጥ ሰሚዎችን ሁሉ የሚያስደነግጥ ዜና ያለኝ አደገኛ ፅንስ መኖሬን ግን በጭራሽ ረስታዋለች ።

አንድ ሰው በጥጓ ሲያልፍ ስለመድኃኔ ዓለም አለቺውና ሳን+ም ሲሰጣት ከጅዋ ላይ ከነበረው ሌላ ሳን+ም ጋር ተጋጭቶ ቅጭል ሲል በሆዷ ውስጥ ከተኛሁት እንቅልፍ ብንን አልሁ። ከእንቅልፍ መንቃት ብቻ አይደለም። ከድንቁርና ስሜትም ነቃሁ ።

ማን እንደሆነ ያላወቅሁት ኃይል ምኞትና ነፃነት ወደሌለበት ዓለም የምሄድ መሆኔን እንዳውቅ አደረገኝ። ስንት ስፋትና መጠን ያላት ዓለም አሁን ከምገኝባት ጠባብ ሆድ እጅግ የምታንስ መሆኗን አሳወቀኝ። ሙሉ ነፃነቴን እንደያዝሁ ባለሁበት የናቴ ሆድ ውስጥ ፍርግጥግጥ አልሁ ። ሆዷንም በርግጫ ደበደብሁት ።

« አዬ ፍዳዬ! እዚሁ ላይ ደረሰብኝ መሰል! ነገሩማ ወዴት ልደርስ ኑሯል? » አለች በቀላሉ የምወለድ መስሏት ።

« በጭራሽ አልወለድም » አልሁ በጩኸት ፡፡ እሷም ሆዷ እንደተለመደው ጩርር ያለ መስሏት ነበር እንጂ እንደዚህ ያለ በሰው ታሪክ ውስጥ እንግዳ የሆነ ነገር ይሆናል ብላ አልተጠራጠረችም ፡፡ በሆድ ውስጥ ሁኖ የሚናገር ሕፃን? ማን ሊጠረጥር ይችላል? ለኔም ለራሴ ማመን ያስቸግረኛል ፡፡

« ደኅና ቦታ ልያዝ መሰል » አለች ከመንገዱ ወዳለው የካብ አጥር ሥር ጠጋ እያለች ፡፡

« በፍጹም አልወለድም » አልሁ አሁንም ጮኽ ብዬ ፡፡ ነገሩ ግራ ሆነባት ወዲያና ወዲህ ፊቷን እያዞረች ሰው እንዳለ ማየት ጀመረች፡፡ ከዚያም ቀጥላ « ወይ ግሩም! ሰይጣን ጠራኝ ልበል? » አለች ፡፡

« አዬ! ደግሞ የምን ሰይጣን? እኔ ነኝ ፡፡ አልወለድም » አሌት ፡፡ ወደሆዷ አንገቷን ዝቅ ደረገችና « አንተ ማነህ? » አለች በታላቅ ፍርሃትና ጭንቅ ፡፡ እንግዳው ነገር የተሠራው በሆዷ ውስጥ ሆነና የምታመልጥበት ዘዴ ባይኖራት እንጂ በዚህ ጊዜ ልቧ እስኪፈርስ ብትሮጥ በወደደች ፡፡

« እኔ በሆድሽ ውስጥ ያለሁት ልጅ ነኝ » አሌት ፡፡

« ታዲያ ለምን አትወለድም? » አለች ፡፡

« ተወልጄ በችግር መሠቃየት አልፈልግም ፡፡ »

« እኔ በተቻለኝ መጠን አሳድግኻለሁ ፡፡ »

« ሊያኖረኝ የሚችል ሀብት አለሽ? »

« እንደዚሁ ለምኜም ቢሆን አሳድግኻለሁ ፡፡ »

« ሞት ይሻላል! እኔ ማን መሰልሁሽ አንቺ?

ልመናን ተማምኜ ነው የምወለድልሽ? በገዛ ሀገርሽ ላይ የምትችይውን ሥርተሽ በመኖር ፈንታ እንዴት ልመናን ተስፋ አድርገሽ ትኖሪያለሽ? ያንቺ በዚህ ሁኔታ መጐሳቆል አንሶ ደግሞ ማደጊያ የሌለው ልጅ ለምን ትወልጃለሽ? »

« ተፈጥሮ ያመጣብኝ ጣጣ ነው እንጂ እኔማ ምን አደረግሁ? »

« ተፈጥሮ! ተፈጥሮማ ራስሽን ችለሽ እንድትኖሪ ፈቅዶልሽ ነበር ። ብቻ ቀማኞች ሁሉን ነገር አመሰቃቀሉት እንጂ ። የቻልሽውን ያህል ለመሥራት ለምን አትሞክሪም? »

« በገረድነት እሠራ ነበር ። የሳንባ በሽታ አለባት ብሎ ሐኪም ስለተናገረ በሽታው ወደ ጌታዬ ቤተሰቦች እንዳይተላለፍ ወዲያው አስወጡኝ »

« እሺ መሬት አለሽ? »

« የለኝም ። »

« ቤት አለሽ? »

« የለኝም ። »

« ትምህርት አለሽ? »

« የለኝም ። »

« ታዲያ ምን አለሽ? »

« ምንም የለኝ ። »

« ታዲያ ድኅነትን በሽታንና ድንቁርናን ልታወርሺኝ ነው ተወለድ የምትዩኝ? »

« ዕድልህን እንዴት ታውቀዋለሁ ልጄ? » አለች በትካዜ ።

« ቀማኞችና ነፍሰ ገዳዮች እንዲሁም የነፃነት ጠላቶች በሠለጠኑበት ዓለም ደግሞ ምን ዕድል አለ? የድሆችን ልጆች የሚጠብቃቸው የወላጆቻቸው መከራና ችግር ብቻ ነው ። መከራንና ችግርን ከድሆች ትክሻ ለማውረድ እንደኔ ከሆድ ውስጥ ጀምሮ ለመብትና ለነፃነት መሟገት ያስፈልጋል » አሌት

በቀጥ። ነገሩም ግራ ሆነባት በዚህ በሆዷ ዓለም የተደረገው ተአምር በውንና በሕልም መኖሯን ለይታ ለማወቅ አላስቻላት አለ ። በመንገድ ላይ

ሁና ብርድ ይውረድባት ወይም በገነት ላይ ትሁን ምኑንም አታውቅም ነበር። ቢሆንም አንዴ የገባችበትን ክርክር በመቀጠል

« እንግዲህ መቸስ ምን ይሆናል ተወለድ እንጂ! » አለችኝ ።

« አልችልም! » አልሁ ። ቀጠል አደረግሁና « ይልቁንስ መርዝ ጠጪና ሁለታችንም እንሙት ። አንቺም ዓለምን ወደሽ ሞትን መፍራትሽ ነው? አንቺ ሙቶ ከማረፍ እየተሠቃዩ መኖርን ትመርጪ እንደሆነ እኔ ለሥቃይ ከመኖር መሞትን እመርጣለሁና የሚያስወርድ ነገር ጠጪልኝና ሙቼ ከሆድሽ ልውጣልሽ » አሌት ።

« ምነው ልጄ? ነፍስ ገደልሽ! ተወልዶ ዘራችንን የሚያበዛውን ልጅ ቀጨሽ ብለው ያሥሩኛል ይቀጡኛልኮ! » አለች ። « እህ! አዎ! እነማን ናቸው እንደዚያ የሚሉ? የኛ መጐሳቆል ለነሱ መቀማጠል ማዳመቂያ እንዲሆን የሚመኙት ግፈኞች! እነዚያ ጉልበታችንንና ባርነታችንን እንጂ ሰው መሆናችንንና ነፃነታችንን የማይወዱ ቀማኞች ናቸው ለኔ ሕይወት የሚቆረቆሩ? እነዚያ በሰው መከራ የመደሰት ሱስ የያዛቸው ጨካኞች ናቸው ለኔ ሕይወት ጠበቆች ነን የሚሉ? ለሰው ሕይወት አሳቢዎች ከሆኑ ለኛ ገና ላልተወለድነው ከማሰብ ለምን የተወለዳችሁትን በወግ አይዟችሁም? » አልሁ በቊጣ ። የቊጣ ንግግሬንም ቀጠልሁና « ወደፊት የሚወለዱ ሕፃናት ሁሉ እንደእኔ በሆድ ውስጥ ሁኖ የማወቅ ጸጋ ቢሰጣቸውና የመገናኛ ዘዴ ቢኖረኝ « ያለመወለድ አድማ » እንዲፈጥሩ ባነሣሤቸው ነበር ። ኖ ደሆች ሕፃናት አትወለዱ! የሚጠብቃችሁ ርስት ችግር በሽታና ድንቁርና ነውና ። ዓለም በትክክለኛና አድልዎ በሌለበት ሕግ እስክትመራ ፤ ሰላም ፤፤ ነፃነት ፤ እኩልነት ፤ ፍቅርና ወንድማማችነት በዓለም ላያ ያላቸውን ቦታ እስኪያገኙ አትወለዱ! እላቸው ነበረ ። የያንዳንዱ ሰው ተገቢ ድርሻና የመኖር ዕድል እስኪታመን ድረስ በሆድ ውስጥ ቆዩ ወይም ሳትወለዱ ሙቱ! እያልሁ አስተምራቸው ነበር! » ስል በፍርሃት ትንቀጠቀጥና ትሸበር ነበር ። ነ

ሰውነቷ ሲንቀጠቀጥ እኔንም ስለጐጨጐጨችኝ ሁኔታዋ ገባኝ እጅግም አሳዘነችኝ ።

« ለምን ትንቀጠቀጫለሽ? » አሌት ።

« በፖለ+ካ እንዳንታሠር ፈርቼ ነው! » አለችኝ ።

« እንግዲህ እንድወለድ የምትፈልጊው እንዳንች ያለች የምትበላው ምግብ የምትጠጋበት ቤት የምትለብሰው ልብስ እንኳ የሌላት ምስኪን ሴት በሥቃይዋ የማዘን ነፃነት ባላገኘችባት ዓለም እንድጨማለቅ ነው? ተዪው እናቴ! ምንጊዜም ቢሆን ለባርነት እንደማልወለድ ዕወቂ! » አሌት ጥቂት ዝም አልሁ ። እሷም በፍርሃትና በጥርጣሬ ተውጣ ዝም አለች ። የተነጋገርነው ሁሉ ዐብዳ ወይም ቃዥታ የታያት ነገር መሰላት ። ይህን ራእይ እውነት ነው ብላ ለማመን ተሳናት። እንደሷ ያሉ ድሆች የወለዷቸው ልጆች ተወልደው አድገው አርጅተው እስኪሞቱ የማያስቡትንና የማይናገሩትን ነገር ገና ተወልዶ ባራትና ባምስት ዓመቱ አፉን እያኮላተፈ በልመና ይረዳኛል ብላ ስትጠብቀኝ የነበርሁት ፅንስ ከሆድ ከመውጣቴ በፊት ዐውቄ እንደዚህ ያለውን የነፃነት ንቅናቄ ስጀምር ምን ይሰማት! በድንጋጤ አለመሞቷም እንዲያው ሞቱም ንቆ ችላ ቢላት ነው!

« መልካም! ሙሉ ነፃነትስ አለሽ! » ብዬ ጠየቄት ።

« አዎ! ነፃ ነሽ ይሉኛል » ብላ መለሰችልኝ ።

« አይርብሽም ፣ አይጠማሽም? »

« ይርበኛል ፣ ይጠማኛል ። »

« አይበርድሽም ፣ ሙቀትም አያቃጥልሽም? »

« ይበርደኛል በፀሐይ ጊዜም ሙቀት ያቃጥለኛል ።

« እሺ ሰዎች የሚፈልጉትን ሁሉ ለማግኘት ምኞት የለሽም? »

« እሱስ ነበረኝ ላገኘው አልችልም እንጂ! »

« አሁን የምትፈልጊው እኔም ተወልጄ አንቺ ስትሞቺ ያለም መከራና ሥቃይ መድረሻ አጥቶ እንዳይጠፋ እኔን ተክተሽለት ልታልፊ ነው! ለመሆኑ አባቴስ ማን ነው? »

« እኔ በገረድነት እሠራበት በነበረው ሰውዬ ቤት ባሽከርነት ይሠራ የነበር ሰው ነው ። አሁን ግን የደረሰበትን አላውቅም! »

መልካም! እሱም እንዳንቺ መድረሻ ያጣ ደሀ ነው ማለት ነው? ታዲያ የሁለት ደሀ የሁለት አገልጋይ ልጅ ልማድና እምነት ባመሰቃቀለው ዓለም መጥቶ ምን ሊሠራ? የናቱን ያባቱን ችግርና መከራ ሊወርስ? ለሰዎች ባሪያ መሆንና ተቸግሮ ማለፍም ሥራ ሁኖ ለዚህ መወለድ? በፍጹም አልወለድም! አንቺም መሞት አለብሽ! »

« እኔስ ሞትን እፈራዋለሁ ። »

« መልካም! መልአከ ሞት ጥርሱን አግጥጦ ዓይኑን አፍጥጦ መጥቶ በረጂም ጥያቄና መልስ ያሠቃይሻል የሚል ተረት ስላደነዘዘሽ ሞትን ትፈሪዋለሽ! ሀብታሞች ካቀማጠለቻቸውና ከሚወዷት እናንተን ባሪያ አድርጋ ካስገዛችላቸውና ከሚደሰቱባት ዓለም ስለሚነጥላቸው ሞትን ቢጠሉና ቢ>ያማርሩ እናንተም ድሆች የነሱ ማሚቶዎች ሁናችሁ ሞትን ማማረራችሁ ነው? » አሌት ። በታላቅ ስሜትም ድምፄን ከፍ አድርጌ « ሞት የድሆች ወዳጅ መሆኑን ዕወቂ! ድሆች ፣ ግፈኞች ከጫኗቸው ቀንበር ነፃ የሚሆኑት በሞት ብቻ ነው ። በሽታ ፣ ችግርና ድንቁርና የሚያሠቃያቸው መከረኞች ከመከራቸው ነፃ የሚወጡት ለሙብታቸው ሲጥሩ ወይም ሲሞቱ ነው ። »

« ሞት! ሞት! ሞት! ሞት!

አንተ ስመ - ክፉ ሥራህ ግን ደግነት!

የድሆች ነፃ አውጪ የእውነት ነፃነት የንቅልፍ ታላቅ ወንድም የዘለዓለም ዕረፍት ፍጡራን በሐሰት ስለሚደለሉ ፣ ደሀም እንደ ሀብታም አንተን ጠላህ አሉ! »

ይህን ስናገር አሽባሪው ንግግሬ ግራ አገባትና « ለካ! በዚህ ባዶ መንገድ ዳር ሳድር ሰይጣን አስረግዞኝ ኑሯል! » አለች እያለቀሰች ።

እኔም እጅግ ስለራራሁላት « እናቴ በመሆንሽ ከዚያም በላይ ደህ ስለሆንሽ አዝንልሻለሁ ። ነገር ግን ራስሽ መብትሽን የማትጠብቂ ሁነሽ ለሌሎች ደግሞ ባርነትን ስለምታስተምሪ መሞት አለብሽ! » አሌት ።

እሷም በመጥፎው ዕድሏ አምርራ ታለቅስ ጀመር ። ያለቀሰችውም ጥቅሙን ያላወቀቺው የነፃነት ነበልባል የሚያነደኝ ፅንስ በሆዷ ስላገኘች እንጂ በእርግጥ የበደላትን መከረኛ ኑሮ በማስታወስ አልነበረም።

# 3

ይህን በመሰለ ጭቅጭቅ አደገኛ የሆንሁት ፅንስና ደሀዋ እናቴ ስንሟገት ብዙ ጊዜ ካጠፋን ቤላ « የምችል ብሆን በዓለም የሚገኘውን ነገር ሁሉ አድርግልኝ ብትዩኝ አደርግልሽ ነበር ። ባርነትን ተቀበል ለባርነት ተወለድ ብለሽ የምታቀርቢውን ልመና ግን እንኳን አንድ ጊዜ መቶ ጊዜ ብትሞቺ እሺ አልልሽም» አሌት ።

« ታዲያ ምን ይሻላል? »

« መብትሽን ለማግኘትና እኔንም ከነመብቴ ለመውለድ ሞክሪ! »

« እንዴት እችላለሁ? »

« ካልቻልሽ እንሙት ። »

« ዋረ ስለፈጠረህ ብለህ ተወለድ! »

« ፈጣሪም የፈጠረኝ ለባርነትና ለችግር ከሆነ እሱንም አሻፈረኝ ብየዋለሁ ። ግን እሱ እስከዚህ ቂል አይደለም ። እሱ የነፃነት ዓለም ፈጠረ ። ግፈኞች ነፃውን ዓለም የባርነት ዓለም አደረጉት። ቂሎችና ደካሞችም ራሳቸውን የባርነት ማስፈሪያ ወደብ አደረጉት። መልካም! ባርነትን የሚሹ ባሪያ ይሁኑ! የነፃነት ጠበቃ ስሆን « ባሪያ የመሆን ነፃነት » ይሰጠን የሚሉትንም የወደዱትን ባርነት እንዲጠግቡት መተው አለብኝ ። እኔን ወደ ባርነት ግባ ሲሉኝ ግን ታላቅ ጠብ መፈጠሩ ነው! ስለዚህ ኖ አሻፈረኝ

ለባርነት አልወለድም! » ብሏል በይ! ሰውን ለመወንጀልና እምቢተኛ ነው ለማለት ዳኛ ሞልቷል ። ዳኛ የማያገኙት ለነፃነት የሚሟገቱት ናቸው እንጂ ነፃነት ፈላጊዎችን ለመክሰስ የዓለም ፍርድ ቤቶች ሁሉ ክፍት ናቸው ክሰሺኝ ። እምቢ አለ በይ! » አልኳት ። ተስፋ ቢሷና ረዳት የለሽዋ እናቴ በዚህ ተአምር! በዚህ በዓለም ላይ ተሰምቶ በማያውቅ ደወል የአእምሮዋ ጆሮ ተሳቀቀ ። ያለችበትን ረሳች ። መፈጠሯም ሕልም መሰላት ።

ጨርሶ ዓለምን ዘነጋችና ድካሙ እስኪያሸንፋት ድረስ እየቃዠችና እየለፈለፈች እመሬቱ ላይ ተዘረረች ። እዚያው ተዘርራ እኔ ብቻ የምሰማውን ትንሽ ትንሽ ትንፋሽ እየተነፈሰች ተላላፊዎች ሰዎችም « አዬ! እዚህ ላይ ሰው ሙቶ ወድቋል መሰል! » እያሉ ሲያልፉዋት ብዙ ጊዜ ቆየች ።

# የመጀመሪያው እሥራቴ ።

ተገድጄና ታሥሬ የማልፈልጋቸውን ነገሮች መሥራቴ ተጀመረ! እናቴ በኔ ምክንያት ደክማ በወ ደቀችበት ጥግ ሁሉት የፖሊስ ወታደሮች ሲያልፉ በድንገት አይዋት ። መቼም እግዚአብሔርም እኔን ለማሠቃየት አሢሮብኛልና በዚሁ ጊዜ ፖሊሶች ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ደነገጡ ። ቶሎ ስልክ ደውለው በድንገተኛ አደጋና በሽታ የተጐዱትን ሰዎች ወደ ሆስፒታል ለማድረስ የተዘጋጀ መኪና (አምቡላንስ) እንዲደርስ ጠየቁ ። መኪናውም ቶሎ ደረሰ ። እነሱም ወደ ደሆች መታከሚያ ሆስፒታል ወሰዱን። የሆስፒታሉ ዋና ሐኪም ቶሎ ብሎ ለምርመራ ቀረበ ። የናቴን ሆድ በጁ እየዳሰሰ ሲያይ ጣቶቹን በርግጫ ለመስበር ፈልጌ ትንንሽ እግሮቼን አወናጭፌ ነበር። ግን በከንቱ የደሀዋንና ራብ የጐዳትን እናቴን ሆድ አቈሰልሁ ። ወዲያው ራጂ እንድትነሣ አዘዘ! ወደ ራጂ ክፍል እንደሄድን የመመርመሪያውን መሣሪያ ብርሃን በዓይኔ ላይ ቡግግ ሲልብኝ « ዋረ ወይድ ዓይኔን እንዳታጠፋ! » አልሁ ። ግን የሰማኝ ያለ አይመስለኝም ። የራጁ ውጤት ያለቀደዳ (ኦፐራሲዮን) ልወለድ የማይቻል መሆኑን መሰከረብኝ ። ደሀዋ እናቴ በኔ ምክንያት ሆዷን መቀደዷ በጣም አሳዘነኝ ። ዝም ብዬ ልወለድላት ፈልጌ ነበረ። ግን ይህን ያሰብሁት ከሐኪም ትእዛዝ ቤላ ሆነ ። ሐኪሞችስ ዘመናውያን በኃይል ገዥዎች

(ዲክቴተሮች) አይደሉ « እኛ ከተናገርነው ውጭ እግዜርም ሊሠራ አይችል። የሕይወት ባለሥልጣኖች እኛ ነን ። » ብለዋል ። በዚህ ምክንያት ምንም ማድረግ ስላልቻልሁ በፖሊስ አስገዳጅነት በሐኪም ቀዳጅነት የሽፍትነት ዋሻዬ ወይም እንደእኔ አስተያየት የነፃነት ምሽጌ ከሆነው የናቴ ሆድ እንድወጣ ተገደድሁ ። እናቴ ሆዷን ልትቀደድ የማደንዘዣው መድኃኒት ተደርጎላት በድን ስትሆን እኔም እሷም ከዚህ ዓለም የባርነት ቀንበር ነፃ ወጣን ብዬ ደስ ብሎኝ ነበር ።

ግን ደስታዬ ከንቱ ኖሯል! ሆዷን ቀደው ከተደበቅሁበትና ሕይወቴ በዚያው እንዲያልፍ ከፈለግሁበት ዋሻ አወጡኝ። በሕይወት ዘመኔ ያየሁትን የተጨማለቀና አሳዛኝ ኑሮ ሁሉ ቁልጭ አድርጎ ያሳየኝን የዚህ ዓለም ብርሃን ለመጀመሪያ ጊዜ ሳይ ምንም እንኳ ሌላ ነገር ለማድረግ ዓቅም ባጣ እጅግ አምርሬ በማልቀስ ኃዘኔንና ቁጭቴን ለተመልካች አሰማሁ ። ወዲያውም ወደሐኪሙ እየተመለከትሁ « ቆይ ግዴለም አንተ ደደብ! መኖርን እንጂ ለመኖር የሚያስፈልገውን የማታውቅ ሟቹን አካል የምትጠብቅ የማይሞተውን መንፈስ ግን የማታውቅ በዚች ቀን አንተ አዋቂ ሐኪም ተባልህባት! እኔ ግን ወደማልፈ ልጋት መከራና ስቃይ አዘጋጅታ ወደምትጠብቀኝ ዓለም መጣሁባት። ዕውቀትህን አደንቃለሁ ። ሰውን በማገልገልህና ጊዜያዊ ሥቃይን በመከላከልህ አመሰግንኻለሁ ።

ነገር ግን በዓለም እስካለሁ ድረስ አብዛኛውን ጊዜ የሚያሠቃዩኝን ችግርን ፣ ድንቁርናን ፣ ግፍን ባርነትን ለመከላከል ቀርቶ መኖራቸውን ስለማታስብ ደደብ እልኻለሁ ። ለመሆኑ ከተደበቅሁበት ጉትተህ ስታወጣኝ ምግቤን ልብሴን ቤቴን አዘጋጅተህልኛል? ወይስ እንደ እናቴ በባዶ ሜዳ ላይ ልትጥለኝ ነው? » ብዬ ስጠይቀው ሽማግሌው ሐኪም ዐይቶትና ሰምቶት በማያውቀው ነገር በጣም ደነገጠና ከቆመበት ወደቀ እኔም ከጁ አምልጬ ወደቅሁ። ቆንጆ ጉረምሳ ካላየች በቀር በዓለም ላይ የሚያስደነግጣት ነገር የሌለ አንዲት ነርስ ምኑንም ሳታስተውል ቆይታ ሐኪሙና እኔ በወደቅን ጊዜ ቶሎ ብላ እኔን አንሥታ በጨርቅ ጠቅልላ አስቀመጠችና ሌላ ሐኪም ጠርታ ዶክተሩንም አነሡት። ሌላው ሐኪም የተቀደደውን የናቴን ሆድ ሰፍቶ ወደ መኝታ ክፍል እስኪልካት ድረስ ሌሎቹ የሕክምና ሠራተኞች በድንጋጤ ለታመመው ሐኪም አስፈላጊውን ርዳታ አድርገውለት ነፍሱን ዐውቆ ቆየ ።

ብዙ ሳይቆይ ከተኛበት ተነሣና «ምን ነበር ያየሁት ምን ነበር ያየሁት! » አለ ።

ከጥጉ የነበረው ሐኪምም « ቆይ! ጥቂት ቆይ! » አለው። የታመመው ሐኪምም መለሰና

« የለም የሆንሁትን ማወቅ አለብኝ? » አለ ።

« በጣም ደንግጠህ ወድቀህ ነወ » አለው ደኅናው ሐኪም ።

« በምን ምክንያት? »

« ኦፐራሲዮን አድርገህ ከናቱ ሆድ ያወጣኸው ሕፃን በጣም ስለወቀሰህ ። »

« እኸ! ገባኝ! ይህን ተአምረኛ ሕፃን ማየት አለብኝ ። »

« ተው ጥቂት ቆይ! »

« በፍጹም አልቆይም! »

ከዚህ ቤላ ታሞ የነበረው ሐኪም ተነሣና በጨርቅ ተጠቅልዬ ወደምልወሰወሰበት ክፍል መጣ። ትክ ብሎም ዐየኝ ። « እስከ ሦስት አራት ወር የናቱን ጡት መጥባት አለበት » ሲል በጥጉ ላለችው ነርስ ነገራት ።

« እምቢ! የናቴን ጡት አልጣባም » አልሁት ። ለምን? » አለኝ ።

የሳንባ ነቀርሳ (ቱቤርኩሎሲስ) አለባትና ታስተላልፍብኛለች በግድ አስወልዳችሁ በበሽታ እንድታሠቃዩኝ አልፈልግም » አልሁ ። በዚህ አዲስ ሁኔታ ሐኪሙ አሁንም ደነገጠ ። እንደመጀመሪያው አልወደቀም እንጂ አሁንም በመጠኑ አእምሮውን ሊስት ጀምሮ ነበር ።

ከጥቂት ጊዜ ቤላ እናቴ እኔ አለባት ስላልሁት በሽታዋ እንድትመረመርና ለኔ ግን ልዩ የሆነ የሕፃን ምግብ እንዲዘጋጅልኝ አዘዘ ። ከዚያም ቀጥሎ « ደግሞ ምን እንዲሆንልህ ትፈልጋለህ? » አለኝ። « እኔም ከዓለም እስከወገድ ድረስ ብዙ ነገር እፈልጋለሁ ። ካንተ የምፈልገው ግን የሰውን ጤንነት ብቻ ሳይሆን የሰውን ክብር የሰውን መብት ፣ የሰውን ነፃነት ፣ የሰውን ፍላጐት

ጨምረህ እንድታውቅ ነው ። ያለዚያ ታላቁ ጋንዲ እንደሰደባችሁ እሰድባቼለሁ ። እንዲህ እያልሁ! እነሱ የሥጋ ሐኪሞች እንጂ የመንፈስ ሐኪሞች አይደሉም! የሰውዬውን ሕይወትና ጤንነት ካልበደለ ወንዱ ሰብአዊ ክብሩን አዋርዶ የሴትነት ሥራ እንዲሠራና ተፈጥሮው በማይፈቅደውና የመንፈስ ክብሩን በሚያጠፋው መንገድ እንዲያመነዝር ይፈቅዱለታል ። ከዚህም ቀጥዬ ግዙፉን ሥጋዊ አካል ብቻ ሳይሆን ረቂቁን መንፈሳዊ አካልም ጠብቁት ። ፍላጐቱንም ለመስጠት የመንፈስ ሐኪሞች ጭምር ሁኑ! እላቼለሁ ፣ አልሁት። « የመንፈሳዊው አካል ምግብም ነፃነትና ዕኩልነት ያለው ኑሮ ነው! » ስል ለደነገጠው ሐኪም ነገርሁት ።

መካከለኛ ዕድሜ ያለው ሐኪም በግንባሩ በኩል የሳሳውንና ትንሽ ነፋስ ሲነካው ብልው ብልው የሚለውን ጠጉሩን በጁ ወደ ኤሊት እያስተኛ « ለመሆኑ ይህን በሕፃንነት ወራት ብዙ የማወቅ ኃይል ከምን አገኘኸው? ከየትስ ተማርኸው? » ሲል ጠየቀኝ ።

በጨርቁ እንደተጠቀለልሁ እንቅስቅስ እያልሁ « እናንተ በአካል ብቻ የምታምኑ! የነፃነት ፍቅር በአስተማሪና በግዙፍ አካል ብቻ ሳይሆን ሕይወት ካለው ፍጡር ሁሉ ስሜት ጋር ተቀላቅሎ የሚፈጠር ነገር ነው ። አውሬው ሲያቈስሉት እጅግ የሚበሳጨውና ታላቅ ጀብዱ የሚሰራው እንስሳው ልረድህ ሲሉት የሚፈራገጠው በናንተ ዩኒቨርሲ+ ውስጥ ስለነፃነት ጥቅም ያስተማረው ኑሮ ነው? የነፃነት ስሜት በደም ሕዋሳት ሁሉ ተሠራጭቶ አብሮ የሚፈጠር ነገር ነው ። ይልቁንም በተንኰል የተፈጠሩ ትምህርቶችና ስብከቶች ፍጡር ሁሉ በተፈጥሮ ያገኘውን የነፃነት ስሜት እየደመሰሱ ወደባርነት የሚያስተላልፉ ጠንቆች ናቸው ። በኃይል ከሚሰበር ኃይል ይልቅ በደም ውስጥ ያለውን የነፃነት ነበልባል እያበረዱ ለባርነት ምቹ ፈረስ የሚያደርጉ በሰዎች የተፈጠሩ ከንቱ እምነቶች ናቸው ። ስለዚህ ከናቴ ሆድ የነፃነትን ስሜት ይዤ ብወለድ አይግረምህ ደግሞም እግዚአብሔር ሰውን ከነፃነት ስሜት ጋር ለመፍጠሩ ምልክት እንድሆነው ያዘጋጀኝ ልዩ ፍጡሩ መሆኔን ማወቅ አለብህ » አልሁት ።

እንግዳ ትርእይትና ድንጋጤ በእውነት መኖሩን ያጠራጠረው ሐኪም ራሱን በተለመደው ሁኔታ ነቀነቀና « መልካም! እኔ የምችለውን ሁሉ

አደርግልኻለሁ » ካለ ቤላ « በጥሩ ሁኔታ አስተኝታችሁ አስፈላጊና ተስማሚ የሆነ ምግብ እንድትሰጡት » ሲል ለአንዷ ነርስ ትእዛዝ ሰጠ። ለብቻዬ ትንሽ የሕፃን አልጋ ተዘጋጀልኝና ተኛሁ ። በዚህ መንገድ ለሁለት ቀኖች በመልካም ሁኔታ እንደቆየሁ የፈራሁት ጥቃት መጣብኝ ።

# የመጀመሪያው አድልዎና አድልዎን መቃወሜ ።

ተገድጄ ከናቴ ሆድ በወጣሁ በሶስተኛው ቀን ጧት የሚያስፈልገኝ ምግብ ቶሎ አልሰጠኝ አለ ።

ነገሩ አድልዎ ኑሮበታል ። በሆስፒታሉ አንዲት ሀብታም ሴት ወልዳ ኑራ እኔን እንዲረዱ የተመደቡት ሠራተኞች ሁሉ እኔን የዱር አዳሪዋን ልጅ ከነመወለዴም ዘንግተው ሀብታሚ ሴትዮ ወደተኛችበት ክፍል ሄደው ሊጠይቅ ከመጣው ያጌጠና የደላው ቤተ ዘመድ ጋር ተዳብለው ያንኑ ክፍል ያጣብቡ ኑረዋል ። የኔውን ነው እንጂ የምነግራችሁ ምስኪኗ እናቴማ በምን ሁኔታ እንዳለች ኅሊናችሁ ሊደርስበት ይችላል።

ነገሩ ሁሉ ገባኝ በቍጣና በብስጭት የሕፃን ደሜ ፈላ ። ያለኝን ዓቅሜ ስገምተው ግን ከማልቀስ የማያልፍ ሁኖ አገኘሁት ። ባለኝ ዓቅም ከተኛሁበት አልጋ ላይ እየተፈራገጥሁ ባልጋው ዙሪያ የቆሙት መከለያዎች ከለከሉኝ እንጂ ከወለሉ ላይ ወድቄ ተፈጥፍጬ ለመሞት እየሞከርሁ ባለኝ ኃይል « እሪ !»

እል ጀመር ። እንደ ተቈጣ አንበሳ የሚያጉረመርም ድምፅና በበደል የሚጮኅ ድምፄንም ለሕዝብ የሚያሰማ የድምፅ ማጉሊያ መሣሪያ ባገኝ ኑሮ የሆስፒታሉን ግቢና ውጭ በጩኸት ባደባልቀው «እናንተ ለሰው ፊት የምታደሉ የእውነትና የቅዱስ ሥራ ጠላቶች! » በሚል ቃል ተነሥቼ ነውራቸውንና ዓመፃቸውን የሚገልጽ ዲስኩር ባወርድባቸው በወደድሁ ነበር ።

ግን አልቻልኹም ። ቢሆንም ባለ ዓቅም ተዋግቶ መጥፋትም እውነተኛ ጀግንነት ነውና የልቤ ምት በሁለት እጥፍ ፈጥኖ እስኪመጣ ድረስ ባለችኝ

ትንሽ ድምፅ እጮኽ ጀመር ። ጥቂት እንደጮሁ ሐኪሙ በዚያ ጥግ ያልፍ ኑሮ ከፍሉን ከፍቶ ገባ ። ብቻዬን ሲያገኘኝም ደነገጠ። ከመደንገጡም በላይ አፈረ ። እኔም ቶሎ አልሁና የቁጭት ንግግሬን ጀመርሁ ። « ምን በደልሁህና ወደማልፈልገው ቦታ አምጥተህ ታሠቃየኛለህ? ምነው መኖርን እንደ ታላቅ ነገር ትቈጥረዋለህ? እኔኮ መኖር የምትሉትን ነገር ታላቅ አድርጌ አልቈጥረውም ። ግፍ አድልዎ ችግርና ባርነት ይከብዱኛል ። እነሱን የሚሸከም ደንዳና የስሜት ትከሻ የለኝም ። ነፃነት የሌለበትን ኑሮ ኑሮ ብትሉኝ እኔ ገሐነም እንጂ ኑሮ አልለውም ። በገሐነም እኖራለሁ ያለ ገብቶ ይቃጠል! ያልፈለገንስ በግድ ገሐነም ግባ ለምን ትሉታላችሁ? ለአንድ ሰው በቂና ተስማሚ ምግብ ያስፈልገዋል ትላላችሁ ። ግን ይህን እንዲያገኝ አትረዱትም ። እንዲያውም እንዳያገኝ ትከለክሉታላችሁ!? አልሁት ።

እሱም በዕረፍት መልክ የሲጋራ ጢስ ያወየባቸው ጥርሶቹን ብልጭ አደረገና « ምግብህን አልሰጡህም? ምግብህ በየጊዜያቱ እየተዘጋጀ እንዲቀርብልህ አዝዤ ነበርኮ! » አለ። « ንጹሕ የሆነውን ባሕርያቸውን የረከሰ እምነትና ወግ ያበላሸባቸው የሕይወታቸውን ዓላማ ወደ አድልዎና ማጭበርበር አቅጣጫ የመሩ ሰዎች ትክክለኛውን ቅዱስ ተግባር ለመፈጸም ይችላሉ ብለህ እንዴት አመንህ? ተለማም ጦና መስሎ ማደርን የሚሹ ሰዎች ጥቅም ካዩባቸው ሰዎች ሥር መልወስወስን ትተው ሰዎችን በትክክለኛ የፍቅር መንፈስ በሚያሳየው ቅዱስ ስሜት ለመደሰት ይሞክራሉ ብለህ እንዴት አሰብህ? ለሚ ፈሩት ተረግጠው የሚደፍሩትን ረግጠው የመኖር ስሜት ቅዱሱን ተግባር ከነፍሳቸው ያስወገደባቸው ፍጡሮች እንደ እኔ ላለው የለማኝ ልጅ ይራራሉ ብለህ እንዴት ጠበቅህ? » አልሁት ።

መካከለኛ ዕድሜ ያለው ሐኪም ፊቱ በድንጋጤ ስሜት ተለወጠ ። በትምህርትና በልምድ ያጠናው ነገር ግን በልማዳዊ ዓይን በማየት ችላ ብሎት የቆየው ነገር ሁሉ ትዝ አለው ። የኔ የትንሹና የደሀው ሕፃን ድምፅም እውነተኛውን የሰው ልጅ ማኅበራዊ ክፋት በኅሊናዊ ጆሮው ስለሰነቀረበት ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ተሰምቶት በማያውቅ የኅሊና መበጥበጥ አመሰው። የሰው ልጆች በአካላዊ መቊሰልና በበሽታ ብቻ ሳይሆን በስንት የመንፈስ ቊስልና በሽታ እንደሚሠቃዩ አስታወሰ ። በማንኛውም ዓይነት ትምህርት የበሰሉ ሊቃውንት በአንድነት ለፍተውና አክመው ያድኑታል ብሎ ለማመን እንኳ

የሚያጠራጥር ብርቱ የመንፈስ በሽታ አብዛኛውን የዓለም ሕዝብ እንደሚያሠቃየው ተገነዘበ ። በአዲስ ስሜትም ታወከ። ራሱንም ነቀነቀ። የደረቁትን ከንፈሮቹን በምላሱ አረጠባቸው ። ወደኔ እየተመለከተም « በምን ዓይነቱ ውቅያኖስ ገብቼ እንድዋኝና እንድሠጥም አሳሰብኸኝ አንት ተአምረኛ ሕፃን? » ሲል ጠየቀኝ ።

« የለም እንደዚህ አትተርጕመው! » አልሁት ። ንግግሬንም በማያያዝ « በጐ ተግባር ሰዎች ሁሉ ንቀው የተዋት ጣፋጭና ንጹሕ ምንጭ የሚጠጣትን ሁሉ ክፉ ተግባር ያሳደረበትን ጥምና ሱስ ቆርጣ የምታረካና የምታድስ ከገነት የምትመነጭ ደስታን የምትሰጥ ከጉድፍ የምታነፃ ከቍስል የምትፈውስ የሕይወት ፈሳሽ እንጂ ማንንም የምታሠጥም የጥፋት ውቅያኖስ አይደለችም! » አልሁት ። ዓቅም አነሰኝና ቀረ እንጂ ራሴን ቀና ለማድረግ እየሞከርሁ « የሚሰማኝ ባገኝ እናንተ የውሸትና የግል ደስታ ለማግኘት የምትጣጣሩ! መንገዳችሁ ጠማማና ወደጕድጓድ የሚመራ ነውና ተመለሱ! ወደ እውነተኛ ደስታና ሰላም የሚመራችሁን ቅንና ነፃ መንገድ ተከተሉት! የሌሎችን ሥቃይ ለማቃለል ራሳችሁንም ከሥጋትና ከኅሊና ሥቃይ ነፃ ለማድረግ የግፍን የአድልዎን የብልጠትንና የክፋትን ከተሞች ለቃችሁ ነፃነት ፣ ሰላም ፣ ደስታና ፍቅር ወዳለበት የደግነት ከተማ ሽሹ! ሰፊውና ሀብታሙ ዓለም ያለው በደግነት ከተማ ነው ። የክፋት ከተማ ችግር ፣ በሽታ ፣ ድንቁርና ፣ ሥጋት ፣ ሥቃይ ትዕቢት ነውርና ጥርጥር ያጨናነቁት የጦርነትና የግድያ ሜዳ ነው! ሁላችሁም ወደ በጐ ሥራ ብርሃን ተመልከቱ! ሁሉም ግልጽና መልካም ሁኖ ይታያቹል! የዓለምን ሰፊነትና መልካምነት እንዳታዩ የሚያደናብራች ሁንና በውስጡ የታሠራችሁበትን የጨለማ ወህኒ ቤት ስበሩ! ራሳችሁንና ወንድሞቻችሁንም ነፃ አድርጉ! እያልሁ እጮህ ነበር ። ነገር ግን የሚሰማኝ እንደማላገኝ በማወቁ የነፃነት ቁንጮ የሆነውንና ሶክራትስ « አሰናካይ የሌለው ጣፋጭ ዕንቅልፍ! ወይም ወደተሻለ ዓለም የሚያሸጋግር ጉዞ » ብሎ የሠየመውን እኔም « ያለ አድልዎ የተሰጠ ዕረፍትና ነፃነት ወይም « ወደትክክለኛ ዳኛ የሚያደርስ ጥሪ » ብዬ የምጠራውን ሞትን አግኝቼ ራሴን ብቻ ከዓለም የጨለማ ጉዞ ነፃ ለማውጣት ወስኜ ነበር ። ግን ለዚህም

ነፃነት አላገኘሁም ። አሁንም የሰው ክፋት እሥረኛ ሁኜ እገኛለሁ » አልሁት ።

ይህን ቃል ከአንድ በዕድሜ እንደሱ ከሆነ ሰው ቢሰማው ቢያስደስተውም ያለመጠን አያስገርመው ነበር። ግን ይህን ሁሉ የሚሰማው ከናቴ ሆድ ከወጣሁና ዓለምን ካዬት ገና ሦስት ቀን ከሆነኝ ሕፃን አንደበት በመሆኑ በጣም እየተገረመ አንዷን ነርስ ጠርቶ ምግቤን እንድትሰጠኝ አዘዘና እናቴ ወደተኛችበት ክፍል ሄደ ። እዚያም እኔ አለባት ያልሁት የሳንባ ነቀርሳ በእውነት ያለባት መሆኑን የሚያረጋግጠውን የምርመራ ውጤት ዐይቶ የባሰውን ከተገረመ ቤላ « ይህን ልጅሽን ከምን ነው የፀነስሽው? » ሲል ጠየቃት ።

እሷም ቶሎ ብላ « የለም ጌታዬ! የሰይጣን ልጅ መሆን አለበትና ቶሎ በመርዝ ግደሉልኝ! » አለች ።

ሐኪሙም በተለመደ ለዘብታው ፈገግ አለና « አ! መልካም ሰይጣን! ሰይጣን እንደዚህ ያለ የሚወልድ ከሆነስ የኛ ሴቶች ሁሉ ከሰይጣን ወንዶች የኛ ወንዶች ሁሉ ከሰይጣን ሴቶች እየተጋባን ምነው ዓለምን እንደዚህ ሕፃን ባሉ ክልስ ትውልዶች በሞላናት አለ ። ንግግሩንም ሳያበዛ « ከኔ የተሻለ የምታው ቂው እንዳለ ብዬ ነው እንጂ! ሰይጣን ላለመሆኑስ አረጋግጬ ዐውቀዋለሁ » አለና መድኃኒትና ምግብ አዝዞላት ወደኔ ተመለሰ ወደኔ ሲመለስም የቀረበልኝን ምግብ አልበላ ብዬ ሳስቸግር ቆየሁት ።

« ምነው አትመገብም? » አለኝ ።

« አልመገብም » አልሁት ።

« ለምን? »

« የረኃብ ዓድማ አደርጋለሁ! »

« ምን ስለሆንህ? »

« አስፈላጊው ምግብ ስላልቀረበልኝ ። »

« ቀርቦልህ የለም? »

« ምንስ አፌ ብዙ እንዲናገር የማላውቀው ኃይል ቢያስገድደኝ ሕፃን መሆኔ ቀረ ደረቅ ገንፎ እንዴት አድርጌ ልዋጥ ከዚህ ጥቂት ተርቤ መሞቱና ማረፉ ይሻለኛል ። ድኀነት ርስት አይደለም ። የሰው ልጅ ሁሉ ፍላጐት አንድ ነው ። ለሀብታሞቹ ልጆች የሚያስፈልገው ወተት ለኔም ያስፈልገኛል። የናቴን ጡት መጥባት ሲገባኝ በበሽታ ስትሠቃይ እንድትኖር ስለተዋቼት የናጥ ጡትን የመጥባት ዕድል አመለጠኝ ። ከዚህ በላይ ደግሞ የላም ወተት ከለከላችሁኝ! የኔ ሆድ ያገራችሁን ሀብት የሚያጐድለው ከሆነ አልፈልግባችሁም ። የናቴ ቅርስ የሆነቿውን ራቤን ወርሼ ባጭሩ እገላገላለሁ » አልሁ ።

በዚህ ጊዜ ሐኪሙ ነርሷን ተቈጣት እጅግም ገላመጧት ። ከዚያም ቀጥሎ « ከዛሬ ጀምሮ »

« በደንብ የተዘጋጀ የከብት ወተት »

« ከጥቂት ቀኖች በኋላ ወተትና የፍራፍሬ ጭማቂ » ከዚያ ቆይቶ ወተት የፍራፍሬ ጭማቂና አጥሚት » ከዚያ ጠንከር ሲል ወተት የፍራፍሬና የቅጠላ ቅጠል ምግቦች እንዲሁም ከዕንቊላል ከዓሣ ከሥጋና ከእህል የተሠሩ ለስላሣ ምግቦች እንዲያገኝ ማድረግ አለብሽ ።

« አንዳንድ ጊዜ ወደውጭ እየወጣም የፀሐይ ብርሃንና ሙቀት እንዲያገኝ መደረግ አለበት » ሲል አዘዘልኝ ።

ሕፃናት ሁሉ እንደእኔ በቆራጥነት ነፃነት ቢፈልጉ ሰዎች ሁሉ እኔን እንዳጋጠመኝ ደግ ሐኪም የሰውን ስሜት ቢያከብሩና በሚቻላቸው ተገቢ ፍላጐቱን ለመፈጸም ቢሞክሩ የዓለም ክፉ ሥራዎች ሁሉ ጠፍተው ሰላምና ፍቅር በገነኑ ነበር ።

# 4

## ከቄስ ጋር ስለመጣላቴ ።

ብዙዎች ክርስ+ያኖች እንደሚያደርጉት ሁሉ ደሀዋ እናቴም እኔን በሕፃንነቴ ወራት ክርስትና ማስነሣት ስለነበረባት ገና ከበሽታዋ ሳትድን እኔን ይዛ ወደቤተ ክርስ+ያን ለመሄድ ተነሣች ። እኔም አልሄድም ልላት ፈልጌ ነበር ።

ነገር ግን በየጊዜው አላሳዝናትም በማለት ዝም ብዬ ስታዝለኝ ታዘልሁ ። ሐኪሙም እኔ የዘወትሩ ታሚጋች ዝም ብዬ ስሄድ ስላየ ለናቴ መሄድዋን ፈቀደላት ።

ወደ ቤተክርስ+ያኑ እንደደረስን አጥማቂው ቄስ ወደኛ መጣ ። የለበሰው ጥቁር እጀ ሰፊና ጥቁር ቦላሌ ከጥቁር ጫማው ጋር ነበር። ሰውየው ልጅ እግር እንደመሆኑ መጠን ለውበት ታስባ የተሰፋች የምትመስለው ቅሽር ቆቡ ሐር ከመሰለው ጢሙ ጋር ለመልኩ ልዩ ውበት ሰጥተውታል ።

ዘመናዊው ቄስ ሰውነታቸውን በረኃብ በመታረዝ በስግደትና በጸሎት አጐሳቁለው ከሚኖሩት ጥንታውያን ቄሶች በማንኛውም ነገር የተለየ ለመሆኑ ከፊቱ ላይና ከደረቱ ስፋት የበለጠ ምስክር አያሻም ነበር ።

ይህ ቄስ ከጓደኞቹ ጋር ሁኖ መጽሐፈ ጥምቀት ካነበበ ቤላ ጥቂት አዜመና በቀዝቃዛ ውኃ ነከረኝ ።

እኔም የመከላከያ መሣሪያዬ የሆነቿው ጩኸቴን ስለቅ የሚሰማኝና የሚተወኝ ባጣ « ምነው አባቴ በጠዋቱ በቀዝቃዛ ውሀ ያደፍቁኛል? » አልሁት ።

ቄሱ በፍጹም ደነገጠ ለሱ ክብር ተአምር ሊወርድለት በዚህ ጊዜ ብቻ የተናገርሁለት ሕፃን መስየውም በመጠኑ የደስታ ስሜት አደረበት ። ነገር ግን ራሱ ተአምር ለማሳየት በቂ አለመሆኑን ውስጣዊ ስሜቱ ሲያስረዳው ሰይጣን ይሆን? ብሎ ጠረጠረ ። የዋሁ ቄስ በልፍለፋ ሳስቸግር መቆየቴን አልሰማ! « ሰይጣን ርኩስ መንፈስ ውጣ! » እያለ በውሀው ሊቸረኩፈኝም ፈለገ ። እኔ

ግን ሰው ስለሆንሁ « አባቴ እንዳይነኩኝ ለመሆኑ ምን ማለትዎ ነው? » አልሁት ።

« አንተ ማን ነህ? » አለኝ ቄሱ ።

« ሰው ነኝ » አልሁት ።

« ከየት መጣህ? »

« ከናቴ ሆድ »

« ማን ፈጠረህ? »

« ሁሉን አስተካክሎ የፈጠረ »

« ሃይማኖትህ ምንድነው? »

« ሁሉን በፈጠረ ፈጣሪ ማመን ። »

« በምን ሁኔታ? በማንስ ትምህርት መሠረት?

« በፍጹም ስሜት ራሱ በሰጠኝ ትምህርት »

« ክርስ+ያን ነህ? እስላም? ወይስ በሌሎች ሃይማኖቶች የምታምን?

« ሁሉንም አይደለሁ ። በፈጣሪ ብቻ የማምን ነኝ »

« ሃይማኖት የለህም ማለት ነዋ? »

« የሃይማኖት ክፍል የለኝም እንጂ ሃይማኖትስ አለኝ »

« ፍሮቴስታንት? ካቶሊክ? ወይስ ኦርቶዶክስ?

« ከማናቸውም የለሁ »

« በል አሁን ክርስ+ያንነትን ተቀበል »

« መቼ ተረዳሁትና ልቀበለው? »

« የናትህ እምነት ስለሆነ ተቀበለው ። »

« እኔ የፈጣሪን እንጂ የናቴን ሃይማኖት አልቀበልም ። እናቴ ምንም አታውቅ። እንደኤ በሕፃንነቷ ተገዳ ተቀበለችው እንጂ ሃይማኖቷ ምን ምሥጢር እንዳለው እስከ ዛሬ እንኳ አታውቅም ። ስለዚህ የሷን ሃይማኖት እውነት ብዬ አልቀበልም ። »

« ታድያ ምን ልትሆን ትፈልጋለህ?

« መልካም! እንደ አንዳንድ ቄሶች እውነት ፈላጊዎችን ሰይጣን የሚሉ ባለመሆንዎና ፍላጐቴን በመጠየቅዎ አመሰግንዎታለሁ ። ፍላጐቴን ከጠየቁኝ የሃይማኖትን ምንጮች ሁሉ መርምሬ የሃይማኖት መጽሐፎችን ሁሉ አንብቤ ከመረዳቴ በፊት ወደማንኛውም የሃይማኖት ክበብ አልገባም ። ለመኖሩ ሥራዎቹ በሚመሰክሩለት ፈጣሪ ግን አምናለሁ ። ፍላጐቴም ይህ ነው » አልሁ ።

« ትክክለኛውንና እውነተኛውን የክርስ+ያንነት እምነት ላስረዳህና ተቀበለዋ! » አለኝ ቄሱ ።

« እውነተኛ እምነት ከያዙ ከናቱ ክንድ ያልወረደና ምንም የማያውቅ ሕፃን ከመስበክ ለማመዛዘንና ለመመራመር የሚችለውን የበሰለ ሰው ለምን አያስተምሩም? በዓለም ውስጥ ክርስ+ያን ያልሆኑት ከክርስ+ያኖች የተወለዱ ሕፃናት ብቻ ናቸው? »

« አንተ ሰይጣን መሆን አለብህ! »

« ሰይጣን ማለት ያልገባውን ነገር አልገባኝም የሚልና እውነትን ፈላጊ ነው? ሰይጣን እንዲህ ከሆነስ ምነው ሰይጣን በሆንሁት! » ስል ቄሱ እያማተበ « አንድ አምላክ በሆነው በአባትና በልጅ በቅዱስ መንፈስም ስም ሰይጣን ከኔ ራቅ! » አለ ።

እኔ ሰይጣን ባለመሆኔ ልርቅ አልቻልሁም ። እናቴ ግን ደንግጣና ዕድሏን አምርራ ይዛኝ ሸሸች ። ቄሱም እኔንና እናቴን በማባረሩ በጸሎቱ በሥራው ኃይል ሳይደሰት አልቀረም ።

# 5

## ከጋዜጠኞች ጋር ስለመነጋገሬ ።

በየቀኑና በየሳምንቱ እየታተሙ የሚወጡት ጋዜጦች አዘጋጅዎችና ወሬ አቅራቢዎች አዲስ ወሬ ለማግኘት በሚያደርጉት መሯሯጥ በየቦታው ሲጣደፉ የኔን ዜናም ፈልገው ደረሱበት ። እኔ ከተወለድሁበትና በሽተኛዋ እናቴ ከተኛችበት ሆስፒታል ድረስ ተሰብስበው መጡና በመጀመሪያ ከሆስፒታሉ ዋና ሐኪም ጋር ተገናኝተው ተነጋገሩ። ሐኪሙንም እየደጋገሙ ፎቶግራፍ አነሡት። ከዚህ ቤላ ሐኪሙ እየመራቸው እኔ ወደተኛሁበት ክፍል ዝርጉድጉድ ብለው ገቡ ። እኔም ትኩር ብዬ ተመለከቴቻቸው ። ማንኛውንም ሁኔታዬን ሲመለከቱ ከብዙዎቹ እምቦፌ እምቦፌ ሕፃናት የማንስ ነበርሁ እንጂ ከሌሎች በምንም ተለይቼ የማልታይ በመሆኔ በሰሙት ወሬ ሁሉ ጥርጣሬ ገባቸው። ከጋዜጠኞች መካከል ትኩስ ወሬዎችን በማቅረብ ዝነኛ የሆነ ወሬ አቅራቢ (ሪፖርተር) « ታዲያ ለተነገረን ወሬ ሁሉ መረጃ አድርገን የምንይዘው ምን የተጨበጠ ነገር አለ? » ብሎ ሐኪሙን ጠየቀ በትክሻው ያነገተውን የፎቶግራፍ ማንሻ መሣሪያ (ካሜራ) በጁ እያስማማ ።

« መልካም! እሱን ልትጠይቁት ትችላላችሁ » አለ ሐኪሙ እንዳልበርቅበት በሥጋት እኔን እየተመለከተ ። ጋዜጠኞች ግን እርስ በርስ እየተያዩ ክፍሉን በሳቅ አደባለቁት። ጩኸታቸው ስላደረቀኝ በጣም ተናደድሁና ላለቅስ ከሞከርሁ ቤላ ልቅሶውን ትቼ « ብዙ ጊዜ እንደምታደርጉት ፈጥራችሁ አውሩ እንጂ ምን መረጃ ያስፈልጋቼል! » ስላቸው ሁሎችም በድንገተኛ ድንጋጤ ክው ብለው እርስ በርሳቸው እየተያዩ ጥቂት ጊዜ ዝም አሉ። ሐኪሙ ግን በተራው ፈገግ ብሎ ያያቸው ጀመር ።

ትንሽ ከቆዩ ቤላ ያው ጋዜጠኛ ወደኔ ቀረብ አለና « ምን ዓይነት ፍጡር ነህ? » ሲል ጠየቀኝ።

« እንደምታየኝ ሰው ነኝ » አልሁት ።

« ሁለተኛ የተወለድህ ፍጡር ነህ? »

« እኸኸ! አንተ ዓለመኛ ነህ ወንድሜ! እንኳን ሁለት ጊዜ ልወለድ ያንድ ጊዜ መወለድ ዕዳ አሠቃይቶኛል ። አንተስ ምን ያለኸው ጨካኝ ነህ ደሞ! »

« ታዲያ የዓለምን ብዙ ጣጣ ከመቸው ዐወቅኸውና ተረዳኸው? »

« እንግዳ የሆነባቸው እኔ ችግሩን ሁሉ በቃሌ ስለገለጽሁላችሁ ነው እንጂ ሕፃናት ሁሉ የዓለምን አስቸጋሪነት ያውቃሉ። ሲርባቸውና ሲጠማቸው እንዲሁም ሲያማቸውና ፍላጐታቸውን ሲያጡ ያለቅሳሉ ይህም የደረሰባቸውን ችግር በሚችሉት ቋንቋ ማለት በልቅሶአቸው ለመቃወም የሚያደርጉትን ሙከራ ያሳያል ። እኔን ግን የሕፃናትን ስሜትና ፍላጐት ለዓለም ሕዝቦች እንዳሰማ ፈጣሪ ከቀና አንደበትና እውነትን ከማወቅ ጋር እንድወለድ አደረገ ።

« በእውነት ትክክለኞችና እውነተኛ ነገር ገላጮች ከሆናችሁ ሂዱና በየጋዜጦቻችሁ የሕፃናትን ድምፅ ለዓለም ሕዝብ አሰሙ ። እኛ ሳናውቅ በየቦታው የሚንገላቱ አሳዳጊ ጠባቂና አስተማሪ ያጡ ሕፃናት ሁሉ ጩኸታቸውን ወደ ፈጣሪያቸው ያቀርቡብናል። ይከሱናል ወንጀላችንንም ይገልጹብናል ብላች%< ተናገሩ ። በብዙ ሕፃናት ላይ የሚደርሰው መከራ ሁሉ የኛ ማፈሪያና መወቀሻ ሊሆን ነው ውለዱን ሳይሉ እየተወለዱ የዓለምን ሥቃይ እንዲሸከሙ በተለምዶ የተፈረደባቸው ሕፃናት በታላቅ የእፍረት ማዕበል ሊያስውጡን ነውና እናስብ። ለሚወለዱ ሕፃናት ሁሉ መልካም ዕድልና የመኖር ተስፋ እንዲኖራቸው ከመወለዳቸው በፊት እናስብላቸው ብላችሁ ስበኩ! » ብዬ ስናገር አንዳንዶቹ ብቻ የምናገረውን ቃል በማስታወሻ ለመያዝ ሲሞክሩ ብዙዎቹ ፈዘው አፍ አፌን ይመለከቱ ነበር ። እኔም ንግግሬን ቀጠልሁና ከሕፃናት የተለየ ሕፃን አገኘን ብላችሁ በምትሰጡት ትኩስ ወሬ ከምታገኙት ጥቂት ገንዘብ ይልቅ የድሆች ሕፃናትን አቤቱታ ለዓለም ሕዝብ በማሰማታችሁ በምታገኙት የመንፈስ ስሜት ለመደሰት ሞክሩ! አሌቸው ።

ከዚህ ቤላ ለጉድ የተወለድሁ ሕፃን መሆኔን በማመን በዚህ በኩል ያለውን ጭቅጭቅ ተውና ከኔ የሚወጣውን ንግግር ለማዳመጥ ፈለጉ ።

ወጣቱ ወሬ አቅራቢ ከሁሉም ቀድሞና ቀልጥፎ ቀረብ አለኝ። ከዚያም « ወደፊት የሚወለዱት ሰዎች ሁሉ ትክክለኛና ቀጥተኛ ኑሮ ለማግኘት

እንዲችሉ ምን ማድረግ ይሻል ይመስልኻል? » ሲል ጠየ ቀኝ ። እኔም የሚከተለውን ሰፊ መልስ ሰጠሁት ።

« ጥያቄው እጅግ ከባድ ነው ። የዚህን ጥያቄ መልስ በቃል መመለሱ ቀላል ነው ። በሥራ ላይ ማዋሉ ግን ከባድ ነው ። ሰዎች ምንም እንኳን በተፈጥሮ በሚያገኝዋቸው አንዳንድ ስጦታዎች ቢለያዩ ፍላጐታቸውና ተፈላጊነታቸው አንድ ነው ። ምንም ዐዋቂ ቢሆን ብቻውን በዓለም ላይ የሚያስፈልገውን ሁሉ ነገር ሊሠራ የሚችል ዐዋቂ ምንም ሀብታም ቢሆን ብቻውን ሠርቶ ሀብታም የሆነ ሀብታም ምንም አላዋቂ ቢሆን ባለም ላይ የሚፈለግበት ነገር የሌለው ደንቆሮ በዓለም ውስጥ አይገኝም።

« በፍላጐት በኩልም ሁሉም ሰው ደኅና ነገሮችን ሊያገኝ ይፈልጋል መጥፎዎች እንዳይደርሱበት ይከላከላል ። የሆነው ሁኖ የሰው ዘሮች በጊዜ ብዛት ብዙዎችን ጐጂ ነገሮች አምነውባቸው ስለተገኙ ሰዎችን ከነዚህ መጥፎ እምነቶች ለመመለስ ብርቱ ትግል አስፈላጊ ነው ።

« ጥቃትና ባርነት አይገባኝም የሚለው ተከላካይና ባሪያ መግዛትና ማጥቃት ይገባኛል የሚለው አጥቂ ሁለቱም አምርረው ሲታገሉ ማየት ለሰው ልጅ ጠቅላላ ሰላማዊ ኑሮ ያለንን ተስፋ ያደክምብናል።

ስለዚህ ስለወደፊቱ መልካም ኑሮ ጠቃሚ ጐዳና ለመክፈት የሚቻል ቢሆን እነዚህን ጠንካራ ሕጎች በሥራ ላይ ማዋል ይገባል ።

1ኛ ፡ በሌሎች ጥቃትና ጒስቁልና የመደሰት ልምድ እንዲቀር ማድረግ ።

2ኛ ፡ የሌላውን ሰው ስሜትና ፍላጐት ከራስ ስሜትና ፍላጐት ጋር ሁልጊዜ ማነጻጸር ።

3ኛ ፡ የገዛ ራስንም የማይገባ ነገር በሚፈልግበት ጊዜ ፍላጐቱን መከልከልና ከወሰኑ እንዳያልፍ በኀሊና ፍርድ መቅጣት ።

4ኛ ፡ የማይሠሩ ሰዎች የሚሠሩትን ሰዎች የድካም ፍሬ እየጋፈፉ በቁንጣንና በትዕቢት እንዳይሞቱ ድሆች ሠራተኞችም የጉልበታቸውን ዋጋ እየተነጠቁ በችግርና በመጐሳቆል እንዳያልቁ የሚከለክል ሚዛናዊ ፍርድ ማቆም ።

5ኛ ፡ ማንኛውም ሰው የሚያኰራው የሚመስለው ልዩ ነገር ቢኖረውም በኰራና ሰዎችን በጐዳበት ጊዜ የሚኰራበት ነገር ከሰው በታች ያዋለው መሆኑን ማወቅ ።

6ኛ ፡ መሬትና ከውስጧ የምናገኛቸው ነገሮች ሁሉ በዚህ ዓለም ባለንበት ጊዜ ብቻ የሚያገለግሉን እንጂ በመቃብር ውስጥ ወይም በሌላ ዓለም ሁነን ስለማንጠቀምባቸው ካስፈላጊ ድርሻችን አልፈን ሌሎችን አስፈላጊ ድርሻቸውን ከማሳጣት መታገድ ።

7ኛ ፡ ዓለምን ጐርበጥባጣ ያደረጋት የነጣቂዎች ጮሌነትና የተነጣቂዎች ነፎዝነት እንጂ እግዚአብሔር ሲፈጥርት ውብና ለሁሉ የምትበቃ የነበረች መሆኗን እያንዳንዱ ሰው እንዲያውቅ ማድረግ።

8ኛ ፡ አንድ ሰው ቢያንስ ቢያንስ ራሱንና አካባቢውን እንዲሁም የሚኖርባትን ዓለም የሚያውቅበት መጠነኛ ትምህርት ሳይኖረው እንዳይቀር ማድረግ ።

9ኛ ፡ ለትምህርትና አዲስ ነገሮችን ለማግኘት ለማሰብና ለመፍጠር የሚያስችል የተሻለ አእምሮ ያላቸው ሁሉ በችግርና ዕድል በማጣት ተሰናክለው እንዳይቀሩ በትምህርት ሜዳ የችሎታን ልዩነት እንጂ የዘርን ልዩነት አለመመልከት ።

10ኛ ፡ ማንኛውም ሰው በችሎታው ይነስም ይደግ በዓለም ውስጥ የሚፈለግበት ቦታ ያለው መሆኑ እንዲታወቅና ባለው ዓቅሙ የሚሠራበት ዕድል እንዲሰጠው ማድረግ ።

11ኛ ፡ በማንኛውም ሰው ምክንያት የሰው ልጆች ማኅበራዊ አቋም እንዳይጐዳና እንዳይበላሽ ለወገን ለዘር ለሀብታም ለደሀ ለታናሽ ለታላቅ ሳይል አጥፊዎችንና በጥባጮችን ያለምሕረት የሚቀጣ ብርቱ ሕግ መመሥረት ።

12ኛ ፡ ማንኛውም ሰው የሌሎችን መብት ሳይጐዳ የራሱን መብትና ድርሻ የሚከላከልበት ፍጹም ነፃነት እንዲኖረው ማድረግ ።

13ኛ ፡ እያንዳንዱ ሰው ሌሎች ከሌሉ ራሱ ብቻ ሊኖር አለመቻሉን ዐውቆ ለሰዎች ሁሉ ፍቅርና ርኅራኄ እንዲኖረው ከልጅነቱ ጀምሮ ፍቅርና ርኅራኄን እንደሃይማኖቶች ሁሉ እንዲያጠና ማድረግ ።

14ኛ ፡ ሀገርንና ነፃነትን ለመጠበቅ የሚያስፈልገው የጦር ሙያ ሲቀር ሌላው ጀግንነትና ፍሬ ቢስ ውድድር ሰላምን ፣ ፍቅርን ፣ ነፃነትን ፣ ዕውቀትንና ብልጽግናን የሚያጠፋ ድኅነትን ፣ ብጥብጥን ችግርን ፣ በሽታንና ረኃብን የሚያስከትል የልማድ ጠንቅ መሆኑን መረዳት ።

15ኛ ፡ መከበርና መወደድ በጉልበትና በመፈራት ሳይሆን በመልካም አድራጊነትና ለመከበር በሚያበቁ ቅንነትና ትሕትና ባልተለያቸው ሥራዎች እንዲመሠረቱ ማድረግ ።

16ኛ ፡ እያንዳንዱ ሰው ለሚያደርገው ሥራ ሁሉ መገደድንና እንደእንስሳ በነጂ ኃይል መነዳቱን ትቶ ተገቢ ተግባሩን በሚያመለክተው ቅን ኅሊናው የመታዘዝና የመመራት ልምድ እንዲኖረው ማስተማር።

17ኛ ፡ በሃይማኖትም ሆነ በሌሎች የአማኙን ሰው የግል ስሜት ብቻ በሚመለከቱ መንፈሳዊ እምነቶች ላንድ ሰው ፍጹም ነፃነት እንዲኖረውና በነዚህ ነገሮች ምክንያት ከሰዎች ጋር ተባብሮ የመኖር መብቱ እንዳይነካበት ማድረግ ።

18ኛ ፡ እያንዳንዱ ሰው ለግል እምነቱና ስሜቱ ብቻ በማድላት ከላይ በተጠቀሱት እምነቶች የጠነከረውን ማኅበራዊ ኑሮ የሚጐዳ ሥራ ቢሠራ ለከፍተኛ ወንጀሎች የተደነገገ ቅጣት እንዲፈጸምበት ማድረግ ።

19ኛ ፡ ከፍተኛ ትምህርትና ዕውቀት ያላቸው ሰዎች የክብራቸው ምንጮች ፣

ሀ/ ያላወቁት እንዲያውቁ ማድረግ ።

ለ/ አዲስ ሐሳቦችንና ነገሮችን ማግኘት ።

ሐ/ ሕዝብን በማገልገልና በትሕትና ተቀዳሚ አርአያ መሆን እንጂ ሌሎች ነገሮች አለመሆናቸውን ማመን ።

20ኛ ፡ ሰዎችን ወደጠብ ወደደካማ ባሕርይ ፣ ወደ ግብዝነት ወደራስ ብቻ ፍቅር ወደአድልዎና ወደሌሎችም አስፈላጊውን የመግባባትና የፍቅር መንፈስ ወደሚያጠፉ መንገዶች የሚመሩ የልማድ ስሕተቶችን በእውነተኛ ትምህርት አውድሞ በነሱ ቦታ የእውነተኛ ትምህርትን ፍሬ መዝራት በግድ ያስፈልጋል ።

በዚህ ሁኔታ ብዙ ጥረት ቢደረግ ምናልባት አብዛኛውን የሰው ልጅ ለድንቍርና ለችግር ለጕስቍልና ለጥቃትና ለሌሎችም መጥፎ ነገሮች ተገዥ ያደረጉት የእምነት መርዞች ተወግደው እያንዳንዱ ሰው በዓለም ላይ ያለውን ተገቢ ድርሻ ሊያገኝ የሚችልበት ጊዜ ሊመጣ ይችላል ። »

ይህን በምናገርበት ጊዜ ጋዜጠኞች እርስ በርሳቸው ለመተያየት አንገታቸውን ቀና ወይም ዘወር ሲያደርጉ ከሚንኮሻኮሸው እንዲሁም በርሳስና በብርዕ ሲነካ ኮሽ ከሚለው የወረቀትና የልብስ ኮሽታ በቀር ምን የማይሰማበት ፀጥታ ነበር ።

ከዚህ ቤላ አንድ በዕድሜው በሰል ያለ ወፍራም አንገቱን ቀና ሲያደርግ የማጅራቱ ኩልኩልት የኮቱንና የሸሚዙን አንገትዬ ዋጥ የሚያደርግና ሆዱ ለመውለድ የምትጠብቅ እርጉዝ ሴት ያስመሰለው በጠቅላላው መካከለኛ ቁመቱን የዋጠው ውፍረቱ ወደቄራ ለመነዳት አንድ ቀን የቀረው የአሳማ ሙክት ያስመሰለው ጋዜጠኛ « ማንም እንደሚያውቀውና አንተም እንደምትናገረው ማንኛውም ሰው ከክፋት ደግነትን ይወዳል ። በሥራ ግን ከደግነት ይልቅ ክፋት አይሎ ይገኛል የክፋትን ብዛት ለመቀነስ ምን ማድረግ ይሻል ይመስልኻል? » ሲል ጠየቀኝ ።

እኔም « የክፋትን ብዛት ለመቀነስ ራስን የመግዛት ችሎታ ለያንዳንዱ ሰው እንዲኖረው ያስፈልጋል » ብዬ መለስሁለት ።ከሱም ቀጥሎ ሁኔታው የዚህኛው ተቃራኒ የሆነ ቁመቱ ረጅም ከእግር እስከራሱ አንድ አይነት ቅርጽ ያለው የተመለመለ አጠና የሚመስል የጉንጩ አጥንቶች ከምግብና ከመጠጥ ተለይቶ የኖረ የሚያስመስሉት ከቅጥነቱ ብዛት የተነሣ የለበሳቸው ልብሶች በዘንግ ተሰክተው የቆሙ የሚመስሉበት ጋዜጠኛ « እኩልነት በሰው ልጆች መካከል ሊኖር የሚችል ነገር ይመስልኻል? » ሲል ጠየቀኝ ።

እኔም መለስሁና « ሰው በተፈጥሮ የሚለያይባቸው ብዙ ነገሮች አሉ ። የአእምሮ ልዩነት ፣ የሥራ ልዩነት ፣ የችሎታ ልዩነት በሰዎች መካከል መኖሩ አይካድም ። ይሁንና እነዚህ ልዩነቶች በመጠኑ ሰዎችን ያበላልጡ እንጂ እንደሰማይና ምድር ሊያራርቋቸው አይችሉም ። በጠቅላላው በዓለማችን ውስጥ የሚገኙት ልዩነቶች በእውነተኞች የተፈጥሮ ልዩነቶች የተመሠረቱ አይደሉም ። የልማድና የወግ ልዩነቶች ናቸው ።» አልሁት ። «ትክክለኛ ልዩነቶች የማይመስሉህ የትኞቹ ልዩነቶች ናቸው? » ሲል ጠየቀኝ ።

« ሌላውን እንተወውና » አልሁት « ከዚህ ስንመለከት አንተና ካንተ ቀደም ብሎ የጠየቀኝ ሰውዬ በአካላዊ ተፈጥሯችሁ ታላቅ ልዩነት አለባችሁ ። እሱ ቁመቱ አጠር ብሎ ያለመጠን የወፈረ ሲሆን አንተ ደግሞ ቁመትህ ረዘም ብሎ ክሳት አጥቅቶኻል ። ይህ ራሱ አንድ ልዩነት ነው ። ይሁን እንጂ ሁላችሁም ለመሥራት የምትችሉ ሲሆን በደኅና መኖርንም ሁለታችሁም ትፈልጋላችሁ ። እንግዲህ እናንተ በሰውነታችሁ ቅርፅ ልዩነት መሠረት ኑሯችሁን ቢለያዩት ትፈልጋላችሁ? እንደማትፈልጉ እርግጠኛ ነኝ።

ምናልባት አድልዎ የተደረገለት ደስ ቢለው እንኳ የተደላበቱን እንደሚከፋው ግልጽ ነው ። ስለዚህ የተፈጥሮ ልዩነቶች በሰዎች መካከል ቢኖሩም ሁሉም ሰው በሚፈልገው የጋራ ጉዳይ እየገቡ ያንዳንዶቹን እድል ከመጠን በላይ አሳድገው የሌሎችን ጨርሰው መደምሰስ አይገባቸውም! » ስል ሁሎችም በሳቅ እየ

ተንከተከቱ ለመውጣት ተዘጋጁ። ከዚያም ቤላ ፎቶ ግራፍ ሊያነሡኝ ካሜራዎቻቸውን ሲያስማሙ « ስለፈጠራችሁ ብላችሁ ገና ከሕፃንነቴ አታሳጡኝ » አሌቸው ። « ምናለበት? ሰዎች እንዲያውቁህኮ ነወ !» አለኝ ወጣቱ ወሬ አቅራቢ ።

« የለም ሳይሠሩ በጋዜጣ ዓምድ ላይ ተለጥፎ መታየት በቂ መተዋወቂያ አይደለም ። ሥሠራ ታስተዋውቁኛላችሁ » አልሁት። « ሥራህ ሁሉኮ! ታላቅና አዲስ ነገር ነው ለምን አልሠራሁም ትላለህ?» ሲል ጠየቀኝ ።

እኔም መለስሁና ፈጣሪ ባሳደረብኝ መንፈስ እርግጥ አዲስ ነገር ታይቶብኝ ይሆናል። ነገር ግን ታላቅ ሁኖ መወለድ የሚባል ያለሥራና ያለሙያ

የሚያስከብር ተረት ስላለ ይህን ተረት ለመቃወም ስል ታላቅ ሁኖ ተወለደ እንድትሉኝ አልሻም !» ካልሁት ቤላ ንግግሬን በመቀጠል « ምናልባት ታላቅ ሰው ሁኜ የተወለድሁ አስመስሎ ያሳያችሁ በዓለም ውስጥ የሚገኙትን ብዙ አስቸጋሪ ነገሮች በናቴ ሆድ እንዳለሁ ዐውቄ መወለዴ ይሆናል። ይሁን! ይህ ልዩ ነገር ነው ። ቢሆንም ፈጣሪ ያደረገው ነገር እንጂ እኔ ደክሜ ያገኘሁት ዕውቀት አይደለም። ሌሎችም ሲወለዱ ይዘውት ተወልደዋል የሚባል ታላቅነት አላቸው ። ከፍተኛ ልደት የሚሉትን ማለቴ ነው ። ግን ከፍተኛ ልደት የሚሉት ነገር ከታላላቆቹ የስንፍናና የንጥቂያ መሣሪያዎች አንዱ ነው እንጂ በሰው ማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ እውነተኛ ተገቢ ቦታ የለውም ። የታላቅነት ምልክት ታላቅ ሥራ ብቻ ነው ። ስለዚህ ብዙ ሥሠራ የፈለጋችሁትን ልታደርጉ ትችላላችሁ። አሁን ግን ተውኝ» ስላቸው « በቸር እደግ! » እያሉ ሰላምታ እየሰጡኝ ከክፍሉ ወጡ ።

# 6

## የአካል ዕድገትና የአካባቢ ለውጥ ።

እኔና ደህዋ እናቴ በሆስፒታሉ ብዙ ከቆየን ቤላ እናቴ ከበሽታዋ ፈጽማ ስትድን ሐኪሙ በዚያው ሆስፒታል መጠነኛ ሥራ እንድትሠራና የማስታመም ትምህርትም እንድትከታተል አድርጎ ቀጠራት ። እኔንም በአቅራቢያው ላለ አንድ ሚሲዮን ሰጠኝ። ሲከፋኝ ሰዎችን መውቀሴና እሞታለሁ ማለቴ መቼም ያልተለየኝ ነገር ነው ። የሚሲዮኑን አስተማሪዎች ሁልጊዜ እንደተሟገትኋቸው ነበር። ከሚሲዮኑ አባሎች ብዙ መልካም ሰዎች ማየቴን አልክድም ። በርኅራ ተቀብለው በሚችሉት መጠን ምቾት አግኝቼ እንዳድግ ይሞክሩ ነበር ። ጉድ የመጣው ቤላ ነው ። ጥቂት አደግ ስል የኛን ሃይማኖት መቀበል አለብህ እያሉ ያስጨንቁኝ ጀመር ። እኔም ማንኛውንም ሃይማኖት ከመቀበሌ በፊት ሁሉን መመርመር ይገባኛል በማለት በየጊዜው ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች በሚሰበኩባቸው ቦታዎች እየዞርሁ መስማት ጀመርሁ ። ግን በማንኛውም የሃይማኖት አስተማሪ አንደበት ሲነገር ያገኘሁት አንድ ያልተለወጠ አስተያየት ነው ። እያንዳንዱ የሃይማኖት ሰባኪ ስለራሱ

ሃይማኖት ታላቅነት ብቻ ይናገራል ። የሃይማኖቱንም ቅንነት ያረጋግጣል ። አስተዋይ ኅሊና ያለው እውነተኛ ሰው ተረድተው ሳይሆን ከናት ካባታቸው ወርሰው የያዙትን ነገር እጅግ ከሚመኩበት ሰዎች ጋር እንዴት ሊስማማ ይችላል? በእውነቱ ከማንኛዎቹም ሃይማኖቶች ጠቃሚ የሆኑ መንፈሳዊ ፍሬዎች መኖራቸውን አልካድሁም ። በአንድ ክፍል ሁኜ ሌላውን ዋጋ የለውም የምልበት መረጃ ግን ፈጣሪ ያውቃል አላገኘሁም። ስለዚህ ከማንኛውም የሃይማኖት ክፍል አልራቅሁ ። ከማንኛውም አልገባሁ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶችን የተቀበሉ የሃገሬ ልጆችን ሁሉ በአንድ ዓይነት የወንድምነት መልክ እያዩቸው ለመኖርም ቆረጥሁ ።

እግዚአብሔር አንዱን ሃይማኖት ብቻ የሚወድ ቢሆን የሚወደውን የዓለም ሃይማኖት አድርጎ የቀሩትን አያጠፋቸውም? እሱ ካላጠፋቸውስ ማን ሊያጠፋቸው ይችላል? ከሱ የበለጠ እሱ የሚወደውን ነገር እናውቃለን? እንግዲህ እግዚአብሔር በዕውቀቱ የሚያኖራቸውን ልዩ ልዩ ሃይማኖት የያዙ ሰዎች በልዩነት ማየትን እንተው። በሚል እምነት ላይ ባለሁበት ጊዜ ያሳደገኝ ሚሲዮን ሰባኪዎች በነሱ ሃይማኖት ገብቼ በዚሁ እንድወሰን ነጋ ጠባ ይወተውተኝ ነበር ። በዚህ ሰምቼ በዚህ በማፍሰስ ጥቂት ዓመታት እንደቆየሁ ስብከቱና ወቀሳው በዛብኝ። በጣምም ሰለቸኝ ።

አንድ እሑድ ጠዋት ሰባኪው « በተቀደሰችው ሃይማኖታችን አታምንም ወይ? » ሲል ጠየቀኝ።

« የረከሰ ሃይማኖት መኖሩን ለይቼ ሳላውቅ የተቀደሰውን ለይቼ ለማወቅ አልቻልሁም። ስለዚህ በዚህ ባያስገድዱኝ መልካም ነው? አልሁት ።

« ካንተ የሚበልጡት የሚነግሩህን አታምንም ማለት ነው? አንተ ትዕቢተኛ ነህ! » አለኝ ሰባኪው ግንባሩን ኮስኮስ አድርጎ እኔን እየተመለከተ ።

« እውነተኛ እንጂ ትዕቢተኛ አይደለሁም » አልሁት ።

« ዲያብሎስም እውነተኛ ነዋ? » ሲል ሰባኪው ጠየቀ ።

« አዬ! በናንተ አስተያየት ከሄድንማ እግዚአብሔርን አጥፊ ዲያብሎስን ቅዱስ አድርጋቹቸዋል።

« እናንተ እንደምትሉት ከሆነ ሰዎች እንዳይሠቃዩ የሚሟገተውና የሚያስተምረው ጨካኙ ዲያብሎስ ሲሆን በግድ ተሠቃዩ የሚለው ቸሩ እግዚአብሔር ነው ። ብሉ ፣ ጠጡ ፣ ተደሰቱ ፣ ነፃ ሆኑ ፣ አትጠቁ ፣ ተመራመሩ ፣ ዕወቁ፡ የሚለው ጨካኙ ሰይጣን ሲሆን ተጨቆኑ ፣ እዘኑ ፣ አትብሉ አትጠጡ ፣ አትወቁ ፣ አትደሰቱ ፣ የሚለው ቸሩና ቅዱሱ መንፈስ ነው ። እንደናንተ ትምህርት ሲሆን አእምሮን ፈጥሮ አትመራመሩ ፣ ምግብና ራብን ፈጥሮ አትብሉ ፣ ወንድንና ሴትን ከመፈላለግ ስሜት ጋር ፈጥሮ አትነካኩ ፣ የሚል በጠቅላላው ሰውን ከፍላጐት ጋር ፈጥሮ ፍላጐቱን ደግሞ እንዳያገኝ የሚከለክል የሰው ጠላት ቸሩ እግዚአብሔር ሆኖ ከሆነ እስከ ዛሬ ለሰው ነፃነት የሚሟገት ጨካኙ ሰይጣን ሁኗል ማለት ነው! እንግዲህ ነፃነትንና መሻሻልን የሚወድ ዲያብሎስ ከሆነ ነፃነትንና መሻሻልን የሚወዱ ሁሉ ከዚህ የመሻሻልና የነፃነት መሥራች ጀግና ጋር መኖርን ሊመርጡ ነዋ! እሱም በደግ ሥራው ቅዱስ ሊባል ነዋ! የናንተ አምላክ የሚወደው መከራን ችግርን ድንቁርናን ከሆነ ከዚያ ከተጠላው የነፃነት ጀግና ጋር እንኑረዋ! እናንተ የምትሉት አምላክ እውነትንና ነፃነትን የማይወድ ከሆነ መቼም ውሸትንና ባርነትን የማይወዱ ሁሉ ወደሌላው ወገን መሄዳቸው አይቀርምና እነሱ ወደሄዱበት ብንሄድ ይሻላል። እናንተም ብትሆኑ ተሳስታችሁ ነው እንጂ ዐውቃችሁ አይመስለኝም። ሳታውቁ እውነተኛውን ቸር አምላክ ዲያብሎስ ዲያብሎስን ቸር አምላክ አድርጋችኋቸዋል። በመከራ ኑሩ ብሎ የሚያዝዝ ጥቂት ሲሳሳቱ በእሳት የሚያቃጥል ቸር አለን? እናንተ ጨካኞች! የራሳችሁን የጭካኔ ስሜት በእውነተኛው ቸር አምላክ ላይ ለምን ታላክካላችሁ? አንድ ሰው አፉን ያልፈታና በመዳህ የሚንፏቀቅ ትንሽ ሕፃን ቢሰድበውስ ሆነ ቢመታው በርሱ ተቀይሞ በእሳት ሲያቃጥለው ሊኖር ይፈቅዳል? አንድ ሰው በትንሽ ሕፃን ላይ የማይቀየምና እንኳንስ በእሳት በጨንገር ሊቀጣው የማይመኝ ሲሆን ከሰዎች ተመሳሳይ ያልሆነ ዕውቀት ተመሳሳይ የሌለው ብልጫ ተመሳሳይ የሌለው ቸርነት ያለው አምላክ ራሱ የፈጠረውን ደካማ ፍጡር በእሳት ሊቀጣው እንዴት ይጨክናል? እኛ ጨካኞቹ እንኳ ልንወልደው እንጂ ልንፈጥረው በማንችለው በዕድሜ እንጂ በሌላ በማንበልጠው ሕፃን የማንቀየም ስንሆን በመፍጠርና በመፈጠር ልዩነት የሚበልጠን አምላክ እንዴት በኛ መከራ ሊደሰት ይፈልጋል? ፍጹም ውሸት ነው ። ዓለምን የፈጠራት የምትሉት በአንዳንድ ጨካኝ ሰዎች ጠባብ ስሜት

ውስጥ ያለውን አምላክ ከሆነስ ከአምላካችሁ ይልቅ ዲያብሎሳችሁን አሸላችሁታል ። ይህንንም ስል እውነተኛውን ፈጣሪ መካዴና መስደቤ አይደለም ። እኔ ስለማመልከውና በስሜቴ ስላለው ቸር አምላክ ልንገራችሁ ።

ሰውን ፣ መሬትን በመሰለ መልካም ቦታ የፈጠረ ለሕይወት መኖር ዋና ምክንያት የሆነውን ዓየርን ለማንኛውም ፍጡር ያለአድልዎ በሚደርስ ሁኔታ በመላው ዓለም በማያቋርጥ መሥመር የዘረጋ ወደላይም እስከ ከፍተኛ ርቀት እንዲኖር ያደረገ ሰው የፈለገውን ሁሉ እንዲያገኝ ማንኛውንም ጠቃሚ ነገር ከመሬት ውስጥ የፈጠረ ሰው የፈለገውን እንዲሠራ ከፍ ያለና ተመራማሪ አእምሮ የሰጠ ሰው እንዲረዳዳና እንዲተዛዘን ርኅራኄን ፍቅርን የተዘምዶና ሌሎችንም ስሜቶች ከተፈጥሮአችን የቀላቀለ ሁሉም መብቱንና ነፃነቱን ጠብቆ እንዲኖር ሲጠቁ የመቆጨት ስሜትን የፈጠረ አንዱ ሌላውን በመበደል ደስታ እንዳያገኝ በኅሊና የመወቀስን የመሳቀቅን በመጥፎ ሥራ የመሥጋትንና ሰላም የማጣትን የመቅጣትንና የመቀጣትን ስሜት የፈጠረ ፣

በጠቅላላው ተቈጥሮ የማይዘለቀውን መልካም ነገር ሁሉ የፈጠረ ቸር አምላክ ነው ። የሰዎችን ደስታና ሰላም ይወዳል ። ክብሩ የሚገለጸው በፈጠራቸው ነገሮች መልካምነት እንጂ በፍጡሮቹ ጉስቊልናና ሥቃይ አይደለም ። እንግዲህ እኔ የማመልከው አምላክ ይህ ነው ። ይህን መልካም ነገር ከሠራ ዲያብሎስ ነው ትሉት እንደሆነ እንደፈለጋችሁ ስደቡት እንጂ እኔ ከመውደድ በቀር አልጠላውም ።

ጨካኞችን ፣ ቊጡዎችን ፣ አራጆችን ጠባሾችንና ቀቃዮች አምላኮቻችሁን አልነካምም አላመልካቸውም ። ቸሩን አድልዎ የማያውቀውን ለሰው ልጆች ሁሉ ያለአድልዎ ጸጋውን የሰጠውን አምላክ ግን ካመንሁት ብዙ ዘመኔ ነው! » ስል መለስሁለት ። « አንተ በፍጹም ነገረኛ ሰው ነህ! እኛ ጨካኝ አምላክ አለን አላልንህም እኛም የምናምነውም አንተ አምንበታለሁ የምትለውን ቸር አምላክ ነው! አለኝ። « ታዲያ በቸሩ አምላክ ካመናችሁ አትብሉ ፣ አትጠጡ ፣ተቆረጡ፣ ተፈለጡ ፣ ስገዱ ፣ ውጡ ፣

ውረዱ! ለምን ትላላችሁ? እኛ ብንሠቃይ ምን ደስታ የሚያገኝ ሁኖ ነው። እግዚአብሔር በኛ መከራ የሚደሰት? እውነተኛው እግዚአብሔር

የዓለምን ሕዝብ በእኩልነት ቢፈጥር ግፈኞች ሰዎች ደግሞ ለነሱ ዓላማ ምቹ የሆነ ግብዝና ጨቋኝ አምላክ በሓሳብ ፈጠሩ » አልሁ ።

« እኛ ይህን ሁሉ አላልንም ብቻ በኛ ቤተ ክርስ+ያን እምነት መሠረት ክርስ+ያንነትን ተቀበል ነው የምንልህ! » አለ ሰባኪው ።

« ክርስቲያንነት ትክክለኛ ሃይማኖት መስሎኝ ብቀበል እንኳ በክርስቶስ አምናለሁ እንጂ በአንድ ክፍል የተመሠረተ ቤተ ክርስቲያንን አላመልክም ። በአንድ ክፍል የምገባ ከሆነም እናቴ መጀመሪያ እንድገባበት በጠየቀችኝ ክፍል እገባለሁ ።ከዚህ የተሻለ ለማድረግ ግን እግዚአብሔር ራሱ አዝዞኝ አደርገው እንደሆነ እንጂ በሰው ትእዛዝ አላደርገውም » ስለው ሰባኪው በትካዜ አንገቱን ቅልስ አድርጎ ከጥቋቊር ልብሶቹ ጋር የተዋሐዱትን ጫማዎቹን እየተመለከተ « አሳድገን አሳድገን ዋጋችን ይህ ሆነ? » ሲል በፀፀት መልክ ጠየቀኝ ።

እኔም መለስሁና « ቢሆን ቢሆን በሰብአዊ ርኅራኄ ለፈጸማችሁት በጐ ተግባር ዋጋ መጠየቅ ባልተገባችሁ ነበር ። ዋጋ የምትጠይቁስ ከሆነ ያሳደጋችሁበትን ዋጋ እየሠራሁ እንድከፍል ጠይቁኝ እንጂ ለማሳደጊያ ዋጋ የመንፈሴን ነፃነት እንድከፍላችሁ ትፈልጋላችሁ? በፍጹም መጥፎ ጥያቄ ነው ። በወዳጅነትም ሆነ በውለታ አስጠግቶ የሰውን መንፈስ ለመያዝ መሞከር ታላቅ ስሕተት ነው » አልሁት ።

ሰባኪው ተስፋ ቆርጦ ሲመለስ እኔም በዚያ ለመኖር የነበረኝን ተስፋ በፍጹም ቆርጬ በተወለድሁ በ!ኛው ዓመት ትምህርት በጀመርሁ ባሥራ ሦስተኛው ዓመት ትምህርቴን ሳልጨርስ ከሚሲዮኑ ኰሌጅ ወጥቼ እናቴና በኦፕራሲዮን ከናቴ ሆድ ያወጣኝ ሐኪም ወዳሉበት ሆስፒታል ሄድሁ ። እናቴ ይህን ሁሉ ዘመን ስታገለግልና ብዙ ነገር ተምራ ሥራዋን ስታሻሻል ከሆስፒታሉ ታገኘው የነበረው ደመወዝ ያው በመጀመሪያ ስትቀጠር ታገኘው የነበረው ነው ።

ሰውነቷ ምንም እንኳ ከድሮው መጐሳቆል ቢድን በሥራ ብዛትና በኑሮ ችግር ተጐድቶና ከስቶ ነበር ።

እነሱ እየመጡ ከመጠየቅ በቀር እኔ ወደነሱ ሄጄ ስለማላውቅ እሆስፒታሉ በደረስሁ ጊዜ እናቴና ሐኪሙ በጣም ደነገጡ ።

በዚህም ጊዜ « ምነው? በደኅና መጣህ? » ሲል ሐኪሙ ጠየቀኝ ።

« በቃኝ! » አልሁት ።

« ትምህርትህን ሳትጨርስ? »

« መንፈሴን ሽጬ የማገኘው ትምህርት ይቅርብኝ ። እነሱ የማሳደጊያና የማስተማሪያ ዋጋ የመንፈሴን ነፃነት እንድሰጣቸው ይሻሉ ። »

« ታዲያ ምን ይሻላል? »

« ባለኝ ዓቅምና ችሎታ እየሠራሁ ራሴን ረዳለሁ ፤ » ካልሁት ቤላ « የሆነውስ ሆነና የናቴን ደመወዝ ባገልግሎቷና የሥራ ልምድ በማግኘቷ መጠን ስታሳድግላት ቆየሁ? » አልሁት ።

ልዝቡና መልካሙ ሰው አንገቱን ለባለይሉኝታ ሰዎች በሚሰማው ሰብአዊ ዕፍረት ወደታች ቀለስ አድርጎ « ደመወዝ አሻሻዩ ቦርድ አልስማማልኝ እያለ ምንም ላደርግላት አልቻልሁም! » ሲል ከይቅርታ ጋር ነገረኝ ።

« እንዴት አንድ ሰው የዕድሜውን አጋማሽ መሻሻል በሌለው ትንሽ ደመወዝ ያሳልፈዋል? የረጅም ዘመን አገልግሎትና በረጅም ዘመን ሥራና ጥናት የተገኘ ከፍተኛ የሥራ ልምድ ምን ያህል ጠቃሚ መሆኑ እንዴት ይካድ? እናንተም እንደሌሎች እስከዚህ የዋሆች ናችሁ? የርሷን ያህል የመሥራት ችሎታና የረጅም ዘመን አገልግሎት የሌላቸውን ሰዎች በያዙት ወረቀት ብቻ እየተመራችሁ የሥራ መጀመሪያ ከፍተኛ ደመወዝና በያመቱ ዕድገት የሚያገኙበት ባጀት እየሰጣችሁ አልቀጠራችሁም? ብዙ ዘመን ማገልገልና የሥራ ልምድ ማግኘት ጥፋት ነው? ዕውቀቱስ ይቅር! የሰው ዕውቀት መደምደሚያ በትምህርት ቤት ክፍል ውስጥ ብቻ የሚያገኘው ዕውቀት እንጂ በሕይወቱ ሙሉ በሥራም ሆነ በጥናትና በማንበብ የሚያገኘው ዕውቀት ዕውቀት አይደለም ብላችኋል ።

« የረጅም ዘመን አገልግሎትንስ ወዴት ትጥሉት? አገልግሎትንም ዋጋ የለውም ትሉ ይሆን? አሀ! ምን ዓይነት ዕውር ዓለም ነው እባካችሁ! ጕረምሳ ሲያዩ አሮጌን መናቅ! ምን ዓይነት የልማድ ጠንቅ ነው? የዛሬ ሽማግሌዎች የትናንት ወጣቶች የዛሬም ወጣቶች የነገ ሽማግሎች መሆናቸው ሲታወቅ በዕድሜ የገፉት ሰዎች ዋጋና በጊዜአቸው አስፈላጊ ሁነው የፈጸሙት አገልግሎት ያገኙትም የረጅም ዘመን ጥናት ለምን ዋጋ ይጣ? ሁልጊዜ ዛሬን ነገ እየነቀፈው ሊኖር ነው? የተከበረ ተፈጥሮ ያላቸው የሰው ዘሮችስ ሲያገለግሉ ኑረው ያገልግሎታቸው ዋጋ እንዳረጀ የባብ ጐፋ ከነበሩበት አካል ተገፈው መውደቅ ነው? ይህ ፍጹም የፍርድ ጉድለት ነው ። ይህን የምናገረውን ቃል የዛሬዎቹ ባለጊዜዎች ለዛሬ ይጠሉታል ። ነገ ግን በተራቸው ያገልግሎታቸው ዋጋ ከንቱ ሲሆን እውነተኛነቱን በመረዳት ይወዱታል ።

ስለዚህ ለዛሬና ለነገን ብቻ ሳይሆን ለሁልጊዜ የሚከተሉትን ሐሳቦች መከተል ይገባል ።

1ኛ፡ ብዙ ዘመን ያገለገሉ ሰዎች ባገልግሎታቸው መጠን ኑሮአቸውን የማሻሻልና የሥራ ዕድገት ዕድል ሊኖራቸው ያስፈልጋል ።

2ኛ፡ በሥራ በኑሮ ዕውቀትን በመከታተል በዕድሜአቸው ሙሉ ያገኙት ዕውቀት እየታየ የዕውቀታቸውን መጠን በየጊዜው መመዘን ይገባዋል ።

3ኛ፡ አንድ ሠራተኛ ችሎታ ካላጠረው በቀር ከሱ ቤላ ከተቀጠረ ሌላ ሠራተኛ ቀድሞ በሥራ ደረጃ የመሻሻል ዕድል እንዲኖረው ማድረግ የሚያስፈልግ ነው ።

አሁንም ስለፈጠረህ አምላክ ብለህ እናቴ ባገልግሎቷና ባገኘችው የሥራ ልምድ መጠን የደመወዝና የሥራ ዕድገት አግኝታ ሆዷን ሞልታ እንድትኖር አድርግልኝ ። እርግጠኛ ነኝ እናቴ በዚህ የረጅም ዘመን አገልግሎቷና ጥናቷ በትምህርት እያሠለጠናችሁ ከምታወጧቸው አስታማሚዎችና ነርሶች የበለጠ በሽተኞችን ትረዳለች። ነገር ግን ደመወዟና የኑሮ ደረጃዋ ከነሱ ገረዶች ኑሮ አይሻልም» አልሁት ።

ከመጀመሪያ ጀምሮ ሓሳቤን በትክክል ሲረዳልኝ የኖረው ለኔና ለናቴ ሞግዚትነት እግዜር የመረጠው እኔም በጣም የምወደው ሐኪም ራሱን

እየነቀነቀ « አንተ እውነተኛ ልጅ የሚሰማህ የለም እንጂ የምትናገረው ሁሉ እውነት ነው እኮ! እውነት ተናገርህ! እኔ እንኳ ብዙ ተምሯል የምባለው አብዛኛውን ዕውቀቴን ያገኘሁት በሥራ ላይ ሁኜ ነው ። እናትህም አንተ እንዳልኸው ብዙ ዕውቀት አግኝታለች ። ያላገኘችው በሥራዋ የማደግ ዕድል ነው ። በል አሁንም የሚገባትን ሁሉ አደርግላታለሁ » አለኝ ። እውነትም ተገቢ ዋጋዋን አሰጣት ። እኔም በዚያችው ከተማ ባንድ ሥራ ተቋራጭ ድርጅት ተቀጥሬ በሥራ ተቆጣጣሪነት በደመወዝ ከፋይነት መሥራት ጀመርሁ ። ደጉን ሐኪምና እናቴንም ሁልጊዜ በየበዓሉ ቀን እየሄድሁ እጠይቃቸው ነበር ።

# 7

## ሰላማዊ ሰልፍ ስለማስነሣቴ ።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በተመደብሁበት ቦታ በትጋት እሠራ ጀመር ። በልዩ ልዩ አጋጣሚ ምክንያቶችም በብዙ የሥራ ክፍሎች እየተዘዋወርሁ ዐየሁ ።

መሐንዲሱ ሥራ ተቋራጭ እየተቋረጠ በሚቀበለው ሥራ ሁሉ የቤትም ይሁን የመንገድ ወይም የድልድይ ሥራ ዘወትር በሥራው ላይ የምንገኝ እኔ ገንቢዎች ፣ አናጢዎችና ከሁላችን ይበልጥ አድካሚ ሥራ የሚሠሩት የጉልበት ሠራተኞች (ኩሊዎች) ነበርን ።

ነገር ግን ሥራውን የሚቋረጠው ሰው እኛ ሁላችን ካንድ ላይ ከምናገኘው ገንዘብ ይበልጥ ብቻውን ይወስድ ነበር ።

ምስኪኖቹ የጉልበት ሠራተኞች ከጧት እስከ ማታ ድንጋይ ሲሸከሙ ውለው የሚያገኙት ገንዘብ የሥራ ብዛት ያስከተለባቸውን ከፍተኛ የምግብ ፍላጐት የማይቀንስ ነበር ። ብዙ ይሠራሉ ፣ ጥቂት ያገኛሉ ። የሚያገኙትም ገንዘብ ለምኞት ቀርቶ ለመኖር የሚበቃ አልነበረም። እስኪ ምናለበት ለመኖራቸው እንኳ ቢቀር በሥራ ለመጥቀማቸው ሲሉ ቢያስቡላቸው? እኔ የሥራው ተቆጣጣሪና ጸሓፊ ሁኜ የማሠራው ገንቢዎችና ሐናጺዎች የምናገኘው እንኳ ለጊዜው ይበቃን ነበር ።

የጉልበት ሠራተኞች (የኩሊዎች) ችግር ግን አይነሣ! ጉልበታቸውና ሕይወታቸው ለነሱ ተፈጥሯል ከማለት ይልቅ ለሥራ ተቋራጮችና ለሌሎች ተፈጥሯል ማለት ይቻላል ።

አብሬአቸው በምሠራው የጉልበት ሠራተኞች ላይ የሚፈጸመውን ሁሉ ግፍ ካየሁ ቤላ በሌላው የሥራ ክፍል ሁሉ ይህን የመሰለ የግፍ ተግባርና የፍርድ ጉድለት እንዳለ በማለት ሳጠናና ስመረምር በፋብሪካዎችም ፣ በርሻ ድርጅቶችም ፣ በቢሮ ሥራዎችም ፣ በንግድ ቤቶችም በጠቅላላው ሥራ የሚባል ባለበት ሁሉ ዝቅ ያለውንና አድካሚውን ሥራ የሚሠሩት የበታች ሠራተኞች ለማሰብ እንኳ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ተጨቁነውና ተጠቅተው ዐየሁ ።

ሁኔታውም አሳዘነኝ ። ከኃዘንም አልፎ አበሳጨኝ ።ከብስጭት አልፎ አንድ ተግባር እንድፈጽም አስገደደኝ ። አንድ ቀን ቅዳሜ ለቀን ሠራተኞች ፣ ለገንቢዎችና ፣ ለሐናጺዎች ደመወዝ ስከፍል ሁሉንም ሰበሰብሁና « የነገ ዕሑድ ሳምንት በየክፍሉ ያሉ ተራ ሠራተኞችን ሰብስባችሁ « ፍላቶስ አደባባይ » በ8 ሰዓት እንድንገናኝ! አደራ! » አሌቻው ።

« እንዴት እናገኛቸዋለን? » አሉኝ ።

« ሁላችሁም ወደየምታውቋቸው ጓደኞቻችሁ ሂዳችሁ እነሱም ወደየሚያውቋቸው እየሄዱ ተሰበሰቡና ብትመጡ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው » አሌቻው ።

እነሱም በቅርብ የሚያውቁኝ የነፃነትና የእውነት ተሟጋች ስለሆንሁ ለጥቅም እንጂ ለጉዳት ያሰብሁት አለመሆኑን በመረዳት « እሺ እንሞክራለን » እያሉ ሄዱ ።

ሰኞ ጧት ተገናኝተን ሳምንቱን ባንድ ላይ ስንሠራ ለዕሑድ ያሰብሁትን ነገር የሥራ ጓደኞቼ ለሆኑት የጉልበት ሠራተኞች ነገሬቻው።

ያልሁትም ነገር ሁሎች የሚፈልጉት ትክክለኛ ሃሳብ ነበር። እጅግ ተደሰቱበት ። ተስፋ ጣሉበት ነገሩም ተስፋ የሚያስደርግ ነበር። ሳምንቱን ሳምንቱን በደኅና ስንሠራ ሰንብተን ቅዳሜ ማምሻ ደመወዝ ስከፍላቸው «

ጐበዝ እንግዲህ እንዳትረሡ! የነገ ነገር ዋዛ አይደለም! » ስል ያሰብሁትን ጉዳይ ደግሜ አሳሰብሁ ።

እነሱም ግማሾቹ « ግዴለም ሁሉም ተስማምቷል! » ሲሉ አንዳንዶቹም « ችግር ያለ አይመስለኝም! » እያሉ « በፍላቶስ አደባባይ » ልንገናኝ ተቃጥረን ተለያየን ። ጉዳዩ የተጠና በመሆኑ ዕሑድ በስምንት ሰዓት ከገመትሁት በላይ የሆነ ሕዝብ ተሰበሰበ ። የተቃጠርንበት አደባባይ በሕዘብ ተሞላ ። ከግምት በላይም ስለሆነ ያዘጋጀሁትን ንግግር ሳልነግራቸውና ሰላማዊ ሰልፉን ሳናሳይ ፖሊስ እንዳይበትነን ሰጋሁ ። ቱታ ለብሶ ከሲሚንቶ ከጭቃና ከቀለም ጋር ሲጨማለቅ ሌላ ነገር ይመስል የነበረው ገንቢ፣ በንጨት ጥራቢ ዱቄት ያፈናት ገረድ ይመስል የነበረው አናጺ ፣ የድንጋይ ብናጭ ጭቃ ኖራና ቀለም ሰው የሚያስመስለውን ቀለሙን አጥፍቶበት የነበረው ተራ ሠራተኛ ያለቺውን የበዓል ልብሱን አጸዳድቶና አሳምሮ ለዘወትሩ ጫማ የማያደርገው ጫማ አድርጎ ባንድ ላይ እጅብ እያለ ሲመጣ በልብሳቸው የሚመኩትን ሰዎች ከንቱነት ከማረጋገጡ በላይ « ሰው ሰው ነው » በሚል እምነት ለሚመሩ ሰዎች ታላቅ ደስታ ነበር ።

የስብሰባው ብዛት አሥጊ በመሆኑ ሕዝብ እንደተሰበሰበ ፖሊስ ከመምጣቱ በፊት ቶሎ ብሎ ጉዳዩን መፈጸም አስፈላጊ ሁኖ አገኘሁት ። እኛን ስላዩ ለዕረፍት የወጡ የቤት አሽከሮችና ገረዶችም እየመጡ ከኛ ተቀላቀሉ ። ከዚያም የሚከተለውን ንግግር ለተሰበሰበው ሕዝብ አሰማሁ ።

« እናንተ ወንድሞቼና እኅቶቼ! እኛ ያገራችንና የመንግሥታችን ፍጹም ታማኞች ነን ። ማንም ሰው የኛን ጩኸትና አቤቱታ እንደ አድማና ሤራ ወይም በመንግሥት ላይ እንደ ማመፅ ቢቈጥረው ጥፋቱና ኃላፊነቱ የራሱ ነው ። መንግሥታችን የኛ ተመሳሳይ ደመወዝ ካለው ከማንኛውም ሠራተኛ የሚፈልገውን ግብርና ቀረጥ ሲጠይቀን በደስታ እንከፍላለን ።

ነገር ግን የጉልበታችንን ዋጋ የሚቀሙንና ለራሳቸው ብቻ የሚያደርጉትን የግል ድርጅት መሥራቾችና ባለሞኖፖሊዎች እንቃወማለን ። የቤት አሽከርና ገረድ ለሥራቸው ተመሳሳይ ባልሆነ ደመወዝ እየቀጠሩ ከዚያም በላይ ባጋጣሚ ወድቀውና አርጅተው በተሰበሩ ዕቃዎችና በሌሎችም ትንንሽ ምክንያቶች እያመካኙ ትንሻን ደመወዛችንን አስቀርተው በፈለጋቸው ጊዜ ከቤታቸው ያባርሩናል። ባለፋብሪካዎችና ባለታላላቅ ኩባንያዎች በወር ብዙ

ገቢ ያላቸው ሲሆኑ እኛን ለዕለት ሆዳችን በማይበቃ ደመወዝ ይገዙናል ። ስንታመምና በሥራችን ላይ አደጋ ሲደርስብን ያለአንዳች ርኅራኄ አውጥተው ይጥሉናል ። መሐንዲሶችና ሥራ ተቋራጮች የተቋረጡትን ነገር በወረቀት ነድፈው በገመድ ቀይሰው ይሰጡናል ። እኛም ድንጋዩን ጠርበን ፣ ጭቃውንና ሲሚንቶውን ለውሰን ተሸክመን አገጣጥመን በወረቀት ላይ የነበረውን ንድፍ ቤትም ሆነ ድልድይ መንገድም ቢሆን ሌላ ነገር ወደአካልነት እንለውጠዋለን ። ገንዘቡ ግን ለነርሱ ይሆናል ። የሥራችንንና የድካማችንን ዋጋ እኛ ካልጠየቅን ማን ይጠይቅልናል? የኑሮአችንን ፀጥታስ እኛ ካልጠበቅነው ማን ይጠብቅልናል? ማንም ሰው በዕውቀቱም ሆነ በሀብቱ በመጠኑ ይብለጠን እንጂ የጉልበታችንን ዋጋ እየቀማ እኛን በማስራብና በማስጠማት እሱ በቁንጣንና በስካር እንዲሞት ዝም ብለን ማየት የለብንም። እኛ ብቻ አልተጐዳንም እነሱንም ጐዳናቸው ። ምንም ስለማይሠሩና ስለማይንቀሳቀሱ ከዚያም በላይ በሥራ ምክንያት የማይንቀሳቀሰውን ሰውነታቸውን ከሚያስፈልገው በላይ የሆነ ምግብና መጠጥ ሲጭኑት በድሎትና በብዙ አስካሪ መጠጥ የሚመጡ በሽታዎች ያለጊዜያቸው ይገድሏቸዋል። ባይሞቱም ያሠቃዩዋቸዋል ። እንዲሁም ልጆቻቸው ምንም እንኳ ከድሆች ልጆች ይበልጥ የመማር ዕድል ቢኖራቸው ራሳቸውን ወደ ዕውቀትና ወደ ትምሕርት በመምራት ፈንታ ወላጆቻቸው የኛን የድካም ዋጋ እየቀሙ በሰበሰቡት ሀብት ለነገ የማይገኘውን ሀገርንና ትውልድን ሊያኮራ የማይችለውን ከንቱ ደስታ ሲያሳድዱ በከንቱ ይቀራሉ። ለሌሎችም የብልጽግናና የስንፍና አርአያ ይሆናሉ ። ልጆቻቸውን ለማባለግ የሚያውሉትን ገንዘብ ለሠራተኞቻቸው የጉልበት ዋጋ ቢያደርጉት ምናለበት?

አሁንም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማቅረብና ሕሊና ቢኖራቸው እነሱ አስበው እንዲፈጽሙልን ካላሰቡ መንግሥት እንዲያስፈጽምልን ፣

1፡ ማንኛውም ባለ ፋብሪካ የገቢውና የወጪው መጠን በመንግሥት ታውቆ ለማንኛውም ሠራተኛ በሥራው መጠን ተገቢ ደመወዝ እንዲከፍልና ባለቤቱም ከሚገባው ድርሻ በላይ እንዳይወስድ መቈጣጠር ፣ ይህም ሲሆን

ሀ/ ሠራተኛው በሥራው ላይ ሳለ ቢታመም እንዲያስታምም ፣

ለ/ በሥራው ላይ ሳለ አደጋ ደርሶበት ቢሞት ከቤተ ሰቡ ውስጥ ለዚህ ሥራ የሚበቃ ሰው ቢኖር እሱን እንዲተካ ያለዚያም ለቤተ ሰቡ መርጃ እንዲከፍል ፣

ሐ/ ሠራተኛው በሥራ ላይ ሳለ አደጋ ደርሶበት አካሉ ቢጐድል የዕድሜ ልክ መጦሪያ እንዲከፍለው ይህ ሁሉ ካልሆነ ለኑሮው በቅቶ ለኢንሹራንስ የሚከፍለው ወይም በባንክ የሚቆጥበው በቂ ደመወዝ መክፈል የባለ ዕጣነት መብትም መስጠት ይገባዋል

2ኛ፡ የንግድ ኩባንያዎችም ይህን የመሰለውን ተግባር መፈጸም ይገባቸዋል ። ከዚህም ጋር አንዱን ሠራተኛ በፈለጉ ጊዜ ያለበቂ ምክንያት እያባረሩ ሌላውን በመቅጠር እንዳያጭበረብሩ መከላከል ለኛ ይገባናል ።

3ኛ ፡ አሽከርና ገረድ የሚቀጥራቸው ሰው የወር ገቢ የሚሠሩትም ሥራ ታይቶ ደመወዛቸው በደንብ እንዲወሰን ያስፈልጋል ።

ይህም ሲሆን ፡

ሀ/ አልተስማሙኝም የሚል ሰው ቀደም ብሎ በማስታወቅ የሥራ መፈለጊያ ጊዜ እንዲሰጣቸው ፣

ለ/ ደመወዛቸውን በቂ ባልሆነ ምክንያት እንዳይቆርጥባቸው ።

ሐ/ በአገልግሎት ላይ በሚኖሩበት ጊዜ ሰብአዊ ኅሊናቸው የማይቀበለው ሥቃይና መንገላታት እንዳይደርስባቸው ማድረግ ያስፈልጋል ።

4ኛ/ አንድ የሥራ ተቋራጭ ለተቋረጠው ሥራ የተመደበው ገንዘብ ታይቶ ለልዩ ለዩ አስፈላጊ ነገሮች የሚያወጣው ገንዘብ በመተማመኛ ወረቀት (ፋክቱር) ተረጋግጦ በሚያገኘው ትርፍ መጠን ለሥራ ጓደኞቹ በቂ ደመወዝ እንዲከፍልና ራሱም ሊያገኝ በሚገባው መጠን ብቻ እንዲያገኝ ማድረግ ይገባል ።

ሀብታሞች ሀብታቸውን በሥራ ላይ እንዲያውሉ የሚማሩት ዕውቀታቸውን እንዲያሻሽሉ ባለሥልጣኖች በሥልጣናቸው እንዲከበሩ

የምንጥረው የሀገራቸውን ጠቅላላ ኑሮ እንዲያሻሽሉ ነው እንጂ የወንድሞቻቸውን ደምና ላብ እየመጠጡ በግል እንዲወፍሩ አይደለም ።

የውጭ አገር ባለሀብቶችም በከፈቱት ሥራ እኛን እንዲጠቅሙን እንጂ ያገራችንን ሀብትና ጉልበታችንን ዘርፈው እንዲሄዱ አንፈልግም ።

ሀብት ያለው ገንዘቡን ዐዋቂው ዕውቀቱን ሠሪውም ጉልበቱን ፣ ተስማምተው ተፋቅረው ያውሉልንና በጠቃሚ ሥራ ሁሉም እንደያቅሙ በመብቱ ይኩራ ።

ግን ከተመረጡ ሀብታሞች አዋቆች ለምኞት ፣ ለጥቅም ፣

ድሆች ለመከራ ፣ ለችግር ፣ ለድካም ፣

ምንጊዜም ባንድ አገር ጭቅጭቅ አይጠፉም ። » ይህን ስናገር በየደቂቃው ጭብጨባው ይነጐድ ነበር ።

ንግግሬንም ቀጠልሁና « እንግዲህ እኛ ምኞታችንን ማስማትና ማስፈጸም የምንችለው በሁለት ዋና ዋና ነገሮች ብቻ ነው ። እነዚህም ፣

1ኛ፡ መንግሥት የኛ መተዳደሪያ ልዩ ደንብ እንዲያዘጋጅልንና ደንቡን አስፈጻሚ ድርጅት እንዲያቋቁምልን ማስደረግ ፣

2ኛ፡ እኛ ሠራተኞች አንዱ ወንድማችን ከወጣበትና ከተባረረበት ሥራ ቅጠሩን እያልን ከመንከውከው ባንድ ላይ ተባብረን ሥራውን በማቆም መብታችንን ባንድ ድምፅ መጠየቅ ናቸው ። ያንዱ ክፍል ሠራተኛ ሲበደል ድንበር እስከ ድንበር እንደተበደልን መቊጠር አለብን ። አንለያይ ፣ አንነጣጠል ፣ መለያየት ለደም ጠቢዎች ያጋልጠናል ። መንግሥት በጉዳዩ ሲገባልን ግን እኛም ዝም ብለን እንሠራለን መንግሥትም መብታችንን ይጠብቅልናል ። » ይህን በምናገርበት ጊዜ ሁለት ጓደኞቻችን ይዘነው ልንሰለፍ ያዘጋጀነውን ሰሌዳ ያገራችንን ትንንሽ ሰንደቅ ዓላማዎችና አንድ ትልቅ ሰንደቅ ዓላማ ይዘው ብቅ አሉ ።

እኛም በደስታ እየተጓዝን ከነሱ ጋር ተገናኘን። በሰሌዳው ላይ የሚከተሉት ቃሎች በጉልህ ተጽፈው ነበር።

« እኛ ተገቢ ድርሻችንንና መብታችንን የተቀማን ተራና የጉልበት ሠራተኞች የሥራችንን ዋጋ እንጠይቃለን ። »

« እኛ ምንም የኑሮ ችግር ቢኖርብን በዓቅማችን መጠን ለሀገራችንና ለመንግሥታችን ታማኞች ነን ። »

« እኛ የምንጠይቀው ቀላል ነው ። ይኸውም ጠቃሚነታችንና ያለኛ መኖር የማይቻል መሆኑን አሠሪዎች ሁሉ ዐውቀው እነሱም ሳይጐዱ ድርሻችንን እንዲሰጡን መብታችንንም እንዲያከብሩልን ነው ።

ይህን ሰሌዳ ይዘን ያገራችንን ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለብን የሀገራችንን ሕዝብ መዝሙር እየዘመርን በከተማው ታላላቅ መንገዶች መጓዝ ጀመርን ። ከየቦታው እየመጣ ከኛ ጋር የሚደረበው ሕዝብ እጅግ በዛ ። በልዩ ልዩ ኩባንያዎችና የፋብሪካ ቤቶች እየዞርን ሰልፉን ካሳየን ቤላ ቀኑ ዕሑድ የነበረ ከመሆኑ በላይ አንዳንድ ፖሊሶች ወደኛ እየመጡ ስላስቸገሩን ለበነጋው ጧት ተቃጥረን ተበታተንን።

በበነጋው ሰኞ ከቀኑ በሁለት ሰዓት በተቃጠርንበት ቦታ ከትናንትናው በበለጠ ተሰብስበንና ተሰልፈን ጒዞ ጀመርን ። ልክ በሦስት ሰዓት አሠሪ ሁሉ ወደየሥራው ቦታ ቢሄድ በማንኛውም ቦታ ሠራተኛ የለም ። በየቦታው ዓይን ፍጥጥ አለ ። ከየቦታው ተለቃቅመን ለዘመቻ የታዘዘ ሠራዊት መስለን ስንተም ይንቁን የነበሩት አለቆቻችን በመስኮት እየሠረቁ በፍርሃትና በጭንቀት ይመለከቱን ነበር ። በየሥራው ቦታ እያወካንና አሠሪዎችን እየወቀስን ካለፍን ቤላ ወደብሔራዊ ምክር ቤታችን ሄድንና ጩኸታችንን አሰማን ። ከዚያም ወደጠቅላይ ሚኒስቴር መ/ቤት ስንሄድ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከቢሮው ወጥቶ ሲጠብቀን ቆየ ።

ከዚያም ደርሰን ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ከመገናኘታችን በፊት ፖሊሶች በመኪና በመኪና ሁነው ደረሱና የሚያስለቅስ ጢስ ሊተኩሱብን ፈለጉ ። እኛ ግን ቶሎ ብለን « እናንት ፖሊሶች እንዳትነኩን! እኛ ለመንግሥታችን አቤቱታ የምናቀርብ ተበዳዮች ነን እንጂ በጥባጮች አይደለንም ። እሱን ጢስ ወስዳችሁ በባለኩባንያዎች ፥ በባለ ሥራ ተቋራጮችና ፥ በቢሮ አለቆች ዓይኖች ተኩሱት! እነሱ ናቸው በጥባጮች! ማየት ያቃታቸውም የነሱ ዓይኖች ናቸው! » አልናቸው ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩም በጁ እየጠቀሰ እንዲተዉን አዘዛቸው ። ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፊት እንደቀረብንም የሚከተለውን አጭር ምክር ሰጠን ።

« አሁን ሥራውን ስታቆሙት በቂ ተቀማጭ ገንዘብ ስለሌለን እናንተንም አገራችሁንም ትጐዳላችሁ ። ሥራችሁን እየሠራችሁ ችግራችሁን ለኔም ሆነ ለሌሎች ባለሥልጣኖች ብታስታውቁን ተገቢውን ከማድረግ ችላ አንልም ።

አሁንም ጉዳዩን እያጠና መብታችሁና ኑሮአችሁ ዋስትና የሚያገኝበትን ደንብ የሚያዘጋጅ ኮሚቴ እንዲቋቋም አሁን የሥራዬ መጀመሪያ አደርገዋለሁ ። ስለዚህ በየሥራችሁ ግቡ! » ይህን ቃል በደስታ ተቀብለን ተመለስን ። ከቅድሙም ተገቢ መብታችንን ለማግኘት እንጂ ለብጥበጣ አልወጣንም።

ሁላችንም በየሥራችን ተሠማርተን ስንሠራ ውስጥ ውስጡን አነሳሺ መሆኔ በየቦታው ተነግሮ ኑሮ በማናቸውም ሥራ ማንም እንዳይቀበለኝ ከተደረገ ቤላ « ለሥራችን አታስፈልግም » የሚል ስንብት ደረሰኝ ። እኔም በሁኔታው ከማዘኔ በቀር በምንም ሳልደነግጥ ከሥራው ወጣሁ ። ነገሩን ሁሉ ስለተረዳሁት ከሌላ ቦታም ሥራ አልጠየቅሁ ።

# 8

## ከጓደኞች ጋር ለግብርና ሥራ ስለመዘጋጀቴ ።

የሥራ ቀጣሪዎችንና የከተማዎችን ግፈኛ ሥራ ማየት እንደኔ የሰለቻቸውና በግል ሥራና በግል ኑሮ ሰላምና ፀጥታ ለማግኘት የሚሹ ለካ ብዙ ሰዎች ኑረዋል ። በሳምንት ጊዜ ውስጥ ባንድ ደን ተሠማርተው በግብርና ለመኖር የሚሹ ድሮ የማውቃቸው ብዙ ጓደኞች አገኘሁ ። ደግሞ የእግዜር ነገር ጥሎ አይጥልምና ያገኜቸው ጓደኞቼ ልዩ ልዩ ሙያ ያላቸው ነበሩ ። አንዱ ጓደኛዬና እኔ የርሻ ችሎታ ሲኖረን ሦስተኛው ጓደኛችንና ባለቤቱ እንዳጋጣሚ ሁለቱም በነርስነት ደረጃ ያለ የሕክምና ሙያ ነበራቸው።

እንዲሁም አንዱ እስከሁለተኛ ደረጃ የማስተማር ችሎታ ሲኖረው የቀሩትም በሐናፂነትና ብረት በመቀጥቀጥ በቀሩትም ልዩ ልዩ ሥራዎች ችሎታ

ያላቸው ነበሩ ። በጠቅላላው አሥሩ ጓደኞች አሥር ልዩ ልዩ ስጦታ ነበረን ። ከኛ ሦስቱ ብቻ ያለሚስት ስንገኝ ሰባቱ ከሚስቶቻቸው ጋር ነበሩ ። እኛም ለማግባት ተስፋ ነበረን ።

ሁላችንም ተገናኝተን ተመካክረን በአንድ ጠፍ ቦታ ተሠማርተን የሰውን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርንም እጅ ተማምነን እያረስንና እየቆፈርን ምድር ገነት መሆኗን በሚያስመሰክር ሰላማዊ ኑሮ ለመኖር ቆረጥን ። ያለንን ሀብት ከሰበሰብን ቤላ ወደልማት ሚኒስቴር መ/ቤት ሂደን ለመሬት አልሚዎች ከተፈቀደው የብድር ባጀት ብድር እንዲሰጠን አመለከትን ።

በዚህም ጊዜ አንደኛ ልታለሙት የምትችሉት መሬት ያላችሁ ለመሆኑ መረጃ እንድታቀርቡ ። ሁለተኛ ለምትበደሩት ገንዘብ ሊታመን የሚችል ዋስ እንድታቀርቡ የሚል ጥያቄ ቀረበልን ።

በዚህ ነገር ስንበሳጭ ጥቂት ቀኖች እንዳሳለፍን አንድ ቀን ወደሚኒስትሩ ቢሮ ሄድንና ለሚኒስትሩ አመለከትን ። ሚኒስትሩም ከፍ ብዬ የጠቀሴቸውን ግዳጆች መፈጸም ያለብን መሆኑን ሲነግረን ነገሩን ካፉ ቀበል አድርጌ « ጌታዬ! መሬት ያለን ለመሆኑ በቂ መረጃችን ያገሪቱ ተወላጆች መሆናችን ነው ። ያገሪቱ ተወላጆች መሆናችንን የሚክድ የለም ። የሀገሪቱ ተወላጆች ከሆንም አብዛኛው ክፍሏ በጠፍነት ከሚገኘው አገራችን መሬት ጠቧልና ርስት አይገባችሁም ሊለን የሚችል አይገኝም ። ከዚህ ላይ ባለርስቶች መሆናችንን መረጋገጡ ነው ። የሰውን እርሻና ወደቅ (እዳሪ) ታርሳላችሁ እንዳትሉን እኛ የምንፈልገው ፍጹም ደንና ድንግል የሆነ ከሰው የራቀ ቦታ ነው ። ዋስ ለሚሉንም እኛ በመንግሥታችን እጅ ያለን አገራችንን የምንወድ ታማኞች ነን ካጠፋንም የትም አናመልጥም ራሳችን እንቀጣለን ። ከዚህም በቀር ገንዘብን በከንቱ እያባከኑ በዕዳ የሚዋኙ ወሮበሎች የሚገኙ ጋለሞቶችና የመጠጥ ነጋዴዎች በብዛት በሚገኙበት ከተማ ነው እንጂ አንድ የመጠጥ ቤት ወይም አንዲት የከተማ ቅሬ በማይገኝበት ደን ገብተን ለመሥራት ከፈለግን ገንዘባችንን በምን እናባክነዋለን? ከሁሉም በላይ በማንኛውም ቦታ በማንኛውም ጊዜ ራሳችንን የምንቈጣጠር ሰዎች መሆናችን ዋጋ ሊኖረው ይገባል ።

ስለዚህ ከያንዳንዳችን ብዙ ብዙ ቅጅ ፎቶግራፍ ይያዝና ገንዘቡ በእምነትና በፊርማ ይሰጠን። ካልተረዳዳን ካልተማመንንና በራሳችን ካላመንን የተሻለ ሥራ ልንሠራ እንዴት እንችላለን?» ስል አስረዳሁት ።

ሚኒስትሩ አንገቱን ወደጠረጴዛው ቀለስ አድርጎ ጥቂት ካሰበ ቤላ « በሉ እስኪ አሁን የነገራችሁኝን ሁሉ  በጽሑፍ አርጋችሁ አቅርቡልኝና ለቦርዱ አስተላልፈዋለሁ ። » አለ ።

እኛም ትእዛዙን ተቀብለን ከወጣን ቤላ በሁለተኛው ቀን ሓሳባችንን ሁሉ በዝርዝር ጽፈን ለሚኒስትሩ አቀረብን ። ሚኒስትሩም ካነበበው ቤላ «በሉ ደኅና ነው ። ለቦርዱ አቀርብላቼለሁ » አለን። እኛም እየተመላለስን ደጅ ስንጠና ጥቂት ወሮች ካለፉ ቤላ በሰባት ከመጠነኛ ወለድ ጋር በሙሉ የሚከፈል ለያንዳንዳችን አራት ሺ በድምሩ አርባ ሺህ ብር እንዲሰጠን ቦርዱ ወስኖ ሥርዓቱ እስኪፈጸም ደግሞ ብዙ ሳምንት አለፈና ቸኩ ተሰጥቶን ከልማት ባንክ ገንዘቡን ተቀብለን ልዩ ልዩ የርሻ መሣሪያዎችን የምግብ ማብሰያዎችን ትንንሽ ድንኳኖችን የሸራ አልጋዎችን ቡት ጫማዎችን የጫካ መመንጠሪያና የዛፍ መቁረጫ መሣሪያዎችን ሁሉ ገዛን ።

ከዚህም በላይ ልንሄድ ያቀድንበት ቦታ ድንግልና ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ የማይሻ መሆኑን ብናውቅም መሬትን ለማዳበር የሚጠቅሙ ልዩ ልዩ ቅመሞች (ኬሚካልስ) በመጠኑ ገዝተን ያዝን ። እንዲሁም ልዩ ልዩ የሕክምና መድኃኒቶችን የተባይ ማጥፊያ ዲዲ+ ጠመንጃዎችና ጥይቶች አዘጋጀን ። በጠቅላላው ሁሉንም አዘጋጅተን መጽሐፎቻችንን ፣ ትራንዚስተር ሬዲዮዎቻችንን ሸከፍን ። ሸራ የመሰሉ ቱታዎች በጥንድ በጥንዱ ተዘጋጁ። ሁሉ ከተዘጋጀ ቤላ ካገር ግዛት ሚኒስቴር የፈቃድና የመታወቂያ ወረቀት አስወጥተን ወደ አንድ ጠፍ የሚበዛበት አውራጃ ጓዛችንን ሁሉ በባቡር ጫንና የኖርንባትን ከተማ ወዳጆቻችንንና ዘመዶቻችንን ተሰናብተን በሌሊት ባቡር ተጓዝን ። ሌሊቱን በሙሉ ስንጓዝ አድረን በበነጋው እስከ እኩለ ቀን ከተጓዝን ቤላ ከምንፈልገው አውራጃ ደርሰን ከዚያም ጥቂት ሳናርፍ ያን ሁሉ ዝግንትል ዕቃችንን ማውረድ ጀመርን ። ሴቶቹ እንኳ ደከመን ሳይሉ ከኛ ጋር ከባዱንም ቀላሉንም ዕቃ እየተረዳዱ ሲያወርዱ ማየት ባንድ መንፈስ ለአንድ ዓላማ ቆርጠው የተነሡ ሰዎች ምን ያህል ኅብረት ያላቸው መሆኑን ያረጋግጥ ነበረ ። ከወረድንበት ጣቢያ ዕቃችንን ሁሉ ደብረን ውለን እዚያው አደርን ።

በበነጋው አምስቱን ወንዶች ሴቶችንና ዕቃችንን እዚያው ትተን ከወንዶቹ አምስቱ ብቻ ለሦስት ለአራት ቀን የሚሆን የቆርቆሮ ምግብ ሰርዲን ቶኖ ልዩ ልዩ ፍራፍሬዎችን ደረቅ ዳቦ የውሃ ኮዳዎች ታጣፊ የሸራ አልጋዎችና አንድ ትንሽ ድንኳን እንዲሁም በቊጥራችን አንዳንድ ጠመንጃና ጥይቶች ይዘን ከሕዝብ ተለይቶ በጠፍነት የሚኖር ደን ለመፈለግ ሄድን። አንድ ቀን ተኩል በግር ከተጓዝን ቤላ ማዶ ለማዶ አንድ ታላቅ ጫካ ዐየን። ያለ መጠን ገንግነው የሚታዩ የፅድ የዝግባ የወይራና የሰሳ ዛፎች ቅርንጫፍ ለቅርንጫፍ ተያይዘው በደኑ አናት ላይ ዱቄት ቢፈስ እንኳ የሚያሳፍሱ ከመምሰላቸው በላይ በሥራቸው የበቀሉት ትንንሽ ዛፎችና ቁጥቋጦዎች እንዲሁም ሐረጎች ጫፋቸው ወደታላላቆቹ ዛፎች ቅርንጫፍ በመድረሱ ደኑን ጥቂት ራቅ ብለው ሲያስተውሉት ያ ሰፊ ደን ለተአምር የተፈጠረ አንድ እንግዳ ዛፍ የበቀለበት ይመስል ነበር እንጂ እውነትስ ብዙ ዛፎች ባንድ ላይ በመብቀላቸው እንደዚያ የተስማማና አንድ የሆነ ትርእይት ይገኛል ለማለት ያስቸግር ነበር ።

ጥቂት ጥቂት ድካም ተሰምቶን ነበር። ቢሆንም አትፍረዱብን የፒያሣ ወጣቶች ነበርን። እስከዚህ መሞከራችንም ጀግኖች ነን ደኑ እንደዚያ ሁኖ ሲታየን ግን በደስታ ስሜት ደማችን ሞቀ ። ዛል ባለ ሁኔታ ነወዝ ነወዝ ማለቱ ቀረና ርምጃችን ቀልጠፍ ቀልጠፍ አለ ።

በዚህ ሁኔታ አንድ ሰዓት ያህል እንደተጓዝን ከደኑ ደረስን ። ደኑ ጥቅጥቅ መሆኑ ባይካድም በሩቁ እንዳየነው ያህል ፍጹም ጨለማ አልነበረም ። ሌላው እንኳ ቢቀር ውስጥ ለውስጥ እየተሽሎኰሎኩ ለመሄድ ከሾኻሞቹ ቁጥቋጦዎችና ከጋሬጦች አስቸጋሪነት በቀር ሌላ ችግር አልነበረም ። ጠመንጃዎቻችንን በሚችሉት መጠን ጥይት ካጐረስንና በካርታ የሞሉ ጥይቶችንም በጃኬቶቻችን ኪሶች ካደረግን ቤላ ወደደኑ ውስጥ መግባት ጀመርን ።

ባንድ በኩል ገብተን ቀጥታውን ለመሄድ ብንፈልግ እጅግ አዳጋች ሆነ። አራት አምስት ጊዜ እንደተራመድን አንድ እሾኻም ቁጥቋጦ በግንባራችን ሁኖ ማለፍ አይቻልም ይለናል። ወደሌላ አቅጣጫ ዘወር እንበል ስንል በጥፍራም ሾኹ ጨርቃችንን ጠልፎ ይይዝና እንደ ቸር ጋባዥ ምንም ቢሆን ሳትቆዩ አትሄዱም የሚል ይመስል ነበር ። ያደረግነው ቡት ጫማ ከጋሬጣውና ከድቡሽቱ ጣጣ ሁሉ ስለጠበቀን ዋጋው ምን ያህል መሆኑን ያስረዳን ነበር። በዚህ ሁኔታ ጥቂት እንደተጓዝን አንድ ሾኻም ቁጥቋጦ የነብር ጥፍር የመሰለ

ሾኹ ጃኬቴን ለቀም አድርጎ ያዘብኝ ። ሾኹን ለማስለቀቅ ወደቁጥቋጦው ዞር ስል አንድ ወጣት ዘንዶ አፉን በጣም ከፍቶ አንገቱን ወደኔ መዘዝ ሲያደርግ ዐየኹት ። በዚህም ጊዜ ወደፊትም ሆነ ወዴላ ወደቀኝም ሆነ ወደግራ ሩጦ ለማምለጥ ወይም ጥይት ለመተኮስ የማልችል መሆኔን ስለተረዳሁ አንገቱን ቀጥ አድርጎ በቁመቴ ልክ በሚሆን መጠን ወደላይ የቆመውን ዘንዶ ወደኔ ደርሶ ሊይዘኝ ሁለት ጫማ ያህል ርቀት ብቻ ሲቀረው ጠመንጃዬን እንዳነገትሁ ሞተ ነፍሴን ዘልዬ በሁለት እጄ አንገቱን ያዝሁት።

ከዚያም ስንታገል አንገቱን በሙሉ መያዙ ለጄ አስቸጋሪ ስለሆነብኝ ስልሞውን ብቻ ለይቼ ይዤ ስታገለው መተንፈሻ አጥቶ ሆዱ ተነፋፋ። ቀስ በቀስ በወገቤ እየተጠመጠመ ሲገርፈኝ ያደርግብኝ የነበረው ከፍተኛ ጉዳት ተቀነሰልኝ ።

ጓደኞቼ ርስ በራሳቸው ሲፈቃቀዱ እኔን አጥተውኛል። በዚህ ጊዜ በሾኽና በቊጥቋጦው ምክንያት ሩቅ ለመሄድ ያልቻሉ ስለነበር በሄዱበት ተመልሰው እኔ ካለሁበት ቢደርሱ ከዘንዶ ጋር ስታገል አገኙኝ ። በጣም የተጐዳሁ ስለመሰላቸው ለመጀመሪያው በጣም ተደናግጠው የሚያደርጉት ጠፍቷቸው ነበር። ጥቂት ከቆዩ ቤላ ግን እያስተዋሉና ልብ እየገዙ ስለሄዱ እኔ ሳልጐዳ ዘንዶውን ሊገድሉ የሚችሉበትን መንገድ ፈለጉ ።

በዚህም ጊዜ አናጺው ጓደኛችን በወገቡ ያለውን ሽጉጥ መዘዘና ለነርሱ ጓደኛችን ከሰጠው ቤላ ከቀሩት ሁለት ጓደኞቻችን ጋር ሁኖ የዘንዶውን ጅራት ያዙና ሌሊት ወጥረው ሳቡት። እኔም ምንም እንኳ በጣም ደክሜ የነበረ ቢሆን እጄ ስልሞውን ከድንጋጤ ጋር አክርሮ እንደያዘው በጣም ጠብቆ ስለነበረ በራሱ በኩል ብቻዬን ሁኜ እስብ ነበር። በተቻለ መጠን ጥቂት ግትር አድርገን እንደያዝነው ነርሱ ጓደኛችን ቀረበና ዘንዶውን እሆዱ ላይ አራት የሽጉጥ ጥይት ከነመረቁ ሲያጠጣው በፂዕረ ሞት ኩምትር ሲል እኔንም ባለሁበት ጓደኞቼንም ባሉበት ሌሊት በሀይል ጣለን። ይህ ዘንዶ ልባላ በማለቱና ክፉ አውሬ በመሆኑ ባያናድደኝ ኑሮ ተሰብስበን ያለርኅራኄ ባደረግንበት ማጥቃት አሳዝኖኝ ነበር።

ታዲያ ምን ይሆናል? ላጥቃ ማለት ክፉ ነው። ሰው ራሱን ከጥቃትና ከጉዳት ለማዳን ባለው የተፈጥሮ ስሜትና ግዳጅ እንኳንስ በተፈጥሮ የማይመሳሰለውን የዱር አውሬና መሰሉ የሆነውንና ወንድሙን ሰውን ያለርኅራኄ ማጥቃቱ ጥርጥር የለበትም። ዘንዶውን ከገደልን ቤላ አነሡኝ ።

ምንም ከዘንዶ ጋር ስታገል ብዙ ብደክም ለመሄድ እስኪሳነኝ ባለመጐዳቴ ወደፊት ጉዞአችንን ለመቀጠል ጀመርን። ነገር ግን አናጺው ጓደኛችን « ቆይ እንግፈፈው » አለ ።

እኛም በሐሳቡ ተስማምተን ሁለት ሁነው በያዝናቸው ሰንጢዎች ሲገፉ ሁለቱ ቆመው ይመለከቱ ነበር ። እኔ ግን በጣም ደከም ስላለኝ ካንድ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብዬ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ከዚህ ዘንዶ ጋር ያደረግሁትን ትግል በመሳቀቅ አስታውስ ነበር ።

ቶሎ ብለው ገፈፉትና ቆዳውን ይዘን ወደ ፊት ልንሄድ ስንል ነርሱ ጓደኞችን « የለም! የለም! አሁን ወደጫካው ውስጥ አንግፋ? አንድ ብልሃት ትዝ ብሎኛል ። ከዚህ የዘንዶ ሥጋ የቻልነውን ያህል ቆርጠን እንያዝና ከዚህ ጫካ ከመድረሳችን በፊት ተሻግረነው ወደመጣነው ወንዝ እንሂድ ። ከዚያ ጉንዳን አይታችሁ የለም? » አለ ።

« እንጃ! እኔ ልብም አላልሁት » አለ አናጺው ጓደኛችን ።

ሁላችንም « አላየነውም! » አልን ።

ነርሱ ጓደኞችን ግን « ግዴለም እኔ ዐይቻለሁ » አለ ።

« ለመሆኑ ምን እንዲያደርግልን ነው? » አለ አንዱ ጓደኛችን ።

« ግዴለም እኔ አሳያቼለሁ » ሲል ነርሱ ከተናገረ ቤላ ከዘንዶው ሥጋ አምስት ስድስት ጉማጅ ያዝንና ወደመጣንበት ተመለስን ። ከዚያም ጫካውን ወጥተን ጥቂት እንደተጓዝን ተሻግረናት ከሄድነው ወንዝ ደረስን ። ከዚያ ስንደርስ ነርሱ ጓደኛችን እንደነገረን ሁሉ በወንዙ ድንበር ለድንበር እጅግ ብዙ የሆነ ጉንዳን ይልመጠመጣል ። ነርሱ ጓደኛችን የያዝነውን የዘንዶ ሥጋ ጉማጅ ግራና ቀኝ አልፎ አልፎ ጉንዳኖች በሚጓዙበት ግንገን ጥግ ለጥግ ጣል ጣል አደረገውና እጃችንን እዚያው ከወንዙ ሙልጭ አድርገን ታጥበን ከወንዙ ጥቂት አለፍ ብለን ድንኳናችንን ተክለን እዚያው አደርን። የኔ ቅዠት ብቻ ከዘንዶ ጋር መታገል ሁኖ ሲያድር ሌሎች ጓደኞቼ መልካም መልካም ሕልም ማየታቸውን ጧት ነገሩኝ። ጧት ተነሥተን የምንሄድበትን ስንመካከር ነርሱ ጓደኞችን « አሁን ወደወንዙ እንሂድ! » አለ ።

እኛም ትናንት ማታ ያደረገውን እናውቅ ስለነበር እሺ ብለን ወደወንዙ ጉዞ ስንጀምር አንዱን ጥቂት አርጀት ያለ አንሶላውን ያዘና ሄድን። እወንዙ ስንደርስ ያ ሁሉ ጉንዳን አልፈን አልፈን ካስቀመጥናቸው የዘንዶ ሥጋ ቁራጮች ላይ ሰፍሮ ሰፍሮ ተጠቅሎ የተቀመጠ ማቅ መስሎ ነበር።

ያን ሁሉ ጉንዳን ከነሥጋው ቀስ አድርጎ በሁለት እንጨት እያነሣ ካሮጌው አንሶላ ላይ ከደረደረው ቤላ የአንሶላውን ጠርዞች ስብስብ አድርጎ እህል እንደተሞላ ጆንያ አፉን በገመድ አሠረና « እንግዲህ ጫካችንን በፊት የሚያቀኑልን እነዚህ ጉንዳኖች ናቸው » አለ ።

እኔም ቀበል አድርጌ « መልካም! መልካም! » አልሁ ።

እኛ ሌሎችን ዕቃዎቻችንን ነርሱ ጓደኞችን የጉንዳኑን መንጋ ተሸክመን ወደጫካው ከተመለስን ቤላ እጫካው ስንደርስ ጥቂት ወደ ውስጥ ገባ ብለን ጉንዳኑን እዚያ ላይ ዘረገፍነው ። ገና እዚያው ላይ እያለን ጉንዳኑ በጫካው ውስጥ የሚገኙ ተባዮችንና ነፍሳቱን ሁሉ እያሰሰ የወረራ ሥራውን ቀጠለ ። በጓደኞችን ዘዴም ተደነቅን ። ጉንዳኖች ምንም እንኳ በጫካው የሚገኙትን አራዊት ሁሉ ጨርሰው ሊያጠፉልን ባይችሉ ብዙ አራዊትን እንደሚያባርሩልን እርግጠኞች ነበርን ።

ከዚህ በኋላ ጉንዳኖችም የወረራውን ሥራ ሲያከናውኑ እንዲቆዩ እኛም ሰዎቻችንን ይዘን እንድንመጣ በማለት ሰዎቻችንና ዕቃችን ወዳሉበት መጠነኛ ከተማ ተመለስን ።

ሰዎቻችንንና ዕቃዎቻችንን ሁሉ በብዙ ድካምና መላ እንደምንም አጓጉዘን ወደጫካው ከደረስን ቤላ እጫካው ጥቂት ወጣ ብላ በምትገኝ ገላጣ ቦታ ላይ ድንኳኖቻችንን ተክለን ለጊዜው እዚያው ላይ ሰፈርን ።

በየቀኑ ቁጥቋጦዎችንና ዛፎችን እየቆረጥን ለከሰልነትና ለማገዶነት የሚያገለግለውን እንጨት ለብቻ እየከመርን የቀረውንም ጥቂት መጠጥ ሲል በቆርቆሮ ከያዝነው ቤንዚን በመጠኑ በመጠኑ እያርከፈከፍን እያቃጠልን በጫካው መሓል ሰፊ የሆነ ገላጣ ቦታ ከማውጣታችን በላይ መሓል ለመሓል ሰፋ ያለ መንገድ አውጥተንለት ነበር ። መቼም መልካም ቦታ ምኑም አይጐድልበትና ከፍተኛነት ካለው ሥፍራ ላይ መንጭታ የጫካውን መሓል አቋርጣ የምትወርድ ጥሩ ምንጭ ነበረች ። መንገዳችንን እስከምነጪ አናት

ካደረስን ቤላ ያን ቡክቡካ በመቆፈሪያ መሣሪያ ቀርቶ በጅና በግር ቢነኩት እንኳ የሚናደውን ልል መሬት እየማስን ቦይ በማውጣት ያችን ቀዝቃዛና ጥሩ ምንጭ ወደፈለግነው አቅጣጫ እንወስዳት ጀመር። በዚህ ሁኔታ የማልማት ሥራ ወደምንጀምርበት ሥፍራ የሚያወርዳት አንድ ቦይ ለጊዜው ወደሰፈርንባት ቦታ የሚያወርዳት አንድ ቦይ ከፈትንና ምንጯን በሁለት መንገድ እንጠቀምባት ጀመር ። ብዙ ቦታ ከመነጠርንና ምንጥሩን ካቃጠልን ቤላ ከኛ ጥቂቶች ገበሬዎች ወደሚገኙበት ቀበሌ ሂደው በሬዎች ፣ ፈረሶች ፣ ላሞች፣ በጐችና ፍየሎች ገዝተው እንዲመጡ አደረግን ። ከቀሪዎችም ግማሾቻችን ያን ለስላሳ መሬት በመደብ በመደብ እየከፈልን ለወጉ ያህል በመቆፈሪያ ጫር ጫር እያደረግን የልዩ ልዩ አትክልቶችን ዘሮች ( ችግኞችን ) አበቀልን ። በሬዎችና ፈረሶች ከመጡ ቤላ በነሱ በሚሳቡ የርሻ መሣሪያዎች መሬቱን ስናለሰልስ ቆይተን ዝናብ መጣል ሲጀምር ልዩ ልዩ የእህል ዓይነቶች ዘራን። በጫካው መካከል በአናጺው ጓደኛችን መሪነት ለያንዳንዳችን መኖሪያ የሚሆን መጠነኛና ጥሩ ጥሩ የሣር ክዳን ቤቶች ከመሥራታችን በላይ አንድ በመደዳ የተሠራና ብዙ ታላላቅ ክፍሎች ያሉት ሰቀላ ቤት ለምግብ ማብሰያ እንዲሆን አዘጋጀን ። በጠቅላላው ብዙ ዝግጅት አከናውነን ኑሮ ከጀመርን ቤላ ያን የልዩ ልዩ አራዊትና ተባዮች ርስት የነበረ ጫካ ካላዩት በቀር በቃል ለመግለጽ በሚያስቸግር ውበት አስጌጥነው ።

ከጊዜ ቤላማ ከመንግሥት የተበደርነውን ገንዘብ የተወሰነው ጊዜ ከመድረሱ በፊት ከፍለን ጨርሰን ነፃ ሰዎች ስንሆን አንድ የልጆቻችን ትምህርት ቤት አንድ ጥቂት አልጋዎች ያሉት ክሊኒክ ከመሥራታችን በላይ የርሻ መኪናዎችና አንድ የኤሌክትሪክ ጄኔሬተር ሌሎችም አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች ገዛን ። ቤታችን እንደድሮው የአፈር ወለልና የሣር ክዳን መሆኑ ቀርቶ ክዳኑ ቆርቆሮ ወለሉ ሳንቃ ሆነ። እህሉና ፍራፍሬው ሥጋው በሰፊው ይሸጥ ጀመር ።

እኛም በሥራችን እየተደሰትን ከድሮው በበለጠ ትጋት እንሠራ ጀመርን። ከአደር አደር ልዩ ልዩ ሙያ ያላቸውን ሠራተኞች እየተቀበልን ከኛ ድርሻ ምንም ያህል በማያንስ አበል እያስገባን በትምህርት በርሻ በሕክምና በሌሎችም ጉዳዮችም ራሳችንን ችለን መኖር ጀመርን ። መልካም ቦታ ለሚሠራበት ሰው የገነት ቁንጮ መሆኑን እግዚአብሔርም ሰውን እንዴት እንደሚወደው የመሬት ጌታ ማድረጉ ብቻ በቂ መሆኑን ያስረዳ ነበር። ይህ

ሁሉ ሲሆን መንግሥት ከኛ የሚጠይቀውን ግብር ያለ አንዳች ሹም አስገዳጅነት ቀደም እያደረግን ከመክፈላችን በላይ ለማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና አደጋ ለደረሰባቸው ሰዎች መራጃ ድርጅቶች በዓመት ብዙ ሺህ ብር እንከፍል ነበር ።

ከዚህም በቀር በየጊዜው በጣም ተቸግረውና መድረሻ አጥተው የምናገኛቸውን ሰዎች ወደርሻ ድርጅታችን እየወሰድን ለኑሮአቸው የሚበቃ ደመወዝ እየሰጠን ልጆቻቸውን ከልጆቻችን ጋር እኩል እያስተማርን በሥርዓት በፍቅር በጨዋነት እናሳድግ ጀመርን ። ልጆቻችን ከሚማሩባቸው መጻሕፍት መካከል ግፍን አጥቂነትን ሌብነትን ፣ አጭበርባሪነትን አንዱን ፍጡር ለሌላው መጫወቻ አሻንጉሊት አድርጎ ማሳየትን ነጣቂነትን በወራሪነት የሚገኝ ጀግንነትን ታላቅ ነገር እያስመሰሉ የሚያወሩ ተረቶችንና ታሪኮችን አናስገባቸውም ነበር። የልጆቻችን የንባብ መልመጃ ተረቶች ሁሉ አንድ ሰው ጥበብን ለመከታተል መሬትን ለማልማት ሲደክም በሽታ ወይም አደጋ ደርሶበት ሲጨነቅ ሌላው ሰው ደርሶ እንዴት እንደረዳውና እንዳዳነው በዚህም ምክንያት እንዴት ወዳጆች ሊሆኑ እንደቻሉ አንድ ሰው እናቱ በልጅነቱ በአንድ በሽታ ሙታበት ርኅራኄ በሌላት መጥፎ የንጀራ እናት ሲሠቃይ አድጎ የቀሩት ልጆች ሁሉ እንደሱ እናቶቻቸው ሙተውባቸው እንዳይሠቃዩ እናቱን የገደለበትን ዓይነት በሽታ የሚከላከል መድኃኒት እንዳገኘ ተንኮልና ክፉ ሥራዎች በሠሪያቸው ላይ ከፍ ያለ ሥቃይ እንዳደረሱ የሚያሳዩና ይህን የመሰሉ ነበሩ ።

በሃይማኖት በኩልም ሁሉን የፈጠረ አምላክ ምን ያህል ቸርና ለሰው ከፍተኛ አእምሮን የሰጠ መሆኑን እግዚአብሔርን ለማስደሰትም እንደሱ ቸር መሆንና ለሰው ይቅርና ለእንስሶችና ለአራዊት እንኳ መራራት የሚገባን መሆኑን እናስተምራቸው ነበር ። አጥቂን ለመከላከል ብቻ ካልሆነ በቀር ሌሎችን አጥቅቶ የመጠቀምም ሆነ ክብር የማግኘት ስሜት በልጆቻችን አእምሮ ሳይሠረጽ በቅን ትምህርት ቀጭተን አስቀርተነዋል ።

ለምሳሌ አንድ ታሪክ ተራኪ « ናፖሊዎን የሚባለው የፈረንሳይ ንጉሥ ዓለምን ለመግዛት ብርቱ ምኞት ነበረው ። በዚህም ምክንያት ብዙ አገሮች ወረረ። በብዙ የጦር ሜዳዎች ድል አደረገ ከተከላካዮቹና ከሱ ወገን ብዙ ወታደሮች አስፈጀ ። ብዙ አገሮች በጣም ይፈሩት ነበር። ቤላ ግን በዎተርሉ

የጦር ሜዳ ላይ እንግሊዞች ማርከውት በአንዲት ደሴት ስድስት ዓመት ሙሉ ታሥሮ ከቆየ ቤላ በዚያው ሞተ ። የርሱ ጀግንነት ለዘለዓለም ሲታወስ ይኖራል » ብሎ ለኛ ልጆች ቢተረክ በሌላ እምነት ያሳደግናቸው ልጆቻችን « ናፖሊዎን ዘመን ያነሣው ትዕቢተኛ አውሬ ነበር። እንግሊዞች ግን ጀግና የሆኑ አውሬ ገዳዮች ናቸው » ብለው እንደሚመልሱ እተማመንባቸዋለሁ ።

ከዚህም በቀር ልጆቻችን በሥነ ፍጥረት ፣በፍልስፍና፣ በኪነጥበብ፣ በቴክኒክ፣ በርሻ፣ በሕክምና ዓቅማቸውና አእምሯቸው በቻለ መጠን እንዲራመዱ እናስተምራቸው ነበር። በጠቅላላው የድንቁርናው ፣ የስስቱ ፣ የችግሩ ፣ የበሽታው፣ የተንኰሉ ዓለም ልጆቻችንን ከፋፍሎ እንዳይጫወትባቸው ፍጹምና ንጹሕ ትምህርት እያስተማርን ወደመልካም እንመራቸው ነበር።

እኛም ምንም እንኳ አንዳንዶቻችን ጥቂት ጥቂት ሰብአዊ ጉድለት ብናሳይ ክፋትን ወንጀልን መመቀኛነትን ስስትን አስወግደን አንዱ ለሌላው በማሰብ ከእውነተኛው ቅዱስ ኑሮ ልንደርስ ነበር ።

በኛ መካከል ወንጀለኛን ለመያዝና ወንጀልን ለመከላከል የሚያስፈልጉት ፖሊሶች ሁለት ጠበኞችን ለማከራከርና ሕግን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉት ዳኞች ቦታ አልነበራቸውም ። ወንጀልንና ጭቅጭቅን በመተዛዘን በፍቅርና በሰላም ከመካከላችን አጥፍተን ነበር። የራስ ፍቅር ደ« ራሱን መርዞ ሌሎችን የሚያስመርዘው በሽተኛ በመካከላችን አልነበረም ።

# 9

## ከሳሽ ስለመነሣቱ

አሀ! አዬ ፈጣሪ! ሰዎቹ በሙሉ ደኅና ካልሆኑ ወይም ለመልካሞቹ ሰዎች ሌላ የተለየ ዓለም ካልተገኘላቸው ሰላማዊዎች ሰዎች እንዴት በሰላም ሊኖሩ ይችላሉ? አሥራ አምስት ዓመት ሙሉ በሰላም ተቀምጠን ከባብ ፣ ከዘንዶ ፣ ከሌሎችም አራዊት ተዋግተን አቅንተን እኛንም ሌሎችንም ረድተን ገነታዊ ኑሮን በምድር ላይ ከመጣን ቤላ ከመንግሥቱ ታላላቅ ባለሥልጣኖች አንዱ

« መሬት ያባቱ ነው ። ሳያስፈቅዱኝና ሳይከራዩኝ በመውረራቸው ወንጀለኞች ናቸው » ሲል ከሰሰን ። ክሱንም ለማጣፈጥ ከመወለዴ በፊት ጀምሬ ወንጀለኛ መሆኔን ዘርዝሮ በክሱ ላይ አቅርቦት ነበር ። ከዚህም በቀር « ሕግና ትእዛዝ የማያውቁ የጫካ ወንበዴዎች ብሎ ሠይሞን ስለነበር እኛ የጫካ አውሬዎች ባሠራነው መንገድ በብዙ ጁፖች የጦር ሠራዊትና የፖሊስ ባልደረቦች ከልዩ ልዩ የጦር መሣሪያዎች ጋር ይዞ መጣብን ።

ከዚያም እንደደረሱ ይህን የመሰለ ሁኔታ ዐይተው የማያውቁት ልጆቻችን ከትምህርት ቤታቸው ወጥተው በመገረም ይመለከቱ ነበር ። የወታደሮች መሪ የሆነው ኰሎኔል ከከሳሾችን ባለሥልጣን ኤላ ሁኖ ሁለቱ ወደኔ ቀረቡና የመጥሪያውን ደብዳቤ ሰጡኝ ።

ደብዳቤውን ሳነበው ከመገረሜ በላይ ለዚህ የግፍ ክስ ደግሞ ይህ ሁሉ ወታደር ሲግበሰበስ መምጣቱ እጅግ አበሳጨኝ ። የሰውን በዚህ ዓለም ላይ መኖርም ጠላሁ ። የከሰሰኝ ሰውዬ በግፈኛነቱ ቢያናድደኝም በግብዝነቱ አሳዘነኝ ። ንዴቴ በረድ ሲልልኝ ወደኰሎኔሉ ዘወር ብዬ « ታዲያ ይህ ሁሉ ሠራዊትና የጦር መሣሪያ የተጫነብን መቼ የክሱን ጥሪ ሽረን ነው? » ስል በንዴት የቀሉ ዓይኖቼን በርሱ ላይ እንዳሳረፍሁ ጠየቅሁት ። « እኔ እንደናንተ ያለውን ከሕግ ውጭ የሆነ ሕዝብ እፈራለሁ ። ስለዚህ በወታደር እንድትጠሩልኝ የጠየቅሁ እኔ ነኝ » ሲል የከሰሰን ባለሥልጣን በሁለቱ የሱሪው ኪሶች እጆቹን ሽጉጦ ሴዴርያውን የርጉዝ ሹራብ ያስመሰለውን ዘረኰት ሆዱን እየገለበጠና በራማ ራሱን እያብለጨለጨ ተናገረ ።

« የርስዎ ክስ ብቻኮ እኛን ወንጀለኛ ሊያደርገን አይችልም ። ወንጀለኛ ሁኖ ለመገኘት ወንጀል መሥራት እንጂ መከሰስ በቂ አይደለም አልሁት ከዘራዬን እንደተመረኰዝሁና የፀሐይ ባርኔጣዬን እንዳደረግሁ ።

በዚህ ጊዜ አንድ የፖሊስ ሻምበል አነሣና « ያም ይሁን ይህ ተከስሳቼል አሁን መሄድ አለብን » አለ ።

እኔም መለስሁና ወዳጄ ሕግ የተፈጠረው የያንዳንዱን ሰው ፀጥታና ሰላም ለመጠበቅ እንጂ ላንተ ሥልጣን ተብሎ አለመሆኑን ዕወቅና ከዚያ ወዲያ ተናገር ። በግፍ ካልሆነ በቀር በሕግ መንገድ አንተ በኛ ውስጥ ቦታ የለህም ። ሂድና በከተማችሁ ውስጥ ያሉትን ቀማኞችና ነፍሰ ገዳዮች አድን ።

እኛ ለራሳችን ፖሊሶች ዳኞችና ሕግ አስከባሪዎች ነን ። መንግሥት እኛን ለመጠየቅ የሚፈልገው ካለም ያንተን አጀብና አስገዳጅነት ሳንሻ ወደተፈለግንበት ራሳችን እንሄዳለን » አልሁት ።

ኰሎኔሉ ይህን ሁሉ ስንነጋገር ዝም ብሎ ይሰማን ነበርና ወደከሳሻችን ሰውዬ ዘወር ብሎ « ከተከሰስን እንቀርባለን የሚሉ ይመስለኛልኮ! » አለ ። ከሳሻችንም « እኔ እነሱን አላምንም አሁን ተይዘው መሄድ አለባቸው » አለ ሁለት እጁን በጆሮ ጥላው ግርር አንገቱን ወደታች ቆፍጠጥ አድርጎ ። እኔም አነሣሁና « ወንድም እኛኮ ዝም ብለን የምናየው በመካከላችን ሕግ አለ በማለትና ለሕግ በመገዛት እንጂ የመጣህብን በጉልበት ከሆነ ባሉን አሮጌ ጠመንጃዎች ተከላክለን ልንጠፋ እንችላለን ። ወታደሮችም የመንግሥት ወታደሮች ናቸው ብለን ነው እንጂ ካንተ ጋር አሢረው ሊያንገላቱን የመጡ አጥቂዎች ከሆኑ ዝም ብለን እጃችንን አንሰጣቸውም ። ይህን ሁሉ ደን መንጥረን እንደዚህ ያለ ገነት ስንፈጥር ብዙ አራዊት ብዙ ሌባና ወንበዴ እያባረርን ነው ። ወንበዴ ከሆንህ አንተንም አንፈራህም ። የጠየቅኸን በሕግ ከሆነ ሕጉን አክብረን ራሳችን እንመጣለን » ስለው ሦስቱ ጓደኞቼ ተንኮለኛ አውሬዎችን ለማደን ሂደው ከቆዩበት ጠመንጃ ጠመንጃቸውን ይዘው ብቅ ሲሉ ከከሳሹና የርሱ አሽከሮች ሁነው ከመጡት ወታደሮች ጋር ቁሜ ስጨቃጨቅ ስላዩኝ ራቅ ብለው እንደቆሙ « ነገሩ ምንድን ነው? » ሲሉ ጠየቁኝ ።

« ምንም አይደል ወደቤታችሁ ግቡ ትንሽ ጉዳይ ነው! » አልኋቸው ።

በዚህ ጊዜ አንድ ሁከት ቢነሣ ከኛ በኩል የምትፈነዳው የመጀመሪያዋ ጥይት ያን ብራና ጭንቅላቱን ወይም ዘረከቦ ሆዱን እንደማትምር ተገነዘበው መሰል « እሺ በቀጠሮው ቀን ሕጉን አክብረው ከቀረቡ እኔ ምን ቸገረኝ ወረቀቱን ተቀብለዋል » አለ ከሳሹ ።

ኰሎኔሉ ቀበል አድርጎ « ከመጀመሪያውም ተሳስተናል » አለና ወደጅፖቻቸውና ላንድሮቨሮቻቸው ሲገቡ ያንድ ግፈኛ ፍላጐት ለመሙላት በከንቱ የደከሙት ወታደሮች ስላሳዘኑኝ ከሳሼና ኰሎኔሉ ወዳሉበት ላንድሮቨር መኪና ቀረብ ብዬ « እስኪ ለጥቂት ጊዜ ይቅርታ አድርጉልንና ቤቶቻችንንም ፣ ርሻዎቻችንንም ፣ ከብቶቻችንንም ፣ ትምህርት ቤታችንንም

የቀረውንም ዝግጅት ተመልከቱልን » አሌቸው ። ከሳሹም « እህ! ከናንተ ቤት የምንገባ በመርዝ ለማለቅ ነው? » አለ ቀልድ አስመስሎ ስሜቱን በመግለጽና ፊቱን በማጥናት ።

እኔ ግን ፈገግ እንዳልሁ « ይህ በናንተ የእምነት ደረጃ ያሉ ሰዎች የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው ። እኔንና ጓደኞቼን እግዚአብሔር ሲፈጥረን ከናንተ ደረጃ አሳልፎ ነው ። ሰውን ገድሎና አጥቅቶ መጠቀም የሰይጥንነት ምልክት መሆኑን ከመወለዳችን በፊት ዐውቀነዋል » አልሁት ።

ለጥቂት ጊዜ እንደቀልድም እንደቁምነገርም እያደረግን ትንሽ ከተነጋገርን ቤላ ምግብና መጠጥ በልጆቻችን የቴያትርና የተንቀሳቃሽ ሥዕል ማሳያ አዳራሽ ውስጥ ተሰናድቶ እንዲቆየን ነግረን እኔና ጥቂት ጓደኞቼ እጅግ ሰፊና ለም የሆነውን ርሻችንን ፣ ላሞችን ፣ በሬዎችን ፣ ፈረሶችን ልዩ ልዩ ዓይነት በጐችንና ፍየሎችን ፣ አሳማዎችን ፣ ዶሮዎችን ፣ በየተራ ካድጐበኘናቸው ቤላ ለማዳ አራዊቶችና እንስሶችን ወደምናረባበት ክፍል ወስደን ደግሞ እጅግ የሚያማምሩ የዱ እንስሶችን ፣ ወፎችንና አሞሮችን አሳየናቸው ። ኰሎኔሉ በቅን ልቡ « አዳም ሳይረገም ነበረበት የሚባለውን ገነት አምላክ አውርዶ ሰጥቷችሁ እንደሆነ እንጂ በእውነት የሰው ሥራ ምድርን እስከዚህ ገነት ካደረጋት ግሩም ነው » አለ ።

እኔም መለስሁና « ሰዎች በቅንነት በዘዴና በብርታት ከሠሩባት ምድር የተረገመች ሳትሆን የተመረቀች ገነት ናት ።

እግዜር ገነት አድርጎ ቢፈጥራት እንደ ወንድማችን ( እንደ ከሳሹ ) ያሉት የማይሠሩ የማያሠሩ ሰዎች ገሐነም አደረጓት » አልሁ ።

« እኛኮ ድርሻችንን ስጡን አልን እንጂ አትሥሩ አላልንም ነበር » አለ ከሳሹ ። መልኩን ልብ ብሎ እንደኔ ላየው ሰው ያን ሁሉ ስንት ሰዎች ደክመን ያለማነውን ቦታና ያፈራነውን ሀብት አጭበርብሮ ለመውረስ ያዘጋጀውን የተንኰል ፣ የብልጠት የይሉኝታ ቢስነት የትምክሕትና የግፍ ዓቅድ ግንባሩ ያስነብብ ነበር ።

የዚህን ክፍል ጉብኝት ከፈጸምን ቤላ ወደልጆቻችን ትምህርት ቤት ሄደን ልጆች በየክፍሉ በትምህርት ላይ እንዳሉ ከነአስተማሪዎቻቸው ከዚያም

ወደክሊኒኮቻችን ሂደን የሐኪሞችን መመርመሪያና ማከሚያ ክፍል የመድኃኒት ቤቱን አስጐበኘናቸው ።

እንዲሁም የመጻሕፍት ቤታችንን በመሠራት ላይ የነበሩትን የጸሎት ቤታችንን ፣ ቤተክርስ+ያናችንን እንደ የምነታችን የምንሰግድባቸውና የምንጸልይባቸው መስጊዶችን ጐበኘን ። ( ይህን ስላችሁ ሃይመኖታችን ፈጣሪያችንን በየጎሊናችን ቅን መስሎ በታየን ጎዳና ለማምለክ በመንፈስ ብቻ የምንከተለው እምነት ነበር እንጂ በወንድማማችነታችንና በአብሮ መኖር ዘዴአችን ውስጥ ለሃይማኖታችን ልዩነት ቦታ አልነበረውም ። ) ሁለት ሰዓቶች ሙሉ ዞረን ብዙ ሺ ሰዎችን በደስታና በምቾት አደላድሎ ያስቀመጠውን ሰፊ የሥራ ይዞታችንን በከፊል ከጎበኘን ቤላ እንግዶችን እንዳናደክም በማለት ግብዣው ወደተዘጋጀበት አዳራሽ ስናመራ እግረ መንገዳችንን ወደኔ ቤት ደረስ አልንና የመኖሪያ ቤቶቻችንን ዓይነቶች አሳየናቸው ። በዚህ ጊዜ « ሁላችሁም እንደዚህ ያለ ቤት አላችሁ? ሲል ኰሎኔል ጠየቀኝ ። « አዎ አዲስ ለመጡት ብቻ ገና በመሠራት ላይ ያለ ሲሆን ለኖርነዎች በሙሉ አለን » አልሁት ።

« በዚህ የእርሻ ሥራ ተካፋይ የሆኑት ሠራተኞች ስንት ይሆናሉ? ስትጀምሩስ ስንት ሁናችሁ ጀመራችሁት? » ሲል ጠየቀኝ ።

« በዚህ ሥራ ውስጥ ሐኪሞችም አስተማሪዎችም በጠቅላላው ልዩ ልዩ ባለሙያዎች ሁሉ ባንድ ላይ ተቆጥረው አሥር ሺ ሠራተኞች እንገኝበታለን ። ሥራውን የጀመርነው የዛሬ አሥራ አምስት ዓመት ከመንግሥት ገንዘብ ተበድረን ሲሆን ጀማሪዎችም አሥር ሰዎች ብቻ ነበርን » ብዬ ስነግረው ኰሎኔሉ ጣቱን ካፍንጫው ላይ አርጎ በመገረም « አሥር ሰዎች ታዲያ አሁን የመጀመሪያዎቹ ጓደኞችዎ አሉ? » አለ ።

« አዎን አሉ! » አልሁና ከመጀመሪያዎቹ ጓደኞቼ ሦስቱ አብረውን ስለነበሩ እነሱን አስተዋወቅሁትና የቀሩትን ከያሉበት እንዲጠራ ለልጅ ነግረን ወዳደራሹ መጓዝ ጀመርን ።

« መሥራቾቹ ስንት ስንት የሀብት ተቀማጭ አላችሁ? ሲል ኰሎኔል ጠየቀኝ ።

« ሀብት ቀባሪዎች ብንሆን የወጠንነው ድርጅት ይህን ያህል መች ይስፋፋ ነበር? በና ዘንድ ሀብትን ማከማቸት ነውርና ብልግና ነው ። ገንዘብ ስናገኝ ሥራውን በማስፋፋት ሙያ እያላቸው በሥራ ፈትነት የሚንቀዋለሉትን ወገኖቻችንን ሥራ እያስያዝን ልጆቻችንንና ልጆቻቸውን እኩል እያስተማርንና እኩል እያኖርን በወንድማማችነት እያሳደግን ስናይ የኛ የመጨረሻው ታላቅ ቅርስና ደስታ ይህ ነው » ካልሁት ቤላ ወደ አዳራሹ ገብተን ከየቤቱ የተውጣጣውንና የተትረፈረፈውን ድግስ እንበላ እንጠጣ ጀመር። ከሳሾችን ብቻ ያ ሁሉ ሲሆን የመቀማት ፍላጐቱ ከነበረበት አልተንቀሳቀሰም ነበር ። ከግብዣው ቤላ በሽላም ተሰነባብተን ልንለያይ ስንል ከሳሾችን ወደኔ እየተመለከተ « ይህ ሁሉ የማረሳሻ ዘዴ እንዳይሆንና በቀጠሮው እንዳትቀሩ! » ሲል ኰሎኔሉ በብስጭት ብድግ አደረገና « ምነው ጌታዬ ያለ ልክ ሰውን ያስቀይማሉ! እነሱ የሥራ እንጂ የተንኰል ሰዎች አይደሉም » አለና ወደ መኪና ሁሎችም ገቡ ።

ከሳሹም « እኸኸ! ተገዛህ እንዴ? » እያለ ኰሎኔሉን ሲነዘንዘው መኪናዎች መነሣት ጀመሩ ። እኛም ወደየተግባራችን ተመለስን ።

የቀጠሮው ቀን ከመድረሱ በፊት ወደዋናው ከተማ ሄጄ ከቆየሁ ቤላ ወደ ተከሰስሁበት ፍርድ በት በቀጠሮው ሰዓት ቀረብሁ ።

ለባለ ሥልጣኑ ከሳሼ ሲል ነጻነት የሌለውና በጉልበት የሚመራው ፍርድ ቤት ገና በጧቱ ጠራን። ከዚያም « የሰውን ርስት ያለባላባቱ ፈቃድ አርሰህ ለባለቤቱም የሚገባውን አበል ሳትከፍል ቀርተኻል ። አሁንም ስለድፍረትህ ለመንግሥት መቀጫ ከፍለህ ያለማኸውን መሬት ያለግምት ለቅቀህ ለባለቤቱም በመሬቱ መጠቀም ከጀመርህበት ጊዜ ጀምሮ የሚገባውን አበል ከነወለዱ ከፍለህ ትሄዳለህ » ተብሎ ለቀረበብኝ ክስ መልሱን እንድሰጥ በዳኞች ተጠየቅሁ ።

እኔም በፍርድ ቤቱ የነበረውን ብዙ ተመልካችና ጋዜጠኛ ሁሉ በሳቅ ያናጋውን አሳቂ ነገር ተናገርሁ ። « ከሁሉ አስቀድሜ ፍርድ ቤቱ ለክሴ መልስ ተገቢ ሁኖ የምናገረውን ቃል ከድፍረት እንዳይቈጥርብኝ እጠይቃለሁ ። ለመሆኑ እኚህ ከሳሼ የዝንጀሮ ልጅ ናቸው ወይስ የጦጣ? የዝንጀሮ ልጅ ሁነው የተገኙ እንደሆነ ቻርልስ ዳርዊን የተባለው እንግሊዛዊ ሰው ከዝንጀሮ የመጣ

የአውሬዎች የልጅ ልጅ ነው ብሎ የሰጠው አስተያየት እውነት መሆኑን ስለሚያረጋግጡ ለተአምር የተፈጠሩ ሰው ናቸው ማለት ነው ።

የዝንጀሮ ልጅ አይደለሁም ካሉ ግን እኔ ያለማሁትን ጫካ ወርሰውት የነበሩ በግድም ያስለቀቋቸው ጦጣዎችና ዝንጀሮዎች ናቸው እንጂ የርሳቸውን አባት ከዚያ ጫካ አላባረርሁም ። ግዴለም የዝንጀሮና የጦጣ ልጅ ካልሆኑ አልልም ። የባብና የዘንዶ ልጅ ከሆኑም እርግጥ የዚያ ጫካ ባላባት ናቸው ። በጫካው ውስጥ ብዙ እባብና ዘንዶ እንዲሁም ብዙ ተተናኳይ አውሬዎች ስላጠፋሁ እንዲያውም አባቴን ገድሏል ብለው በነፍስ ገዳይነት ሊከሱኝ ይችላሉ ።

ከነዚህ ሁሉ አውሬዎች ካልተወለዱ ግን የነሱ ርስት የነበረውን ጫካ ባለማሁ እሳቸው የሚከሱበት ምክንያት የለም » ስል « እንዴ! እንዴ! አሰደባችሁኝኮ! » ሲል በዳኞች ላይ ጮኸባቸው ።

ንግግር ከጀመርሁ አንሥቶ ሲስቅ ዳኛ « እንዴ መልስ እየሰጡኮ ነው ጌታዬ! » አለ ።

ከሳሼም « የዛሬስ መልስ ስድብ ሆነ! » አለና እጁን እየጸፋ ቁጭ ሲል እኔም ንግግሬን ቀጠልሁና « ጦጣዎችና ዝንጀሮዎች ተኩላዎችና ቀበሮዎችስ ተሳስቼ ነው እንጂ እንደውም የርሳቸውን ጥብቅና አይፈልጉም ። ጦጣዎችና ዝንጀሮዎች ከፍሬዎቻችን ተኩላዎችና ቀበሮዎች ከጠቦቶቻችን በመጠኑም ቢሆን የመካፈል ዕድል ስላላቸው እኛን ክደው ለርሳቸው የሚያደሉ አይመስለኝም ። ስለቦታቸው ይቅርና ስለራሳቸው ልጠይቅ ። ያ ጫካ ርስታቸው ከሆነ ለምን አንድ ቀርጥ መሬት እንኳ አላለሙም? ማልማት ቢያቅታቸውስ እኛን ሰማይ ቤት ሂዳችሁ ቆፍሩ የሚሉ ከሆነ ለምን ቀደም ብለው አይነግሩንም ነበር? ያን ጫካ ማልማት ከጀመርነው አሥራ አምስት ዓመት አለፈው ። አሥር ቤት ሰቦች ጀምረነው ዛሬ አሥር ሺ ቤተ ሰቦች በተድላ ይኖሩበታል ። ወደፊትም የብዙ ሰው እድል ይከፍቱበታል ። ምን ዓይነት ዕውርነት ነው? ምን ዓይነት ድንቁርና ነው? እስከመቼ ድረስ ነው ሰዎችን መድረሻ አሳጥታችሁ የምትኖሩ? ለመሆኑ ያገሬን የናቴን የምዬን ጠፍ ጫካ መንጥሬ ያገሬ ውበት የሆኑትንና በነጻነት የሚረቡትን እንስሳትና አራዊት ገድዬና አሳድጄ የፈጠርሁትን ገነት የራሴና የጓደኞቼ ላብና ደም ተንጠፍጥፎ

ያለመለመውን ገነት በጊዜና በሥልጣን የተመካ ትዕቢተኛ ልንጠቅህ ሲለኝ ዝም ብዬ የማይ ይመስላቼል? የዓለምን ሁኔታና የሰው ልጆች በአካላዊና በመንፈሳዊ ሥልጣኔ የደረሱበትን ደረጃ አጣርቶ የሚያውቅ ሰብኣዊ ክብሩንና ነጻነቱን ከሕይወቱ በላይ የሚወድ ፍጡር በማንኛውም ዓይነት ትዕቢት ለተወጠረ ዕቡይ የማይንበረከክ መሆኑን አታውቁም? የመጽሐፍ ቅዱስ አክአብ ናቡቴን ገድሎ የአትክልቱን ቦታ እንደወረሰ ንጉሥ ዳዊትም ኦርዮንን ገድሎ ሚስቱን እንደወረሰ በፊት እኛን ገድላችሁ ዓይናችሁ የቀላበትን ለም ምድር ዝረፉ እንጂ በሕይወት እያለንስ አይቻልም ። መግደሉም ችግር ነው ። አሥርና ሐያ ሰው በተንኰልም በምንም መግደል ይቻላል ። አሥር ሺ ሕዝብ ከነቤተሰቡ በተንኮል መፍጀት ግን የማይቻል ነገር ነው ።

ውድ ከሳሼ ሆይ! እንደበቀደም ለቱ የሚታዘዝልዎ የጦር ኃይል ካለዎ አሥር ሺውን ሕዝብ ከነልጆቹ ሊፈጁና የጐመጁበትን ምድር ሊወርሱም ይችላሉ ። ጥቂት ሠራዊት ከዘመናውያን መትረየሶችና መድፎች ጋር ካለዎት ብዙ አይቸገሩም ። የኔ ጓደኞች በሥራ ላይ እንጂ ሌሎችን ለማጥቃት በማድፈጥ ላይ ስለማይገኙ በቀላሉ ሊያልቁልዎ ይችላሉ ። ካልጨረሱን ግን እሺ ብለን አንለቅም ። እንዲሁም ለመንግሥት እንጂ ለርስዎ አንገብርም » ብዬ ዕቅጩን ተናገርሁ ።

« ርስቴን አርሳችሁ እንዴት ድርሻዬን አትከፍሉኝም? » አለ ከሳሼ ከተቀመጠበት ሳይነሣ ። እኔም እንደሱ ቁጭ አልሁና « ዋረ ለመሆኑ ርስዎ ያየሩ ፣ የባሕሩ ፣ የቆላው ፣ የደጋው ባላባት ሲሆኑ እኛ ለራሳችን አርሰን የምንጠቀምበት አንድ ምድረ በዳ ተከልክለን አሥር ሺ ሰዎች ላንድ በቃኝ አይል ገባሮች የምንሆንበት ምክንያት ምንድን ነው? እንደዚህ ካለው የግፍ ጥያቄ የባሰ ሰብኣዊ ክብርን የሚያዋርድ ነገር በዓለም ላይ ይኖር ይሆን? » ብዬ ስናገር ሕግ አስከባሪው « ያላችሁበት ቦታ ፍርድ ቤት ነበርኮ! ምነው እንደደንቡ ቁማችሁ ብትነጋገሩ? » አለ ።

« እሳቸው ተቀምጠው እኔ ቁሜ ስንነጋገር ትዕቢታቸው የባሰውን ይጠጥራል በማለት ከሳቸው ጋር ያለኝን የእኩልነት መብት ለማሳየት እንጂ ፍርድ ቤቱን ለመድፈር አይደለምና ይቅርታ አድርጉልኝ! ብዬ ስነሣ ከሳሼ « ሞት ይሻላል! ለመሆኑ አንተ እኩያዬ ነህ? » አለኝ ።

« በስስታምነትህ እንዲሁም በትዕቢትህ ምክንያት ከኔ የምታንስ ፍጡር ከመሆንህ በቀር በሰብአዊ ተፈጥሮአችን እርግጥ እኩዮች ነን » አልሁት ። ይህ ሰው ድሆችን እንደልቡ እየገላመጠና እያጭበረበረ ሀብታቸውንና ርስታቸውን ሲነጥቅ በኖረበት ፍርድ ቤት ጌታ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ እስከዚህ ቀን ድረስ ደርሶበት የማያውቀውን የዕፍረት ሸማ ስላከናነብሁት በንዴት ተነሣና ከኪሱ ሽጉጥ መዘዝ አደረገ ።

እኔም በፍጥነት ዘለልሁና ምኑንም ሳያስብ ሽጉጡን ከጁ ነጥቄ ያዝሁ ። በዚህ ጊዜ ዳኞች ሁለታችንም ወደማረፊያ ቤት ሂደን እንድንቆይ አዘዙ ። « እንዴት! » አለ ከሳሼ « እንዴት? እስከዚህም ተዳርሰናል? ከዚህ የለማኝ ልጅ ጋር ነው የምታሥሩኝ! መልካም ነገ ሁልህም ከጐንህ ታገኛታለህ! ባለጌ ሁሉ! » ሲል እኔ ቀበል አደረግሁና « አዎን እናቴ ለማኝ ነበረች ። አንተ ግን ራስህ አሁንም ለማኝ ነህ። ለምና ትቀበል ከነበረችው ደሀ ልጅ ከኔ ልትሠርቅ መጥተህ ዛሬ አጋልጬኻለሁ ሠርቆ መኖር ክብር መሆኑ በቃ! ሌባ በምንም ሁኔታ ቢሠርቅ ያው ሌባ መሆኑ ታውቋል! » ካልሁት ቤላ ሁለታችንም በመኪና ገብተን ወደማረፊያ ቤት መሄድ ጀመርን ። ገና ከመውጣታችን ዳኞች በስልክ ተወቅሰው ኑሮ የፍርድ ቤቱን በር ወጥተን ጥቂት እንደሄድን አንዱ ዳኛ በመኪና እየበረረ መጣና ከመኪና ወርዶ « ቁሙ ጌታዬ ይመለሱ ይቅርታ ያርጉልን! እኛ ሕጉን ለማስከበር ስንል እንጂ የርስዎን ክብር ለመድፈር አይደለም » አለና እየተለማመጠ ከእሥር ቤቱ መኪና ወደራሱ መኪና ሲያዛውረው « አንተ የለማኝ ልጅ አሁንስ ጓደኛዬ አለመሆንህን አላወቅህም? » አለኝ ።

« አንተ ግብዝ! የፍርድ ቤቱ ሥልጣን አንዳንተ ባሉት ግብዞች ተረግጦ ዓቅም ስላነሰው ያንተ የግብዙ ክብር የሠራው ተአምር መሰለህ? በል እሺ የነጻነትና የህግ ምንጭ ገንዘብ ከሆነ በዚህም ቢሆን አልሰንፍልህ! » ስል ቦርጫሙን ከሳሼን ያውቁት የነበሩት እንደአምላክ ወይም ቁጡ መልአክ እንደሚሉት እንደቅዱስ ገብርኤል ይፈሩት የነበሩ ፖሊሶች እኔ የምናገረው ቃል የውስጡን የፍርሃት ስሜታቸውን እየነካው ከነሱ አንደበት እንደወጣ ያህል ይዘገንናቸውና በፍርሃት ያንቀጠቅጣቸው ነበር ።

ያም ሁኖ ይህ ለጊዜው እኔ ወደእሥር ቤት እሱ ወደቤቱ እንድንሄድ ተደረገ ። በመንገድ ላይ ከፖሊሶች ጋር ተነጋገርሁና ወዳንድ ቡና ቤት ገብቼ ለየወዳጆቹ ስልክ እየደወልሁ ጉዳዬን ከተነጋገርሁ ቤላ ጓደኞቼም ብዙ ገንዘብ ይዘው እንዲመጡ አስቸኳይ መልእክት ላክሁ ።

ሕግና ነጻነት በገንዘብና በጉልበት ሥር በወደቁባት አገሬ ገንዘቤ የነጻነቴ ጠበቃ እንዲሆን ለጊዜው በእልክ ሠራሁበት ። ትክክለኛ ነገርን ለማስረዳት ብሞክር ቋንቋ የሌለው የእብድ ጩኸት ስለሆነ ዱላን በዱላ ለመከላከል ተገደድሁ ። የጥቅም ጓደኞቹን ሁሉ በገንዘብ ገዛሁበት ። እሱም እኔም ነጻ ሁነን ሙግታችንን እንድንቀጥል ተደረገ ። የሱ ፍጹም አጥቂነት የኔ ፍጹም ተጠቂነትም ቀረ ።

# 10

## ስለ ድንገተኛው ለውጥ

በዚህ ነገር ስንጨቃጨቅ በቀጠሮ መመላለሱ ሰልችቶኝ ስበሳጭ ያ ከናቴ ሆድ ያወጣኝ ሐኪም ሞተ የሚሉ መርዶ ደረሰኝ ። ምንም እንኳ በዕድሜ መግፋቱን ባውቅ በጣም እወደው ስለነበር አንድ በዕድሜው ለጋ የሆነ ሰው እንደሞተ ያህል ስቅቅ ብዬ አለቀስሁ ። ወደቤተሰቡም ሂጄ ሚስቱንና ልጆቹን ካፅናኔቸው ቤላ ገንዘብ ረድቻቸው ተመለስሁ ።

ወደ መኖሪያችንና የሥራ ቦታችን እንደሄድሁ ለአሮጊቷ እናቴ የዚያን የደጉን ወዳጃችንን የሐኪሙን ሞት ነገሬት ። ብዙ ጊዜ አብራው የሠራችውን እኔንም እሷንም እጅግ ብዙ የረዳንን ሰው ሞት ስትሰማ እጅግ በጣም አዘነች ። ብዙ ቀኖችም አለቀሰችለት ። እኔ እያፅናናሁና እየተቆጣሁ እስካስተዋት ድረስ ልቅሶዋን አላቋርጥ ብላ ነበር ።

በዚህ ጊዜ እናቴን ወደቤቴ ከወሰዴት ሰባት ስምነት ዓመት ግድም አልፎ ነበር ። እናቴ በችግርና በሥቃይ ታውቃት የነበረችውን ቀማኞች እንዳበላሻት ያየቻትን መራራ ዓለም ልጅዋን የልጅዋ ጓደኞች ገነት አድርገው በሰላም ሲኖሩባት እሷንና እንደርሷ ያረጁትንና የደከሙትን በሰላም ሲጦሩባት ሕፃናት

ልጆቻቸውን ለወደፊት ኑሮአቸው ጠቃሚ በሆነ ትምህርት ሲያንጹባት አየች ። ዓለምን ወደተሻለ መልክ የሚመሯት የሰይጣን ልጅ ነው ብላ ትጠላኝ ከነበረው ልጅዋና ከመሰሎቹ የሚመነጩት የእውነት የሙብት የነጻነት ፣ የሠራተኛነትና የማወቅ ፍላጎቶች እንጂ እሷና ሌሎች ያምኑባቸው የነበሩ የጨለሙ እምነቶችስ የሰው ልጆች መከራና ችግር ምንጮች እንጂ እውነተኛ መንገዶች እንዳልነበሩ ተረዳች ።

እኔን የወለደችበትን ቀንም በጧትና ማታ ጸሎቷ ትመርቀው ነበር ። በዚህ ሁኔታ ስንኖር እኔና ብዙዎች ጓደኞቼ ባንድ ላይ እየተሰበሰብን ማታ ማታ ሬድዮ እናዳምጥ ነበር ።

አንድ ቀን ማታ እንደልማዳችን ተሰብስበን ሬዲዮ ከፍተን ወሬ ስናዳምጥ መጀመሪያ ምሥራቅና ምዕራብ ተብሎ በእምነትም በኑሮም በአስተዳደርም በተከፈለው ዓለም ከሁለቱም ክፍሎች አንዱ በሌላው ላይ የሚያደርገውን ዛቻና ነቀፋ ስንሰማ ከቆየን ቤላ በሁለቱም ክፍሎች ታላላቅና አደገኛ የኑክሌዩር ቦምቦች ተሞክረዋል የሚል ወሬ በተጨማሪ ሰማን በዚህ ጊዜ አንዱ ጓደኛችን አነሣና የፖለ+ካ ሰዎችስ ካበዱ ብዙ ዘመን ሁኗቸዋል ። ሳይን+ስቶች የሚባሉ የዋሆች ደግሞ የሰው ዘር ማጥፊያ መሣሪያ እያራቀቁ እየሠሩ በዕብዶች እጅ የሚያገቡ ለምን ይሆን? » ሲል ጠየቀን ።

« ምን ያድርጉ? እነሱኮ የእውቀት ጌቶች እንጂ የሥልጣን ጌቶች አይደሉም ። ሥልጣን የሚሠራውን አንተም አይተኻል ። እንረስ ብንል ግድ ተሟገቱ ተብለናል ። እነሱም ጠቃሚ ነገሮች እንሥራ ሲሉ አጥፊ ነገር ሥሩ ተብለው ይሆናል ። » አልሁት ።

« ከመጀመሪያው እንዲህ ያለ የሰው መፍጃ መሣሪያ ሊፈጠር መቻሉን ለምን ይናገራሉ? » ሲል ጠየቀኝ ።

« መጀመሪያማ ለጥፋት ብለው መቼ ይገልጡታል? ለምሳሌ እ፡ኤ፡አ በ08)ሞ3 ዓ.ም ተወልዶ በ 08)(6 ዓዓ.ም የሞተው ስዊድናዊው አልፍሬድ ቤርናርድ ኖቤል ድንጋዮችን በመፍለጥ አለቶችን በማፍለስ ሌሎችንም ብዙ ነገሮች በመለያየት የነበረውን ብርቱ ድካም ለማስወገድ ብሎ ዲናሚት የተባለውን ፈንጂ አዘጋጀ ። ሰዎች ግን ይህን ፈንጂ ነገር ለጦር መሣሪያነት አውለው ብዙ ሕዝቦችን ያለርኅራኄ ሲፈጁበት አየ ። የዚህ ፈንጂ አግኝ

የሆነው ኖቤል ለሰው ዘር ጥቅም ብሎ የሠራው ነገር የብዙ ንጹሕ ደም መፍሰሻ ሁኖ ስላየ በኃዘንና በፀፀት ሲሠቃይ ከኖረ ቤላ በሞተ ጊዜ ያጠራቀመው ሀብት ሁሉ የሰውን ልጆች መንፈስ ወደ መልካም ነገር የሚመራና ከፍተኛ አስተያየት ያለው መጽሐፍ ለጻፈ ታላቅ ደራሲ የሰውን ልጆች በሽታ ፣ ድካምና ችግር ለማቃለል የሚጠቅም አዲስ ነገር ላገኘ የሳይንስ ሊቅ የሰው ልጆችን የሚያሠቃዩ ጦርነቶችና ስደቶች እንዳይደርሱ ሰላምና ዕርቅ ላስገኘ የሰላም ሰው ሽልማት እየሆነ እንዲሰጥ ተናዝዞ ሞተ ።

የአቶሚክ ኃይልና ምሥጢር ለመጀመሪያ ጊዜ በሥራ ላይ ያዋለው ሳይንተስት አልበርት አይንስታይንም እሱ በፈጠረው የአቶሚክ ቦምብ አሜሪካውያን ሂሮሽማና ናጋሳኪ በተባሉት የጃፓን ከተሞች የሚኖሩ ሕዝቦችን በፈጁዋቸው ጊዜ በገለጸው ጥበብ በጣም አዝኗል ይባላል ። ሌሎችም እንደዚሁ በሠሩት መሣሪያ የዓለም ሕዝብ ሲሠቀይ በፀፀት መቃጠላቸው የሚቀር አይመስልም ። » አልሁት ።

« አይመስለኝም » አለ ።

« እንዴት? » አልሁት ።

« አልበርት አይንስታይን በዘመኑ ለነበረው የአሜሪካ ፕሬዚዴንት ለፍራንክሊን ዴላኖ ሩዝቤልት « የተወደዱና የተከበሩ ፕሬዚዴንት! በቅርቡ ጊዜ በኢ ፡ ፈርሚና በኤል፡ ስዚላርድ የተሠራውን ሥራ በጽሑፍ አግኝቼ በማየቴ ዩራኒዩም የተባለውን የማዕድን ዓይነት በቅርቡ ጊዜ አዲስና ከፍተኛ ወደሆነ ኃይል ሊለወጥ እንደሚችል ወደማመን መርቶኛል ። ከዚህ ኃይል የተሠራ አንድ ቦምብ ባንድ ወደብ ላይ ቢፈነዳ ወደቡንና በአካባቢው ያሉ ቀበሌዎችን በጣም ሊያጠፋቸው ይችላል ። » ሲል ከዩራኒየም ኃይለኛና አጥፊ ቦምብ ሊሠራ መቻሉን የገለጸበትን ደብዳቤ በመጽሐፍ ላይ አይቻለሁ » አለኝ ።

እኔም « ሊሆን ይችላል ዓለምኮ ከጭምቶቿ ዕብዶቿ የሚበዙባት ቦታ ናት » ስል ሌላው ጓደኛችን ብድግ አደረገና « እስኪ ወሬ ማዳመጡንና በየቀኑ በሚጐርፈው ሽለላ መደንገጡን ትተን ዓለምን ያለሥጋት እንያት! » አለ ። ሁላችንም በጣም ሳቅንና እስከሁለት ሳምንት ማንኛችንም ወሬ ላናዳምጥ

ተመካክረን ለጓደኞቻችን ሁሉ ምክሩን አሰምተን ተቀመጥን ። በሁለቷ ሳምንት ውስጥ ከኛ አንዱም ተሳስቶት ወሬ ሳይሰማ ከቆየን ቤላ አንዳንዶቹ እንደቀልድ እያደረጉ « ኤዲያ! ቅጀት ፈርቶ ሳይተኙ አያድሩም ተብሏል ዋረ እስኪ ሁሉንም እንስማው! » ማለት ጀመሩ ።

ከሁለት ሳምንት ቤላ አንድ ቀን ማታ ከኔ ቤት ብዙ ሁነን ተሰብስበን ስንጫወት ቆየንና ለመጀመሪያ ጊዜ ሬዲዮ ከፍተን ስንሰማ « የነጻነትና የሕዝብ ጠላቶች ሁሉ ተደምስሰዋል ። በማርሻል ጃፈሮስ መሪነት የተቋቋመው አዲሱ የሬፑብሊክ መንግሥት የሕዝብ ጠላት የነበሩትን ሁሉ እያደነ በመቅጣት ላይ ነው ። » ሲል ሁላችንም በድንጋጤ ክው አልን ። መቼም ማንም እንደሚያውቀው አንድ አምባሳደር ወደአንድ መንግሥት ተልኮ ሲሄድ « የሁለቱን አገሮች የቆየና በታሪክ የተሣሠረ ወዳጅነት ለማጠንከር » ማለቱ አንድ የዋጋ መቆጣጠሪያ ሕግ በሌለበት አገር የሚነግድ ነጋዴ ዕቃ ሲሸጥ ዕጥፍ በዕጥፍ ቢያተርፍም « ያውም ስጎዳ! » ማለቱ አንድ የሬቦሊሽን ድርጅት ሥልጣን ሲይዝ ያለፈውን መንግሥት « ጨቋኝ ፣ የሕዝብ ጠላት ፣ አረመኔ! » ማለቱ የተለመዱና የማይታለፉ ቃሎች እንደመሆናቸው መጠን የማርሻል ጃፈሮስ የፕሮፓጋንዳ ሰዎችም « የኢይዝራኤሉስ ሕዝብ ሆይ! በጨቋኞች ፣ በቆራጭ ፈላጮችና በዘራፊዎች እጅ ተጨብጦ የነበረው መብትህ ጥቅምህና ነጻነትህ ዛሬ ተለቀቀ ። ደስ ይበልህ! የድሮውን የጭቆናና የአውሬነት አገዛዝ ለመመለስ የሚሞክሩ የሀገርና የሕዝብ ጠላቶችን ስታገኝ በያለህበት የሞት ቅጣት እንድትፈጽምባቸው ። ለነሱ ፍርድ አያሻም ። ያለፍርድ ሲያፈሱት የኖሩት ንጹሕ ደም ሁሉ ተፋርዷቸዋል ። ፍርዱን እናንተ ፈጽሙባቸው ። ያዲሱ ሬፑብሊክ ፍርድ ቤት ብዙ የሕዝብ ጠላቶችን በሞት ቀጥቷል ። » ካለ ቤላ ወሬውን በመቀጠል የተገደሉትን ሰዎች ስም ዝርዝር ሲናገር « 0ኛ ሙሴ ገራቢዶስ » ሲል ከጓደኞቼ ብዙዎች እያጨበጨቡ ሳቃቸውን ለቀቁት ሙሴ ገራቢዶስ ያለማነውን መሬት ለመቀማት ያሠቃየን የነበረው ሰው ነው ። በእውነቱ እኔ የምፈልገው ከኛ እንዳይደርስ በሕግ እንዲታገድ እንጂ እንዲሞት አልነበረም ። መገደሉን ስሰማ ከደስታዬ ይልቅ ኃዘኔ ያመዝን ነበር ። የተደረገው ለውጥም ምንም ያህል ስሜት አልሰጠኝ ። መሻሻል ነበር እንጂ ብዙ ሰው የሚያልቅበቱ ለውጥም ዋጋ ያለው አልመሰለኝም ። በብዙ ነገር የበሰልሁና ያወቅሁ ሰው በመሆኔ አዲሱ ሁሉ

መልካም የቆየ ሁሉ መጥፎ ከሚመስላቸው ሰዎች እጅግ የተለየ አስተያየት ነበረኝ ።

ማርሻል ጃፈሮስን አውቀዋለሁ ። የሕዝብ ጠላቶች እያለ ከሚፈጃቸው ሰዎች የተለየ ጠባይ በሕይወቱ ሙሉ ታይቶበት አያውቅም ። ካለፉት ዘራፊዎች አንዱ እሱ ራሱ ነበር ። ሌሎች ከተገደሉ እሱም መሞት ነበረበት ። እሱን ንጹሕ ያደረጉት ያሰለፋቸው ወታደሮቹና በጁ ያሉት የጦር መሣሪያዎች ናቸው እንጂ በሕግ ፊት ካለፉትና እሱ ከሚፈጃቸው ሰዎች ጋር አንድ ነው ።

አገር የምትሻሻለው የጥበብ ፍላጐታቸውን ድካምና ችግር ወይም ምቾትና ተድላ በማይመልሳቸው ጠቢባን ሰብኣዊ ከፍተኛነታቸውንና ፅኑዕ ሞራላቸውን የግል ደስታና ድሎት ወይም መከራና ሥቃይ በማይሰብርባቸው አዋቂዎች እንጂ እንደማርሻል ጃፈሮስ ባለው ነፋስ አይቶ በሚነሣ ሰው መቼ ነውና!

ያለፉትን ሰዎች ጨቋኞችና የሕዝብ ጠላቶች ናቸወ ይላል ። እሺ በርግጥ የሕዝብ ጠላቶች ናቸው። እሱስ ሕዝብን በማጥቃቱ ሥራ ተካፋይ ካልሆነ የሕዝብ ጠላቶች እንደምን አምነው የጦር ጠቅላይ አዛዥ አደረጉት? ለአንዳንድ ሀብታሞች ፈቃድ ሲል ወደሰላማዊ ሕዝብ ወታደር ይልክ የነበር እሱ አይደለምን? ዛሬ ለገደለው ለሙሴ ግራቢዶስስ አንድ መንጋ ሠራዊት ሰጥቶ እኛን በኃይል ሊያሳፍሰን አልነበረምን? በእውነቱ እንደኔ አስተያየት ካለፈው የሚከፋ እንዳይሆን ከመፍራት በቀር የተሻለ ዕድል ይኖራል ብዬ አላስብም ፡ እንዴ! ወደዲሞክራሲ ዓለም ጉዞ ጀምረን ነበርኮ! ምንም ብዙ መጥፎ እምነቶችና ልማዶች ርምጃችንን ፈዛዛ ቢያደርጉት መንገድ መንገዱን ጀምረነው ነበር ። አንዳንድ ገራም ሚኒስትሮችን እየወቀስን ማሠራትም ጀምረን ነበር ።

እኛ ከዚህ ሁሉ የደረስነው አሁን የሚረገሙትና ያለፉት ሰዎች ለልማት ባዘጋጁት ባጀት ተደግፈን ነው ።

እስኪ እንግዲህ የተሻለውን ደግሞ እናያለን! ስል ጓደኞቼ ሁሉ ወደኔ እየተመለከቱ ያዳምጡኝ ነበር ። ሬዲዮውም ወሬውን ቀጥሎ « በዘርና በወግ በሚመኩ ገዢዎች ስር ወድቆ መጨቆን ዘመኑ አለፈ! » ሲል ። ቀበል አደረግሁና « በግል ጥቅም አሳዳጆች ሥር ወድቆ መጨቆንስ አለፈ? » ስል

ሁሉም ጓደኞቼ በሳቅ አወኩ ። « ሰው የሚለካው » አልሁ « ሰው የሚለካው በሚሠራው ሥራ እንጂ በስሙ አይደለም ። ንጉሥ ወይም መስፍን ማለት የነውር ስም አይደለም ። ለሀገራቸው ሰንት መልካም ሥራ የሠሩ ነገሥታትና መሳፍንት አሉ ። ክፉ የሠራ በክፋቱ ለራሱ ይወቀስ ። ደጎችም በደግነታቸው ይመስገኑ ። የሰዎችን የማመዛዘኛ አእምሮ ያደነዘዘው ዘመናዊው የዕብደት ዓየር የዓለምን ሕዝቦች አንድ ዓይና አድርጓቸዋል ። ብዙ ሕዝቦች ያለፈውን ዓይነት አገዛዝ ከነመሪዎቹ አጥፍተው ሌላ ገዥ ሲፈጥሩ ያለሥራ ያለኅብረትና ፣ ያለነጻነት ሊከናወን የማይቻለውን መልካም ዕድል የደረሱበት ይመስላቸዋል ። ግን አድረው ውለው ሲያመዛዝኑት አንድ ሕዝብ በመተባበር የጭቆናን ቀንበር እያስወገደ በኅብረትና በብርታት በመሥራት በፍቅርና በሰላም በመራመድ እንጂ ሥልጣንን የሚሹ ገዢዎች በተለዋወጡ ቊጥር የሚሰጡትን የትንፋሽ ተስፋና ባለፉት መሪዎች ላይ የሚያወርዱትን ነቀፋ ሲመገቡ በመኖር መልካም ዕድል እንደማይገኝ ይረዱታል » ብዬ ስናገር ሬዲዮውም ወሬውን ስለቀጠለ ንግግሬን አቋርጬ መስማት ጀመርን ። « አሁን በጦር ኃይል የተቋቋመው መንግሥት ለጊዜው የሚመራው በተወደዱት በተከበሩትና የሕዝብ ነጻ አውጪ በሆኑት በማርሻል ጃፈሮስ ቢሆንም የጥንት አዋኪዎች ድራሽ እስኪጠፋ የሚቆይ እንጂ ከጥቂት ጊዜ ቤላ የመንግሥቱ ሥልጣን የሕዝብን የመምራት ችሎታ ላላቸው ሰላማዊ መሪዎች ተላልፎ አገራችን በእውነተኛው የዲሞክራሲ ሕግ ትመራለች » ሲል ሬዲዮው አወጀ ።

አዲስ ወታደራዊ መንግሥት በሚሰብክበት ጊዜ ሕዝቡ በየቦታው ተስፋውን እየተመገበ ይፈነጭ ነበር ። በየጊዜው ወደከተማ ስመላለስ እንዳየሁት ሕዝቡ አዲሱን መንግሥት ያለአንዳች መቃወም ተቀብሎት ነበር ። የባላገሩ ኗሪም ምንም አልተንቀሳቀሰም ነበር ። ነገር ግን ከጊዜ ቤላ አንድ ሁለት ዓመት ቆይቶ በገበሬው ፣ በነጋዴው ፣ በባለእንዱስትሪውና በሌላውም ሠርቶ ኗሪ ሕዝብ ላይ ግብርና ቀረጥ እየተደራረበ ለጦር አለቆች መቀማጠያ ለጦር መሣሪያዎች ማደርጃና ማብዣ ሆነ ።

የሕዝቡም ጠቅላላ ኑሮ ሰላም ከማጣቱና የፍርሃት መንሰራፊያ ከመሆኑ በቀር ከድሮው በምንም አልተሻሻለ ። የግል ጋዜጦች ሁሉ በወታደራዊው መንግሥት ሥልጣን ሥር ከመዋላቸው አንዳንዶችም አንዳንዶቹም

ከመዘጋታቸው በላይ ስለሕዝቡ ኑሮ ጥቂት ማጉረምረም የሚያሳ የፖለ+ካ ሰዎች ሁሉ እየተያዙ ያለፍርድ ይታሠሩ ጀመር ። አንድ ሰው በጽሑፍም ሆነ በንግግር ወታደራዊውን መንግሥት ከማመስገንና የድሮዎችን መሪዎችና ሀብታሞች ከመንቀፍ ያለፈ ሓሳብ የመግለጽ መብት አጣ ። ፓርላሜንቱ ከመጀመሪያው እንደተዘጋ ሳይከፈት ቀረ ። ማንም ሰው ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ አድርጎ የመቃወሚያ ቀርቶ የአቤቱታ ድምፅ እንዲያሰማ የማይፈቀድለት ሆነ ።

ለሥልጣንና ለሹመት የሚመረጡት የጦር መኰንኖች ብቻ ስለሆኑ ስንቱ አዋቂ በንግድና በርሻ ሥራ ራሱን ለመርዳት ካልሆነ በቀር በመንግሥቱ ድርጅቶች ገብቶ የሥራ ተካፋይ ለመሆን ዕድል አጣ ።

እኔም ከሥራ ቦታችን ወደከተማ ስመላለስ ሁሉን ለመረዳት ችዬ ነበር ። እርግጥ ነው ያለማሁን መሬት ልንጠቅህ የሚል ከሳሽ አልመጣብኝም ። ቢሆንም ይህን በማየት ብቻ ለሕዝብ ጥሩ ዕድል መጣ ልል አልችልም ። ጠቅላላው የአገዛዝ ዘዴ ከድሮው የአሁኑ ከፍቷል ። የድሮው መንግሥት ቀስ በቀስ ቢሆንም ሕዝቡን ወደተሻለ መንገድ መምራት ጀምሮ ነበር ። ያሁኑ መንግሥት ግን የአገዛዙን መሠረት ለማጠንከር ከመታገል በቀር ሌላ የመሻሻል ሙከራ አላሳየም ። አንድ ቀን ከከተማ ወደ ሥራችን ቦታ ተመልሼ ከጓደኞቼ ጋር ስላዲሱ መንግሥት ሁኔታ ስናወራ ከጓደኞቼ አንዱ « በአሁኑ ዘመን እውነተኛው ዲሞክራሲ ያለ በየትኛው ክፍል ይሆን? » ሲል ጠየቀኝ ። እኔም የሚከተለውን መለስሁለት ።

« በአሁኑ ዘመን ማንኛውም ሕዝብ የሚመካው « ዲሞክራዊ » በሚባለው ታላቅ ያስተዳደር እምነት እንደሆነ በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነው ።

የዲሞክራሲ ትርጒም የሕዝብ ነጻ አስተዳደር የሚል መንግሥታዊ አቅዋም መሆኑ ይታመናል ።

ነገር ግን ልዩ ልዩ በሆኑ በማኅበራዊ ኑሮዎችና አስተዳደሮች የሚተዳደሩትን የልዩ ልዩ አህጉር ሕዝቦች ሁሉ የየራሳቸውን አስተዳደር ብቻ እውነተኛ ዲሞክራሲ እያሉ ይናገራሉ ።

ከዚህም በላይ ለሌሎች ሕዝቦች ዋቢዎች ነን በማለት በሌላው አገር አስተዳደር ላይ የነቀፋ ድምፅ ያሰማሉ ።

ይህን እንጂ አንድ ሰው በእውነተኛ መንገድ ጉዳዩን ተመልክቶ እውነተኛውን የዲሞክራሲ ድንጋጌ በሥራ ላይ ያዋለው እንዳለ ለመረዳት ቢፈልግ ይህን አጣርቶ ለማወቅ ካለመቻሉ በላይ በየቀበሌው የሚነጉደው ራስን የማመስገንና ሌላውን የመንቀፍ ነጐድጓድ ጆሮውን አደንቁሮ መንገዱን እንደሚያሳጣው ጥርጥር የሌለበት ጉዳይ ነው ።

በአሁኑ ዘመን ውስጥ « ዲሞክራቶች ነን » የማይሉ አይገኙም ። በሌሎች አገር ገብተው የሌሎችን ሀብትና ርስት ቀምተው የሚገኙ ኮሎኒያሊስቶች እንኳ ሳያፍሩ ዲሞክራቶች ነን ሲሉ ይገኛሉ ።

ዲሞክራሲ ያለ በየት አገር እንደሆነ ሊያውቅ የሚችል ግን ተጠቃሚው ሕዝብ ራሱ ብቻ እንጂ አንዳንድ የፖለ+ካ ሰዎች የሚያወሩትን ወሬ በመስማት ብቻ አንድ የውጭ ሕዝብ የአንዱን አገር አስተዳደር በሙሉ ለማወቅ አይችልም ።

የመሪዎች ዲስኩር ብቻ ለአንድ ሕዝብ ጥቅምና ታላቅነት በቂ ቢሆን ኑሮ በመላው ዓለም ውስጥ ተመሳሳይ በሌለው ጥብቅ ዲክቴተራዊ አገዛዝ ሕዝብን የሚያሠቃየው የደቡብ አፍሪቃ የአረመኔ ፈረንጆች መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትርም የደቡብ አፍሪቃ ተወላጆች በዲሞክራሲ መንገድ ነው የሚተዳደሩት በማለት ጩኸቱን ባላቋረጠ ነበር ።

ነገር ግን ማንኛውም ሕዝብ በአንድ አገር የሚደረገውን ነገር በሙሉ ለማወቅ ባይችልም አንዳንድ በግልጽ የሚሠራባቸውን ጭቆናዎችና የዲክቴተርነት ቅርሶች ለማወቅ ስለማይቸግረው የዲሞክራሲ ገናና ስም ገና በስሙ ብቻ እንዳለና በሥራ ላይ እንዳልዋለ ለማመን የሚያግደው ነገር አይገኝም ።

ዲሞክራሲ በየትኛው ክፍል ድርጅቶች ይገኛል? ብለን ስንጠይቅ የሚሰጡንን መልሶች ከብዙው በጥቂቱ ብናገራቸው የሚከተሉት ይመስሉኛል ፡፤

የምዕራብ አውሮፓ መንግሥታት « ዲሞክራሲ በትክክል የሚሠራበት በኛ ሀገር ነው ። ሕዝባችን የወደደውን ለመምረጥ የጠላውን ለመጣል መብት አለው ።

እንዲሁም አንድ ሰው የሚፈልገውን ዓይነት ሥራ ለመሥራት የመሰለው አስተያየት ለመግለጽ የወደደውን እምነትና ፍልስፍና ለመከተል በሥራውና በችሎታው ከታናሽ ደረጃ ወደታላቅ ደረጃ ለመድረስ መሰናክልና ጭቆና የለበትም ። ሰው የሚታዘዘውና የሚተዳደረው በሕግ እንጂ በጉልበት አይደለም » ይላሉ ።

እንዲሁም የኮሚዩኒስት አገሮች « የዲሞክራሲ ዓላማ « የሕዝብን ለሕዝብ » የሚል ምሥጢር ያለበት ሲሆን የሕዝብ የሆነውን የሀገር ጠቅላላ ሀብትና ጥቅም እኩል ተከፋፍለን የምንስተዳደር ወንድሞቻችንን አደህይተን ካፒታሊስቶች መሆንን የማናውቅ ለሀገራችን እኩል የምናስብ እኩል የምንሠራ በሀገራችን ሀብት እኩል የምንጠቀም እኩልነት ያለን ሕዝቦች ነን » ይላሉ ። በመነቃቀፍ በኩል ያለውን ጣጣ ስንመለከትም ምዕራባውያን ኮሚዩኒስቶችን በዲክቴተርነት ሥር ተቀጥቅጠው በብረት መጋረጃ ተከበው በግል ሕይወታቸው የማያዙ ተጨቋኞች የሚበዙባቸው እንደሆኑ ሲናገሩ ኮሚዩኒስቶችም የምዕራብ ሕዝቦችን በአንዳንድ ካፒታሊስቶች ያገራቸው ሀብት ሁሉ ተዘርፎ ሥራም ጠፍቶ በወሮበላነት በድህነት የሚንገላቱ ሕዝቦች እንደሞሉባቸው በመግለጽ ሁሎችም ዲሞክራሲን የምንከተል እኛ ብቻ ነን እያሉ የየራሳቸውን መንገድ ያሞግሳሉ ።

ከዚህ በቀር ደግሞ ኮሎኒያሊስቶችም ዲሞክራ+ኮች ነን እያሉ ሰሚን ሁሉ ያስቃሉ ። በጠቅላላው በዓለም የሚገኙት ሕዝቦች ሁሉ የዲሞክራሲን ስምና ዲሞክራሲ በዓለም እንደገነነ በየአገሩ የሚነዛውን ወሬ ይሰማሉ ።

ነገር ግን እውነተኛው ዲሞክራሲ በዚህ ክፍል ያለው ነው ብለው ለመፍረድ ብዙ የኅሊና ሙግት ያጋጥማቸዋል ።

ይህ የሚሆንበትም እውነተኛው ዲሞክራሲ በየት እንዳለ ተለይቶ ስለማይታወቅ ነው ። በእውነት የዲሞክራሲን ዓላማ የሚያምን ሕዝብ ቢኖር « ዲሞክራ+ኮች ነን » ከሚለው ቃል የሰውን ዘር እኩልነት እንዲሁም ነጻነትንና ወንድማማችነትን ለማክበር የሚያሳየውን ሰላማዊ ሥራ ማስቀደም ነበረበት ።

« ዲሞክራ+ክ » ለመባል የሚያበቃውን ዲሞክራሲ ያከበረውን የሰው ዘር ማክበር እንጂ « እኔ ዲሞክራት ነኝ ሌሎች ዲክቴተሮች (በኃይላቸው ብቻ የሚገዙ ) ናቸው » ማለት ብቻ በቂ አይሆንም ።

ስለዚህ ማንኛውም ሕዝብ « ዲሞክራ+ኮች ነን » ብሎ በሚያወራበት ጊዜ የዲሞክራሲ ሕጎችን አክብሮ መገኘቱ ብቻ በሌሎች ዘንድ ሊያሳምነው መቻሉንና በአፍ ግን ሁሉም « ዲሞክራቶች ነን » ባይ መሆኑን ተረድቶ ከትዝብት መጠንቀቅ የሚገባው መሆኑን ማወቅ አለበት ።

በአፍ ከሆነ ግን በመለዋ ዓለም ላይ የሰፈሩት ሕዝቦች በሙሉ በዲሞክራሲ መንገድ እንደሚተዳደሩ አውቀናል ማለት ነው ።

ምክንያቱም በአፉ በዲሞክራሲ የሚያምነውና በሥራውም መዶሻ ዲክቴተር ሁኖ የሚገኘው ሁሉም በመሆኑ ነው ።

የሆነ ሁኖ በዘመናችን ላይ የሚገኘው የፉክክርና የውድድር ሜዳ የእውነትንና የውሸትን መለያ በውስጡ ደብቆ የያዘ በመሆኑ እውነትንና ሐሰትን ለይቶ በቀላሉ ለመፍረድ አይቻልም ።

የኛዎቹ አዲስ መንግሥት መሥራቾችም በኃይል ጭጭ አድርገው እየገዙን እያየን « አገራችንን ከጭቆና አገዛዝ ወደነፃነት መራናት » እያሉ ይፎክሩብናል ። ይኸውም የጊዜውን ነፋስ በመከተል ነው። » አልሁ ።

« ለመሆኑኮ ብዙ ለውጥ ተደርጓል! » አለኝ አንዱ ጓደኛዬ እኔን እየተመለከተ ።

« ለውጡ የትኛው ነው? እናንተ ለውጥ ብላችሁ የምታምኑት የጥቂት ሀብታሞችን መሞትና መንገላታት ነው? እኛ የምንፈልገው እንዳይጎዱንና እንዳያጠቁን እንጂ እነሱ ቢሞቱ ደማቸውን አንጠጣው ቢሠቃዩና ቢንገላቱ የመንፈስም ሆነ የአካል ደስታ አናገኝበት! ወይስ መሻሻል የምትሉት ሲቪል ሹም ሽሮ ወታደራዊ ሹም መሾሙን ነው? ወይስ ከሕዝብ አንዱ ድምፅ ሊሰጥበት የማይችለውን ለስሙ ግን የህዝብ መንግሥት ( ሬፑብሊክ ) የሚባል መንግሥት መቋቋሙን ነው? ዋረ ለውጥ የምትሉት የቱን ነው? ድርብ ቀረጥና ግብር መክፈሉን ነው? ጠቃሚ ድርጅቶችን እያደከሙ ለውጭ

ጠላት እንኳ ሳይሆን ያገርን ሕዝብ ለማጥቃት የጦር ድርጅቶችን ማስፋፋቱን ነው? እንግዲህ አዲሱ መንግሥት ያሳየን ለውጥ ይህን ነው ይህን ከሆነ መሻሻል የምትሉት ሌላ ነገር ነው ።

እኔ መሻሻል የምላቸው ግን ከነዚህ የተለዩ ለውጦች ናቸው ። ሕዝብን ነጻ በሆነ ትምህርት ከድንቁርና ነጻ ማውጣት በሕዝብ መካከል ሰላምን ፣ መግባባትንና አንድነትን መፍጠር ፣ ሕዝብ ሥርቶ ኑሮውን የሚያሻሽልባቸውን ጤናውን የሚጠብቅባቸውን ድርጅቶች ማስፋፋት የያንዳንዱን ሰው የግል እምነትና ነጻነት አለመድፈር ለሕግና ለአስተዳደር ከፍተኛ ቦታ መስጠት የያንዳንዱን ሰው ዕውቀትና የተፈጥሮ ስጦታ ማክበርና በተገቢ ቦታው ማዋል እነዚህንና የቀሩትን የሕዝብን ፍላጎት የሚመለከቱ ርምጃዎች በርግጥ ታላቅ ለውጦች እላቸዋለሁ ። እነማርሻል ጃፈሮስን የመሰሉ የበግ ቆዳ ለብሰው የተነሡ ተኩላዎች ያመጡትን ጨቋኝና አደገኛ ለውጥ ግን ለውጥ አልለውም ። የነሱን ዓይነቱን ለውጥ እስከ ንጋት የፀሐይ ብርሃን ታደርሰናለች ብለው በጨረቃ በሚጓዙ የሌሊት መንገደኞች ላይ ጨረቃዋ በድንገት ስትጠልቅ ከሚደርስባቸው ድንገተኛ ጨለማ ጋር እንጂ ከሌላ ጋር አላመሳስለውም ። በሥልጣን ፈላጊዎች የሚመጣው ድንገተኛ ለውጥ በፀሐይና በጨረቃ መካከል ያለ ጨለማ ነው ። እውነተኛውና ጠቃሚው ለውጥ መላው ሕዝብ በአካላዊና በመንፈሳዊ ሥልጣኔ ደርጅቶ በራሱ የሚያገኘው ከፀሐይ ብርሃን ጋር የሚመሳሰለው ታላቅ ለውጥ ነው » ብዬ አስረዳሁ ።

« አስተውሎ ለሚያይኮ ይህች ዓለም ችግር የሞላባት ቦታ ናት » ብሎ አንዱ ጓደኛችን ሲናገር ቀበል አደረግሁና « እኔማ አስቸጋሪነቷን አውቄ በናቴ ሆድ እንዳለሁ « አልወለድም! » ብዬ ነበር ። ግን ተወልደናልና ከዚች ዓለም እስክንገላገል ድረስ በትዕግሥትና በቆራጥነት ለእውነተኛ ነገር መታገል አለብን » ካልሁ ቤላ ሬዲዮ ከፍተን ወሬ መስማታችንን ጀመርን ።

# 11

## ስለ አዲሱ አገዛዝ ፈጽሞ መበላሸት ።

በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ያለማቋረጥ ታግዬ ታግዬ የ»2ኛውን የመወለጃዬን ዓመት ባለፍሁ ባምስተኛው ቀን ሁለመናው ወደ ተለዋወጠባት የተወለድሁባት ከተማ ሄድሁ ። ወደከተማዋ ስገባ ሁኔታው ሁሉ አላስደሰተኝም ። በያንዳንዱ ሰው ግንባር ላይ የፍርሃትና የጥርጥር መልክ ይታያል። እግሩ በቻለ ተዝናንቶ ሲራመድ የማየው የወታደር አለቃ የሆነ ብቻ ነበር ።

ገራሙና ሰላማዊው ሕዝብ በሚኖርባት ከተማ የጦር ታንኮች ፣ መኪናዎችን መንገድ አጣበዋቸው እንዲያውም መተላለፊያ ከልክለዋቸው ይታያሉ ። ድግን ድግን መትረየስና ዘመናውያን ጠብመንጃዎች ይዘው ሽጉጥና ሳንጃ ታጥቀው በራሳቸው የብረት ቁር ደፍተው የሚንጎራደዱ ወታደሮች በየመንገዱ ይተራመሱ ነበር ። ሰልፉ ለምን እንደሆነ ግን አልገባኝም ። በሀገሩ ውስጥ የመንግሥት ለውጥ መደረጉንና ወታደራዊው አገዛዝ በጣም መጨማለቁን ባውቅም ርስ በርስ የተደረገ ልውውጥ ይህን ያህል ትርምስ የሚያስፈልገው መሆኑ አልገባኝም ጊዜውም ዘግይቷል ለውጡ ከተደረገ አራት ዓመት አልፎት አምስተኛውን ጀምሯል ።

የቆየውን ማማረር አዲሱን ማመስገን ልማዱ የሆነው የዚህ ዓለም ወረተኛ ሕዝብ ከአዲሱ መንግሥት ጋር ጨርሶ የተሰላቸ ይመስላል ። በመጀመሪያ ጊዜ በየቦታው ሲጨፍርና ሲፈነድቅ የነበረው ዛሬ አንገቱን እየቀለሰ ይሄዳል ። ለሕዝብ ጥቅም የተነሡ ይመስሉ የነበሩት ወታደራዊ ባለሥልጣኖችም ሕዝቡን ባለማመንና በመጠራጠር ያላቸውን ኃይል ለማሳየትና ለማስፈራራት ታጥቀው የተነሡ ይመስላል። ድሮ ሲቪል ባለሥልጣኖች የነበሩባቸው መሥሪያ ቤቶች ሁሉ በዩኒፎርምና በመዳሊያ ባጌጡ ወታደራዊ ሹማምንቶች ተሞልተዋል ።

ከሚኒስትር እስከ ክፍል ሹም ያሉት ሹማምንት የጦር መኰንኖች ከመሆናቸው በላይ ለተላላኪነት የቆሙት እንኳ ተራ ወታደሮች ብቻ ነበሩ ። ያ ሁሉ ሰላማዊ ሠራተኛ ወዴት ደረሰ? ከሰላማዊ ሠራተኞች መካከል

በቀድሞ ቦታቸው ላይ ያሉት ወታደራዊ ነክ የሆኑት የፖሊስ ባልደረቦች ብቻ ነበሩ ። ምናልባት አንዳች የጦርነት ወሬ ተሰምቶ ያገሩ ሕዝብ ሁሉ በሙሉ ወታደር ሁኖ ይሆን? እኛስ ታዲያ ለምን ቀረን? እንጃ !!

ይህ ሁሉ ግራ አጋብቶኝ ነበር ። በስሙ የምሰማው ፍጹሙ ወታደራዊ ቆራጭ ፈላጭነት (ዲክቴተርሽፕ) በኔም ሀገር ላይ ደርሶ ይሆን? ያን በመጠኑ እንኳ ቢሆን የነበረንን ነጻነት አጥተነው ይሆን? በርግጥ ይህ ሁሉ ትክሻ ማሳየት የገዛ ወገንን እያስፈራሩ ለመግዛት ይሆን? ሀገራችንንና ራሳችንን እንዲጠብቁ ያሠለጠንናቸው የመከላከያ ኃይላችንን ሁሉ አምነን አደራ የሰጠናቸው በነሱ እጅ ያለው መሣሪያ ሁሉ የኛ ነው በማለት ባዶ እጃችንን ለመቀመጥ የደፈርንባቸው ወንድሞቻችን በገዛ ኃይላችን እኛኑ መልሰው ለማጥቃት አስበው ይሆን? አይደረግም! ይህን የመሰለውን ስሜት እያሰላሰልሁ በየቦታው እንድትቆምና እንድትፈትሽ የምትገደደውን ላንድሮቨር መኪናዬን እየነዳሁ ከሁለት ሦስት ታላላቅ መሥሪያ ቤቶች ከደረስሁ ቤላ ድሮ የማውቃቸው ባለሥልጣኖች አንዱንም ሳላገኝ ከመሥሪያ ቤቱ በር ጠመንጃ ይዘው ከቆሙት ዘበኞች ጋር ብቻ ትኅትና በራቀው ንግግር እየተነጋገርሁ ተመለስሁ ።

ከዚያም ድሮ አርፍበት ወደነበረው « ኑቫኖ ሆቴል » ወደሚባለው ሆቴል ሄድሁ ። የሆቴሉ ስም ተለውጦ « ማርሻል ጇፈሮስ ሆቴል » በሚል አዲስ ስም ተሠይሞ አገኘሁት ።

በሆቴሉ ቡና ቤት በረንዳ ተሰብስበው ሰንጠረጅ ካርታና ሌሎችንም ጨዋታዎች የሚጫወቱት የጦር መኰንኖች ብቻ ነበሩ ። ነገሩ አዲስና እንግዳ ሆነብኝ ። ጥንት የማውቀው የሀገሬ ሕዝብ ትርዕይት ናፈቀኝ ። ቢከፉም ቢበጁ ወታደሩና ሲቪሉ ሴቱና ወንዱ ወጣቱና ሽማግሌው በአንድነት ተቀላቅሎ ሳየው መራራው የዓለም ኑሮ በመጠኑ ምሬቱን ይቀንስልኝ ነበር ። የዛሬው ትርዕይት ግን በፍጹም አላስደሰተኝም ። የሀገሬ ሕዝብ « በጨቋኝና በተጨቋኝ » ሁለት ድርጅቶች ተከፍሎ እንዳይሆን ሠጋሁ ። የማያዋጣ አጉል ምኞትም ተወጥኖ እንዳይሆን ፈራሁ ። ችግርን ፣ በሽታንና ፣ ድንቁርናን እንዲሁም የውጭ ጠላትን የምንከላከልበት ኃይል ገና ሳናደራጅ ለርስ በርስ መጠቃቃት እንዳንሰላለፍ በማሰብ ኅሊናዬ ተጨነቀ ። እስኪ መጨረሻውን ልየው ። ወደሆቴሉ ገብቼ ክፍል ያዝሁ ። ሻንጣዬን አስቀምጬ የክፍሌን በር

ቆለፍሁና ወደበረንዳ ሄጄ ቡና ከጠጣሁ ቤላ የከተማውን ሁኔታ ለማየት በግሬ መዘዋወር ጀመርሁ ። ከልጅነት እስከ እውቀት ከድኅነት ራስን ችሎ እስከመኖር በደረስሁበት ጊዜ ሁሉ የማውቃት የታሠርሁባት የተፈታሁባት በጠቅላላውም ብዙ ጉድ ያየሁባት ብዙ ነገር ያሳየሁባትና ያስተማርሁባት ከተማ በሁኔታዋ ሁሉ እንግዳና ባዕድ ሆነችብኝ ። ነጻ የነበሩት ብዙ መንገዶች « ማለፍ ክልክል ነው ። » ወይም « ቁም » የሚል ምልክትና ድግን ድግን መትረየስ የያዙ ወታደሮች ይታዩባቸዋል ።

የተከለከሉትን መንገዶች እየተውሁ ባልተከለከሉት መንገዶች በትካዜ ስጓዝ « ጳውሊ » ለተባለው ታላቅ ባለቅኔ ወደተሠራለት ሐውልት የሚወስደውን « የጳውሊ » መንገድ የሚባለውን ጐዳና ይዤ ለመሄድ ብፈልግ ሰሌዳው ጥቁር ሁኖ በቀይ ቀለም የተጻፈ « ቁም » የሚል ምልክት ተደርጎበታል ። የመንገዱን ሥያሜ የሚገልጸው ሰሌዳ ተነሥቶ ሌላ ስምም ሳይሰጠው ይገኛል ። «ቁም » የሚለውን ምልክት አልፌ ለመሄድ ስፈልግ ከምልክቱ አለፍ ብሎ ቁሞ የነበረ መትረየስ የያዘ ወታደር የመትረየሱን አፈሙዝ ወደኔ አዙሮ « ምነው ሰውዬ! ማንበብ አትችልም እንዴ? እስኪ አልፈኸው የመጣኸውን ምልክት ተመልከተው! » አለኝ ወደምልክቱ በጁ እያሳየ ። « እሱን አይቸዋለሁ የሆነ ሁኖ የጳውሊን ሐውልት እጐበኛለሁ! » አልሁት ።

« ክልክል ነው! » አለኝ ።

« ለምን? »

« እኔ ምን አውቃለሁ! የበላይ ትእዛዝ ነው! »

« የማን ሥራ ያጣ የበላይ ነው ሐውልት አትዩ የሚል? »

« አ! የኔ ወንድም እኔ ይህን አላውቅም ታዝዣለሁ ትእዛዙን መፈጸም አለብኝ ። »

« እንግዲያስ በመንገድ የሚያልፍን ሁሉ ግደል ተብለህ ትእዛዝ ተሰጥቶ እንደሆነ ግደለኝ እንጂ አልቀርም » ብዬ በተከለከለው መንገድ መሄድ ስጀምር አንተ ሰው ዕብድ ነህ እንዴ? ኤላ ጉድ ይፈላብሃል! » እያለ ፊሽካ በመንፋት

ተከተለኝ ። እንዳይተኩስብኝ ትእዛዝ ስላልተሰጠው ነው እንጂ ለኔ ሕይወት አዝኖ ዝም እንዳላለ በሁኔታው ተረድቻለሁ ።

ፊሽካው ተደጋግሞ ሲጮህ አንድ ድሮ የምንተዋወቅ ሻለቃ ከሁለት ወታደሮች ጋር መጣና በትሕትና ሰላምታ ሰጠኝ እኔም እንደዚሁ በትሕትና ሰላምታ ሰጠሁት ።

« ርስዎ ነዎት እንዴ? » አለኝ ፈገግ ብሎ ።

« እባክዎ ይህ ሁሉ ጣጣ ምንድን ነው? የባሰ አለ አገርህን አትጣል አሉ! » አልሁ ።

« እባክዎ መኖር ችግር ነው! » አለኝ ።

« ነገሩ ምንድነው ሐውልት ለማየት የሚያስከለክል? »

« ሐውልቱ እንዳይታይ አይደለም ጽሑፉ ተፍቆ ሌላ ለጊዜው ተስማሚ የሆነ ቃል እስኪተካበት ድረስ ነው ።

እንደሚያውቁት እዚህ ላይ ያለው ቃል ነፃነት! ነፃነት! እኩልነት ፣ ወንድማማችነት የሚል ነገር ስለሚበዛበት ለጊዜው አስቸጋሪ ነው » ሲለኝ ባለመትረየሱ ወታደር « እባክዎ የሻለቃዬ ወደዚህ ወጣ በሉና ተነጋገሩ » አለ ።

ሻለቃውም ንግግራችንን ሳንጨርስ እየሰጋና እየፈራ « ይበሉ እስኪ ደንቡ ጥብቅ ሁኗልና መለስ እንበል » አለኝ ። እኔም ለጊዜው ተመለስሁ ።

ይህ ሐውልቱ እንዳይታይ የተከለከለው ጸሓፊ ከጻፋቸው ታላላቅ የፍልስፍናና የሞራል መጽሐፎች መካከል አንዱ « ነፃነትና እኩልነት » የተባለው መጽሐፍ ነበር ።

ከዚህ መጽሐፉ ውስጥ የሚከተሉት ግጥሞች ተጠቅሰው በሐውልቱ ግርጌ ተቀርጸው ነበር ።

« ተረግጦ ፡ ተገፍቶ ፣

« አልቅሶ ፡ ተጠቅቶ ፣

« ተርቦ ፡ ተጠምቶ ፣

« በድንቁርና በሕማም በሥቃይ በረኃብ በችግር

« እየተንገላቱ ዘላለም ከመኖር ፣

« ከኩልነትና ከነፃነት ጋራ ይሻላል መቃብር

« እንኳን ከውርደት ጋር እንኳን ከችግር ጋር ከደ« ከጥቃት ፣

« ከክብር ጋር ቢሆን ከብዙ ጌትነት

« ኑሮ ጣዕም የለውም ከሌለው ነፃነት ፣

« ባይንህ አስመስክረህ አላፊ መሆኑን ሁሉም በየተራ ፣

« ሞት አይቀርምና ብትደፍርም ብትፈራ ፣

« ያገሬ ልጅ ቁረጥ! መቃብር ለመውረድ ከመብትህ ጋራ ።

« ወንድም ሲሆንና መልካም ሲሠራ እንጂ ከባዕድ የሚለየው

« ነፃነትንና መብትን ከነሣህ ወገንም ጠላት ነው »

እነዚህ ብርቱ የነፃነት ደዎሎች የተፂፉበትን ሐውልት ያየ ሁሉ ከፍ ብዬ የገለጽሁላችሁን አዲስ የአገዛዝ ዘዴና እነዚህን ቃሎች እያመዛዘነ የንቅናቄ መንፈስ እንዳይፈጥር መከልከል ግድ ሁኗል ። ይህን ብቻ ሳይሆን የሕዝብ ባለውለታ የሆኑ ያለፉ ብዙ ታላላቅ ሰዎች መታሰቢያዎች ሁሉ እንዲጠፉ ጥረት በመደረግ ላይ ነበር ።

የሆነ ሁኖ ይህ ሁሉ ድካም እንዲያው ለጊዜው የሚደረግ ቂን ቂን ነበር እንጂ በየቀኑ እየገነፈለ የሚያድረውን የዘመኑን የሕዝብ ፍላጐትና የነፃነት ስሜት ሊደመስስ የሚችል አልነበረም ። እኔም ሁሉን አይቼ አንድ ጊዜ ጉዳቸውን እስከገልጸው መታገሥ ግድ ስለሆነብኝ ዝም ብዬ ወደሆቴሌ ተመለስሁ ።

# 12

## ከፍተኛ እንቅስቃሴ ስለመመሥረታችን

ማታውኑ ወደ አንድ ወዳጄ ቤት ሄድሁ ከዚያው ራት እንድበላ ጋበዘኝና እቤቱ ቆየሁ ።

ራት ገና ከምሽቱ በ 1 ሰዓት ተኩል ቀረበ ። ባየሁት ሁሉ ነገር በጣም ተገርሜ ነበር ። ከወዳጄ ጋር ያስደነገጠኝን ነገር ሁሉ እያነሣሁ ስንጨዋወት ራትም ስንበላ ጊዜው ተፋጥኖ ለሦስት ሩብ ጉዳይ ሆነ ።

እኔም የኪስ ሰዓቴን አውጥቼ አየሁና « ሦስት ሰዓት መሆኑ ነው? እንግዲህ ወደሆቴሌ ልሂድ » አልሁ ።

ወዲያው የቤቱ ባለቤት የሆነው ወዳጄ የጅ ሰዓቱን አየና « ሰዓት አልፎ የለም እንዴ! አሁን አትደርስም ። ለመሆኑ ከየትኛው ሆቴል ነው ያረፍኸው? አለኝ ።

ኑቫኖ ሆቴል ነው »

« ማርሻል ጃፈሮስ? »

« አዎ ተብሏል መሰል! ለመሆኑ አሁን ሰዓት የሚያልፈው እንዴት ነው? »

« ከሦስት ሰዓት በኋላ አትንቀሳቀሱ ተብሏል ። »

« ለመሆኑ ይህ ሁሉ ድካም ለምን ነው? »

« እንዲያው መጨነቅ ነዋ! » ሲል ከመለሰልኝ ቤላ ወዳጄ ንግግሩን በመቀጠል « ባለፈው ጊዜ የገቡት ቃል ሁሉ ሌላ ነበር ። የሕዝቡን ጥቅም ፣ የሕዝቡን መብትና ነፃነት እናከብራለን ፣ ሕጎችን ለማስፈጸም ሙሉ ነፃነት ያለው ሕጋዊ ፍርድ ቤት ሕዝብን ለመምራት ስጦታና ልምድ እንዲሁም ዕውቀት ያላቸው ሰዎች አባሎቹ የሆኑ ሰላማዊ መንግሥት እናቋቁማለን ፣ የሕዝብን የኑሮ ፍላጎት ሊያረኩ የሚችሉ የልማት ድርጅቶች እንዲስፋፉና

እንዲቋቋሙ እናደርጋለን ፣ ትምህርትንና የሥራ ይዞታን በችሎታ እንዲካሄድ እናደርጋለን ። ያለምክንያት የሕዝቡን ጥቅም የሚዘርፉ የውጭ አገር ዘራፊዎችን እንቆጣጠራለን የሚወጡትንም እናስወጣለን » ብለው ነበር ። ይህም ሕዝቡን በጣም ያስደሰተ ታላቅ ተስፋ ነበር ። ነገር ግን ተስፋው ሁሉ ተዘንግቶ በሕልም እንኳ ያልታሰበ ነገር ሆነ « ከፊተኛው ዬለኛው ይከፋል » የተባለው ነገርም ተፈጸመ ።

ሌላውን ጥቃት በዛብን ይል የነበረው ሕዝብ የርግጫ ማረፊያ ሆነ ። የትናንትናዎቹ የሕዝብ ጠበቃዎች ነን ባዮች ዛሬ የባሱ የሕዝብ ጠላቶች ሆኑ » ሲል ከቁጭት ጋር ነገረኝ ። « እኔኮ ድሮም አልሁት ። « ሕዝብ ተጣጥሮ ጥቅሙንና መብቱን ካልጠበቁ አንድ ዓይነት ልዩ እምነት ያለው ድርጅት ብቻ ለጠቅላላው ሕዝብ ተስማሚ የሆነ መንገድ ሊከፍት አለመቻሉን ደጋግሜ ነግሬአቼለሁ ። ወታደሮች የሀገርን ነፃነት እንዲጠብቁ እምነት የተጣለባቸው በመሆናቸው በዚህ በኩል ያላቸውን ሁሉ ልናከብርላቸው ይገባል ።

ለሀገር ነፃነት አብረናቸው ልንሞትም ይገባናል ። አስቀድሞ ለመሞት የተዘጋጁ እንደመሆናቸው መጠን ለጤንነታቸውና ለመልካም አኗኗራቸው ልናስብላቸው ልንጠነቀቅላቸው አደጋና ሞት በደረሰባቸው ጊዜም ለቤተ ሰቦቻቸው ልናዝንላቸውና ልንራራላቸው አስፈላጊም ሲሆን ልንረዳቸው ይገባናል ። እንግዛችሁ እንዲሉ ግን አንሻም ። መሪዎች እንጂ ገዢዎች አንፈልግም ለመሪነትም ታንክ መድፍ የጦር አኤሮፕላንና መትረየስ ሳይሆኑ የበሰለ አእምሮና ሰዎችን የመቻል ልምድ አስፈላጊዎች ናቸው ። የጦር ኃይል የሚፈለግበት አንድ ቀዋሚ ጉዳይ አለ ። ይኸውም ከሕዝብ ጋር ተረዳድቶ አጥቂ ጠላትን መመለስና ጸጥታን መጠበቅ ነው ። ሁሉም ነገር ሠሪውን ይፈልጋል ። ሆስፒታሎች በከፍተኛ የሕክምና ሙያ የሠለጠኑ ሐኪሞችንና በተራቀቁ ሳይን+ስቶች የተገኙ መድኃኒቶችን ፣ ርሻዎች የርሻ ትምህርት ወይም ልምድ ያላቸው ገበሬዎችንና የርሻ መሣሪያዎችን ፣ ፋብሪካዎች ፣ የመኪናዎቻቸውን ጉድለትና መሙላት የሚያውቁ የቴክኒክ አዋቂዎችን ፣ የጉልበት ሠራተኞችንና ፋብሪካው ሠርቶ ለሚያወጣቸው ልዩ ልዩ ዕቃዎች የሚያስፈልጉ ጥሬ ነገሮችን ፣ ትምህርት ቤቶች ፣ የበሰሉ አስተማሪዎችን ፣ የመማር ችሎታ ያላቸው ወጣቶችንና የትምህርት መሣሪያዎችን በጠቅላላው ማንኛዎችንም የሥራ ድርጅቶች ተስማሚያቸው የሆኑ አዋቂዎችንና ሌሎችን ነገሮች ይሻሉ ።

ሕግና አስተዳደርም ለብቻቸው ተስማሚዎቻቸውንና አዋቂዎቻቸውን የሚፈልጉ ናቸው ። የዓለም ፍላጐት ይህ ሲሆን በታንክና በመድፍ ኃይል ብቻ ዓለምን እናንቀሳቅሳታለን ብሎ መወጠንና ሁሉንም የኃይል ጥገኛ ማድረግ የሁከትና የድኅነት ምንጮችን አውቆ መከፈት ነው » ካልሁት ቤላ ንግግሬን በመቀጠል « ሀገራችንንና ነፃነታችንን የሚያሠጋ ነገር ሲመጣ ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ሴቶች ጭምር ጐልማሶች ብቻ ሳይሆኑ ሽማግሎችና ወጣቶች ጭምር ለጦርነት መሰለፍ አለባቸው በሰላም ጊዜ ግን ሁላችንም በየሥራችን ስጦታችንና ችሎታችን በየሚፈቅድልን ቦታ ተሠማርተን ለኑሮአችን አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን መሥራት አለብን ።

በሰላም ጊዜ የምን መጨነቅ? የምን መረገጥ? የምን መታሰር? » ስል ተናገርሁ ።

ወዳጄም « ጠብመንጃ የያዘ ብቻ ይርገጣችሁ! አሉና ! » አለ ።

« ሰባራ ሁሉ! መልሶ አይረግጠውም? የሱ እግር ተሰብሯል? ለጠመንጃ ለመገዛት ነው ፉን ፉኑ? » አልሁ ከተቀመጥሁበት ወንበር ብድግ ብዬ እጄን ለመታጠብ እየሄድሁ ።

« መቼ ነገሩ ገባቸውና » አለ ወዳጄ ።

« ቆይ እንዲገባቸው እናደርጋለን! » አልሁ እጄን እየታጠብሁና እሱን እሱን እየተመለከትሁ ።

« ለሁሉምኮ እኮ ዕውቀት ያሻል » አለ ወዳጄ ። እኔም እጄን በፎጣ እያደረቅሁ « መልካም! በዳዮች ለማወቅ ቢሳናቸው ተበዳዮች ለምን አያውቁም? » አልሁት ። ከዚያም ወደነበርሁበት ወንበር ሄጄ እንደተቀመጥሁ የባልንጀራዬ ሚስት ትንሽ የቡና ማንቆርቆሪያና ስኒዎች በቡና ማቅረቢያ ዕቃ ላይ አምጥታ ከጠረጴዛው ላይ ካስቀመጠች ቤላ ከባሏ ወንበር ጥግ ካለ አንድ ወንበር ላይ ተቀመጠችና በሦስቱ ታላላቅ ስኒዎች ቡና ቀድታ በሦስታችን ፊት አስቀመጠች ። ጥቂት ፀጥ ብለን ቡናውን ከስኳሩ ስናገናኝ ቆየን ። እኔም « ይህ ሁሉኮ የፍርሃትና የራስ ብቻ ፍቅር ውጤት ነው » በማለት ከወዳጄ ጋር ጀምሬው የነበረውን ውይይት ቀጠልሁ ።

የባልንጀራዬ ሚስትም ንግግራችንን ስትሰማ ቆይታ ስለነበር « ምን አሞት ያለው ወንድ አለ ብለው ነው? ባሁኑ ጊዜ ከወንዶች ይልቅ ሴቶች እንሻላለን ። እኛስ ብንጠቃም ሴቶች ነን እምብዛም አያሳፍር ። ወንድ ወንድ እያየ ሲንቀጠቀጥና ሲረጋገጥ የሚኖረው ለምን ነው? » አለች ከስሜት ጋር ። « አይ! ሁሉም ዝም የሚለውና የሚታገሠው እስኪሰለቸው ነው እንጂ ሲብሰው ማን ዝም ይል ብለሽ?» አለ ወዳጄ ።

ይህስ የተረቱ ነገር ነው » አለች የወዳጄ ሚስት ። ንግግሯንም ቀጥላ « አንድ ፈሪና ሁለት ደፋር ሰዎች ለአደን ሂደው በበረሃ ሲዞሩ ከዋሉ ቤላ ጊዜው ስለመሸባቸው በአንድ ዱር ጥግ ማደር ግድ ሆነባቸው ። ከዚያም ሲተኙ ፈሪው ሰውዬ እፈራለሁና እመሃል አስተኙኝ ብሎ ሁለቱን ጓደኞቹን ለመነ ። ጓደኞቹም ልመናውን ተቀብለው እመሃል አስተኙት ።

ነገር ግን አጥቂ ሁሉ ፈሪን ማደን ልማዱ ነውና ሌሊት ጅብ መጥቶ የፈሪውን ሰው እግር ይዞ መቆርጠም ጀመረ ። ፈሪው ሰውዬ ጅቡን ለማባረር ፈርቶ እግሩን እየተቆረጠመ ዝም አለ ። አጥንቱ ጐርደምደም ሲል ጓደኞቹ ሰምተው « ምን ነገር መጣ? አውሬ ምን አጥንት ይቆረጥማል? » እያሉ ራሳቸውን ቀና ቀና ሲያደርጉ ፈሪው ሰውዬ « ዝምበሉ ዝምበሉ ጅብ ነው! እንዳይበላን » ሲል በሹክሹክታ ተናገረ ። « አሁን ምን አጥንት ነው የሚቆረጥም? ዋረ ተነሱ እዛፉ ባላ ላይ ያንጠለጠልነውን ሥጋ አውርዶ በልቶት እንደሆን! » አለ አንዱ ጓደኛ ። « ዝምበል ዝምበል እግሬን ነው የሚበላ! እንዳይበላን ዝምበል! » አለ ፈሪው ሰው በሹክሹክታ አፉን በጁ እየተመተመ ።

ጓደኞቹም « ዋረ ይኸ ቡርቂ! ምን እስከትሆን ነው የምትጠብቀው ሥጋህንማ በልቶታል ነፍስህን እንዳይበላት ነው የምትጠብቀው? » ብለው በፍጥነት ተነሡና ጅቡን ካባረሩ ቤላ በበነጋው እግረ ቆራጣውን ፈሪ ጓደኛ ባልጋ ይዘው ወደመንደራቸው ጉዞ ጀመሩ » የሚል ተረት በመጽሐፍ ላይ አንብቤ ነበር ። አሁንም የኛ ወንዶች ነፍሳችሁ እስከትኰንን ትጠብቁ እንደሆነ እንጂ ሥጋዊ ክብራችሁስ እስከመጨረሻው ተገፍፏል » አለች ። በዚች ሴት ንግግር ሁለታችንም ተነካን ። ካልሽ ከነገ ማታ ጀምሮ ከቤታችን ብዙ እንግዶች ይመጣሉና ብዙ ስኳርና ሻይ ቅጠል አዘጋጂ » አላት።

« ይሁንልህ እንጂ አንዳንድ ጆንያ ስኳር እገዛለሁ » አለች ።

« አንተም እዚሁ መሰንበት አለብህ » አለኝ ወደኔ ዘወር ብሎ « ዋረ እኔስ አለሁ! » አልሁት ከዚህ ቤላ ሴትየዋ የንግዳውን አልጋ ልታስነጥፍልኝ ወደእንግዳ መኝታ ቤት ሄደች ። እኛም እስከተኛንበት ጊዜ ድረስ ስንመካከር ቆየን ።

በሳምንቱ ማምሻ በወዳጄ ቤት ሳሎን ብዙ ወንበሮች ተደርድረው ነበር ። ሳሎኑ ልክ የስብሰባ አዳራሽ ከመምሰሉ በላይ የጸጥታና የሥጋት ዓየር ይንሳፈፍበታል ። በሳሎኑ ውስጥ ከወዳጄናኔ በቀር ከድሮ የምናውቃቸውና በሳምንቱ ውስጥ ጉዳዩን ያማከርናቸው የድሮው የትምህርትና የማስታወቂያ ሚኒስቴር ፣ አንድ ወጣት ዶክተር ፣ አንድ ነጋዴ ፣ አንድ ባለእንዱስትሪ ሰውዬ ፣ አንድ የማተሚያ ቤት ባለቤት ባለቤት ሌሎችም ብዙ ሰዎች አብረውን ተቀምጠው ነበሩ ።

ምንም እንኳ የስሜት ሥጋት በቤቱ ጣራ ሥር ቢያንዣብብ በያንዳንዳችን ግንባር የፈገግታ መልክ ይታይ ነበር ። የወዳጄ ሚስት ከገረዷ ጋር ሁና ከቁጥራችን ልክ የሚበልጡ ስኒዎችና ሻይ አምጥታ ሁላችንንም በሳቅና በፈገግታ ሰላም ካለችን ቤላ ሻይውን ቀዳችልንና ገረዷ ወደማድቤት ስትመለስ በሩን ዘግታ ከኛ ጋር ተቀመጠች ። ምንም እንኳ ሴትን ምሥጢር ማካፈል አደገኛ ነው የሚባለው ነገር ብዙ ጊዜ እየሆነ ባገኘው እንደ ወዳጄ ሚስት ያለችውን ጀግና ሴት ከወንድ በበለጠ ስለምተማመናት አብራን መቀመጧ አስደሰተኝ እንጂ አላጠራጠረኝም ።

ሻይውን ከጠጣን ቤላ ሁሉም አንዱ የሌላውን አፍ እየተመለከተ ዝም ብሎ ሌላ ሌላውን ማውራት ሆነ ። በስሜትና በፍላጐት አንድ የሆኑ ሰዎች ሐሳብ ለሐሳብ ለመለዋወጥ ርስ በርሳቸው እንዴት እንደሚጠራጠሩ ለማመን የኛው የዚያ ጊዜ ሁኔታ ይመሰክር ነበር ።

ሁሉም ዳር ዳር እያለ ጥቂት እንዳወራን « እስከዚህ ተፈራርተን ነው ቁም ነገር የምንሠራው?»

ስል በድንገት ብበርቅባቸው ጊዜ ሁሉም ደነገጡ ። ንግግሬን ቀጠልሁና « ምንድነው ፍራቱ? ልንመካከር ተሰብስበናል እንመካከር! » አልሁ ። የድሮው ሚኒስትር « እህህህ! » እያለ ጉሮሮውን ካጠራ ቤላ ወደኔ

እየተመለከተ « እውነት ነው! ነገሩ መቼም ግልጽ ነው ። ችግሩ ሕዝቡ በአንድ ላይ እንዲነሣ ማድረጉና መሰብሰቡ ነው እንጂ ለመመረሩ ሁሉም ተመሯል! » አለ ።

« መሰብሰቡ ቀላል ነው ። ሁሉም በያለበት ከመሰሉ እየተሰበሰበ ይመካከርና አንዴ ገንፍሎ መነሣት አለበት ይህ ከዛሬ በፊትም የምናውቀው ነገር ነው » አልሁ ።

ወጣቱ ዶክተር ክርኑን ከወንበሩ ላይ አስደግፎ ወፈር ያለችና ጠርታ የተላጨች ጉንጩን በመዳፉ አስደግፎ ሻይ የነበረበትን ስኒውን እየተመለከተ « እሱስ ሁሉም ደኅና ነው ። ነገር ግን መጀመሪያ ለሁሉም ነገር አቅድና ጥናት ማድረግ ጠቃሚ ነው » አለ ።

« እውነት ነው ዓቅድ ማዘጋጀት ያሻል ። ነገር ግን ጉዳዩ የተፋጠነ መሆን አለበት ። እኛ እስከዚህ ምን አስጨነቀን? እኛ መንግሥት ገልብጠን ለመያዝ አንፈልግ ። እኛ የምንሻው ሕዝቡ በአንድ ላይ ተነሥቶ በሕግ እንመራለን እንጂ በጠመንጃ አንገዛም ለክፉ ጊዜ ሁላችንም ወታደሮች ነን ። ለነፃነታችንና ላገራችን ሁላችንም ለመሞት ዝግጁ ነን ። ለዚህ ትፈልጉን እንደሆነ አብረን እንሰለፍ! ጊዜው ሰላም ከሆነ ግን በናንተ ሥር መጨቆንን አንቀበልም እንዲል ነው » አልሁ ። ዶክተሩ መለሰና « ታዲያኮ ለዚህም ሕዝቡ እንዲያውቅ ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን እያዘጋጁና እያተሙ ውስጥ ውስጡን ለሕዝቡ ማዳረስ ያሻል አለ ።

« ታዲያ ምን አለ? » አለ ወፈር ያለው የማተሚያ ቤት ባለቤት ገለል ብሎና እግሩን ዘርጋ አድርጎ ተቀምጦበት ከነበረው ወንበር ላይ ቀና ብሎ እየተደላደለ ። ንግግሩንም ቀጥሎ « ማተሚያ ቤቱ በጃችን ነው » አለ ። እኔም ሁለቱን እጆቼን ግጥም አድርጌ እንደያዝሁ « በእውነቱ ርስ በርስ ተማምነንና ቆርጠን ከተነሣን በዚህ ብዙ ችግር የሚያጋጥመን አይመስለኝም ።

እነሱ እነማን ናቸው? በድሮው መንግሥት ጊዜ ከመንግሥቱ መሪዎች ይልቅ ሕዝብን ያጠቁ እነሱ ነበሩ ። በሰዎች ተጠግተው ያደርጉት የነበረው አጥቂነት አልበቃቸው ብሎ አሁን ደግሞ ሁሉንም በጃቸው አድርገው በሕዝብ

ሊጫወቱ ተነሡ ። የነሱ ዓላማ ይህ ከሆነ እኛ ደግሞ ሌላ ዓላማ መፍጠር አለብን ። እኛ ሁሉ ነገር በጃችን ያለ ሕዝቦች ከተባበርን አንድ ድርጅት አፍርሰን ሌላ መመሥረት አያቅተንም ። የገዛ አገሩን ሕዝቦች ጨቁኖ መግዛት ከፍተኛ ዓላማው የሆነ ማርሻል የሚመራውን የጦር ድርጅት አፍርሰን ከሀገሩ ሕዝብ ጋር ተመሳስሎ የሀገሩን ነፃነትና ፀጥታ የወገኖቹን መብት መጠበቅ የመጨረሻ ዓላማው የሆነ ማርሻል የሚመራው የጦር ድርጅት ማቋቋም አለብን ። ለነፃነት ጥበቃና ሕግን ለማስከበር የተደራጀ ኃይል ያሻናል ። ነገር ግን ይህ ኃይል ራሱ የሕግ ተቃዋሚና የነፃነት ጠላት ከሆነ እሱን አፍርሶ ለታሰበው ዓላማ የሚውል ድርጅት ማቋቋም ያሻል ። የዛሬዋ ዓለም የድሮዋ ዓለም አይደለችም ። በዛሬዋ ዓለም በራሳቸው መንደር ብቻ ለሚንጐራደዱና የገዛ ወገናቸውን ለሚጨቁኑ ጦረኞች ቀርቶ ለዩልዮስ ቄሣር ፣ ለናፖሌዎን ፣ ለሂትለርና ለሌሎችም ታላላቅ ጦረኞች ቦታ የላቸውም። በዛሬዋ ዓለም ሰዎች የሚሹት በሰላምና በነፃነት ተቀምጠው የኪነ ጥበባትና የሥነ ጥበባት ሥራዎችን ከጉልበት ሥራዎች ጋር አዋሕደው በማሳደግ የተሟላ ኑሮ ማግኘትን ነው እንጂ መውረርን ወይም መወረርን አይደለም ። ጭቆና ርኩስ ነገር ነው ። ጭቆና የድንቁርና መጋረጃ ነው ። ጭቆናን የምንቃወመው ለጊዜው በሰዎች ላይ በሚያደርሰው ጉዳትና ጥቃት ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱ ለሰው ትውልድ መልካም መንገዶች የሚከፍቱ አካላዊና ፣ መንፈሳዊ ዕውቀቶችን አፍኖ ስለሚያስቀር ነው ። ፍርሃት የመሻሻል ሓሳቦች መቅሠፍት ነው ። ሰው ሳይደርስባቸው ከቀሩ ጥበቦች ይልቅ በፍርሃት ታፍነው የቀሩት ብዙዎች ናቸው ። ክፋትን ወንጀልን ፣ ብልግናን ፣ ራሳችን ከራሳችን እናርቃቸው ። ከዚህም ለመድረስ በዕውቀትና በትምህርት መሻሻል እንጂ በጠመንጃ መቃጣት አያሻንም እንግዲህ ሕዝብ ይህን ማወቅ አለበት » አልሁ ።

« እውነት ተናገሩ! » አለ ባለእንዱስትሪው ሰውዬ ወደኔ እየተመለከተ ። ንግግሩንም በመቀጠል « እኛ መቼም የወታደርነት ሥራ ተቃዋሚዎች አይደለንም ። ለማንም አገር የጠነከረ ወታደራዊ ድርጅት ያሻዋል ። እኛ የተቃወምነው ወታደራዊ አገዛዝን ነው ። ስለዚህ ሕዝብና ወታደርን ከመከፋፈል ይልቅ የገዥነት ጥም የያዛቸው የጦር አለቆችን ተቃውመን ወታደሮቻችንን ባሉበት እንዲፀኑ ማድረግ ይገባናል » አለ ።

በዚህ ጊዜ የድሮው ሚኒስትር ቀበል አደረገና « ችግሩ ዝቅተኛ መኰንኖችና ወታደሮች ያለቆቻቸውን ቃል ስለሚያመልኩ ነው እንጂ ጉዳዩን ከተረዱትማ ነገሩ ቀላል ነው ። ወታደሮች ያገራቸውን ሕዝብ ለጦር አለቆቻቸው ለማስገዛት ከመታጠቅ ይልቅ ወገናቸውን ወደ መልካም ዕድል ሊያደርሱ የሚችሉ መሪዎችን ቢደግፉ ሕዝብ የነሱ ጠላትና ተቃዋሚ ሁኖ ከመነሣት ይልቅ በሰላም አርፎ እየሠራ ኑሮውን ሲያሻሽል የነሱም ኑሮ አብሮ ይሻሻል ነበር ። ወታደሮች ጥቅማቸውን የሚያገኙት ሥርቶ ግብር ከሚከፍለው ሕዝብ እንጂ ከማርሻሎቻቸውና ከጄኔራሎቻቸው ጌጣጌጥ አይደለም ።

ስለዚህ ከሕዝብ ጐን መሆን እንጂ ለጥቂት የጦር መኰንኖች ደስታና ፍላጐት ብለው ከወገናቸው ጋር መዋጋት አይገባቸውም ። ሁከት ቢነሣ የሚያልቁትና ቤተ ሰባቸውን በመከራ ላይ ጥለው የሚያልፉት ዝቅተኛ መኰንኖችና ሹማምንቶች እንዲሁም ተራ ወታደሮች ናቸው ። ጄኔራሎች ግን መጀመሪያም ወደጦር ግንባር አይገቡ ገብተው ቢሞቱም ለቤተሰባቸው የሚሆን በቂ ሀብት አላቸው ። ቤተሰባቸው በችግር ላይ አይወድቅም ። » አለ ።

« በገዢነቱም ቢሆን » አለ ወጣቱ ዶክተር ። « በገዢነቱም ቢሆን ወታደራዊ አገዛዝ ስለተባለ በስሙ ብቻ ይደሰቱ እንደሆነ እንጂ ሰውን ጨቁኖ የሚገኘው ክብር ፣ ከማርሻሎችና ከጄኔራሎች አልፎ ለምስኪኑ ዝቅተኛ መኰንንና ተራ ወታደር የሚተርፈው ነገር የለም ። »

« ታዲያ ወታደሮች ይህን ሁሉ እንዲያውቁት ለማድረግና ርስ በርሳችን ደም ከመፋሰስ ለመዳን ምን ማድረግ ይሻለናል? » ስል ሁሎችንም ጠየቅሁ ።

የድሮው ሚኒስትር ቀበል አደረገና « እኔ የማውቀው ወዳጄ የሆነ አንድ ለሕዝብ ጥቅምና ለእውነተኛ ነገር የሚሞት አሁን በሚደረገው ነገርም በጣም የሚበሳጭ አንድ ሙሉ ጄኔራል አለ እሱ ለተራው ወታደርና ለአንዳንድ እውነትን ለሚፈልጉ መኰንኖች ጉዳዩን ሊያስረዳልን ይችላል ። » አለ ።

« በጣም ጥሩ! » አልሁ ። ንግግሬንም ቀጥዬ « ይህ ከሆነ ሁላችንም በያለንበት እንዳይታወቅብን ሁነን ሕዝብን ወጥረን ማስረዳት አለብን » አልሁ

። ከዚህና ከቀረውም ውይይት ቤላ ሁላችንም በያለንበት እያስረዳን ባለማተሚያ ቤቱ ፣ ባለእንዱስትሪውና ሌሎችም ብዙ እየረዱን ፣ ገበሬውንም ፣ ነጋዴውንም ፣ ባላገሩንም ፣ የጠመንጃ ተገዥ ከመሆን ነፃ ወጥቶ ፓርላማና ሕጋውያን መሪዎች ያሉበት መንግሥት አቋቁሞ ራሱን በራሱ ሕግ እንዲመራ አስተማርነው ። ሁሉም ጉዳዩን ያስብበት ጀመር እኔም ከርሻዬ ቦታ እየተመላለስሁ ከጓደኞቼ ጋር እመካከር ነበር ። ሁላችንም በያለንበት ብዙ ተግባር ከፈጸምንና አብዛኛውን ሕዝብ ከኛ ጋር ካደረግን ቤላ ጠቅላላ ውሳኔ በምናደርግበትና አቅዱን በምናጸድቅበት የመጨረሻ ቀን ሰፊ ቦታ አስፈልገን ። ይህን ለማድረግ ካንድ ሰፊ ደን በቀር ሌላ ስለማይሻለን አንድ እሑድ ቀን ጧት እያንዳንዳችን እየተሾለክን ከከተማ በመውጣት ከተቃጠርንበት ደን ተገናኘን ። ከዚያም በብዛት እንደተሰበሰብን ጥቂት ከተወያየን ቤላ አቅዱን እንድናዘጋጅ በጓደኞቻችን የተጠየቅነዎች ሰዎች ረቂቁን አውጥተን ለተሰበሰቡት የነፃነት ሠራዊቶች አቀረብን ።

የተዘጋጀው አቅድም (ፕላን) ባጭሩ ሲገለጽ የሚከተለው ነበር ።

«1ኛ ፡ በየቦታው ተሠራጭተው ሕዝቡን እንዲያስነሡ የተመደቡት ሰዎች ቀደም ብለው በየተመደቡበት ቦታ እንዲደርሱና ከተወሰነው ቀን አንድ ቀን ቀደም ብለው ሕዝቡን ያለውን ማንኛውንም መሣሪያ ሌላ የሌለው እንኳ መጥረቢያና ዱላ ይዞ እንዲጠባበቅና የሬዲዮና የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን ለመያዝ ችለን መልእክተኞቻችን በያዙዋቸው የነፋስ ሬዲዮዎች ዓማካይነት ዓዋጃችን ሲሰማ ወዲያውኑ ወደዋናዋ ከተማችን እንዲገሠግሥ አስቀድሞ መልእክተኞችን በየቦታው መላክ ።

2ኛ ፡ ከሕዝብ ጋር ያልተባበሩትና ለወታደራዊ መሪዎች ታማኞች ነን የሚሉ ወታደሮቸ በሚጠቀሙባቸው መገናኛዎች ላይ ያለታሰበ አደጋ በመጣል የባቡር መሥመሮችን በመቁረጥ በአኤሮፕላን ማረፊያዎች ላይ ማሰናከያዎችን በመደርደር የቴሌፎን መሥመሮችን በመቁረጥ ድንገተኛ ተግባር መፈጸም

3ኛ ፡ ከሕዝብ ጋር የሆኑት ወታደሮች ከኛ ጋር በሆነው ጄኔራል እየታዘዙ ከያሉበት ክፍል ያለውን መሣሪያ ታንክም ቢሆን መድፍ አኤሮፕላንም ቢሆን ጠመንጃ ያገኙትን ሁሉ እየያዙ ከሕዝቡ እንዲቀላቀሉና ከርስ በርስ ጦርነት እንዲያድኑን እንግዛ ባዮች ከገፉም በሥራ ላይ እንዲያውሉልን ።

4ኛ ፡ ሕዝብን በኃይላችን መግዛት አለብን ያሉትን ፓርላሜንቱን የዘጉትን የሕዝብን መብት የቀሙትን ወታደራዊ ባለሥልጣኖች ቢቻል እጃቸውን የሚይዙ ያለዚያ የትም መውጣት እንዳይችሉ ቤት ቤታቸውን ከበው የሚጠብቁ ወታደሮችና ሌሎችም ባለመሣሪያዎች መመደብ ።

5ኛ ፡ ከሁሉ አስቀድሞ የመናገሪያ መሣሪያዎችን እጅ ማድረግና የተመከረውና የተጠነቀቀው ሕዝብ እንዲነሣ ማወጅ ።

6ኛ ፡ በተቻለ መጠን ደም እንዳይፋሰስ ሁከት አጫሪ ሁኖ አለመገኘትና መብታችንን እንጂ ጦርነት የማንፈልግ መሆናችንን ማስረዳት ።

7ኛ ፡ የተዘጋው ፓርላሜንት ተከፍቶ በጦር ኃይል ታግደው የኖሩት የሁለቱም ምክር ቤት አባሎች እንዲሰበሰቡና ስላገራችን የወደፊት ዕድል አንድ ውሳኔ እንዲሰጡ ማድረግ ።

8ኛ ፡ ያለምክንያት የታሠሩ የፖለ+ካ እሥረኞች ሁሉ እንዲፈቱ ማድረግ ።

9ኛ ፡ ለጊዜው ከሲቪልና ከወታደራዊ ታላላቅ ሰዎች የአስተዋይነታቸውና ለሕዝብ የነበራቸው ግምት ከፍተኛነት የታወቀላቸው ሹማምንት ተመርጠው የምክር ቤቱን ሓሳብ እየተቀበለ ለሕዝቡ የሚስማማውን መንግሥት ለማቋቋም የሚያስችልና ለጊዜው ሕዝቡን የሚመራ ድርጅት እንዲያቋቁም ማድረግ ።

10ኛ ፡ ይህን እንዳናደርግና በጦር ኃይል ሥር ጭጭ ብለን እንድንኖር ብቻ የሚፈልጉት ወገኖች ከዚህ ዓላማችን ቢያግዱን ሳንወድ በግድ ባለን ኃይል መጠቀም ።

11ኛ ፡ ጦርነት ከተጀመረ አይቀር ድል ማድረግ ስላለብን በግንባር ለግንባር ውጊያ ብቻ ሳይሆን በደፈጣና በአደጋ መጣል ውጊያ መጠቀም ። ይህም ሲሆን ፣

ሀ/ ታንኮችና ሌሎች የጦር መኪናዎች በሚያልፉበት መንገድ የኤሌክትሪክ ሽቦዎችን እየቆረጡ ማጥመድና ብረት የሆኑ

ነገሮችን ሁሉ እንዲይዙ ማድረግ ። ዲናሚቶችንና ሌሎችንም ፈንጂ ነገሮች እየቀበሩ ማጥመድ

ለ/ ቤንዚን የተሞሉ ታላላቅ ጠርሙሶችን በመስኮት እያሾለኩ እየወረወሩ በመኪናዎችና ታንኮች ላይ እየጣሉ ቤንዚኑ እዚያ ላይ ሲፈስ አከታትሎ የጅ ቦምብ በመጣል በነሱ ላይ ቃጠሎ ማስነሣት ።

ሐ/ በየቤቱና በየቦታው እያደፈጡ ግንባር ለግንባር ሳይሆን እየተበታተኑ የሚሄዱትን

የህዝብ ጠላቶች በጥይትም ሆነ በምርኮ መልቀም ።

መ/ ባለሆቴሎችና ባለምግብ ሸቀጦችና ሌሎችም የከተማና የባላገር ኗሪዎች እህል ፣ ውሃ ለመፈለግ ለሚመጣው የተቃዋሚ ክፍል ወታደር ምንም አለመስጠትና እንዲማረክ መጠየቅ ለማጥቃት የሚፈልግ ከሆነም አስቀድሞ እሱን ማጥቃት ።

12ኛ ፡ በሬዲዮ ሳያቋርጡ ሕዝቡን ማበረታታትና የተቃዋሚው ክፍል ወታደሮችም በከንቱ ሕይወታቸውን እንዳያጡና ለሌሎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት እንዳይሆኑ እየደጋገሙ መምከር ።

13ኛ ፡ በዚህም ሁኔታ እንቅስቃሴውን መቀጠል ። ምናልባት በዚህ መንገድ ፍጹም ድል ያልተገኘ እንደሆነም ካገራችን ከተሞች ወዳንዱ ተዛውረን ሕጋዊውን መንግሥት ማቋቋምና ጨቁኖ የመግዛት ሱስ የያዛቸውን ወንበዴዎች እስከመጨረሻው መዋጋትና የሕዝብን መብት በውድም ሆነ በግድ ማስመለስ ።

14ኛ ፡ እርቅና ስምምነት የሚፈልጉ ሁነው ሲገኙ ቶሎ ብሎ ለሕዝብ መብት ተቃዋሚ ያልሆነ ዕርቅ ማድረግ ።

15ኛ ፡ ማንም የውጭ መንግሥት በኛም ሆነ በወንበዴዎች በኩል እጁን እንዳያገባ በጥንቃቄ መጠባበቅ ። »

ይህ ያዘጋጀነው ዓቅድ በተሰበሰበው ሕዝብ መካከል ተነቦ ሁሉም ተስማምተውበት ከጸደቀ ቤላ ዓቅዳችንን በሥራ ላይ የምናውልበትን ቀን በቀጠሮ ወስነን ተለያየን ። ወዳገር ቤት እንዲበተኑ የተመደቡትም ተላኩ ።

# 13

# የመጨረሻው ንቅናቄ

በተወሰነው ቀን ዋዜማ ማታውኑ ከከተማው አለፍ ብሎ ወደሚገኘው ሰፊ ሜዳ ሁሉም ከያለበት ያለውን የጦር መሣሪያ እየያዘ መጣ ። ከኛ ጋር የሆኑት መኰንኖችና ወታደሮችም ከያሉበት ብዙ ልዩ ልዩ መሣሪያዎች እየያዙ ሲመጡ የቀሩትም ለጦርነት ሲታዘዙ በዚህ ምክንያት ተፈላጊ የሆኑትን ዘመናውያን መሣሪያዎች እየያዙ ለመውጣት እንዲመቻቸው በየጦር ሰፈራቸው ቆይተው ነበር ።

ከዚያም ከዚያም ሲል ሁለት መቶ ሺህ ያህል ሕዝብ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ተሰበሰበ ። ወዲያው « ማርሻል ጃፈሮስ » የተባለውን ዲክቴተራችንን ቢቻል እጁን እንዲይዙት ያለዚያም ከቤቱ ለመውጣት እንዳይችል ከቤቱ የተያያዘውን ማንኛውንም የሽቦ መሥመር ቆርጠው የቤቱን ዙሪያ ከበው እንዲጠብቁት ዐሥር ሺህ ሰዎች ጥቂት መትረየሶች ቦምቦችና በቊጥራቸው ልክ ጠመንጃዎች እንዲሁም ብዙ ብዙ ጥይት እንደያዙ መደብን ። እንዲሁም ሌሎችን ማርሻሎችና ጄኔራሎች እንደዚሁ ቢቻል እንዲይዙዋቸው ባይቻል እንደዚያው እንዲጠብቋቸው ለያንዳንዳቸው አምስት አምስት ሺህ ሰዎች መደብን ።

አምስት ሺህ የሚሆኑ ሰዎች የመገናኛ ዘዴዎችን እንዲያሰናክሉ የባቡር ሐዲዶችን ለማሰናከል ያህል እንዲቆርጡ መንገዶችን በመቆፈርና ማሰናከያዎችን በመደርደር እንዲያሰናክሉ የአኤሮፕላን ማረፊያዎችን በላያቸው ላይ ልዩ ልዩ ነገሮችን በመደርደር እንዲዘጉና በዚያውም ሁነው የሚመጣባቸውን ሁሉ እንዲከላከሉ መደብን ። ሐያ ሺህ የምንሆን ሰዎች ወደ

ሬዲዮ ጣቢያዎች ሂደን ሕዝቡ ከዳር ዳር ተነሥቶ ተገቢ መብቱን እንዲጠይቅ ለማሳሰብ ዓላማችንን ለማስረዳትና ሁኔታውን እየተከታተልን ርምጃችንን ለማቃናት ተመደብን ። የቀረው ሕዝብ ደግሞ በየቦታውና በየግንባሩ ተሰልፎ መጀመሪያ ሰላማዊ ጥያቄውን እንዲያቀርብ አጥቂ ሲመጣ ግን እንዲከላከል ተመደበ ።

ከዚያም ቤላ ሁላችንም በቆራጥነትና በልበ ሙሉነት ወደየተመደብንበት ቦታ ሂደን ። ታላቁን የሬዲዮ ጣቢያ ይዘን በዚያው አስፈላጊውን ሁሉ እንድናስተላልፍ የተመደብነዎች ሰዎች አስደንጋጭ በሆነ ብዛት በሬዲዮ ጣቢያው ደርሰን ጣቢያውን የሚጠብቁት ዘበኞች ያለአንዳች ማመንታት ከለቀቁልን ቤላ እዚያው ተዘጋጅተን ቆይተን ከሌሊቱ ዐሥራ አንድ ሰዓት ሲሆን ያዘጋጀነውን ልዩ ልዩ ጽሑፍ አንባቢዎችን እያቀያየርን ማሰማት ጀመርን ።

ለጃፈሮስ ታማኞች ለነበሩ ወታደሮችም እየደጋገምን ማስጠንቀቂያዎችንንና ልመናችንን አቀረብን ። ከሰጠናቸው ምክሮች መካከል የሚከተለው ቃል ነበረበት ። « እኛም የሀገራችንን ፀጥታና ሰላም ለመጠበቅ በተዘጋጃችሁ ወታደሮቻችን ላይ ተነሥተን እናንተም እኅቶች ወንድሞቻችሁ ፣ እናቶች አባቶቻችሁ ከመካከሉ ባሉበት ለናንተ በወታደርነት መኖር ምክንያት በሆናችሁ ባሠለጠናችሁ በሚያኖራችሁ ሕዝብ ላይ ተነሥታችሁ ርስ በራሳችን ብንጠፋ ከሞት በሚተርፉት ወገኖቻችን ላይ የሚደርሰውን ጉዳት አስታውሱ ። ለግል ሥልጣኑና ጥቅሙ ለሚታገል አንድ ማርሻል ክብር ብላችሁ የወገናችሁንና የራሳችሁን ደም በከንቱ ብታስፈስሱ የምታገኙት ጥቅምና ክብር የለም ። እኛ አሁን የምንጠይቀው የገበሬውንም፣ የነጋዴውንም፣ የጸሐፊውንም፣ የወታደሩንም፣ የባለእንዱስትሪውንም ፣ የጥበበኛውንም፣ መብት በትክክል ለመጠበቅ የሚችል ሰላማዊ መንግሥት እንዲቋቋም የተዘጋው ፓርላማ እንዲከፈት እንጂ ማንኛውንም ክፍል የሚጐዳ አጥቂ ሥራ ለመሥራት አይደለም ። ስለባልቴቶችና ሽማግሌዎች ፣ ስለሕፃናትና ፣ እኅቶች ብላችሁ ተለመኑን ። አደገኛ የሆነውና ብዙ አገሮችን ያጐሳቆለው የብዙ ሕዝብ ደም መጉረፊያ የሆነውና ለውድቀቱ ቀላል መድኃኒት የማይገኝለት የርስ በርስ ጦርነት በሀገራችን ላይ እንዳይደርስ ተጠንቀቁ ።

ኃጢአትና ትዕቢት ለዕውር ጎሊና ለመጀመሪያው ጊዜ ጣፋጭ ናቸው ። ነገር ግን የኃጢአትና የትዕቢት በቀሎች በሚመጡበት ዬለኛ ጊዜ ትዕቢተኛውንና ትሑቱን ግፈኛውንና ተገፊውን ፣ ንጹሑንና ኃጢአተኛውን በአንድ ላይ ያሠቃያሉ ወንድሞቻችን ሆይ! እኛ የምንጠይቀው ሁላችንም በየቦታችን ተግባራችንን እየፈጸምን አንዳችን ላንዳችን ተቃዋሚ ሳንሆን ለመኖር እንጂ አንዱን ክፍል ጥለን ሌላው ክፍል እንዲፈነጭበት ለማድረግ አይደለም ።

ይልቁንስ እኛ ርስ በራሳችን ስንጠቃቃ ጠረፋችን በጠላቶቻችን እንዳይደፈርና እንዳይሰለል ሁላችሁም አገራችሁን በያላችሁበት ሁናችሁ በመጠበቅ ወታደራዊ ግዳጃችሁን ጠብቁ ። ወታደራዊ ግዳጅ አገርን ከወራሪ ጠላት መጠበቅ እንጂ የገዛ ወገንን ለአንድ ማርሻል ለማስገዛት ከወገን ጋር መዋጋት አይደለም ። ልብ ብላችሁ አስተውሉት! እነዚህ የግል ጥቅምና የሥልጣን ፍላጐት ያወራቸው አለቆቻችሁ ለግል ፍላጐታቸው ሲሉ በገንዘብ እየገዙና እያበጣበጡ እጃቸውን ወደሰው አገር ማስገባት በለመዱ ኢምፔሪያሊስቶች ተገዝተው አገራችሁንና ፀጥታችሁን እስከመጨረሻው እንዳያበላሹ ንቁባቸው ። » ይህንና የቀሩትንም ብዙ ነገሮች ከተናገርን ቤላ « ሁከት ቢነሣ ብዙ ደም ይፈሳል በማለት ነው እንጂ እንዳንሸነፍ ሰግተን አይደለም ። በብዙ ሚሊዮን የምንቈጠር ሕዝቦች ከመካከላችን በወጣችሁ ጥቂት ሺ ሰዎች ልንጠቃና ልንጨቆን አንችልም ። ሰዎችን ሲያጠቃቸው የኖረው ሳይመከሩና አንድ ሳይሆኑ መነሣት በኛ ዘንድ የለም ። ያገራችን ሕዝብ ዳር እስከ ዳር እንጂ እኛ ብቻ አልተነሣንም ። ብቻን መነሣት እንደናንተ አለቆች ያሉት የግል ጥቅምና ሥልጣን ፈላጊዎች ዓላማ ነው ። እኛ ግን የምንፈልገው የጋራ ጥቅምና መብትን ስለሆነ በአንድ ላይ ተነሥተናል ። ወታደርና ሲቪል ባላገርና ከተሜ አዋቂና መሃይማን ሳይለይበት ሁሉም ለትክክለኛ ጥያቄ ተነሥቷል ።

ስለዚህ እውነትን ለመረዳት ያልቻላችሁ ጥቂት የደም ነጠብጣቦች ታላቁን ባሕር በናንተ ቀለም ለመለወጥ ብትሹና በባሕሩ ላይ ብትንጠባጠቡ በውቅያኖሱ ሠጥማችሁ ከመቅረት በቀር ለመንጠባጠባችሁ እንኳ ቀሪ ምልክት አይገኝለትም » ይህን የመሰለውንና የቀረውንም ብዙ ምክርና ማስጠንቀቂያ ስንሰጥ ሕዝቡንም በሰልፉ ላይ እንዲገኝ ስናነሣሣ ጊዜው በጣም ረፊድ ሲል ሕዝቡ ከያቅጣጫው እየጐረፈ ከተማውን በፍጹም አጥለቀለቀው

፡፡ አንዳንድ መኰንኖች ወታደሩ ሕዝቡን በማንኛውም መሣሪያ ያለማመንታት እንዲደበድብ ሲያዙት አብዛኛው ወታደርና ብዙ መኰንኖች ማንኛውንም መሣሪያ እየያዙ ከሕዝቡ ጋር ይቀላቀሉ ጀመረ ፡፡ እንዲያውም በአንዳንድ ክፍልስ አዛዦቹን መኰንን እያሠሩ ይዘው በሙሉ ከሕዝቡ ይቀላቀሉ ነበረ ፡፡ ጥቂቶቹ የማርሻል ጃፈሮስ ታማኞች ብቻ ዓይናቸውን ጨፍነው ባነሡት ሁከት ብዙ ሰዎች በሁለቱም በኩል በድንገት ሞቱብን ፡፡ የማርሻል ጃፈሮስ የቀኝ ክንድ የነበረው የዓየር ኃይል ማርሻል የዓየር ኃይል ወታደሮቹንና መኰንኖቹን ሕዝቡን በከባድ ቦምብ ያለርኅራኄ እንዲደበድቡት አዝዞ አኤሮፕላኖች አስነሣ ፡፡ እነሱ ግን ከሙብቱ በቀር ሌላ ያልጠየቀውን ወገናቸውን መደብደብ ወንጀል መሆኑ ስላልተሠወራቸው ዝም ብለው እየበረሩ እጁን ባይሰጥ ሕዝቡን ሳይሆን የሱንና የማርሻል ጃፈሮስን ቤቶች በቦምብ የሚደበድቡ መሆናቸውን አስረዱት ፡፡ ይህን በመሰለ ሁኔታ የፈራነውን ያህል ታላቅ ጥፋት ሳይከተል ለዕርቅ ከመቃረብ ደረስን ፡፡ ለማርሻል ጃፈሮስ የመጨረሻ የደም ጠብታችንን እናፈሳለን ብለው ቆርጠው በመነሣት የራሳቸውንም የሌሎችንም ሕይወት በማጥፋት ላይ የነበሩትን ወታደሮች ያዝዙ የነበሩት መኰንኖች ከርሱ ጋር በሬዲዮ ከተነጋገሩ ቤላ ጦርነቱ እንዲቆም ተደረገ ፡፡

ከዚህ ቤላ ሕዝቡም ወታደሩም ፀጥ እንዲል ተደረገና ከፍተኛ የጦር መኰንኖችና ታላላቅ የፖለ+ካ ሰዎች አንዳንድ ሽማግሌዎችና የሕዝብ እንደራሴዎች በድሮው ፓርላሜንት ውስጥ ተሰብስበን ስላገራችን የወደፊት አመራር ተመካክረን ውሳኔ እንድንሰጥ ተስማማን ፡፡

በዚህም ጊዜ እያንዳንዳችን ሓሳብ ስናቀርብ ማርሻል ጃፈሮስ በተራው ሲያስረዳ « እኛኮ የሕዝቡን አለሙብሰልና ለከፍተኛ በዲሞክራሲ የመመራት ደረጃ አለመድረስ በማየት ነው እንጂ እንደዚህ እስክትነሡብን ድረስ የመግዛት ፍላጐት ኑሮን አይደለም ፡፡ ከእውነተኛው ሰብአዊ ደረጃ ላልደረሰና በነፃነት የመጠቀም ችሎታ ለሌለው ከሕግ ይልቅ በኃይል መገዛትን ለሚፈልግ ሕዝብ እናንተ ካሰባችሁት ይልቅ እኛ ያሰብንለት መንገድ ይሻል ይመስለኛል ፡፡ ካላችሁም ይሁን! እኛ ነፃ አወጣነው እንጂ ሌላ አላደረግነውም » አለ ፡፡

እኔም አነሣሁና « የተከበሩ ማርሻል! አሁን የተናገሩት ቃል እውነትም ሐሰትም ሊሆን የሚችል ነው ፡፡ አልሠለጠኑምና ይጨቆኑ ማለት የቅኝ

ገዢዎችና ሕዝብን አደንቁረው ለመኖር የሚፈልጉ ገዢዎች ዓላማ ሲሆን እውነተኛ መሪዎች ግን የሚሉት ወገናችን አልሠለጠነምና ቶሎ ብለን የጥቅሙና የሙብቱ መሥራች የሚሆንበት መንገድ እናስተምር ነው ። ሕንዳዊው ታላቅ መሪ ማኅአትማ ጋንዲ ሕንድ ራሷን ለመግዛትና በነፃነቷ ለመጠቀም የሥልጣኔዋ ደረጃ አይፈቅድላትም እያሉ የርስዎን ሓሳብ በመሰለ መንገድ ያደከሙት ለነበሩ ቅኝ ገዢዎች ሲመልስ « በውጭ ጌቶች ፣ ራሱን ለመግዛት አይችልም እየተባለ የሚጨቆን ሕዝብ ምንጊዜም ራሱን ለመግዛት አይችልም ። ራሱን ለመግዛት እንዲችል ነፃ ሁኖ መማር አለበት » እያለ ይከራከር ነበር ። ስለዚህ እንዲሠለጥን ይማር እንጂ እንዲሰለጥን ይታፈን የሚሉትን እምነት አንቀበልም » ካልሁት ቤላ ንግግሬን በመቀጠል « ነፃ አወጣናችሁ የሚሉን ሻል ካለ ጭቆና ወደባሰ ጭቆና አሸጋገሩን እንጂ ከምን ነፃ አወጡን? ስል ተናገርሁ ።

ይህና ይህን የመሳሰሉ ብዙ ጭቅጭቆች ሲደረጉ ከሰነበትን ቤላ ለጊዜው የመሪነቱን ሥልጣን ይዞ የሚቆይ አንድ ምክር ቤት አቋቁመን ለእርቅ ሲባል ማርሻል ጃፈሮስንም ያገር ግዛት ሚኒስትር አድርገን በዕድሜ ገፋ ካሉት አስተዋይነትና የሥራ ልምድ ካቸው የፖለ+ካ ሰዎች መካከል አንዱን ጠቅላይ ሚኒስትር አድርገን የወደፊቱን የህዝብ ጠቅላላ ምርጫና አስተያየት ለመጠበቅ ተስማምተን ካፈራነው ታላቅ ጥፋት ሳንደርስ ተለያየን ።

እኔም እንኳ በመንግሥቱ ሥራ ተካፋይ እንድሆን ተጠይቄ ነበር ። ነገር ግን በሁኔታው ገና ስላልጠገብሁ ለጊዜው በርሻዬ ብቆይ ለራሴም የበለጠ ሰላም ለሰዎችም የተሻለ ጥቅም ልሰጥ የምችል መሆኔን አስረድቼ ጥያቄውን አስቀረሁት ።

ከጥቂት ጊዜ ቤላ ግን ፍጡርን ሁሉ የሚያስገርም ግፍ ተፈጸመብኝ ። በእውነተኞችና የነፃነት ስሜት አንዳንድ ሰዎች ላይ የደረሰው ደረሰብኝ ። አሁንም ደግሞ ስንት ሰዎች ደክመን ሥልጣን ያስያዝናቸው ሰዎች በተራቸው ገዢ ሁነው ለመኖር በመፈለጋቸው ፍርድ ከጐደለ ጨኸቴን እንደማላቋርጥ በደንብ የሚያውቁኝን ሰው እኔን በወንጀል ከሰው በድንገት በፖሊስ አስይዘው በሥር ቤት ካቆዩኝ ቤላ ወደፍርድ ሸንጎ አቀረቡኝ ።

# 14

## ፍርድ ቤት ስለመቅረቤ ።

ለኔ እነሱ እንደሚጠሩኝ ፍጹም ወንጀለኛ ለተባልሁት ሰው የተደረገው የፍርድ ሥነ ሥርዓት ለሌሎች ከሚደረገው የተለየ ነበር ።

ፍርድ ቤቱ የተለመደው መጠነኛ ቤት መሆኑ ቀርቶ ብዙ መቶ ሺ ሕዝብ የሚይዘው የስፖርት ጨዋታ ሜዳ እንዲሆን ተደርጎ የእውነትና የነፃነት ስሜት ያላቸው ሁሉ እኔን ዐይተው በኔ ቅጣት ተስፋ እንዲቆርጡ በጨዋታ ሜዳ የተደረገው ፍርድ ለማንኛውም ሰው ክፍት ነበር ።

በኔ ላይ የሚቀርበውን ክስና የምሰጠውን መልስ እንዲሁም የሚወሰንብኝን ቅጣት ለመስማት የጓጓው ያገሬ ሕዝብ በሜዳው ሞልቶ የተረፈውም የሜዳውን ዙሪያ ከቦ ቁሞ በኔና በዳኞች እንዲሁም በሕግ አስከባሪው ተጨዋችነት የሚሠራውን አስቂኝና አሳዛኝ ድራማ ለመመልከት በናፍቆት ይጠባበቅ ነበር ። አንድ ማርሻል ፣ አንድ ጄኔራል ፣ ሦስት ሲቪል ሚኒስትሮች የዳኝነቱን ሥራ እንዲያከናውኑ ከመመረጣቸው በላይ በዕድሜ ገፋ ያለና በነሱ እምነት ጠቃሚ ሰው ተብሎ የተገመተ ሌላ ጄኔራል ለሕግ አስከባሪነት ተመድቦ ነበር ።

ዳኞች ፊት ለፊት ረጅምና ሰፊ ጠረጴዛ ከፊታቸው አድርገው ተቀምጠዋል ። ሕግ አስከባሪውም ከዳኞች ግንባር ተቀምጧል ። ዳኞችና እኔ የምንነጋገረው ሁሉ ለሕዝብ እንዲሰማ ለማድረግ እኔና በምንነጋገርበት ቦታ መካከል ታላቅ የድምፅ ማስተላለፊያ መሣሪያ ( ማይክሮፎን ) ተደርጓል ። በየማዕዘኑም ታላላቅ የድምፅ ማጉሊያ መሣሪያዎች ( ላውድስፒከሮች ) ተደርገው በሽቦ መሥመር ከድምፅ ማስተላለፊያው መሣሪያ ጋር ተያይዘዋል ። በሕዝቡ መካከል በብዙ ፖሊሶች አስተናባሪነት የተከፈተ አንድ ጠባብ መንገድ ነበር ። ሦስት የወህኒ ቤት ዘበኞች በጠመንጃ እያጀቡኝ ግራና ቀኝ ግድግዳ መስሎ በቆመው ሕዝብ መካከል ይዘውኝ ወደዳኞች ለመቅረብ ብቅ ስንል ወደመድረክ እንደሚወጣ ዝነኛ ተጫዋች ሕዝቡ ዳር እስከዳር ጭብጨባውን አደባለቀልኝ ። ለደስታም ይሁን ለኃዘን ቅጡ አልገባኝም ። የምናገራቸውን እውነተኛ ነገሮች ለመስማት በመጓጓት ይሁን ወይም

እንደሚጠሉት ሰዎች በእሥራቴ በመደሰት ይሁን ወይም በአጀ በመነዳት ይሁን የህዝቡ ጭብጨባ ትርጉሙ አልገባኝም ። ቢሆንም አልከፋኝም ። ቀስ ብዬ እየተራመድሁ ወደዳኞች ፊት ቀረብሁ ። ሕዝቡ ርስ በራሱ ሲነጋገር የሚዳውን ዓየር ያተመው ስለነበር ሕግ አስከባሪው ጄኔራል ወደማይክሮፎኑ ቀረብ ብሎ ቆመና የወንጀለኛው ክርክር ሊሰማ ነውና ጸጥ እንድትሉ ትጠየቃላችሁ! »ሲል አስታወቀ ። ሕዝቡ ከድንበር ድንበር ጭጭ ሲል ሜዳው ማዕበል ሲያንገላታው ቆይቶ ፀጥ ያለ ባሕር መሰለ ።

ከዚያም ፍርድ አስከባሪው የወንጀሌን ታሪክ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ባጭር ባጭሩ ተናገረ ። ከተጠቀሰው የወንጀል ታሪክ ውስጥ የሚከተሉት ነገሮች ነበሩበት ።

1ኛ ፡ የሕዝብን መንፈስ ወደ መጥፎ ነገር ይመራል ።

2ኛ ፡ ሰው ሁሉ እኩል ነው እያለ በጌታና በሎሌ ፣ በበላይና በበታች ፣ በደህና ፣ በሀብታም ፣ በዐዋቂና ፣ በመሃይም መካከል ያለውን ልዩነት በመካድ በአዛዥና በታዛዥ መካከል ያለውን ወሰን አፍርሷል ።

3ኛ ፡ ሕዝብን ሊያገኝ ከሚገባው በላይ ማግኘት ይገባሃል እያለ ድሆች በሀብታሞች ላይ እንዲነሣሱ አድርጓል ።

4ኛ ፡ አንድ መንግሥት በፈለገው ሁኔታ ሕዝቡን መግዛት ሲገባው ፣

ሀ/ የመንግሥት ባለሥልጣኖች የሕዝብ አሽከሮች ናቸው የሕዝብን ፍላጎት እየተከታተሉ ሕዝብን ማገልገል እንጂ ለነሱ ፍላጎት ሲሉ የሕዝብን ፍላጎትና ጥቅም ለመጋፋት መብት የላቸውም በማለት ፣

ለ/ በዘርም ሆነ በጉልበት በእውቀትም ሆነ በሀብት የተገኘ ታላቅነት ሁሉ የቆራጭ ፈላጭነት ሥልጣንን ከፈለገ ታላቅነቱን መካድ ያሻል በማለት ፣

ሐ/ አንድ ተራ ወታደርና ጄኔራል አንድ መንገድ ጠራጊና ዶክተር አንድ ድሀ ገበሬና ጠቅላይ አገረ ገዢ ምንም እንኳን ባሉበት ሰው ሠራሽ ደረጃ ቢለያዩ በተፈጥሮ እኩል ስለሆኑ እንዲሁም ተመሳሳይ ፍላጎትና በየመሥመራቸው ተፈላጊነት ስላላቸው አንዱ ሌላውን

በማይገባ የሚጫንበት ኃይል ሲያገኝ አይገባውም በማለት ገራሙንና ጨዋውን ሕዝብ አበላሽቷል ።

5ኛ ፡ ከመወለዱ በፊት ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ሰዎች ለሁሉ በምትበቃቸው በዚች ሰፊ ዓለም ላይ ድርሻቸውን ተከልክለው በሥቃይ ከሚኖሩ ሳይወለዱ ቢቀሩ ወይም ቶሎ ቢሞቱ ይሻላቸዋል እያለ በተስፋ እየተጽናኑ መከራውን ሳይመለከቱ በሰላም የሚገዙትን ድሆች በመንፈስ አሸፍቷቸዋል ።

6ኛ ፡ ይህ ሁሉ አልበቃው ብሎ ሰው ትክክለኛ በሆነና አድልዎ በሌለበት ሕግ ሥልጣን እንጂ እንዳህያ በዱላ መገዛት የለበትም በማለት ባስነሣው ዓድማና ረብሻ የብዙ ሕዝብ ሕይወት አስጠፍቷል ። ሰላማዊ የሆነውን አገዛዝም በጥብጧል ።

7ኛ ፡ ለብዙ ዘመን ሲሠራበት የኖረውን የእምነትና የባህል ወግ በመቃወም በሃይማኖት የማይመሳሰሉ ሰዎች በጋብቻም ሆነ በማንኛውም ነገር እንዲገናኙና የተከበሩትን በዓላት እንዲሻሩ በማድረግ እምነትንና ልማድን የሚያረክስ ወንጀል ሠርቷል ።

በዚህ ሁሉ ወንጀል ምክንያት በመንግሥቱና በሀገሩ ላይ የደረሰው ጉዳት እጅግ ከባድ በመሆኑ ለዚህ ተመሳሳይ ለሌለው ወንጀል ምንም እንኳን ሌላ ሕግ ሊፈጠር ባይቻል በመጨረሻው ከፍተኛ ወንጀል የሚታዘዘው ቅጣት እንዲፈጸምበት ፍርድ ቤቱን እጠይቃለሁ ። »

ይህና የቀረውም አስገራሚ ወንጀል በሕግ አስከባሪው አንደበት ሲነገር እውነትንና ሐሰትን ለይተው ያወቁት « ይህ ታዲያ መልካም ትምህርት ነው እንጂ ምን ወንጀል ነው? » እያሉ ርስ በራሳቸው ሲያጉረመርሙ እንዲያው በጨለማ እምነት የሚመሩት ክፉ ነው ሲሉዋቸው ክፉ ነው ደግ ነው ሲሏቸው ደግ ነው ፣ የሚሉ የተሸለመው ሁሉ ባለሙያ የታሠረው ሁሉ ወንጀለኛ የሚመስላቸው የዋሆቹ ወገኖቼ ግን ወየው ጉድ ለካ ይህን ያህል ወንጀለኛ ኑሯልና! ወየው ጉድ ሁኔታውን ሲያዩት ደግ ይመስላል እያሉ ይጠቃቀሱብኝ ነበር ።

ከዚህ ቤላ የዳኞች ሰብሳቢ የሆነው ማርሻል ወደኔ እየተመለከተ « ታዲያ አንተስ የተከሰስህበትን ወንጀል መሥራትህን ታምናለህ ትክዳለህ? » ሲል ጠየቀኝ ፡፡

እኔም « የሠራሁትን ሁሉ አልክድም ፡፡ በቀረበብኝ ክስ ከተዘረዘሩት ነገሮች መካከል ሥራዎቼን ወንጀል ለማስመሰል እየተጠጉ ከተነገሩት ትችቶች በቀር ሁሉንም ሠርቻለሁ ፡፡ ይህን እንጂ ወንጀል ከምትሏቸው ይልቅ ትምህርት ብትሏቸው ተገቢ ስማቸው ነው ፡፡ » አልሁት ፡፡

« ለመሆኑ ጠበቃው ለምን አያቀርብም? » ሲል ከሲቪሎቹ ዳኞች አንዱ ወደማርሻሉ ዳኛ ዘወር ብሎ ጠየቀ ፡፡

እኔን ከመጠየቃቸው በፊት « ጠበቃ አልፈልግም » አልሁ ፡፡ ንግግሬንም በመቀጠል « አይገኝም እንጂ የምፈልግስ እውነተኛ ዳኛ ነበር ፡፡ እውነትን ተከትሎ የሚፈርድ ኃይልና የመኖር ፍላጐት ነፍሱንና አካሉን አሥረው ነፃነቱን ያልገፈፉት ፣ በፍርሃትና በአድርባይነት ወህኒ ቤት ያልገባ እውነተኛ ዳኛ ባገኝ በጥብቅናዬ ችሎታ ላንዲቷ ቅንጣት ለኔ ሕይወት ቀርቶ በዓለም ላሉ የተገፉ ሰዎች ሁሉ ተሟግቼ በረታሁላቸው ነበር ፡፡ ነገር ግን ዳኛ የለም ፡፡ ዳኛም ከሌለ የጠበቃ መኖርም ሆነ አለመኖር የሚያመጣው ለውጥ የለም ፡፡ » ስለዚህም ጠበቃ አልሻም » አልሁ ፡፡

« እሺ! » አለ ማርሻሉ ወደኔ እየተመለከተና ከወንበሩ ላይ እየተስማማ ፡፡ ቀጠል አድርጎ « ለመሆኑ ወንጀለኛነትህን ታምናለህ አታምንም? » ሲል ጠየቀኝ ፡፡ እኔም ከዚህ የሚከተለውን ረጅም መልስ ሰጠሁ ፡፡

የተከበራችሁ ዳኞችና ተመልካቾች ፡፡

« ለጥቂት ጊዜ ታግሣችሁ እንድታዳምጡኝ እለምናቼለሁ ፡፡

እናንተ የከሰሳችሁኝ ለምን እንደሆነ ስለማውቅ በጥያቄና መልስ ጊዜ ከምናጠፋ ተሰብስቦ የሚመለከተንን ሕዝብም በፀሐይና ቁሞ በመዋል ከምናደክም የክሴን መልስ ባጭሩ ልንገራችሁ ፡፡ እኔ በምንም መንገድ ወንጀለኛ አይደለሁም ፡፡ ይህንም የምነግራችሁ ወንጀልንና ወንጀል ያልሆነ ነገርን ለይታችሁ እንድታውቁ ነው እንጂ እኔን ወንጀለኛ አይደለም ብላችሁ እንድትምሩኝ አይደለም ፡፡

የጎሊናችን ሕግም ሆነ የሃይማኖት ሕግ የማኅበራዊ ኑሮ ሕግም ሆነ የሕግ ሰዎች የመሠረቱት ሕግ እንደሚያስረዳን « ወንጀል » የሚባለው ነገር ሰዎችን በመጉዳት ጥቅማቸውን በመቀማት መብታቸውን በመግፈፍ እነሱን በመጥላት የሚፈጠር ነው ።

መግደል ፣ መቀማት ፣ መሰልን አለመውደድና ሌሎችም ብዙ ጐጂ ነገሮችን « ወንጀል » ተብለው ያልተጠቀሱበት ሕግ ይኖር ይሆን? ያለ አይመስለኝም ። እንግዲህ እኔ የነዚህ ወንጀሎች ተቃዋሚ እንጂ ሠሪና አድራጊ አይደለሁም ። ክብራን ሆይ! በዚህ መሠረትማ ለቅሚያ ለመግደል ፣ ለድንቁርናና ፣ ለችግር ጠበቃ ሁናችሁ የምትከራከሩትና እነዚህ ነገሮች በሰው ዘር ላይ ሰፍረው እንዲኖሩ የምትወዱት እናንተ ወንጀለኞች ሁናችሁ የነዚህ ነገሮች ተቃዋሚ የሆንሁት እኔ እውነተኛ ዳኛ ነኝ ማለት ነው ።

ምናልባት ከዚህ ተሰብስቦ ከሚሰማንና ከሚመለከተን ሕዝብ መካከል በናንተ ምክንያት የተሠቃየ ብዙ ሰው ይኖራል ። ይህ ቦታ ለእውነተኞች አደገኛ ባይሆን ኑሮ እዚህ እየቀረቡም ይመሰክሩባችሁ ነበር። ነገር ግን እውነትን በመናገርና በመሥራት የኖርሁት ሰው የደረሰብኝን መጉላላት በዓይናቸው ስላዩ ወንጀላችሁን ሊመሰክሩባችሁ አይችሉም ።

እኔ ግን ምናልባት በችግ ጊዜ የተረዳሁት ከድንቁርና ነፃ እንዲሆን ያስተማርሁት ፍቅርንና ርኅራኄን በሓሳብና በሥራ ያሳየሁት ወዳጅ ይኖረኝ እንደሆነ እንጂ ግፍ የሠራሁበትና የጨከንሁበት ጠላት እንደሌለኝ ከሕሊናዬና በቅርብ ከሚያውቁኝ ሰዎች የበለጠ ምስክር አልሻም ። የናንተም ቢሆን አፋችሁ እንጂ ኅሊናችሁ አይቃወመኝም ። መልካም! እንግዲህ ችግሩ እዚህ ላይ ነው ። ወንጀለኛ እናንተም ሆናችሁ ወይም እኔ በናንተና በኔ መካከል ታላቅና አስታራቂ የሌለው ልዩነት አለ ።

በእውነቱ በኔ እምነት ነገሩን ስመለከተው በጣም ያስገርመኛል ። ወንጀለኞች እናንተ መሆናችሁን ሥራችሁ እየመሰከረ ሰላማዊውን ሰው ወንጀለኛ ብላችሁ አሥራችሁ ትጠይቁኛላችሁ ። አሁን የምንሟገተው ለሕግ ወይም በሕግ አይደለም ። እናንተ የምትሟገቱት ለወንጀላችሁ መልካም አኗኗር ሲሆን እኔ ደግሞ ለሰዎች መልካም አኗኗር ነው ። ወንጀሎች ካልጠፉ ሰዎች በደኅና ሊኖሩ አይችሉም ። ወንጀልን የሚቃወሙት ሰዎች ካልጠፉም ወንጀሎች የክብር ቦታቸውን እንደያዙ ሊኖሩ አይችሉም ። የምትሟገቱ

ወንጀሎቻችሁ እንዳይነኩባችሁ ከሆነ እነሱን ለማጥፋት የምሞክረው ሰው በናንተ በወንጀል አምባዎቹ ፊት ወንጀለኛ ነኝ ። የምትከራከሩት ለእውነተኛ ነገር ቢሆን ኑሮ ግን ተስማምተን መልካም ነገሮችን ከመሥራት አልፈን እንደዚህ ባለው የድራማ መድረክ ላይ ከመታየት ባልደረስን ነበር ።

ድሮም ቢሆን የኃይልን አገዛዝ የምቃወመው ሕግንና ነፃነትን እንዳያጠፉቸው በማለት ነው እንጂ ራሱን መምራትና መግዛት የማይችልን ፍጡር እንደሕፃን ልጅ እየቆነጠጠ መልካም ትምህርት የሚያስገኝ በሆነበት ጊዜስ እኔም የኃይል አገዛዝ ደጋፊ ነኝ ። ነገር ግን በኃይል ሲገዙና ሲፈሩ ለመኖር ማደንቆርና ማስቸገር በፍጹም እቃወማለሁ ። ይህን ወንጀል ነው ካላችሁም ያሻችሁን ሥሩ ። ሞትም ብትፈርዱብኝ ራሴን ሌቦችና ወንበዴዎች አድፍጠው ከገደሏቸው ወገኖቼ እንዳንዱ ከመቊጠር በቀር በወንጀለኛነት እንደተቀጣሁ አልቈጥረውም ።

## ክቡራን!

ሕጉ ሁሉ የተዘጋጀው የናንተን የአውሬነት ጥቅም ለመጠበቅ ብቻ ነው? ሕግ የምትሉት የናንተን የግል ደስታ የሚቃወሙትንና ለእውነተኛ ነገር የሚከራከሩትን ሰዎች የምታጠፉበትን የተንኰል ዓቅድ ነው? ሕግ የምትሉት ድሆችንና ጠበቆቻቸውን አሳዶ ለማጥቃት ታላላቆችን ሌቦችና ነፍሰ ገዳዮች በክብር ለመጠበቅ ያረቀቃችሁትን ማጭበርበሪያ ነው? በዚህ ዓይነቱ ሕጋችሁ እርግጥ ወንጀለኛ ነኝ ።

በእውነተኛው ሕግ ፊት ግን እናንተ ወንጀለኞች እኔ ሕግ አስከባሪ ነኝ ። » ብዬ ስናገር ሁለተኛው ሲቪል ዳኛ « በቃ! ሐተታ አታብዛብን ። የተከሰስህበትን ወንጀል ፈጽመኻል አልፈጸምህም? ለዚህ አዎን ወይም የለም የሚል መልስ ስጠን » አለኝ ቆጣ ብሎ ።

« እኔ ደግሞ ሠራሁም አልሠራሁም ለማለቴ ዋጋ አልሰጠውም ። የቀረበብኝ ክስ በማስቀጣት ፈንታ እናንተም እንድትከተሉት የሚያስፈልግ ጠቃሚ ትምህርት ነው ብዬ ነው የምነግራችሁ » አልሁት።

መልካም ትምህርት ነው የምትለው የቱን የቱን ነው? » ኢል ለዳኝነት የተመረጠው ማርሻል ጠየቀኝ ።

« የኔ የሕይወቴ መመሪያ አላማዎች የሚከተሉት ናቸው ።

1ኛ ፡ ሰዎች ሁሉ በዚህ ዓለም እስካሉ ድረስ ከመከራ ፣ ከችግርና ከድንቁርና በተቻለ መጠን ነፃ እንዲሆኑ ማስተማር ፣

2ኛ ፡ ሌሎችን ሳይበድሉ ራሳቸውም ነፃ ሁነው እንዲኖሩ ማሳወቅ ፣

3ኛ ፡ እያንዳንዱ ሰው ሲቻለው የሌሎችን ችግርና መከራ ለማቃለል እንዲሞክር በይቻለው ደግሞ የራሱ የሆነውን መልካም አኗኗር እንዲጠብቅ እንጂ ሌሎችን እንዳይጐዳ መከላከል ፣

4ኛ ፡ ሰዎች ሁሉ ኑሯቸውን በማሻሻል ከሰላማዊና ንጹሕ ኑሮ እንዲደርሱ በተቻለ መጠን በትምህርትና በሥራ መገፋፋት ለነዚህም አርአያ ሁኖ መገኘት ፣

እነዚህ ሥራዎቼ ወንጀሎች ናቸው? በፍጹም አይደሉም » አልሁ ።

« ታዲያ ለዚህማ አዲሱ አስተዳደር ማሰቡን አታውቅም? » ሲል ሲቪሉ ዳኛ ጠየቀኝ ።

« እኔ ስለዚህ ጉዳይ ብዙ የማውቅ ይመስለኛል ። እኔ በስም አላምንም ። ንጉሣዊ አገዛዝ ( ሞናርኪ ) በምክር በት ሥልጣን ሥር ያለ ንጉሣዊ አገዛዝ (ኮንስ+ቱሽናል ሞናርኪ ) በብዙ ሀብታሞች ሥልጣን የሚመራ አገዛዝ (አሪስቶክራሲ) በወታደራዊ ኃይል ብቻ የሚመራ አገዛዝ ( ሚሊተሪ ዲክቴተርሽፕ )ሕዝብ ሊሾማቸውና ሊሽራቸው በሚችል መሪዎች የሚመራ አገዛዝ (ዲሞክራሲ) እንዲሁም ሌሎችን ብትሏቸው ሁሎችም ለሕዝብ ከተስማሙና መልካም ከሠሩ መልካም ናቸው ። ሕዝብን ከበደሉ ግን ሁሉም መጥፎ ናቸው ። እኔም የምደግፈው ስሙን ብቻ በማምለክ ሳይሆን ለሕዝብ የሚሰጠውን ጥቅም በማየት ብቻ ነው ።

በፓርላሜንት ሥልጣን ሥር ባለ ንጉሣዊ መንግሥት ሥር ነፃነታቸው መብታቸውና ጥቅማቸው ተጠብቆ የሚኖሩ ሕዝቦች በብሪታንያ ፣ በስዊድን ፣ በኖር«ይ ፣ በዴንማርክና በሌሎችም አገሮች ይገኛሉ ። ስሙ የሕዝብ መንግሥት (ሬፑብሊክ ) በሚባል መንግሥት ሥር ተጨቁነው ታፍነው

መብታቸውንና ጥቅማቸውን ተገፈው የሚኖሩ ሕዝቦች በብዙ አገሮች ይገኛሉ ።

ስለዚህ ለሕዝብ የሚስማማ ካልሆነ « የሕዝብ መንግሥት » (ሪፑብሊክ) ብላችሁ ያቋቋማችሁትን ጨቋኝ ድርጅት አልደግፍም ።

ለሕዝብ መልካም የሚሠሩ ከሆነ በነገሥታትም ቢሆን በሌሎች ዓይነት መሪዎች « ያለምክንያት የተፈጠረ የስሜት ጥላቻ » (ፕሪጁዲስ) የለብኝም ። ሕዝብን በነጻነትና በርኅራኄ በቅን መንገድ የሚመራ ከሆነ ለጨካኞችና ለግፈኞች ሁሉ ምሳሌ ሁኖ ሲጠራ የኖረው የሮማው ንጉሠ ነገሥት ኔሮን ቄሳር እንኳ ከሞት ተመልሶ ቢነግሥና ለሕዝብ መልካም ቢሠራ በሙሉ መንፈሴ እንደምደግፈው እርግጠኛ ነኝ ።

እንዲሁም ይመራቸው ለነበረ ያገሩ ሕዝቦች ርኅሩኅና ቸር በመሆን ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ሕንዳዊው ማኅአተማ ጋንዲ ከመቃብሩ ተነሥቶ ድሮ ያልታየበትን ቆራጭ ፈላጭነት ቢፈልግ በሙሉ መንፈሴ እቃወመዋለሁ ።

ስለዚህ « የሕዝብ መንግሥት » የሚል የመሸንገያ ስም ሰጥቻችሁ ከማንም በበለጠ ሕዝብን የምትጨቁኑበትን መንግሥት በፍጹም እቃወመዋለሁ ። በዚህ ምክንያትም ልትገድሉኝ ትችላላችሁ ። ሞት ስትፈርዱብኝም የምፀፀት ይመስላቼል ። እኔ በዚህ ብፀፀት እንደናንተ ቂል ነኝ ። መጥፎ ሥራችሁንና ሕዝብን መጨቆናችሁን የምትተው ካልሆነ መቶ ጊዜ እየሞትሁ እንደገና ብወለድ መቶ ጊዜ የገደላችሁኝ መሆናችሁንም ባስታውስ ይህ መቀጣጫ ሁኖኝ ዝም ልላችሁ አልችልም ።

እኔ ዓለምን የማያት እናንተ በምታዩበት ዓይን አይደለም ። እናንተ እንደምታዩዋት ዓለም ጠባብ ናት ። ግማሹ ካልተሠቃየባት ግማሹ ሊደሰትባት የሚችል አይመስላችሁም ። ግማሹ ባሪያ ካልሆነ ግማሹ ጌታ የሚሆን አይመስላችሁም ። ስለዚህም ራሳችሁን ጌታ ለማድረግ ወንድሞቻችሁን ባሪያና ደንቆሮ ማድረግ ፈለጋችሁ ።

እኔ ግን ዓለምን የማያት እንደናንተ አይደለም ብያለሁ ። ዓለም በኔ ዓይን ውብና ሰፊ ናት ። ድንቁርናን ጭካኔን መመቀኛነትን ራስን ብቻ መውደድን አስወግደን ተባብረንና ተፋቅረን ብንሠራ ከመካከላችን ባሪያና ደንቆሮ ሳይኖር ሁላችንም በጌትነት እንኖራለን ። ለቅሶና ኀዘንን እየተመለከቱ ባንድ ጆሮ

ዘፈንን ባንድ ጆሮ ለቅሶን እየሰሙ በአንድ ዓይን መከራን በአንድ ዓይን ደስታን እያዩ ከመኖር በተቻለ መጠን ክፉ ነገሮችን ሁሉ አስወግዶ የጋራ ደስታን መፍጠር አይሻልም? ምነው ልብ ሲታይ እምነቱንና ምሥጢሩን ገልጾ የሚያሳይ በሆነና ልቤን ገልጨ ባሳዬቻው ። በንጹሕ ኅሊናዬ የሚታየውን ቅን መንገድ ዓይታችሁ ሐሳባችሁን ትለውጡ ነበር ። ወይም መልካም ነገር ከሞላበትና ያለአድልዎ ከተሰጠ ንፁሕ ዓየር ጋር ተዋሕዶ በመላ ሰውነታችሁ የሚዘዋወረው ደም ኅሊናችሁን ባደነደነው ሞራ ሳይመረዝ ምነው ወደ አንጎላችሁ በደረሰ! ዳሩ ይህ ሁሉ አይሆንም ። እናንተ ልታዩት የምትችሉት በሽፍጥና በሥጋት የተሸፈነ የዛሬ ጥቅማችሁን ብቻ ነው ። ለሌላው ወገናችሁ እንኳ ቢቀር ከአካላችሁ ተከፍለው ለወጡ ልጆቻችሁ አታስቡም? ምንስ ለሰዎች የማሰብ ባሕርይ ባይኖራችሁ በዚያው በጠባቡ አስተያየታችሁ ለግል ልጆቻችሁ አታስቡም? ለነሱ ማሰባችሁ ግልጽ ነው ። ወደመቃብር ይዛችሁት ልትወርዱ ወይም ወደሰማይ ይዛችሁት ልትወጡ የማትችሉትን ወይም በሕይወታችሁ ዘመን ተጠቅማችሁበት ለመጨረስ የማትችሉትን ሀብት ሌሎችን እያስራባችሁና እያስቸገራችሁ የምትሰበስቡት ለግል ልጆቻችሁና ለስስታችሁ ስትሉ እንጂ በልተን እንጨርሰዋለን ብላችሁ እንዳልሆነ የታወቀ ነው ። ከአምሳና ስድሳ ዓመታት በላይ የሆነ ዕድሜ ያላችሁ ለጊዜው መኖሪያም ካስፈላጊው በላይ ሀብት ያላችሁ ሰዎች በብዙ ሚሊዮን የሚቈጠር ገንዘብ በልተንና አጊጠን እንጨርሳለን ብላችሁ የምታስቡ ከሆናችሁስ በእርግጥ ሰው መባል ይቅርና እንስሳና አውሬ ለመባል እንኳ አይገባችሁም ። እንዲያው ልዩ አውሬዎች ናችሁ ።

የምትቀሙት ለልጆቻችሁ ከሆነም በዚህም ደንቁራቼል ። ለልጆቻችሁ በእውነት የምታስቡ ከሆነ የቅሚያና የኃጢአት ገንዘብ ሰብስባችሁ ከሕዝብ አርቃችሁና አጣልታችሁ በብልግናና በስድነት ከምታሳድጓቸው ይልቅ ወደፊት ከወንድሞቻቸው ጋር በደኅና ሁኔታ ሊኖሩ የሚችሉበት የደግነት ቅርስ አውርሷቸው ፅኑዕ በሆነ ሰላም ካልተመሠረተች ዓለም ተለዋዋጭ መሆኗን አትዘንጉ ። የትናንት ጌቶች የዛሬ ድሆች የዛሬ ድሆች የነገ ሀብታሞች መሆናቸውን ከታሪክ ተማሩ ። እንዲሁም የዛሬ ገዳዮች የነገ ተገዳዮች ይሆናሉ ። ለድሆች ወገኖቻቸው የውሾቻቸውን ያህክ ክብር አይሰጡ የነበሩ የፈረንሳይ ባለጸጎች ደማቸው የፓሪስ መንገዶች ማጠቢያ አልሆነም? ይናቁ የነበሩትና « ሬፑብሊካን » በሚል ስም የተነሡት ድሆችስ ማንንም ሳይመርጡ

ሀብታምነትን ብቻ ወንጀል አድርገው ብዙ ሕዝብ አልፈጁም? ይህስ ነገር በብዙ አገሮች አልደረሰም? አውጣኝ ጌታዬ! ይህ ነገር ባገሬ ላይ እንዲደርስ አልመኝም። እኔ የምመኘው ዛሬ አርጂ ነገ ልታረድ ዛሬ ቀምቼ ነገ ልቀማ የሚለው የልበደንዳናነት እምነት ተወግዶ እንዲሁም ዛሬ እንደተጠቃሁ ነገ ማጥቃት አለብኝ የሚለው የተጠቁት ሰዎች የመበቀል ስሜት ተወግዶ ታላቅ እርቅና ሰላም ወርዶ የነገዋ ዓላማችን ለሁሉም መልካምና ሰላማዊ ኑሮ እንድትሰጥ ነው ።

የሰው መከራና ችግር የሚያሳዝነው የቸርነትና የፍቅር አምላክም በዚች ውብ አድርጎ በፈጠራት ዓለም የሚወዳቸው ፍጡሮቹ በደስታና በፍቅር ለመኖር ችለው ሲያመሰግኑት አይቶ ይደሰት ።

ክቡራን! የኔ ምኞትና ሓሳብ ሁሉ በዚህ እምነት ላይ የተመሠረተ ነው ። የምደክመውም የማስተምረውም ለዚህ ግብ እንጂ ከሰዎች መካከል ማንኛውም ወገን እንዲጎዳ አይደለም ። የወንድሞቻችሁን ጥቅም እንደራሳችሁ ጉዳት አድርጋችሁ ትቈጥሩታላችሁ? እነሱ በተጠቀሙ እናንተ ምን ትጐዳላችሁ? ባሮች እናጣለን ብላችሁ ነው? ግዴለም በዚህ አትስጉ ዘመናዊው የግዙፍ ጥበብ ዕድገት ያስገኛቸው ልዩ ልዩ መሣሪያዎች የብዙ ባሮችን ጉልበት የሚፈልጉ አይደሉም ። አንድ ዘመናዊ የርሻ መሣሪያ ከብዙ መቶ ገባሮች የበለጠ ያገለግላል ። ይህን ለምሳሌ ጠቀስሁት እንጂ ማንኛውም ሥራ በዘመናዊ ዘዴ እየተፋጠነና የሚፈለገው ብዙ ድካም በጣም እየተቀነሰ ሂዷል ። ከዘመናዊው እድገት የሚገኘው ፍሬም ሰላምና መተዛዘን ካለ ለሁሉም በቅቶ የሚተርፍ ነው ።

ነገር ግን ብዙ ጥቅምን ምቾትንና ደስታን ለማግኘት በግዙፍ ሥልጣኔ የምንራመደውን ያህል ወይም ከዚህ በበለጠ በመንፈስ ሥልጣኔ ተራምደን የምናገኘውን ነገር ሁሉ በፍቅርና በሰላም ተካፍለን ካልተጠቀምንበት ችግርና ጭቅጭቅ ሁልጊዜ ከኛ ጋር ይኖራሉ ።

የኔና እኔን የመሳሰሉት ሰዎች ጥረትም የፍቅርና የሰላም ጠንቆች የሆኑት አሮጌዎቹ የቅሚያና የብልጠት ልምዶች ከመሰሎቻቸው ጋር ተወግደው እውነተኛው ቅዱስና ሰላማዊ ኑሮ እንዲመሠረት ነው ። አእምሯችሁ ጮርቃ ነው ። « ፍቅር » በምላችሁ ጊዜ አዝማሪዎችና አንዳንድ ግጥም ጸሓፊዎች

እየደጋገሙ የሚያሰሙንን አመንዝራ መንፈሳችንን የሚያረካልንን የሴትና የወንድ ፍቅር ማለቴ አይደለም። እኔ የምነግራችሁ የሰዎችን ተዘምዶና መተዛዘን ገልጾ የሚያሳየውን ፍርሃትና ፣ ጥርጥርን ፣ መጋደልን ፣ ስስትን ፣ ንፍገትን ፣ ተንኰልንና ፣ ምቀኝነትን ፣ ደምስሶ ሰላምን በግዙፍ አካል ሊያመጣት የሚችለውን ረቂቅ ፍቅር ነው ።

እኔ የምሞትለቱ ፍቅር ዓለምን በብልግናና በስድነት ለመሙላትና ግብረ ገብነትን ከሰዎች ኅሊና ለመፋቅ ሰብአዊ ክብርን በገንዘብ የሸጡት የሆሊውድ አክተሮች የሚገልጹት ርኩስ ፍቅር አይደለም ። ርኅራኄን ፣ ፀጥታን ፣ ጨዋነትን ፣ ለሚያስተምረው ብዙ ቅዱሶች ለተሠውለት ሰው ከእንስሶች የተለየ ፍጡር መሆኑን ለሚመሰክረው ቅዱስ ፍቅር ግን ለሴት ፣ ለወንድ ፣ ለትንሽ ፣ ለትልቅ ሳልል እሞታለሁ አሁን ዳኞችንም ተመልካቾችንም አዳከሜችሁ መሰል ። እምነቴን በቀላሉ ለማስረዳት እንደማልችል ሳውቀው በከንቱ አላድክማችሁ ። ቢሆንም እንግዲህ ወደፊት ብዙ የማደክማችሁ አይመስለኝም ።

ፍቅር ሰላም እንዲኖር ከፈለጋችሁ እኔንም ሆነ ሌሎችን የኔ መሰሎች ልታስወግዱ ትችላላችሁ ። ግን ምርጫችሁ ለናንተም ሆነ ለሌሎች ደግ አይመስለኝም ። ክፉ ሥራዎች ካልጠፉ በክፉ ሥራዎች ኀሊናቸው የቆሰለ ሁሉ አንዱን ስታጠፉ ሌላው እየተተካ ሰላም ይነሣቹል ። ሲብስም ሁልጊዜ አጥፊ መሆናችሁ ቀርቶ አንድ ቀን ትጠፋላችሁ ። ከዚህ ሁሉ ለጋራ ሰላምና ደስታ የግል ፍላጎትን መሥዋዕት ማድረግ አይሻልም? » ይህን ከተናገርሁ ቤላ ፍርዱ በሌላ ቀን ሊሰጥ ቀጠሮ ሆነ ። እኔም በመጣሁበት ሁኔታ ወደወህኒ ቤት ተመለስሁ ። ሁሉም ወደቤቱ ተመለሰ ።

# 15

## ስለ ሁለተኛው ቀን ችሎት

በቀጠሮው ቀን ከጧቱ በአራት ሰዓት ከአጃቢዎቼ የወህኒ ዘበኞች ጋር ለፍርድ ቤትነት ወደተመረጠልኝ የጨዋታ ሜዳ ስደርስ ሕዝቡ ከቀደምለቱ

በጣም በሚበዛ መጠን ተሰብስቦ ነበር ። ዳኞችም እንደተለመደው ተቀምጠው ነበር ። ሕግ አስከባሪው ወደማይክሮፎኑ ቀረብ ብሎ « ዳኞች ሰሞኑን ጉዳዩን ሲመረምሩት ሰንብተው አሁን የመጨረሻውን ፍርድ ሊሰጡ ነውና ፀጥ ብላችሁ እንድታዳምጡ ፍርድ ቤቱ ያዝዛቼል » ሲል አስታወቀ ። ሕዝቡም ፀጥ አለ ። በሕዝቡ በጣም መብዛት የዛሬው ሁኔታ ከመለየቱ በቀር ማንኛውም ሁኔታ እንደቀደም ለቱ ነበር ።

ሕዝቡ ፀጥ ብሎ ማዳመጥ ከጀመረ ቤላ ማርሻሉ ዳኛ ከፊቱ ያለውን ፋይሌን አነሣና የንባብ መነጽሩን በዓይኑ ላይ አድርጎ ባጭሩ ያገላገለውን ንባብ ጀመረ ። የተነበበው አጭር ቃልም የሚከተለው ነበር « ተከሳሹ ሕዝብንና መንግሥትን የሚበድሉ ከፍተኛ ወንጀሎች ሠርቶ ከተከሰሰ ቤላ ምሥክርም ሆነ ሌላ መረጃ ከመፈለጉ በፊት የተከሰሰበትን ወንጀል ሁሉ በሙሉ ስላመነ በወንጀሉ ከፍተኛነት መጠን ፍርድ ቤቱ በሞት ሊቀጣው ሲገባ ርኅራኄ በማድረግ በ!4 ሰዓቶች ውስጥ ከኢይዝራኤሎስ ግዛት እንዲወጣና የሀገሪቱ ተወላጅነት መብቱም እንዲገፈፍ ተፈርዷል ። ለዚህ ፍርድ ማሻሻያ አቤቱታ አቀርባለሁ የሚል ቢሆን ፍርድ ቤቱ በተለመደ ርኅራኄው ማመልከቻውን ተቀብሎ ጉዳዩን እንደገና ይመረምርለታል » ብሎ ሲጨርስ ከዳኞች መካከል ሕግ አዋቂ ነኝ ብሎ የሚመካው ወጣት ቢጤው ሲቪል ዳኛ « ክቡር ማርሻል ሕግኮ መሠረቱን እንጂ አስተያየቱን መከተል የለበትም በሕግ የተከሰሰ ሰው በሕግ መቀጣት አለበት ። ሕግ እንደተማርነው ከሆነ ቊጥር ፣ አንቀጹና ንዑስ አንቀጹ ታይቶ ለወንጀሉ ተመሳሳይ የሆነው ቅጣት ይወሰናል ። ይህ ሰው አስተያየት ሊደረግለት የማይገባ ታላቅ ወንጀለኛ ሲሆን ለርሱ አስተያየት ማድረጋችን ራሱ ወንጀልና ሕግን መቃወም ነው ። » ሲል የሕግ አዋቂ መሆኑን ለመግለጽ በሚሞክር ስሜት ተናገረ ። በዚህ ጊዜ ተናደድሁና « አንተ የዋህ » አልሁት ። ቀጠል አድርጌ « ለመሆኑ ሕግ ለምን እንደተሠራ ማንስ እንደሠራው ታውቃለህ? ሕግ መጥፎ ሥራዎች የሰውን ፀጥታና ሰላም እንዳያበላሹ ከባሕርያችን ያገኘነው ረቂቅ መከላከያ ነው ። የሕግ ስሜት ቢኖርህ ኑሮ የክፉ ሥራዎች መከላከያ የሆነውን የሕግ ወሰን ጥሰህ ንጹሕ ሰዎችን ከሚገድሉ ወንበዴዎች ጋር ባልተደባለቅህ ነበር ። አንተ ግብዝ! በቀደምለት አዲሱ ሬፑብሊካችሁ የተመሠረተበትን ዓመታዊ በዓል ስታከብሩ ። ለብዙ ሌቦችና ነፍሰ ገዳዮች ምሕረት ስታደርጉ ከፖለ+ካ እሥረኞቻችሁ

ውስጥ አንዱን እንኳ ሳትጠይቁት አልቀራችሁም? » ስል ማርሻሉ ዳኛ ተቀበለና « መቼም ፍርዱ አንዴ ተሰጥቷል » ሲል ተናገረ ።

እኔም መለስሁና የሚከተለውን ተናገርሁ ። « አገርህን ለቀህ ውጣ የምትሉት ፍርድ መቸም የማይታለም ነው ። እግዚአብሔር እንድወለድ ያደረገኝ በዚች አገር ነው ። ከተወለድሁ እስከ ዛሬ የኖርሁትም በዚችው እግዚአብሔር በሰጠኝ አገሬ ነው ። በመላው ዓለም ያሉ መልካም ሰዎችን ሁሉ ብወድም እንደ ሀገሬ ሰዎች የመልኬ ቅርጽና ቀለም ልማዴና ሁኔታዬ እንደሚመስላቸው ወገኖቼ ላያቸው አልችልም ። እግዚአብሔር የፈጠረው ዓየርና ፀሐይ አንድ ቢሆንም ከሀገሬ ተፈጥሮ ጋር እንደለመድሁት ሁኖ በሌሎች አገር ስለማላገኘው በሰው አገር ሁኜ አልሠቃይም ። እዚሁ እንዳለሁ ያሻችሁን ፍርድ ፈጽሙብኝ ። በናንተ አስተያየት አገርን ለቆ መኖር ከሞት የሚሻል መስሏችሁ የሞቱን ፍርድ ካገር ወደመውጣት በመለወጣችሁ ስለመልካም ምኞታችሁና ስለርኅራኄያችሁ አመሰግናቼለሁ። ነገር ግን በኔ አስተያየት ካገር ወጥቶ በብዙ ነገር ከማይመሳሰል ሕዝብ ጋር መኖር የሞት ሞት እንጂ ኑሮ ስላልሆነ አገሬን አጥቼ ከመኖር ሞቴን እመርጣለሁ ። ከሞት ይልቅ ስደትን የምመርጥ ከሆነስ ለእውነተኛ ነገር ሳይሆን ለራሴ ብቻ እታገል ነበር ማለት ነው ።

በሰው አገር ሁኜ አገሬን ፣ ወገኔን ፣ ሌላውንም ያገሬ የሆነውን ነገር ሁሉ በትዝታና በሰቀቀን እያስታወስሁ ከመኖር ብዙ ጊዜ መሞትን እመርጣለሁ ።

ምናልባት በሌላ አገር ሁኜ አገሬን ባስታውሳት ወዳጆቼና መልካሞች ነገሮች ብቻ ሳይሆኑ እናንተና ክፋታችሁ ጭምር በናፍቆት እንደምትታሰቡኝ እርግጠኛ ነኝ ። ለጥቂት ጊዜ ወደውጭ አገር ሂጄ ብቆይ ያደረብኝን ናፍቆትና ትዝታ እኔ ነኝ የማውቀው በዚያ ጊዜ ያደረብኝን ስሜት የገለጽኩባቸውን ግጥሞች ባጭሩ ብገልጽላችሁ ፍላጎቴን ትረዱልኝ ይሆናል ።

« ወንዱም ሆነ ሴቱ አሮጌው ሕጻኑ ፣

« ባለጌው ትሑቱ ተንኮለኛው ቅኑ ፣

« ሰነፉ ትጉሁ ሊቁ መሃይምኑ ፣

« ዓየሩ ፀሐዩ ጨለማና ቀኑ ፣

« ደጋውና ቆላው ሜዳውና ደኑ ።

« ፍቅሩና ጥላቻው ልቅሶው ዘፈኑ ፣

« ሁሉን ሲያስታውሱት ሁነው በባዕድ ቦታ ፣

« መልካሙ ይቅርና ክፉው ይናፍቃል ይሆናል ትዝታ ፣

« ሀገሬ ሀገሬ የሀገሬ ቅርሶች እንዲሁም ወገኔ ፣

« እናንተን አጥቼ በልሜም ልኖር አልችል እንኳንስ በውኔ ፣

« እናንተን አጥቼ ከመቀመጥ ይልቅ በምቾት በተድላ ፣

« እናንተን ሳላጣ ልሠቃይ ልጉላላ ፣

« ወይም ጭራሽ ልሙት አፈር መሬት ልብላ ። » የኔ ስሜት ይህ ነው ፣ ይህን ስሜቴን ከተቃወማችሁና ካገሬ ልታስወጡኝ ከፈለጋችሁ ግን እናንተ የምትችሉትን አድርጉ በጦር ወይም በንግድ አኤሮፕላናችሁ ወስዳችሁ ከሀገራችን ውጭ በሆነ ዓየር ላይ አምዘግዝጋችሁ ጣሉኝ። ወይም በመርከባችሁ ወስዳችሁ በውቅያኖስ ላይ ጣሉኝ ። ለኔ ግን ይህን ሁሉ ከምታሠቃዩኝ በቀላሉ ብትገድሉኝ ይሻለኛል ። የምትፈልጉት እኔ እንዳልኖር ከሆነ ሳታሠቃዩኝ ልታስወግዱኝ እንደምትችሉ አታውቁም? ለዚህ እንኳ የሚሆን ዕውቀት ቸገራችሁ? ይህ ከተሳናችሁ ይህንንም እኔው ራሴ ላስተምራችሁ ። የምትፈልጉት እኔን ማራቅ ከሆነ በመግደል እንዳልመለስባችሁ አርጋችሁ ልታርቁኝ ትችላላችሁ ። አታስዋሹኝ ውሸት አልወድም ። መከራና ሥቃይ ባታደርሱብኝ እወዳለሁ ። እንዳትገድሉኝ ግን አልለምናችሁም ። » ብዬ ስናገር የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ እጁን ጭራሮ አስመስሎ አውጥቶ ወደኔ በፍቅር እየተመለከተ ከብዛቱ የተነሣ እጅግ በሚነጉድ ድምጽ « አትሙት! አትሙት? » በማንኛውም አገር ሊያኖርህ የሚችል በሺ ሳይሆን በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ አዋጥተን እንረዳሃለን ብዙ ሁነን አንድ ሰው መርዳት ምንም አይጎዳንና ጎዴቸው ብለህ አትጨነቅ! » ሲል የኅብረት ድምጹን አሰማ ።

እኔ ግን መለስሁና « እህ!! አዬ ውድ ወንድሞቼና እኅቶቼ! አሁን የናንተን ውለታ በምን እከፍለዋለሁ? የኔ ሕይወት ብቻ ለናንተ ፍቅር ስጦታ በቂ ትሆናለች? ግን ሰው ሊያደርግ ከሚችለው በላይ አያደርግምና ላደርግላችሁ የቻልሁት የለም ። ያለችኝን ቋሚ ጥሪት ሕይወቴን ግን ለጋራ ጥቅም ሰጥቻለሁ ሺ ጊዜ የመሞት ዕድል ኑሮኝ ሺ ጊዜ ሙቼ በናንተ ላይ ያለኝን ፍቅር ገልጬ ለማሳየት ምነው ዕድል በኖረኝ!

ውድ ወንድሞቼና እኅቶቼ! እናንተ ለኔ ያሰባችሁትን ቅን መንገድ ሳይ ዕዳ ጨመራችሁብኝ ። እኔ የምወድ እናንተንና ከናንተ ጋር መኖርን እንጂ ለብቻዬ መደሰትን አይደለም ። እንደዚህስ ከሆንሁ ርጉም ልሁን ። ከናንተ ተለይቼ መኖር? በፍጹም ሥራዬ ሁሉ ለዚህ ከሆነስ የናንተና የእውነት ጠላት ነኝ ። እኔ እናንተን እንጂ ገንዘባችሁን መቼ ፈለግሁ? የኔ ከሌሎች መለየት እናንተን በመውደድ እንጂ ከናንተ ይልቅ ገንዘባችሁንማ እነዚህ ቀማኞችስ ይወዱት የለ! ገንዘባችሁን ወስደው ራሳቸው ብቻ በደስታ ለመኖርማ እነዚህ ቀማኞችስ መቼ ሰነፉ? እኔም እንደነሱ እንድሆንባችሁ ነው የምትፈልጉ? የለም በፍጹም! እኔ ሙቼ በምድር ላይ እውነትንና ወንድሞቼን የሚወድ ሰው መኖሩን ማሳየት አለብኝ ። እነዚህ ጮርቃዎች እውነት የሀገርና የወገን ፍቅር በቀልድ እንጂ በእውነት ሊገለጽ የሚቻል የማይመስላቸው ሰብአዊ ስሜትንና ፍቅርና የማያውቁ እንስሶች እውነተኛ ሰው በዓለም መኖሩን እንዲያውቁ ለማድረግ በመንገር አላስተውል ካሉ ሙቶ ማሳየት የሚያስፈልግ ነው ።

ሁሉን ነገር ለጥቅም ማግኛና ለራስ መርጃ ካልሆነ አይደረግም እያሉ የራሳቸውን ስሜት በሌሎች የሚያስጠጉ ቀማኞች ሁሉ እንዲያፍሩ ከሞት የማምለጥ ዕድሌን ንቄ ሞትን መቀበል አለብኝ ስል በፍጹም ልቤ አስረዳሁ ። ማርሻሉ ዳኛም ወደኔ እየተመለከተ « ለመሆኑ በወንጀልህ ተቀጥተህ መሞትን ታከብረዋለህ? » ሲል ጠየቀኝ ።

እኔ ግን መለስሁና « ወንጀለኛ መባሉም ሆነ ሞቱ አያስፈራኝም ። የሚያስፈራኝ ወንጀለኛ መባሉ ከሆነ የነገው ትውልድ እኔን ነጻ አድርጎ እናንተን በወንጀላችሁ እንደሚፈርድባችሁ ስለማውቅ በናንተ አፍ ወንጀለኛ መባሌን እንደጽድቅ እቈጥረዋለሁ እንጂ አላፍርበትም ። ሞትም እንደሆነ ለኔ ብቻ ሳይሆን ለናንተ መኖርን ያለልክ ለምትሹት ቀማኞች ሁሉ የተፈጠረ

በመሆኑ ለሁላችንም የማይቀር ነው ። ከናንተ መካከል ስንቶች ናቸው ላንዳንዷት ሴት ፍቅር የሞቱ? ስንቶችስ ናቸው ባላሰቡት ቀን በአደጋ የሞቱ? ስንቶችስ ናቸው የሚወዱትና ሌሎችን የሚያጠቁበት ድሎት የፈጃቸው? እውነትን ስከተልና የሰዎችን ሁሉ ጥቅም ሳስብ ከሞትሁት ከኔ ይልቅ ለነዚህ ወገኖቻችሁና በዚህ ሁኔታ የመሞት ዕድል ለሚጠባበቀው ለራሳችሁ አታዝኑም? ዛሬ ወንጀለኛ ተብዬ ነገ ነፍሴ ነጻ ከምትሆነው ሰው ይልቅ ዛሬ ሰው ገድላችሁ ከነገ ጀምራችሁ ወንጀለኞች ስትባሉ የምትኖሩት ሰዎች አታፍሩም? ቅዱስነት የግል ጥቅምን ለመጠበቅ እውነተኞችን ማጥፋት ፣ ርኩስነትም ለእውነተኛ ነገር ሲከራከሩ መሞት ከሆነ በሉ ይሁንላችሁ! ለዛሬው እናንተ ቅዱስ እኔ ርኩስ ነን የነገውን ፍርድ ግን እግዜር ያውቀዋል ። » ይህን ከተናገርሁ ቤላ ማርሻሉ ዳኛ « እንግዲህ የምትፈልገው ካገር ከመውጣት ይልቅ ሞትን ነው? » አለኝ ።

« አዎን! » አልሁት ።

« እኛ ምን ቸገረን በጥይት በመደብደብ እንድትሞት አድርገን ፍርዱን እንለውጥልኻለን » አለኝ መነጽሩን ካፍንጫው ላይ እያነሣ ። « ከሀገር የማስወጣቱን ፍርድ ካስወገዳችሁልኝና በሌላ መንገድም ካላሠቃያችሁኝ ለመግደሉ እናንተን ደስ በሚያሰኛችሁ ሁኔታ ግደሉኝ » አልሁት ፍርዱም ካገር መውጣት መሆኑ ቀርቶ ሕዝብ በተሰበሰበበት አደባባይ በጥይት እንድደበደብ ተወሰነ ።

ከዚህ ቤላ እኔም ወደእሥር ቤቴ ሕዝቡም ወደየቤቱ ተመለሰ ።

# 16

## <u>የትግሌና የሕይወት ዘመኔ ፍጻሜ ።</u>

ለሞት ዝግጁ ሁኜ የኖርሁ ሰው ባልሆንና ዘመኔን በከንቱ ባሳልፍ ኑሮ ሞቴ እኔን የሚያፀፀት ተመልካቾችን የሚያሳዝን ገዳዮቼንም የሚያስደስት በሆነ ነበር ።

ነገር ግን ተግባሬን ሁሉ ፈጽሜ ሌሎችንም አስተምሬ በመሞቴ ለፀፀቱም ለኃዘኑም ለደስታውም ቦታ የላቸውም ።

በእሥር ቤት ሁኜ የሞቴን ቀን እጠባበቅ በነበረበት ጊዜ ልዩ ልዩ መጽሐፎችን አነብ ነበር ። ካነበቤቸው መጽሐፎችም ብዙዎቹ እውነትን የሚፈልጉና ቀጥተኛ መንገድን የሚከተሉ ለሰው መልካም የሚሠሩ ሰዎች ሁሉ እንዴት ባለ አስቸጋሪ መንገድ እንደሚያልፉና ስንቱ እንደሚጠላቸው አስረዱኝ ።

በተለይም ጃን ኦፍ አርክ ስለተባለችው የፈረንሳይ ቅድስት የተጻፈ አንድ መጽሐፍ ስመለከት « ቅኝ ግዛቱን የነጠቀቸው የእንግሊዝ ንጉሥና ዘውድ ያቀዳጀችው የፈረንሳይ ንጉሥ ወደድል የመራቻቸው የፈረንሳይ ወታደሮችና ድል አድርጋ ካገሯ ያስወጣቻቸው የእንግሊዝ ወታደሮች ባንድነት ጠሏት ። አሠቃይዋት » የሚል ቃል በማግኘቴ ለእውነተኞች ሰዎች ሁሉ በዓለም ላይ ቦታና ጊዜ እንደሌላቸው አመንሁ ።

ኢየሱስ ክርስቶስን ያህል ቸር መምህር የታመሙትን ስላዳነ ለተጎዱት ርኅራኄን ለተቸገሩት ቸርነትን ፣ ፍቅርን ፣ ሰላምን ስላስተማረ በቅንዓተኞችና ምቀኞች ሤራ በመስቀል ተሠቃየ ።

እንደዚሁም ብዙ ሰዎች መልካም ስለሠሩ በራሳቸው ላይ ብዙ ችግርና መከራ እንዲሁም የሞት ቅጣት ደርሶባቸዋል ።

ሌላው ቀርቶ ከሃይማኖትና ከፖለ+ካ ጋር ያልተያያዙ የሥነ ፍጥረት ምሥጢሮችን በገለጹ ሊቆች ላይ ብዙ ሥቃይ ደርሷል ።

እንግዲህ የመልካም ሰዎች ዕድል በክፉዎች መጠቃት ነው ማለት ነው ።

መልካም! የኔም ዕድል ከመልካሞቹ ሰዎች ዕድል ጋር ከተያያዘ ሞትን በደስታ መቀበል ያለብኝ መሆኑን ተገነዘብሁ ።

ጥቂት ያሳዘነኝ ሠልጥኗል በሚባለው ጊዜም ጨለማ ይባል በነበረውም ጊዜ ሲሠራበት የኖረው ብልግና ሲሠራበት በማየቴ ነው ።

ይሁን እንጂ የተደረገብኝ ሁሉ ለሕዝብ ጥቅም ከሠሬቸው ሥራዎች ጋር የተያያዘ በመሆኑ በትዕግሥት መቀበል አለብኝ እንደኔ ያለ ሰው ከዚህ የተሻለ

ዕድል እንዲኖረው በግብዝነት የተሞላው ማኅበራዊ ኑሮ አይፈቅድለትም ብዬ አምንሁ ።

የሞቴ ቀንም የመባረኬና የሠርጌ ቀን ስለሆነ በናፍቆት መጠባበቄን ቀጠልሁ ። ካለሞት በቀር ሰላም እንደሌለኝ አውቅ ነበርና ይህን የሰላም ቀን በተስፋ ስጠባበቅ ቀኑ በቶሎ ደረሰ ።

አብረን ለጥቂት ቀን የቆየነዎችን የእሥራት ቤት ጓደኞቼን ተሰናበትሁ ። በእሥር ቤት አብረውኝ የቆዩት ነፍሰ ገዳዮችና ሌሎች ወንጀለኞች ከነሱ ይልቅ እኔ ወንጀለኛ ያልሆንሁት ሰው ቀድሜ እንድሞት በመደረጉ በጣም ተገረሙ ። እኔም ሁሉንም ተሰናብቼ ከወህኒ ቤቱ ዘበኞች ጋር ወጥቼ ወደመገደያዬ አደባባይ በመኪና ተጓዝሁ ።

መስታወቶቿ በጥቁር መጋረጃ በተሸፈኑ ጥቁር መኪና ውስጥ ሆኜ በወህኒ ዘበኞች ታጅቤ ወደመገደያዬ አደባባይ በደረስሁ ጊዜ በብዙ መቶ ሺ የሚቈጠር ሕዝብ በአደባባዩ ተሰብስቦ ይጠባበቅ ነበር።

ሕዝቡ ምንም ወንጀል የሌለብኝ ሰው መሆኔን ቢያውቅም እኔን ለማዳን የሚችልበት ሙብትና ዓቅም ስላልነበረው የሚሆነውን ሁሉ ዝም ብሎ በኃዘን ይመለከት ነበር ። ከመኪናው በወረድሁ ጊዜ እጄ በሰንሰለት እንደታሠረ ነበር ። የአምሳ አራቱ ዓመት ሽማግሌ በዕረፍትና በምቾት ሳይሆን በሥራ በመኖሬ ሰውነቴ ገና ጎረምሳ ያስመስለኝ ነበር ። ራሴም እምብዛም አልሸበተም ፊቴም አልተጨማደደም ለሐሰተኞቹ ገዳዮቼ በግፍ ገደሉት ከሚባለው ፍርድ በላይ ያለዕድሜው ቀጬት የሚያሰኝ ትዝብት ጨምሬባቸዋለሁ ።

ካለው ሁሉ ጭካኔያቸው ሓሳቤን ሳልገልጽ እንድሞት አልፈረዱብኝም ነበር ። በጥይት ከመደብደቤ በፊት የኑዛዜ ቃሌን እንድሰጥ ጠይቄ የገደላውን ሥራት ለማስፈጸም ከመጡት ባለሥልጣኖች አስፈቅጄ የሚከተለውን ንግግሬን ጀመርሁ ።

« ከመጀመሪያውም ቢሆን ሳላውቅ ተጸንሼ ሳልወድ በግድ ተወልጄ ያለሰላም ለመኖርና የናንተንም ሰላም ለማጥፋት አልፈለግሁም ነበር ። ከተወለድሁ ቤላ ግን ለዓለም ያለኝን መልካም አስተያየት ሳልገልጽ ለማለፍ አልፈለግሁም ። በዚህ የተነሣ ብሞትም ለዚች የውሸት ዓለም ምንም ያህል ፍቅር ስለሌለኝ አልጨነቅም ። የምጨነቅለቱን መልካም ትምህርት ለሁል ጊዜ

ለሚኖሩትና እየተከታተሉ ወደ ዓለም ለሚመጡት የሰው ትውልዶች ብርሃን የሚሆነውን ቅን መንገድ ኅሊናዬ እየወደደው እሱን አጥፍቼ በትንሽ ነገር ለሚጠፋውና ለማልጨነቅለቱ ብጨነቅለትም የተፈጥሮ ግዳጅ ከሆነው ከሞት ላድነው ለማልችለው ከንቱ ሕይወቴ አልደከምም ። ዓለም በእውነተኛ ኑሮ የተመሠረተች ቢሆን ኑሮ እናንተንም ከመግደል እኔም ከመገደል አንደርስም ነበር ። ነገር ግን የዓለም ኑሮ በውሸት በመመሥረቱ ሰላም አጥተን ይኸው ርስ በራሳችን እንጋደላለን ።

እንግዲህ ስንት ፍጡር ያለማቋረጥ የሚኖርባት ዓለም ሰላም አጥታ ስትኖር ለኔ ካንድ ትል ሕይወት የበለጠ ዕድል ለሌለው ሕይወቴ ምኑ ያስጨንቀኛል? ትሎችም ተወልደው ኑረው አንድ ቀን ይሞታሉ ። ሰዎችም እንዲሁ ነን ። ከሌሎች ፍጡሮች የምንለየው በታላቁ መንፈሳችን ነበር ። እሱንም የነጻነት ዕጦት ደመሰሰው የሰዎች ቅርሶች የሆኑት ርኅራኄ ፣ ዕውነት ፣ ደግነት ፣ ዕውቀት ፣ የነጻነት ክብር ፣ የአራዊት ቅርሶች በሆኑት በጭካኔ በተንኮል ፣ በስድነት ፣ በድንቁርና ተደመሰሱ ።

ስለዚህ ከአውሬዎችና ከእንስሶችም የተሻለ ዕድል የሌለኝ ሁኜ ሰዎችም በዚህ መንገድ ሲኖሩ እያየሁ ከምኖር ሞት የማይቀርለቱን ሕይወቴንም በኃዘንና በብስጭት ሳሠቃየው ከምኖር ሙቼ ማረፉ በጣም ይሻለኛል ። ቀደም ብላችሁ ገድላችሁኝ ቢሆን ጥቂት ፀፀት ነበረብኝ ። ይኸውም አንደኛ ለሰዎች ትምሕርቴን ባለማካፈሌ ሲሆን ሁለተኛ በመሞቴ የምትሠቃይ አሮጊት እናቴ በሕይወቷ ስለነበረች ነው ። አሁን ግን ትምህርቴንም ለሕዝብ ገልጫለሁ ። አሮጊቷ እናቴም የኔን ሞት ሳታይ ቀደም ብላ አርፋለች ። የአደጋ ጥላ ያልተለየውን ሕይወቴን አንድ ቀንም ተማምኘበት ስለማላውቅ በኔ ሞት ምክንያት ልትሠቃይ የምትችል ሚስት አላገባሁም ። በኔ ሞት ምክንያት የሟች ልጆች የሚባሉ ልጆችም አላስወለድሁም ። ወዳጆቼና ጓደኞቼም ማን መሆኔን ስለሚያውቁ በሞቴ ይኮሩበታል እንጂ አይሠቃዩበትም ።

ስለኋለኛው ሕይወትም በርግጥ ነፍሴ በእግዚአብሔር ፊት የምትቀርብ ከሆነች በተስፋ እንጂ በፍርሃት አልሄድም ። እግዚአብሔር እውነትንና ቅንነትን የሚወድ አምላክ እንጂ የግል ክብሩንና ጥቅሙን ለመጠበቅ የሚቆርጥና የሚፈልጥ ዲክቴተር እንዳልሆነ ይሰማኛል ። እውነተኛና ቅን ትምህርት ሲያስተምር የተገደለ ፍጡርን የሚቀጣ ከሆነም ክርስ+ያኖች ልጁ

ሌሎች ባለሃይማኖቶች ነቢዩ ሃይማኖት የለሾችም ታላቁ አስተማሪ እያሉ ሁሎችም በመልካም ስም የሚጠሩትን ነገሮች ግን ፍቅርንና ደግነትን ሲያስተምር በግፍ የተሰቀለውን ናዝራዊ ኢየሱስን በመጀመሪያ ኲንኖ ሌሎችን ለእውነተኛ ነገር የሞቱትን ቤላ ይኲንን ። ሃይማኖት ያለኝ ሰው መሆኔን ከገለጽሁ አይቀር የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ መሆኔን ልግለጸው ። ኢየሱስ የሰው ልጅም ቢሆን የእግዚአብሔር ልጅ በሁለቱም በኲል ቸር መሪ ነው። የሰው ልጅ በመሆኑ ለሰዎች ፍቅርን ርህራሄን ቸርነትን ርዳታን በሥራና በማስተማር ገልጻል። ያምላክ ልጅ በመሆኑም ከፍተኛውና መልካሙ ትምህርቱ በጥቂት ሰዎች አስተማሪነት ለአለም ሕዝብ ሁሉ እንዲደርስ አድርጓል። እንግዲህ ሌሎችን የሃይማኖት መሪዎችም እያከበርሁ እሱን ልከተለው። የኔም ክርስ+ያንነት በአንድ ወላዋይ ቄስ እጅ በውሃ ተጠምቄ ክርስቶስ የሚጠላውን ሀሰትና ማጭበርበር እየሰራሁ ክርስ+ያን ነኝ በማለት ሳይሆን እንደርሱ ቅን ትምህርትን ሳስተምር በግፈኞች እጅ ደሜ ፈስሶ በደሜ ተጠምቄ የክርስ+ያንነትን ጸጋ በመቀበልና የክርስቶስን ምሳሌነት በመከተል ነው ። እናንተ ነፍሰ ገዳዮች እናንተ ለጥቅማቸሁ ስትሉ የምትጠሉዋቸውን ነውራችሁንና ግብዝነታችሁን እየገለጹ ስላሳፈሩዋችሁ የምታሳድዷቸውን ሁሉ እግዚአብሔር የሚጠሏቸው ይመስላቼል? እግዚአብሔር እንደእናንተ የሐሰት ወዳጅ የእውነት ጠላት ከሆነስ እሱንም ከመንቀፍ አልመለስ ። በምድር የተረገሙት ሁሉ እናንተ እንደምትሉት በሰማይ ቤትም የተረገሙ ከሆኑስ በሰማይ አገርም እንደመሬት ቀማኞችና ፣ ተቀሚዎች ፣ አሽቆጥቋጮችና ተሽቆጥቋጮች ፣ ባሮችና ጌቶች ከሚገባቸው በላይ ሀብት የሚሰበስቡና የዕለት ራት ያጡ ችግረኞች ያሉ ከሆነስ ይህን የሚያደርገውን እግዚአብሔራችሁንም ተቃውሜ እሱም እንደገና ይግደለኝና የነፍሴ ነፍስ እንዳለች እሷ ወደውነተኛውና አድልዎና ክፋትን ወደማያውቀው እናንተ ወደማታውቁት ታላቅ እግዚአብሔር ሂዳ ሰላሟንና ፍላጎቷን ታግኝ ።

መልካሙ ሰው ሶክራትስ ሞት በተፈረደበት ጊዜ ከተናገረው ቃል ጥቂት ልንገራችሁ ። አድክሜአችሁም እንደሆነ ዳግመኛ በመካከላችሁ ተገኝቼ ስለማደክማችሁና የመጨረሻ ስንብታችን ስለሆነ ታገሡኝ ። ሞቴን ለማየት የምትጓጉትም ሙቼ ሳርፍ ዓይታችሁ የኔ መሞት ከንቱ ነገር መሆኑን በመረዳት ደስታችሁ ከሚቀነስ አሁን እኔን እስክትገድሉ ባላችሁ የመግደል ፍላጎት ደስታ ስትደሰቱ ጥቂት ብትቆዩ ይሻላቼልና ጥቂት ታገሡኝ ።

ከታገሣችሁኝም የታላቁንና በኔ ስሜት ቅዱሴ የሆነውን ሰው የሶክራትስን ቃል ልጥቀስላችሁ « በኔ ላይ የተደረገው (የሞት ፍርድ) መልካም ነገር እንደሆነ በእውነት እነግራቼለሁ ። ከኛ መካከል ማንኛውም ሰው መሞት ክፉ ነገር ነው ብሎ ቢያስብ ሞትን በቀጥተኛ መንገድ አስቦታል ። ለማለት የማይቻል ነው ። ለዚህም አንድ ታላቅ መረጃ ለኔ ተሰጥቶኛል ። ምክንያቱም ጥቂት መልካም ነገር ለማድረግ ካልሞከርሁ በቀር የዘወትር ስሜቴ በርግጥ ይቃወመኝ ስለነበር ነው ።

እንዲሁም በሌላ መንገድ መልካም የሆነ ተስፋ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንደሆነ እንመልከት ። ሞት ሁለት ነገሮችን የያዘ ነው ። ወይም የሞተው ሰው ወደከንቱነት ተለውጦ ስለምንም ነገር የማያውቅ ይሆናል ። ወይም ሰዎች እንደሚሉት ሞት የነፍስ መለወጥና ከዚህ ዓለም ወደሌላ ቦታ መጓዝ ነው ። ከሞቱ ቤላ ምንም ማወቅ ከሌለ እንደእንቅልፍ ከሆነ አንድ ሰው ምንም ሳያይ በሕልሙ እንኳ ምንም ሳይሰናከል እንደሚተኛበት ጊዜ እንቅልፍ ያለ ከሆነ ሞት አንድ አስደናቂ መመረቅ ነው ። አንድ ሰው ሕልም እንኳ ሳያይ በከባድ ዕንቅልፍ ተውጦ ያሳለፈውን ሌሊት የሚመርጥ ከሆነ በሕይወቱ ሙሉ ያሳለፋቸውን ሌሊቶችና ቀኖች ከዚያ ሌሊት ጋር እያመዛዘነ ከተመለከተ ቤላ በሕይወቱ ሙሉ ካሳለፋቸው ሌሊቶችና ቀኖች ከዚያ ሌሊት ይበልጥ የሚጣፍጡ እንዳሉ ካነጻጸረ ማንኛውም ሰው ተራው ሰው ብቻ ሳይሆን ታላቁ የፋርስ ንጉሥ እንኳ ከዚህ መልካም ሌሊት ጋር ሊያነጻጽራቸው ከሚችላቸው ሌሊቶችና ቀኖች የሚያገኘው ተመሳሳይነት ጥቂት ይመስለኛል ።

እንግዲህ ሞት እንደዚያ መልካም ሌሊት ያለ ከሆነ የዘለዓለሙ ኑሮ በእርግጥ ካንድ ሌሊት የሚበልጥ መስሎ ስለማይሰማ ሞትን መባረክ እለዋለሁ ። ነገር ግን በሌላ መንገድ ሞት ከዚህ ዓለም ወደሌላ ቦታ መጓዝ ቢሆን የሞቱት ሰዎች ሁሉ እዚያ አሉ የሚሉትም እውነት ቢሆን የፍርድ ቤቱ ዳኞች ሆይ! ከዚህ ይልቅ ከዚያ እንዴት ያለ ታላቅና መልካም ነገር አለ? ………….. ወደዚያ ሂዶ ከኦርፊዮስ ከሙሳዮስ ከሄሲዮድና ከሆሜር ጋር ለመኖር ከናንተ አንዱ ለዚህ ታላቅ ነገር ምን ያህል ዋጋ ይሰጣል? በራሴ በኩል የሚባለው ነገር እውነት ከሆነ ለዚህ ነገር ብዙ ጊዜ እሞትለታለሁ ። ምክንያቱም እዚያ አንድ አስደናቂ ነገር እየጠበቀኝ ስለማገኝ ነው ። ከዚያም ፓለሜዴስን ፣ የቴላሞንን ልጅ አየስንና ሌሎችንም በጥንቱ ጊዜ ትክክለኛ

ባልሆነ ፍርድ የሞቱትን ሰዎች አግኝቼ ለራሴ ያጋጠሙኝን ነገሮች እነሱን ከገጠሟቸው ነገሮች ጋር ሳነጻጽራቸው አንድ ዓይነት የሚሆኑ ይመስለኛል ።

ከሁሉም የሚበልጠው ከዚህ ያሉትን ሰዎች መስቀልኛ ጥያቄ እንደጠየቁቸውና ማንኛቸው አዋቂ መሆናቸውን ማንኛውም አዋቂ ሳይሆን አዋቂ ነኝ ብሎ የሚያስብ መሆኑን ለማወቅ እንመረመሬቸው እነዚያንም የምጠይቃቸው መሆኔ ነው ።

ትሮይን ለመውረር መሪ የነበሩትን ኦዲሲዮስን ወይም ሲሲፎስን ፣ ወይም ሌሎችን በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎችን መስቀልኛ ጥያቄ ለመጠየቅ አንድ ሰው ለዚህ ምን ያህል ዋጋ ይከፍላል?

በሌላው ዓለም ከነሱ ጋር መነጋገር ከነሱ ጋር መኖርና እነሱን መስቀልኛ ጥያቄ መጠየቅ ወሰን የሌለው ደስታ ይሆናል። በዚያ አገር በማንኛውም ነገር አንድ ሰው ያን ነገር ስለሠራ ይገድሉታል ብዬ አላስብም ።

ምክንያቱም በዚያ ዓለም የሚኖሩት እነሱ በዚህ ዓለም ከምንኖረው ከኛ የበለጡ ተደሳቾች ናቸው። በተለይም ለቀረው ጊዜ የማይሞቱና የዘለዓለም ሕያዋን ናቸውና ሰዎች የሚሉት እውነት እንደሆን።

የፍርድ ዳኞች ሆይ! እናንተም በሞት ላይ መልካም ተስፋ ሊኖራችሁ ይገባል ። እንዲሁም ይህን አንድ ነገር እውነት መሆኑን አምናችሁ ልትቀበሉት ይገባል ። መልካም ሰው ቢኖርም ቢሞትም ሊደርስበት የሚችል ክፉ ነገር የለም ። » ታላቁ ሶክራትስ ይህን የተናገረው ከዛሬ ሁለት ሺ ሦስት መቶ ዘጠና ዓመት በፊት ግድም ነበር ።

ሶክራትስ ቀድመውት ከሞቱትና በሰማይ ቤት ከሚያገኛቸው ጥቂት ግሪኮች ጋር ተገናኝቶ ለመነጋገር ወደሌላ ዓለም ለመጓዝ ይህን ያህል ሲናፍቅ እኔማ በዚህ ከሁለት ሺ በሚበልጥ ዘመን ውስጥ ወደሌላ ዓለም ከሄዱት ስንት ደግ ሰዎች ጋር ለመገናኘት እንዴት ጉዞዬን መናፈቅ አይገባኝም? የሰማይ ቤቱ ፍርድ ቤት እንደምድሩ ፍርድ ቤት ካልሆነና አድልዎ ከሌለበት ስንቱ የሐሰት ፍርድ ተገልብጦ ስንቱ ወንጀለኛ የተባለ ፍጡር ነጻ ሁኖ ይሆን? እነሶክራትስ ፣ እነኮንፊዩሽስ ፣ እነቡድሐና ሌሎችም የመልካም ነገርና የደግነት መምህሮች ስንቱን ጨካኝና ክፉ ወደደግነት መልሰውት ይሆን? በኔሮን ቄሣር ፊት የዶሮ ያህል ክብር ሳያገኙ የታረዱት እነጴጥሮስና እነጳውሎስ በድንቁርናቸው

ሕዝብን ይፈጁ የነበሩት የሮማ ቄሣሮች ወደሰማይ ቤት ደርሰው ሲያፍሩ የሰዎችን መከራ የማይወዱ ስለሆኑ እንዴት ያዝኑላቸው? ዋረ አታስጎምጁኝ! በመስቀል ላይ ሁኖ እየተሠቃየ እንኳ ሳይቀየም « አባቴ ሆይ ይቅር በላቸው የሚያደርጉትን አያውቁትምና » ሲል ለሰቃዮቹ ምሕረትንና ይቅርታን የጠየቀው ኢየሱስ ኃጢአተኞቹን ሁሉ ምሮ ትጉሁና ጠንካራው ሰባኪ ቅዱስ ጳውሎስ በየቦታው እየዞረ ሰብኮ ቡድሐም ሰላምን እየዞረ አስተምሮ ሞሐመድም ሐሰትንና ማጭበርበርን በግድም በውድም አስትቶት መልካም ሰዎች ብቻ ሊኖሩ ስለሚችሉ ከዚህ ክፉ ሕዝብ ከሞላው ዓለም አምልጬ ወደዚያ መሄዴን እንዴት ልጠላው እችላለሁ? ትልቁ ችግር በርግጥ የምሄድበትን ዓለም ባለማወቄ ነው እንጂ ባውቀው ኑሮስ እስከሁንም አልጠብቃችሁ ነበር ። ራሴ ቀደም ብዬ ቦታ መለወጥ ነበረብኝ ። ግን እግዚአብሔር ለምን እንደፈጠረኝ አላውቅም ። እስካለሁ ኑሬ ሙቼ እንድቀር ይሁን ወይም በምድር እስካለሁ ኑሬ ስሞት ወደሌላ ዓለም እንድሄድ ይሁን አላውቅም ።

ይሁን እንጂ በዚያም ይሁን በዚህ ከዚህ ዓለም ኑሮ የሚሻል ካልሆነ በቀር ከዚህ የከፋ ዓለም እንደማያጋጥመኝ ስለማምን ሞቴን በጭራሽ ክፉ አልለውም ። ሰው ነኝና በሞትና በሕይወት መካከል ያለው ሥቃይ ደመ ነፍሴን በመጠኑ ሲያሰጋት ታዩ ይሆናል ። መንፈሴ ግን ሞትን አትፈራም ። ስለ ጉዞዬ መልካምነት ከነገሬቸው ለናንተ ለኗሪዎችና ከናንተ ቤላ እየተከታተሉ ለሚመጡት ትውልዶች ደግሞ ምክሬን ልስጥ ። በሞት አፋፍ ላይ ያለ ሰው ሊዋሽ ስለማይፈልግ አሁን ውሸት የሌለበት ምክር እንደምሰጣችሁ እመኑ ።

እያንዳንዱ ሰው በዓለም ላይ የሰዎች መልካም ኑሮ ጠላት የሆነው ክፋትና የሰው ዘር መልካም ኑሮ መሠረት የሆነው ደግነት ሲዋጉ መኖራቸውን ይወቅ ። የሰውን መልካም ዕድል ያበላሹትም ከክፋት የሚመነጩ ጠንቆች ናቸው ። ሰዎች ራሳቸውን ከክፋት ነጻ ማድረግ ቢያቅታቸው ለመጥፎ ሥራቸው ኃላፊ ሁኖ እንዲወቀስ ሰይጣን የተባለውን ስም ያቀርባሉ ። መልካም እንሥራ ስትሉ ሰይጣን መጥቶ የከለከላችሁ መቼ ነው? ሰይጣንስ መጥቶ ክፉ ሥሩ ያላችሁ መቼ ነው? ከሰይጣን የሚከፉት ክፉ ሰዎች ናቸው ። በስምም አታምልኩ ። የክርስቲያንነት ፍሬ ክርስቲያንነት የሚያዝዛቸውን መልካም ነገሮች መፈጸም

እንጂ በስም ክርስ+ያን መባል አይደለም ። ስለፍቅር መልካምነት ታወራላችሁ ። ፍቅርን የሚያጎሳቁል ጠብ ትፈጥራላችሁ ። የሕዝብን መብት እንጠብቃለን ብላችሁ ታወራላችሁ ራሳችሁ የሕዝብን መብት ትገፋላችሁ ። አዲሶቹ ገዢዎችም ያለፈውን ያገዛዝ ዓይነት ትነቅፋላችሁ ። ከድሮው በበለጠ ከባድ አገዛዝ ሕዝብን ታሠቃያላችሁ ። ነገሥታትና መሳፍንት ይለብሱት የነበረውን በወርቅ የተንቆጠቆጠ ልብስ ትረግማላችሁ ። ራሳችሁ ደረታችሁንና ትከሻችሁን እስኪከብዳችሁ ድረስ የወርቅ ጌጣ ጌጦችን ትሸከማላችሁ ።

ወዮላችሁ! ተራ ሕዝብ ለሆናችሁ ወገኖቼ! በጡንቻውና ባበጠ ቦርሳው የሚመካ ሁሉ ለባርነት ለሚያጫችሁ ምስኪኖች ወዮ!

እናንተ ሕዝቦች! እውነቱን ልንገራችሁ ያለፈውን ለመንቀፍና ያለውን ለማመስገን ያገኛችሁትን ዕድል እንደዕድገት አትቊጠሩት አዲሱ ፍሬ ሁሉ ጠቃሚ መስሏችሁ ሳትቆረጥሙ አትዋጡት ። ሁሉንም መርምራችሁ እውነተኛ ዋጋውን ስጡ ። ሕዝብ ታላቅ ዕድል አገኘ ሊባል የሚችለውና በሰላም የሚኖረው መሠረታውያን ጠላቶቹ የሆኑ የአካልና የመንፈስ ጠንቆችን በሽታን ፣ ችግርን ፣ ድንቁርናን ፣ ጭቆናን ሲያስወግድ እንጂ አንዱን ጨቋኝ አስወግዶ የባሰ ጨቋኝ በመተካት አይደለም ። ለውጥ የሚባለውን ቃል ያለስሙ አትተርጒሙት ። ለውጥ ማለት ማንኛውም ሰው የተፈጥሮ ጠላቶቹንና አንዳንድ ሰዎች የጫኑትን ቀንበሮች አቸንፎ በነጻ ለመኖር የሚያደርገው አካላዊና አእምሮአዊ እንቅስቃሴ እንጂ ካንድ ቀንበር ወደ ሌላ ቀንበር መዘዋወሩ አይደለም ። ይህንንም ማለቴ ማንኛውንም ነገር በሚሰጣቸው ጥቅም እንጂ በስሙ አታምልኩት ስል ነው ። አዲስ ነገርን ሁሉ በውስጡ ምን እንዳለበት ስለማታውቁ ውስጡን ሳታዩት እምነታችሁን አትጣሉበት ። ለአዲስ ነገር ንቁና ተጠራጣሪ ሁኑ ። ማንኛውም ነገር ከማመስገናችሁ በፊት ታግሣችሁ እዩትና ቤላ እንደሥራው ሁኔታ ልትነቅፉትም ሆነ ልታመሰግኑት ትችላላችሁ ። በኔ ላይ ሞት የፈረደው መንግሥት እኔን የመሰሉት ሰዎች ሥልጣን እንዲይዙ የረዳናቸው ሰዎች ያቋቋሙት መንግሥት ነው ። እኔ የፈለገው ይድረስብኝ ግዴለም ሞትን የማልፈራ አንድ ሰው ነኝ። ግን በሕዝብ ላይ እንዲህ ያለው ግፍ እንዳይሠራ ለሥራችሁ ሁሉ ጥንቃቄና በቂ መሠረት ይኑረው።

« የስንት ቸር መምህሮች ትዕግሥትና ትምህርት ፣

« ለመሆን ካልቻለ ለሰው መልካም ኑሮ ዓምድና መሠረት ፣

« ከተደመሰሱ ፍቅር በጥላቻ ፣ ደግነት በክፋት ፣

« ከተጐሳቆሉ ጤንነት በደ« ፣ ነጻነት በትዕቢት ፣

« በድንቁርና ኃይል ከደከሙ ዕውቀት ፣

« በጉልበት ሥልጣን ሥር ከተቀጠቀጡ ሕግና ሃይማኖት ፣

« ይህንን እያየሁ ዘላለም ከምኖር በኃዘን በፀፀት ፣

« ለኔስ ይሻለኛል ሊሰጥ የሚችለውን የእውነትን ዕረፍት ፣

« ወይ ወደውቡ ዓለም የሚያሸጋግረኝ መልካሙ ነገር ሞት ፣

« ያለም ሰፊ ጥሪት የብልሆች ጥበብ ፣

« ከድንቁርና ፣ ከችግር ፣ ከደዌ የሚያድን ካልሆነ መከራ ያየውን የዚችን ዓለም ሕዝብ ፣

« በጭንቀት ከመኖር የማይሆንን ነገር ሳልምና ሳስብ ፣

« በጣም ይሻለኛል ቶሎ ሄጄ ባርፈው ወደ ሌላው ዓለም ወይም በመቃብር ብዬ ብኖር ሰብሰብ ፣

« እኔስ ይኸው አረፍሁ መገላገሌ ነው ከዚህ ዓለም ጣጣ ፣

« ወዮለት! ለሕጻን ወደዚች ክፉ ዓለም ገና ለሚመጣ ፣

« ወዮ! ለሚመጣው ለመንፈስ ቡቡው እንደኔ ላለው ሰው ፣

« ማንም ሳያውቅለት የርኅራኄ ነዲድ ልቡን ለሚጠብሰው ።

« ወዮ! ለቅን ሰዎች ያለጊዜው መጥተው ምኖች እንደሆኑ ሌሎች ሳያውቋቸው ፣

« ባዘን በርኅራኄ እየተሠቃዩ ሰላም የለሽ ሁኖ እያሸበራቸው ።

« እውነትን በመሻት በሚያደርጉት ጥረት መራራ እየሆነ የግል ሕይወታቸው ፣ « አምርረው ለሚያዝኑት በመፈጠራቸው ።

« እናንተ ሕጻናት እውነትን ይዛችሁ እንግዲህ ወደፊት የምትወለዱ ፣

« ምንም የማታውቁት የጥንት መምጫችሁን ደግሞም የማታውቁት የት እንደምትሄዱ ፣

« እንዴት ልንገራችሁ መራራ መሆኑን የዚህ ዓለም ጣጣ መዘዙና ጉዱ ፣ « እኔስ ምንም አልቻልሁ! ሳትፈቅዱ ሳትወዱ ፣

« እናንተው መጥታችሁ እናንተው ፍረዱ ።

« ሕንዶችና ቻይኖች ፣ « ሌሎችም ብዙዎች የእስያ ሕዝቦች ፣

« በርግጥ ቅን አሳቢ መልካም ሕዝቦች ናቸው አስተዋዮች በምር ፣

« አንድ ሕፃን ተወልዶ በመሃይምነት በደ« በችግር ፣

« እየተንገላታ በሥቃይ ከሚኖር ፣

« እንደሚሻል አውቀው ሳይወለድ ቢቀር ፣

« ታጥቀው ጀምረዋል ዘርን መቈጣጠር ።

« የማንም አገር ሕዝብ ከወገኑ ጋራ የሀገሩን ጥቅም ተካፍሎ መኖርን መንፈሱ ከጠላ ፣

« እርቡ! ብዙ! እያለ ደሃን ከሚያታልል ባሰት በሽንገላ ፣

« የሚጠላቸውን ድሆችን አጥፍቶ ፣

« ሆዱ ከቻለለት ያገሩን ሀብት ሁሉ ጥቂት ሆኖ ይብላ ።

« አሁን ሳስታውሰው የደረሰብኝን ኀዘንና ችግር ፣

« በጣም አዘንሁለት የኔን ስሜት ይዞ ለሚወለድ ሕፃን ኀዘንና ሥቃይ ለተደገሡለት ላሣረኛው ፍጡር ፣

« ሕጻኑ ልንገርህ በኀሊና ካሉ ርኅራኄና እውነት ፣

« ሰላም ያለው ቤትህ መቃብር ብቻ ነው ደጉ እንቅልፍህም ሞት ፣

« በሕይወት ሁነህ ግን ጭራሽ አታገኝም እውነተኛ ሰላም እውነተኛም ዕረፍት፣

« አልወለድም » ስል በግድ ተወልጀ ፣

« አምሳ አራት ዓመታት ነድጄ ነድጄ ፣

« ይኸው ገና ዛሬ ካለም ጥብቅ ሰንሰለት ሊፈታ ነው እጄ ።

« በማየው ጉድ ሁሉ ስጨነቅ ፣ ስጠበብ ፣ ስሠቃይ ስከፋ ፣

« ምን ይውጠኝ ኑሯል ሞት ሆይ አንተ ባትኖር የነፍሴ መጽናኛ የመንፈሴ ተስፋ ።

« የዋሁ ይቅርና ከፉው ትዕቢተኛው ፣

« ጻድቁ ይቅርና ከፉው ኃጢአተኛው ፣

« ሌላው ሁሉ ቀርቶ ምንም ግፍ ሳልሠራ ሞት የፈረደብኝ ዓመፀኛ ዳኛው ፣

« ባይኔ ማየት ቀርቶ መስማት ስለማልፈቅድ መከራ ሲያገኘው ፣

« ፈጣሪ ባለበት በወዲያኛው ዓለም ባልታወቀው አገር ፣

« በእሥራት ፣ በቅጣት ፣ በሥቃይ ፣ በችግር ፣

« የሚገኝ ከሆነ የሚሠቃይ ፍጡር ፣

« ደግሞ በሌላ ዓለም ያውም ሙቶ ማረፍ በማይገኝበት የሰውን ልጅ ሥቃይ እያየሁ ዘወትር ፣

« ሳለቅስ ስጨነቅ ስከፋ ከምኖር ፣

« ሁሉን የፈጠረ ሁሉን የሚፈትን እግዚአብሔር ይመስክር ፣

« ለኔ ይሻለኛል እንዳልነበርሁ ሁኜ በመቃብር ብቀር ፤

« መሞቴ ካልቀረ እርግማኔን አሁን ላሳርፍባችሁ!

« በጭራሽ አልልም እግዚአብሔር ያጥፋችሁ! »

« ሌላም ክፉ ነገር አልመኝላችሁ ፤

« ግን ሳትረዱልኝ ሲጐዳኝ የኖረው ለሰው ልጆች ማዘን ገብቶ በልባችሁ ፤

« እኔን በሕይወቴ ሰላም እንዳሳጣኝ እናንተንም ደግሞ ሰላም ያሳጣችሁ!

« መድኃኒት የለ አንል ብዙ ዓይነት መድኃኒት ባለም ላይ ተገኝቶ ወንድሙን እያየው ባሠቃቂ ደዌ ተጐድቶ ተጠቅቶ ፤

« ወይንም ድሆችን ፤ ሕጻናቱን ሚስቱን ትቶ ሙቶ ፤

« እህሉ የለ አንል ምግቡና መጠጡ ተትረፍርፎ ሞልቶ ፤

« ሥራው በየቦታው የሚሠራው ጠፍቶ ፤

« ጠብደሉ ጎረምሳ እንዲያው ሥራ ፈትቶ ፤

« ሲንቀዋለል ማየት ተርቦ ተጠምቶ ፤

« ተበርዶም ተራቁቶ ፤

« ትምህርትም የለ አንል ስንት የማስተማር አቅድ ባለም ተዘጋጅቶ ፤

« ስንቱ ፍጡር ሲቀር ከውቀት ተለይቶ ፤

« ለድንቁርናና ለልማድ ተገዝቶ ፤

« ሁሉም ፈስሶ ሲቀር አስተናባሪ አጥቶ ፤

« ይህን ሁሉ እያየ የሚጨነቅ ፍጡር ምን ሰላም ያገኛል? ማረፍ እንጂ ሙቶ!

« የምላችሁ ሁሉ ምንም ካልገባችሁ ፤

« እግዜር ልባችሁን ስስ አድርጎባችሁ ፣

« እኔን ውስጤ ገብቶ ያቃጠለኝ ኃዘን ገብቶ በውስጣችሁ ፣

« እናንተን እንደኔ በጣም ያቃጥላችሁ ። » ይህን ስናገር ሕዝቡ በፍጹም ፀጥታ ያዳምጠኝ ነበር ። ከዚህ ቤላ ፍርዱን ለማስፈጸም ከመጡት ባለሥልጣኖች ሌላ ጥያቄ እንዲቀበሉኝ ደግሞ ጠየቅሁና እሺ ስላሉኝ « መቼም ሰነፎች ናችሁና መቃብሬን እናንተ አትቆፍሩትም ። በኔ ምክንያት ኩሊዎችን በከንቱ ከምታደክሙ መቃብሬን እኔ ቆፍሬ እንድሞት አትፈቅዱልኝም? » አልሁ ።

« ከፈለግህ ምን ቸገረን! » አለ አንዱ ሹም ። ከዚያም ቀጥሎ « ከየትኛው ዓይነት ቤተ ክርስ+ያን እንድትቀበር ትፈልጋለህ? » ብሎ ሲጠይቀኝ ከሕዝቡ መካከል የነበሩት የልዩ ልዩ ቤተ ክርስ+ያን ቄሶች እየጮሁ ሁሎችም « ይህ አረመኔ ስንት ቅዱሶች ባረፉበት የኛ መካነ መቃብር አይቀበርም! » አሉ ።

እኔም « እናንተ ዋሾዎች! ኢየሱስ ክርስቶስ ለቀበሮዎች ዋሻ ለዎፎች ጐጆ አላቸው ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት ቤት የለውም ብሎ ነበር ። አሁንም ለናንተ ለቀበሮዎች በድን የተፈቀደው ዋሻ ለኔ የማይፈቀድ ሆነ ። ለኔስ ስንት ውሽታሞችና አጭበርባሪዎች ከተቀበሩበት ቦታ ይልቅ ንጹሑ ሜዳ ይሻለኛል ። » ካልሁ ቤላ ወደ ገዳዮቼ ዘወር አልሁና « ከከተማ ውጭ ወደሆነ ሜዳ ውሰዱኝ እባካችሁ! » አሌቸው ። እነሱም ጥያቄዬን ተቀብለው ከከተማ ውጭ የሕዝቡን መብት ለማስመለስ ተሰብስበንበት ወደነበረው ቦታ መኪናዋን የታላቅ ሀብታም ሬሣ እንደያዘች የሬሣ መኪና ቀስ አድርገው እየነዱ ወሰዱኝ።

ሕዝቡም አብሮን እየተጥመለመለ ከታላቁ ሜዳ ከደረስን ቤላ ከመኪናዋ ስንወርድ ሰንሰለቱን ከጄ እንዲያወልቁልኝ ለምኜ ካንዲት ቁጥቋጦ ጥግ መቃብሬን መቆፈር ጀመርሁ ። መቃብሬን ቆፍሬ ከጨረስሁ ቤላ « ገደላውንስ እኔው ራሴ ልፈጽምላችሁ? ለዚህም የምትሰንፉ ከሆነ ሽጉጥ ስጡኝና ራሴን በራሴ ልግደልላችሁ ። ግን ለዚህ አትሰንፉም ይልቁንም የደስታችሁና የጀግንነታችሁ ምንጭ ሰው መግደል በመሆኑ እኔን በመግደል


የሚሰማችሁ የደስታ ስሜት እንዳይቀነስባችሁ ራሳችሁ ግደሉኝ! » ካልሁ ቤላ ወዳናደዱኝ ቄሶች ዘወር አልሁና « እናንተ የተረት ቄሶች! ሰው ነፍሱና ሥጋው ሲለያዩ ብዙ ሙግት አለበት የምትሉትና ሰውን የምታስፈራሩበት ተረት ከንቱ መሆኑን ተመልከቱ ። እኔ አሁን ግንባሬን ወይም ደረቴን በጥይት ስመታ በደቂቃ ውስጥ እሞታለሁ ። እንግዲህ እናንተ በዒዕረ ሞት ላይ ከመልአከ ሞት ጋር ይደረጋል የምትሉትን ረጂም ጥያቄና መልስ (ኢንተርቪው) መቼ ላደርገው ነው? እንዲያው ሁላችሁም ሕዝብን ስታደናቁሩና ስታስፈራሩ ስታስጨንቁ መኖርን ስለፈጠራችሁ እግዚአብሔር ብላችሁ ተዉ! » አልሁ ።

ወዲያው ለየት ብዬ ቆምሁና « ና በል መግደል የምትሻ ግደል! ብዬ ግንባሬንና ደረቴን ሰጠሁ ። ሰውነቴ ጥቂት ጥቂት ሽምቅቅ ይል ነበር ። ፍርሃትና ጭንቀት ግን መንፈሴን አልነኳትም እንዲያውም ከጭንቅ የመገላገል ስሜት ነበረኝ ።

ሁለት ለገደላ የተመደቡ የወህኒ ቤት ወታደሮች አንዱ በግንባሬ አንዱ በደረቴ ትይዩ ጠመንጃዎቻቸውን አነጣጠሩና « ዓይንህን ሸፍን! » አሉኝ ። « እንኳንስ ወዳጄን ሞትን ለሰከንድ ጊዜ ማየት ሊፈሩ የናንተን የረከሱ ጌቶችና እናንተን »4 ዓመት ሙሉ ሲያዩ ሲኖሩም ዓይኖቼ አልተጨፈኑ ይልቅስ ተኩሱ » አሌቸው ። ጥይቶች ደው ሲሉ ሰማሁ ። ስለዚህ ዓለም ጉዳይ የማውቀው እስከዚህ ጊዜ ነበረ ። ከዚያ ቤላ የሆነውን ግን በፍጹም አላወቅሁም ። ከጥይቱ ተኩስ ጋር ሕይወቴ ተተኩሳለችና ይህን ለማጻፍ የቻልሁትም በመንፈስ መጥቼ ነው ።

## ተፈጸመ።

አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ቸርና እውነተኛ አምላክ የዘለዓለም ምስጋና ይድረሰው።



# ስለደራሲው በጥቂቱ

አቤ ጉበኛ (፲፱፻፳፫ ዓ/ም በባሕር-ዳር አካባቢ፣ ይስማላ ጎጃም ተወልደው - ፲፱፻፸፱ ዓ/ም አዲስ አበባ ላይ አረፉ። ባለቅኔ፤ ደራሲና ገጣሚ የነበሩት አቤ ጉበኛ በስድስት ዓመት ፊደል ቆጥረው ንባብ ከተማሩ በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሲከታተሉ ቆዩ። ከዚያም ወደ ደንጎላ ሄደው በቢትወደድ መንገሻ ጀምበሬ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል።

አቤ ጉበኛ የመጀመሪያ ሥራቸው በማስታወቂያ ሚኒስቴር ሲሆን ቀጥሎም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተቀጥረው በመንግሥት ሥራ ለስድስት ዓመታት ያህል ካገለገሉ በኋላ ሕይወታቸውን በአብዛኛው የገፉት በደራሲነት ነው። በ1967 እ.ኤ.አ. በአዮዋ ክፍለ-ሀገር ወደ ዓለም አቀፍ የጽሑፍ ህብረት ፕሮግራም (International Writing Fellowship Program) ሄዱ።

<u>የደራሲው ሥራዎች፡-</u>

1. መስኮት **(ግጥምና ቅኔ)**
2. እሬትና ማር **(ግጥምና ቅኔ)**
3. ከልታማዋ እኅቴ **(ልብ-ወለድ)**
4. ምልክዐም ሰይፈ ነበልባል **(ልብ-ወለድ)**
5. አንድ ለናቱ **(ታሪካዊ ልብ-ወለድ)**
6. የረገፉ አበቦች **(ልብ-ወለድ)**
7. ከመሰፍት ሠራዊት፥ ይጠንቀቅ ሰውነት **(ተውኔት)**
8. ቂመኛው ባሕታዊ **(ተውኔት)**
9. የሮም አወዳደቅ **(ተውኔት)**
10. የራሔል ዕንባ **(ተውኔት)**

11.የደካሞች ወጥመድ **(ተውኔት)**
12.አልወለድም (፲፱፻፶፫ ዓ.ም.) **(ልብ-ወለድ)**
13.የዓመፅ ኑዛዜ (፲፱፻፶፫ ዓ.ም.) **(ልብ-ወለድ)**
14.መሬት የማን ነው
15.The Savage Girl 1964 እ.ኤ.አ. **(በእንግሊዝኛ)**
16.Defiance 1975 እ.ኤ.አ. **(በእንግሊዝኛ)**

NIGUSS DIGITAL LIBRARY